በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ትምህርት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል


# ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለሥነጽሑፍ ፎክሎር ኹለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

# በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና 2016 ዓ.ም የተዜሙ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ይዘት እና ፋይዳ ትንተና በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ተተኳሪነት


በአባተ አሰፋ ከበበዉ



መጋቢት 2016 ዓ.ም

ኮተቤ / ኢትዮጵያ

# በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና 2016 ዓ.ም የተዜሙ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ይዘትና ፋይዳ ትንተና በአዲስ አበባ፣ የካ ክፍለ ከተማ ተተኳሪነት

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፤ የቋንቋዎች ትምህርት ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለሥነጽሑፍ ፎክሎር ኹለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በአባተ አሰፋ ከበበዉ

አማካሪ

ሥለሺ አባተ (ለዶክተር)

መጋቢት 2016 ዓ.ም.
ኮተቤ / ኢትዮጵያ

# ምስጋና

እንቅልፍና ሥንፍና ሙቆኝ፣ ለመማር አሻፈረኝ፣ ያልኩትን ሰዉዬ ከእንቅልፌ ቀስቅሰህ እና አበረታተህ የምወደዉንና የምመኘዉን የፎክሎር ትምህርት እንድማርና ወደመስመሩ እንድገባ ያደረከኝ የትምህርትና የስራ ባልደረባዬ ጓደኛዬና ወንድሜ ዳንኤል በትረ መለሰ እጅግ አመሰግንሃለሁ፡፡ ዘንድሮ መማር ከዕዉቀት ባለፈ ለኑሮ የሚጨምረዉ እሴት ባይኖርም መማሬ ጥልቁን የፎክሎር ዓለምና እምቁን የቃል ግጥም ገጸ በረከት እንድገነዘብ አድርጎኛልና አንተ ቀስቅሰህ እንድማር ባታበረታኝ ኖሮ የዚህ ጸጋ ባለቤት ለመሆን አልበቃም ነበር፡፡

በመቀጠልም አንተ ከቤቴ ቀስቅሰህ ወደ ዩኒቨርስቲ ስትልከኝ ተቀብለዉ የረሳሁትን አስታዉሰዉ፣ የማላዉቀዉን አስገንዝበዉ አቅምና ፍላጎቴን ቀስቅሰዉ የስነጽሑፍን በተለይም የምወደዉን የፎክሎር ትምህርትና ጥልቁን የቃል ግጥም ምንነት፣ ባህርይ እና ፋይዳ እንድረዳና ይበልጥ እንድወደዉ ያደረጋችሁኝን የሥነጽሑፍ ምሁራን ዶክተር ሥለሺ አባተ፣ ዶክተር ሰብለ ወ/ኪዳንና ዶክተር አራጌ ይመርን እጅግ አመሰገናችኋለሁ፡፡ በተለይም ዶክተር ሥለሺ የፎክሎር ኮርሶችን በዕዉቀት፣ በቁጭትና በስሜት ከማስተማር ባለፈ የዚህን ጥናት ርዕሱ ለመምረጥና ከተመረጠም በኋላ ቅርጽና ይዘቱን በማቃናት ጥናቱ አሁን የያዘዉን መልክ እንዲይዝ በማማከር ላበረከትከዉ አስተዋጽኦ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዶክተር አራጌ ለመጀመሪያ ጊዜ የግጥምን አተናተን መሰረታዊ እዉቀት በዉል እንድረዳና የትንታኔ አቅሜም እንዲጎለብት አድርገሽኛልና ክብርና ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡

በአጋጣሚ ተገናኝተን በቅንነት የጥናቱን ረቂቅ ደጋግመህ በማንበብ በርካታ ማስተካከያ፣ እርማትና ምክር በመስጠት ጥናቱ አሁን ያለዉን ቅርጽ እና ይዘት እንዲይዝ ወንድማዊ አስተያየትህን በመለገስ ድጋፍና እገዛህ ያልተለየኝ የስራ ባልደረባዬ ልጅ እንዳለዉ ሙሉዓለም እጅግ አመሰግንሃለሁ፡፡ በመጨረሻም ዉድ ባለቤቴ ሰላማዊት ጸጋዬና ልጆቼ አቤኔዘር፣ እዩኤልና ኬብሮን አባተ ፍቅርና እንክብካቤያችሁን ቀንሼ ለትምህርትና ለጥናት በማዋል ስራዬን በብቃት እንድወጣ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ማበርከት ብቻ ሳይሆን የወር ደሞዜን ከኑሯችሁ ላይ ቀንሼ ለትምህርት በመክፈል ላሳደርኩባችሁ ጫና ይቅርታና ድጋፋችሁ አልተለየኝምና አመሰግናችኋለሁ፡፡ ፈጣሪ እድሜ፣ ጤናና ፍቅር ያድላችሁ፡፡

# አበርክቶ

የዚህ ጥናት አበርክቶ የጥምቀት በዓልን በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተለይም በየካ ክፍለ ከተማ ሲከበር በባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ታቦታቱን በማጀብ በስርዓት አልበኝነት ተፈርጃችሁ እስርና መንገላታት ለደረሰባችሁ የባህላዊ ጭፈራ የቡድን አባላትና አቀንቃኝ ወጣቶች (የቃል ግጥም መረጃ አቀባዮች) ይሁንልኝ፡፡

ለሠላም፣ ለፍትህና ሃሳብን በነጻነት ለመግለጽ እየታገላችሁ በመልካም አስተዳደር ችግር፣ በብሔር ፖለቲካ ተጽዕኖ እና በእርስ በርስ ጦርነት በመላዉ ሀገራችን የሞት፣ የእስራት፣ የመፈናቀል፣ የስደትና የእገታ ክፉ እድልና አጋጣሚ እንዲሁም የሕይወት፣ የንብረት፣ የአካልና የሞራል መስዋዕትነት የከፈላችሁ ኢትዮጵያዉያን የዚህ ጥናት አበርክቶ ለናንተም ይሁንልኝ፡፡

መረጃ አቀባዮችን ለአደጋ ማጋለጥ ይሆናል በሚል እይታና ለናንተም በገባሁት ቃል መሰረት ስምና ፎቶዎቻችሁን በዚህ ጥናት ላይ ማካተት ያልቻልኩት ሞረሽ አንድና ሁለት በተለይ እጅግ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡ ስራችሁን በዚህ ጥናት ተደራሽነቱን ለማስፋት የበኩሌን ድርሻ ለማበርከት ጥረት ከማድረጌም ባለፈ ለከፈላችሁት መስዋዕትነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም አመሰግናችኋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

*“በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና 2016 ዓ.ም የተዜሙ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ይዘት እና ፋይዳ ትንተና በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ የተደረገዉ ይህ ጥናት ዓይነታዊ የጥናትና ምርምር ዘዴን፣ ገላጭ የጥናትና ምርምር ሥነዘዴን፤ ተግባራዊና የክዋኔ ንድፈ ሐሳቦችን፤ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀምና የተሰበሰቡትን መረጃዎች ዓዉዳዊና ይዘት የትንተና ስልት በመጠቀም የተጠና ነዉ፡፡ በአዲስ አበባ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በማጥናት የሕዝቡን ስሜት፣ አመለካከትና ፍላጎት ለመረዳት የተሰራ ጥናት ስለመኖሩ በቂ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝቡ አመለካከትና ሀሳቡን በጽሑፍም ሆነ በንግግር ለማንጸባረቅ የፍርሃትና የጥርጣሬ ስሜት ስለሚሰማቸዉ የጥምቀት በዓልን ጨምሮ በየክወና አጋጣሚዎች ላይ በመገኘት በዜማና በግጥም አመለካከት፣ ሃሳብና ስሜታቸዉን ሲያንጸባርቁ ይሰማሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል በነቂስ በታደምበት የጥምቀት በዓል ላይ ባህላዊ ዘፈንና ጭፈራዎችን እንደ መተንፈሻና ማምለጫ በመጠቀም የተዜሙ ቃል ግጥሞችን በመሰብሰብና በማጥናት በዘርፉ የተፈጠረዉን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ በዓላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡት አካባቢዎች በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ የሚገኙ  የጃንሜዳ፣ የእድር ሜዳና የአርሴማ ጥምቀተ ባሕሮችና አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። የጥናቱ ዋና አላማ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በጥምቀት በዓል ላይ በአማርኛ የተዜሙ ቃላዊ ግጥሞችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን በባህላዊና ማህበረ ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ዉስጥ ያላቸዉን ይዘት፣ ፋይዳና አስተምህሮ በመመርመር በቀጣይ መሰል ጥናት ለማድረግ፤ የሕዝቡን ፍላጎት፣ ስሜትና ጥያቄ በመገንዘብ ምላሽ ለመስጠት፤ ህብረ ብሔራዊ አንድነትና መግባባት ለመፍጠር፤ ሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን ለሚሰሩ አካላት የተጠቃለለ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነዉ፡፡ ይህን አላማ ለማሳካት፣ ከመስክ ላይ ከተሰበሰቡት 350 ቃል ግጥሞች ውስጥ 150 ያህሉ በሰባት ክፍሎች ተደራጅተዉ ተተንትነዋል፡፡ ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች የሕዝቡን፤ ወቅታዊ የሆኑ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊና ታሪካዊ እዉነታ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ጥናት እንደ መነሻ በመጠቀም የማህበረሰቡን አመለካከት፣ ስሜትና ጥያቄ ለማወቅና ለመፍታት፣ ለመልካም አስተዳደርና ለኅብረብሔራዊ አንድነትና ጠንካራ ሀገረ መንግስት ግንባታ ያለዉን ፋይዳ ተገንዝበዉ ቢገለገሉበት ጥሩ የመረጃ ምንጭና ግብአት ሊሆናቸዉ ይችላል የሚል የይሁንታ ሃሳብ በማቅረብ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡*

# የይዘት ማዉጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና..........I
አበርክቶ..........II
አጠቃሎ..........III
የይዘት ማዉጫ..........iv
ምዕራፍ አንድ..........1
መግቢያ..........1
1.1. የጥናቱ ዳራ..........2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........7
1.3. የጥናቱ ዓላማ..........8
1.3.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ..........8
1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች..........8
1.4. የጥናቱ ወሰን..........9
1.5. የጥናቱ ዉስንነት..........10
1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ..........11
1.7. የጥናቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት..........12
1.8. ያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሔ አማራጮች..........12
1.8.1. ያጋጠሙ ችግሮች..........13
1.8.2. የመፍትሄ አማራጮች..........14
1.9. የመስክ ተመክሮ..........15
1.10. የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ..........17
ምዕራፍ ኹለት..........19
ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት..........19
2.1. ክለሳ ድርሳናት..........19
2.1.1. የጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎች ቅኝት..........19
2.1.1.1. የቃል ግጥም ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያት እና ፋይዳዎች..........19
2.1.1.1.1. የቃል ግጥም ምንነት..........20
2.1.1.1.2. የቃል ግጥም ዓይነቶች..........23
2.1.1.1.3. የቃል ግጥም ባህርያት..........24
2.1.1.1.4. የቃል ግጥም ፋይዳ..........25
2.1.1.2. የቃል ግጥም መሰረታዉያን..........28
2.1.1.2.1. የቃል ግጥም ድረሳ፡-..........29
2.1.1.2.2. የቃል ግጥም ክዋኔ፡-..........30
2.1.1.2.3. የቃል ግጥም አውድ..........32
2.1.1.2.4. የቃል ግጥም ተስተላልፎ፡-..........33
2.1.1.3. የክብረ በዓላት ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያትና ፋይዳዎች..........34
2.1.1.3.1. የክብረ በዓላት ምንነት..........35
2.1.1.3.2. የክብረ በዓላት ዓይነቶች..........37
2.1.1.3.3. የክብረ በዓላት ባህርያት..........41
2.1.1.3.4. የክብረ በዓላት ፋይዳዎች..........44
2.1.1.4. የጥምቀት በዓል ምንነት፣ አጭር ታሪክ እና ፋይዳ..........47
2.1.1.4.1. የጥምቀት በዓል ምንነት እና አከባበር..........48
2.1.1.4.2. የጥምቀት በዓል ታሪካዊ አመጣጥ..........52
2.1.1.4.3. የጥምቀት በዓል ሁለንተናዊ ፋይዳዎች..........55

2.1.2. የንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ዳሰሳ ..... 56
2.1.2.1. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ..... 56
2.1.2.2. የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ..... 58
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 61
ምዕራፍ ሦሥት ..... 70
የጥናቱ ዘዴ ..... 70
3.1. የጥናቱ ዓይነት ..... 71
3.2. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ ..... 71
3.3. የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ..... 72
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች ..... 72
3.5. የመረጃ ምንጭና መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 74
3.5.1. ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች፡- ..... 75
3.5.2. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች፡- ..... 76
3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ..... 77
ምዕራፍ አራት ..... 80
4.1. የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ምደባ እና አደረጃጀት ..... 80
4.2. ተሰብስበዉ የተደራጁ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 81
4.2.1. የማመስገንና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 83
4.2.2. የመምከርና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 101
4.2.3. የመቀስቀስና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 115
4.2.4. ባህልና ማህበራዊ ጉዳዮችን የማጠናከር ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 126
4.2.5. የተቃዉሞና የቅሬታ ድምጽ የማሰማት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 135
4.2.6. የማዉገዝና የመተቸት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 147
4.2.7. የሕዝቡን ፍላጎትና ምኞት የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና ..... 156
ምዕራፍ አምስት ..... 163
የጥናቱ ማጠቃለያ ሐሳብና አስተያየት ..... 163
5.1. ማጠቃለያ ..... 163
5.2. አስተያየቶች (የይሁንታ ሃሳቦች) ..... 166
ዋቢ ጽሑፎች ..... 168
ሀ. በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ..... 168
ለ. በእንግሊዝኛ የቀረቡ ..... 170
አባሪዎች ..... clxxiv
አባሪ አንድ፡- በጥናቱ ትንታኔ የተደረገባቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥም አይነቶች ..... clxxiv
አባሪ ኹለት፡-በጥናቱ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የአማርኛ ቃል ግጥሞች በአይነት ..... 11
አባሪ ሦሥት፡- ከትንታኔዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ፎቶዎች ..... 32
አባሪ አራት፡- ..... 35
ደብዳቤዎችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ..... 35

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ፈቃደ የቃል ግጥምን ምንነት አስመልክቶ ድንጋጌ ለመስጠት በርካታ ምሁራን ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች እንደሆነ ጠቅሰዉ ቃላዊ ግጥም በአንዳንድ የስነቃል ተመራማሪ ስራዎች ውስጥ ብያኔና ስያሜው የተለያየ ሆኖ ይገኛል በማለት ለአብነት የኹለት ምሁራንን እይታ አመላክተዋል፡፡ (ፈቃደ አዘዘ 1991፣ 84)

Ben Amos "*ሥነጽሑፍና ሀገረሰባዊ ስነጽሁፍ*" በማለት ባቀረቡት ገለፃ ውስጥ "ከሰለጠኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር የሀገረሰብ ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግጥም ነው" (Ben Amos 1982፡ 20-22) እንደርሳቸዉ አገላለጽና ግንዛቤ እርሳቸዉ ሀገረሰባዊ ግጥም በማለት የሚጠሩትን ቃል ግጥም በሰለጠነ የኅብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ፣ ባልሰለጠነዉ የሕብረተሰብ ክፍል ግን ዝቅተኛና ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማሳየት የሞከሩ ሲሆን ሃሳባቸዉ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ አይነት መሆኑን ያመላክታል፡፡

Finnegan በበኩላቸዉ ቃል ግጥም የሰው ልጅ በአምዕምሮው የሚያስበዉን፣ በአይኑ አይቶና በጆሮዉ ሰምቶ የተገነዘበዉን፣ በአካባቢና በህይት ዘመኑ ያጋጠመዉን ሁሉ የሚገልጽበት እና ለሌላዉም የሚያስተላልፍበት በመሆኑ በቃል ግጥም ሀሳብን ለማስተላለፍ የሰለጠነና ያልሰለጠነ፣ የተማረና ያልተማረ፣ ልጅና አዋቂ የሚል ውሳኔ የለም በማለት ይገልጻሉ፡፡ አክለዉ ሲያብራሩም "በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት የሚታዩ በደሎችን፣ ጭቆናዎችን፣ ለማንፀባረቅ፣ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችና አስተዳዳሪዎች አስፈሪ በሚሆኑበት ጊዜ ስሜትን እና ፍላጎትን እንዲሁም ብሶትን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ:: በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሚፈጠሩ አሉታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን በአደባባይ አውጥቶ መናገር በማይቻልበት ሁኔታ ቃላዊ ግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል በማለት በዚህ ጥናት ዉስጥ ሊኖረዉ የሚችለዉን ፋይዳ በተጨባጭ ገልጸዉታል፡፡ (Finnegan 1977፡ 223-227)

ከላይ ለአብነት ከተጠቀሱት ከነዚህ ሁለት ምሁራን እይታና ብያኔ የምንረዳዉ የቃል ግጥምን ምንነት፣ ባህርያትና ፋይዳ ከመረዳት አንጻር ያላቸዉ ግንዛቤ የተለያየና አሉታዊና አዎንታዊ ሆኖ ይታያል፡፡ የዚህም ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚገመተዉ Finnegan የአፍሪካ ሥነቃልና ቃል ግጥም ጠለቅ ብለዉ ያጠኑ በመሆናቸዉና እዉነታዉን በሚገባ ለመገንዘብ፣ አወንታዊ ብያኔ ለመስጠት እና የተገነዘቡትን እዉነታ መጻፍ መቻላቸዉን ሲሆን Ben Amos የአፍሪካን ሳይሆን የአዉሮፓን ሥነቃል ለማጥናት እና የአፍሪካ ሥነቃል መነሻዉ አዉሮፓ መሆኑን ላማሳየት የአፍሪካን ሥነቃል በመሰብሰብ ላይ ብቻ በማተኮራቸዉ የተፈጠረ ልዩነት መሆኑን ነዉ፡፡

ይህንንም የሚያሳየዉ "የአፍሪካ ተመራማሪዎች ሌሎች አውሮፓውያን ተመራማሪዎች ሳያስተዉሉት የቀሩትን ጉዳይ መመርመር በመቻላቸው ገለፃቸውና ትንተናቸው ስፋትና ጥልቀት ያለዉ ለመሆን ችሏል፡፡(Finnegan 1970፡ 43) በማለት ያስቀመጡት ብያኔ ነዉ፡፡ በመሆኑም በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም የተዜሙ ቃል ግጥሞች ይዘት እና ፋይዳ ትንተና በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በተከናወነዉ በዚህ ጥናት የክብረ በዓላትን፣ የጥምቀትን እና የቃል ግጥምን ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያት እና ፋይዳ አስመልክቶ የምሁራንን ብያኔ በመጥቀስ ግልጽና ተጨባጭ መረጃ በማቅረብ ለማብራራት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሥነቃል ጥናት በአፍሪካ እንዲሁም በኢትዮጵያ መካሄድ የጀመረው ከ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ማለትም ከ1850ዎቹ ጀምሮ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የሥነቃል ጥናት ስራውንም የጀመሩት ከሌሎች ሀገሮች የመጡ ተመራማሪዎች እንደሆኑ Finnegan እና Okpewho እንደሚከተለዉ ያስረዳሉ፡፡ አውሮፓውያን የአፍሪካውያንን ሥነቃል ማጥናት ሲጀምሩ አላማቸው ለንፅፅራዊ ጥናት የሚሆኑ ሥነቃሎችን፡- ማለትም ተረቶችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን፣ ዘፈኖችን (የቃል ግጥሞችን) ወ.ዘ.ተ. ለመሰብሰብ ስለነበር እነዚህን ቴክስቶች ሲሰበስቡ የነበራቸውን ማህበራዊ ፋይዳና ሥነጽሁፋዊ ጠቀሜታ፣ እንዲሁም ከቀረቡበት ማህበራዊ አዉድ አንጻር ሥነጽሑፋዊና ኪናዊ ለዛቸዉን ጠብቆ ለመሰብሰብ ጥረት አልተደረገም፡፡ (Finnegan 1970: 27-28)

Okepwho በበኩላቸዉ የአፍሪካን የሥነቃል ጥናት ለማየት ስንነሳ እስከዛሬ የነበሩትን የጥናት ሁኔታዎች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ካሉ በኋላ የአዉሮፓዉያን ተመራማሪዎች ፍላጎት ባህልን፣ ህብረተሰብንና ሥነጽሑፍን ለማጥናት ስለነበረ ይከተሏቸው የነበሩት መንገዶችና እይታዎች ከሥነቃል አፈጣጠርና ባህርይ ጋር የተዛመዱ አልነበሩም በማለት ያስረዳሉ፡፡ አያይዘው ሲገልፁም፡- አዉሮፓዉያኑ ሥነቃልን በተጠቃለለ ሁኔታ ስለሚሰበስቡት ብቻ ሳይሆን ውበቱንና ስልቱን ለማሳየት ፍላጎት ስላልነበራቸው የጥናት ሂደቱ የአፍሪካን ሥነቃላዊ ሀብትና የፈጠራ ችሎታ በእጅጉ ጎድቶታል (Okepwho 1992፡ 12-15) በማለት ያስረዳሉ፡፡

Finnegan በበኩላቸዉ በአውሮፖውያን የተጀመረው የሥነቃል ጥናት እያደገ ሂዶ በአፍሪካውያን የሥነቃል ተመራማሪዎች መጠናት ሲጀምር ግን ሥነቃልን ለንፅፅር ከማጥናት ይልቅ ለዉበቱና ለፈጠራዊነቱ ማጥናት ይበልጥ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ በጣም ወጥ ስራ መሰራት የተጀመረውም በራሳቸው ቋንቋ ውስጥ ያለውን ሥነቃል በሚያጠኑ አፍሪካውያን ነው፡፡ እነዚህ የአፍሪካ ተመራማሪዎች ሌሎች አውሮፓውያን ተመራማሪዎች ሳያስተዉሉት የቀሩትን ጉዳይ መመርመር በመቻላቸው ገለፃቸውና ትንተናቸው ስፋትና ጥልቀት ያለዉ ለመሆን ችሏል በማለት ይገልጻሉ፡፡ (Finnegan 1970፡ 43)

በተጨማሪም ከሥነቃል ጥናት ጋር ተያይዞ በተፈጠረው አጋጣሚና ምቹ ሁኔታ የዚህ ጥናት ዋነኛ ማጠንጠኛ የሆነዉን የቃል ግጥም ለይተው ለማጥናት የሞከሩት የሙዚቃ ባለሙያዎች ሲሆኑ እነዚህ ተመራማሪዎች በርካታ የዘፈን ግጥሞችን መሰብሰብና ማጥናት በመጀመራቸው ትኩረት ያላገኘውን የሥነቃል ዘርፍ (አይነት) የሆነዉን ቃል ግጥም የማጥናት ተነሳሽነት በወቅቱ ስለመታየቱ ይገልጻሉ፡፡ (Finnegan 1970: 42)

Finnegan ስለቃል ግጥም በበቂ ሁኔታ ያለመጠናትና ስለዘርፉ ያላቸውን ስሜት በሌላዉ መጽሐፋቸው መቅድም ውስጥ ሲገልጹ መስኩ በጣም የበለጸገ እና አስደሳች ቢሆንም የተረሳ የጥናት መስክ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ ምሁራን በራሳቸው ቋንቋ በሚያደርጉት የተሟላ የጥናት ሁኔታ የቃል ግጥምን ጥናት ወደተሻለ ደረጃ ሊያደርሱት ይችላሉ" በማለት ይገልፃሉ (Finnegan 1977፡ x-xii)

የሀገራችን የሥነቃል አሰባሰብና ጥናትም የተጀመረዉ እንደሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሁሉ በውጭ ሀገር ምሁራን እንደሆነና ዉጭ ሀገር የተማሩ ኢትዮጵያዉያን ግለሰቦችም

እነርሱን ተከትለዉ ሥነቃሎችን እየሰበሰቡ ማሳተም እንደጀመሩ (ፈቃደ፣ 2001) ይገልጻሉ፡፡ በሌላ ስራቸውም የአፍሪካ ቋንቋዎች የማይገቧቸው የውጭ ሀገር ሰዎች እየሰበሰቡ ከሚያሳትሙ ሥነቃል ይልቅ የባህሉ ባለቤት የሆኑ ኢትዮጵያዉያን ግለሰቦችና ተመራማሪዎች ቢያጠኑትና ስብስቡንም ከጥናቱ ጋር አያይዘው ቢያቀርቡት ቅርስ ማስቀረት ይሆናል በማለት ያስረዳሉ፡፡ (ፈቃደ፣ 1991፣ 45)

"የቃል ግጥምን ምንነት አስመልክቶ ድንጋጌ ለመስጠት በርካታ ምሁራን ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች ነው::" እንደሚገልጹት ደግሞ ቃል ግጥም በአንዳንድ የሥነቃል ተመራማሪ ስራዎች ውስጥ አስተሳሰብ የተለያየ ሆኖ ይገኛል። ለአብነትም Ben Amos "ስነጽሑፍና ሀገረሰባዊ ስነጽሁፍ" በማለት ባቀረቡት ገለፃ ውስጥ "ከሰለጠኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር የሀገረሰብ ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግጥም ነው" በማለት እንደገለጹት ያስረዳሉ። (ፈቃደ፣1991፣ 84)

Finnegan በበኩላቸዉ ግጥም የሰው ልጅ በአምዕምሮው የሚያስበዉን፣ በአይኑ አይቶና በጆሮዉ ሰምቶ የተገነዘበዉን፣ በአካባቢና በህይወት ዘመኑ ያጋጠመዉን ሁሉ የሚገልጽበት እና ለሌላዉም የሚያስተላልፍበት በመሆኑ በቃል ግጥም ሀሳብን ለማስተላለፍ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ልጅ አዋቂ የሚል ውሳኔ የለም። የሰው ልጅ ሀሳቡን ለሌሎች በቃል ማስተላለፍ ተፈጥሯዊና የዕለት ተዕለት ኑሮዉ ፍልስፍና አካል ስለሆነ ዘወትር ከሰው ልጅ የማይነጠል ተግባር ነው በማለት ያስረዳሉ። (Finnegan 1977፡ 223-227)

Finnegan ጨምረዉ ሲያብራሩ ቃላዊ ግጥም ስራን ለማቀላጠፍ፣ ራስንና ታዳሚን ለማዝናናት፣ ባህልና ታሪክን ለማቆየት፣ ድጋፍና ተቃውሞን ለማንጸባረቅ፣ ስሜትና ፍላጐትን ለመግለጽ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር፣ እንዲሁም ለማስተማር፣ ለመተቸት፣ ስርዓትን ለመገንባትና ለማፍረስ፣ መልዕክትን ለማስተላለፍ፣ የህይወት ፍልስፍናቸዉን የሚገልፁበት ህይወታቸው፣ የኑሯቸዉ፣ የማንነታቸው መገለጫ እና ተዝቆ የማያልቅ ሀብታቸዉ ነው በማለት የተሻለ ብያኔ ሰጥተዉታል።

በመጨረሻም Finnegan ቃላዊ ግጥሞች በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት የሚታዩ በደሎችን፣ ጭቆናዎችን፣ ለማንፀባረቅ፣ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችና አስተዳዳሪዎች

አስፈሪ በሚሆኑበት ጊዜ ስሜትን እና ፍላጎትን እንዲሁም ብሶትን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ:: በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሚፈጠሩ አሉታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን በአደባባይ አውጥቶ መናገር በማይቻልበት ሁኔታ ቃላዊ ግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ በማለት ፋይዉን ጨምረዉ አብራርተዋል፡፡ (Finnegan 1977፡ 223-227)

Finnegan የአፍሪካ ሥነቃልና የፈጠራ ሁኔታ ከአውሮፖ ሥነቃልና ፈጠራ ጋር ሲነፃፀር በምንም የማይተናነስ መሆኑን በጠቆሙበት በዚህ ጽሑፋቸው ቋንቋዎችን ለማጥናት የተጀመረው እንቅስቃሴ ዝርው ቅርፆችን ብቻ ከመሰብሰብና ከማጥናት ወደ ቃል ግጥም ጥናት እንደተሸጋገረና በዚህም የፍቅር፣ የምፀት፣ የጦርነት፣ ኤፒክ፣ የሙሾ፣ ትምህርታዊና ሀይማኖታዊ ቃል ግጥሞችን (ዘፈኖች) ሰብስቦ በማጥናት Seidle የተባለው ተመራማሪ ዘርዝሮ ለማሳየት ያደረገው ጥረት በወቅቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና የአፍሪካን ሥነጽሁፋዊ ቅርፆች ያስተዋወቀበት እንደነበር አመላክተዋል፡፡ (Finnegan 1970፡ 32)

ከሀገራችን ምሁራን ለአብነት ብርሃኑ እና ፈቃደ በበኩላቸዉ ስለ ቃላዊ ግጥም ብያኔ ተቀራራቢ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ለምሳሌ ብርሃኑ ቃላዊ ግጥም ሙዚቃዊነት በሚሰማባቸው በዘፈን፣ በቀረርቶ፣ በእንጉርጎሮ፣ ወ.ዘ.ተ. መልክ የሚከወኑ ጥበቦችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ካሉ በኋላ እጅጉን የሚዘወተር፣ በጣሙን ደግሞ ልዩ ልዩ መልኮች ያሉት ጥበብ በመሆኑ እያንዳንዱን ዘፈን፣ እንጉርጉሮ፣ ቀረርቶ፣ ከሌላው ጋር ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ እንደሆነና ቃላዊ ግጥምን ለመመደብ መሰረታዊ የሚሆኑት መንገዶች ቀያዊ ስያሜዎች፣ ጭብጦች እና አውዶች መሆናቸዉን አስረድተዋል፡፡ (ብርሃኑ፣ 1995፣31)

ፈቀደ "ቃላዊ ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮ እና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ሕዝባዊ ግጥም ነው፡፡ ሕዝባዊ ግጥም የሚለው ቃላዊ ግጥምን ማንኛውም የዚያ ቡድን ወይም ማኅበረሰብ አባል የሆነ ሁሉ፣ ችሎታው እስከፈቀደለት ድረስ እያስታወሰ፤ እየጨመረ፤ እየቀነሰ ሊያዜመው እንደሚችል የሚያመላክት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ህዝባዊ ባህርይ ሊኖረው የሚችለው በተስተላልፎው እና በክዋኔው ነው፡፡ ፈጠራው ግን ግለሰባዊ ነው" በማለት ይገልጹታል" (ፈቃደ፣ 1992፣ 84-86)

ሰለሞን በበኩላቸዉ  የቃል ግጥሞች በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡ የሥነቃል ዓይነቶች ሲሆኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ስነልቦናዊ ሁነቶችን የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ቃልግጥም በሁሉም የማህበረሰብ ክፍል (በሰለጠነዉም ሆነ ባልሰለጠነዉም) ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን በድሮም ሆነ በአሁኑ ጊዜ የማኅበረሰቡን ማንነት በማሳየት ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክት ሕዝባዊ ጥበብና ማህበራዊ ሀብት ነዉ፡፡ ማኅበረሰቡ በዕለት ከዕለት የህይወት እንቅስቃሴዉ ወቅት የሚያስተውላቸውን ገጠመኞች፣ ከተፈጥሮ ጋር ባለዉ ግንኙነት ምክንያት የሚከሰቱ ገጠመኞችን፣ ያለውን ፍልስፍና፣ ዕዉቀት፣ አስተሳሰብ ወ.ዘ.ተ በቃል ግጥሙ አማካኝነት ለትዉልድ ያስተላልፋል፤ በወቅቱ የተሰማውንም ስሜት ይገልጽበታል በማለት ያስረዳሉ፡፡ (ሰለሞን፣ 2011፣ 129)

በተጨማሪም መስፍን፡- የቃል ግጥም ከሠው ልጅ ታሪክ ጋር የተቆራኘና ባህላዊ የመረጃና የዕውቀት መግለጫ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡ አንዳንዶች ቃል ግጥሞች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ እንደ ወቅቱና ሁኔታው የሚፈጥሩና ይዘታቸውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዬችን የሚዘረዝሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ቃል ግጥሞች የአንድ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የጋራ እሴቶች ተደርገው ይቆጠራሉ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ (መስፍን መሰለ፣ 2000)

ከላይ የቀረቡት የዉጭ ሀገር ምሁራን ሃሳብና ብያኔ የሚያመለክተዉ የአፍሪካ ሥነቃል መጠናት የጀመረዉ በአዉሮፓዉያን ተመራማሪዎች እንደነበረና ጥናታቸዉ ሥነቃልን ከየሀገራቱ በመሰብሰብና በማደራጀት ከራሳቸዉ ሀገር ሥነቃል ጋር ለማነጻጸር እና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዉ የሚያሥቡት ያልሰለጠኑት ማኅበረሰቦች ሥነቃል መነሻዉ እና መድረሻዉ የነሱ ሀገር ሥነቃል አንደሆነ ለማረጋገጥ ስለነበር የሥነቃሉን ትክክለኛ ምንነት፣ ባህርይ፣ ፋይዳ፣ ኪናዊ ለዛ የማያሳይ እንደሆነ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ ምሁራን ከአዉሮፓዉያን ጋር አብሮ በመስራት፣ የነሱን ጥናትና ሌሎች ስራዎች በማንበብ የራሳቸዉን ሀገር ሥነቃል ለማጥናት እንደተነሳሱና እነዚህ የአፍሪካ ምሁራን የራሳቸዉን ሥነቃል በራሳቸዉ ቋንቋ ማጥናት ሲጀምሩ ኪናዊ ለዛቸዉን፣ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳዉን ጠብቀዉ በማጥናት የአፍሪካን ሥነቃል ጥናት ወደተሻለና ከፍተኛ ደረጃ እንዳደረሱት መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻርም የሀገራችን ምሁራን የሥነቃል ጥናት መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ መጻሕፍትን በማሳተም በሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ትዉልድ እንዲማረዉ በማድረግና በርካታ ጥናቶችን በመስራት ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለቸዉ፣ ከዚህ አኳያ

ቃል ግጥም በተፈጠረዉ የሥነቃል ጥናትና ትምህርት ዉስጥ ትኩረት አግኝቶ እንደተሰራበትና የሕብረተሰቡን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ታሪካዊ እዉነታዎች በስፋት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ የሚለከታቸዉ አካላት ሁሉ ፋይዳዉን ተገንዝበዉ ወደፊትም ሊሰሩበት የሚገባ በመሆኑ ትኩረት ሰጥተዉ ሊሰሩበትና ሊገለገሉበት እደሚገባ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ጥናትም ይህንኑ ሃሳብና ስሜት የሚደግፍና የተፈጠረዉን ክፍተት ለመሙላት የተደረገ ነዉ።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በ2015 ዓ.ም ለEthiopian Oral Literature (ELAF 612) ኮርስ ከፊል ማሟያ ጥናት ለመስራት በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ የጥምቀት በዓል ከበራ ላይ በተደረገ ምልከታ እና ቃል ግጥሞችን የማሰባሰብ ስራ ከሀገራችን ነባራዊና ወቅታዊ እውነታዎች ጋር ተያይዞ የተዜሙት ቃል ግጥሞች ይዘትና አንድምታ የአጥኚዉን ስሜት አነቃቅቶታል፡፡ በመሆኑም በ2016 ዓ.ም ተጨማሪ ግጥሞች ተሰብስበዉ ቢጠኑ የዘመኑን መንፈስ እና የሕዝቡን ወቅታዊ ችግር፣ ፍላጎትና አመለካከት ሊያንጸባርቁ ይችላሉ የሚል የአጥኚዉ እምነት መኖር የመጀመሪያዉ አነሳሽ ምክንያት ነዉ፡፡

ይንን ተከትሎ መረጃ ለማሰባሰብ በተደረገዉ የተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ በአዲስ አበባ የጥምቀት በዓል አከባበር ላይ ቃል ግጥሞችን ከወቅታዊና ታሪካዊ ሁኔታ አንጻር የመሰብሰብና የማጥናት ስራ ስለመሰራቱ የሚያመላክቱ በቂ መረጃዎች አልተገኙም፡፡ በመሆኑም በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በሦሥት ታቦታት ማደሪያዎች የተዜሙ የሕዝቡን አመለካከት፣ ስሜትና ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ቃላዊ ግጥሞች ሰብስቦ በማጥናት ያላቸዉን ይዘትና ፋይዳ በመመርመር እንደ ጥናት በዘርፉ የተፈጠረዉን ጎዶሎ የመሙላት ፍላጎት የዚህ ጥናት ኹተኛዉ አነሳሽ ምክንያት ነዉ፡፡

Finnegan ቃላዊ ግጥሞች የወል ስሜትንና አንድነትን በማጠናከር፣ ቡድናዊ ወገናዊነትን ለማንፀባረቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ከማበርከት በተጨማሪ የቃል ግጥሞች ዐቢይ ተግባራት የሚባሉት አመፅን መግለፅ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድረግ እና ለውጥን ማበረታታት ናቸዉ በማለት ይገልጻሉ (Finnegan in Bauman 1992፡126)፡፡ በሀገራችንም ይህ ጥናት እየተጠና ባለበት በዚህ ወቅት ሰዎች ከመልካም አስተዳደር

ችግር የተነሳ አመለካከት እና ሀሳባቸዉን በጽሑፍም ሆነ በንግግር ለማንጸባረቅ የፍርሃትና የጥርጣሬ ስሜት እየተሰማቸዉ በመሆኑ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ቅሬታና ተቃዉሟቸዉን ሲያንጸባርቁ ይሰማሉ፡፡ በመሆኑም ይህንን ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል በነቂስ የሚታደምበትን የጥምቀት በዓል፣ ዘፈንና ጭፈራ እንደመተንፈሻና ማምለጫ በመጠቀም የሚዜሙ የህብረተሰቡን እዉነተኛ ስሜት፣ አመለካከትና ፍላጎት የሚያንጸባርቁ በርካታ ቃል ግጥሞች ማግኘት ይቻላል የሚል የአጥኚዉ ግምት መኖር ሦሥተኛዉና የመጨረሻዉ አነሳሽ ምክንያት ነዉ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት አንድ ዐቢይ እና አራት ዝርዝር ዓላማዎችን ለማሳካት የተደረገ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ዐቢይና ዝርዝር ዓላማዎቹ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ዝርዝር ዓላማዎች ጥናቱ ከሚመልሳቸዉ ጥያቄዎች ጋር የሚመሳሰሉ በመሆናቸዉ ጥናቱ የሚመልሳቸዉ የምርምር ጥያቄዎች በጥናቱ እንደ አንድ ክፍል አልተመላከቱም፡፡

### 1.3.1.የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በጥምቀት በዓል ላይ በአማርኛ የተዜሙ ቃላዊ ግጥሞችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን በባህላዊና ማህበረ ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ዉስጥ ያላቸዉን ይዘት፣ ፋይዳና አስተምህሮ መመርመር በዘርፉ ላይ ለሚሰሩ አካላት የተጠቃለለ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነዉ፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- ❖ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ የሕዝቡን ወቅታዊ አመለካከት፣ ስነልቦና፣ ስሜትና ፍላጎት የሚያጸባርቁ ማህበረ ፖለቲካዊ አንድምታ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞችን መሰብሰብ፡፡
  - ❖ ተሰብስበዉ በጭብጥና በተግበራቸው ተከፋፍለዉ የተደራጁትን የአማርኛ ቃል ግጥሞች የተዜሙበትን ይዘት፣ ፋይዳ እና አዉድ ጠብቆ መተንተን፡፡
  - ❖ ተደራጅተዉ የተተነተኑት የአማርኛ ቃል ግጥሞች በባህላዊና በማህበረ ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ዉስጥ ያላቸዉን ይዘትና ፋይዳ መመርመር፡፡

- በዘርፉ ላይ ለሚሰሩ አካላት ግብአት ሊሆን የሚችል የተደራጀ መረጃና የተጠቃለለ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ናቸዉ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 ዓ.ም እና በ2016 ዓ.ም የተዜሙ ቃል ግጥሞችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ይዘትና ፋይዳቸዉን ለመመርመር የተከናወነ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ወሰን በአራት መሰረታዊ ጉዳዮች ማለትም በቦታ፣ በጊዜ፣ በይዘት እና በክወና አጋጣሚ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ነዉ፡፡

**ከቦታ አንጻር፡-** በአዲስ አበባ በተለይም በየካ ክፍለ ከተማ የጥምቀት በዓል ላይ የሚኖረዉን የክወና አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ታላላቅ አባቶችና ቱሪስቶችን ጨምሮ ብዙሃኑን ምዕመናን ጨምሮ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና በርካታ ታቦታት (ለአብነት በ2016 ዓ.ም. 17 ታቦታት) የታደሙበት የጃንሜዳ ታቦት ማደሪያ፡፡ ከየካ ወረዳ 9 እስከ 12 የመጡ 8 ታዳሚዎችና አብያተ ክርስቲያናት (የአቡነ ተክለ ሐይማኖት፣ የኮተቤ ዳግማዊ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል፣ የአንቆርጫ ጊዮርጊስ፣ የቅዱስ ዑራኤል፣ የአንቆርጫ ቅዱስ አማኑኤል፣ የቅድስት ሃና፣ የየካ ቅዱስ ሚካኤል፣ የሲኤምሲ ቅዱስ ሚካኤል) የታደሙበት የእድር ሜዳ ታቦታት ማደሪያ፡፡

ከኮተቤ ካራና አካባቢዉ የመጡ 5 (የካራ መድሃኒዓለም፣ የቅድስት ሥላሴ፣ የቅድስት ኪዳነምህረት፣ የቅዱስ ጊዮርጊስና ቅድስት አርሴማ) አብያተ ክርስቲያናት እና ታቦታት የታደሙበት የካራ አርሴማ ታቦት ማደሪያ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዉ መረጃ ተሰብስቦባቸዋል፡፡

**ከጊዜ አንጻር፡-** የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ በሁለት ዙር ማለትም በ2015 እና 2016 ዓ.ም በጥር 10፣ 11 እና 12 በተከበሩት የከተራ፣ የጥምቀት እና የቅዱስ ሚካኤል በዓላት የክወና አጋጣሚዎች (አዉዶች) ላይ በመገኘት በታዳሚዎች በተለይም በወጣቶች የተቀነቀኑ የአማርኛ ቃል ግጥሞች በጥራት ተሰብስበዋል፡፡

**ከይዘት አንጻር፡-** መረጃዎች ሐይማኖታዊና ባህላዊ መሰረት ባላቸዉ የከተራ፣ የጥምቀትና የቅዱስ ሚካኤል ክብረ በዓላት ላይ በሚኖር የክወና አጋጣሚ (አዉድ) ላይ የተሰበሰቡ ቢሆንም ከሃይማኖታዊ መዝሙሮች ይልቅ የማህበረሰቡን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ፡- ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ስሜትና

ጥያቄዎችን የሚያንጸባርቁ በዘፈን በሆታና በጭፈራ የተቀነቀኑ ቃል ግጥሞች ብቻ ተሰብስበዋል፡፡

**ከክወና አጋጣሚ አንጻር፡-** ከሌሎች የክወና አጋጣሚዎች ሁሉ በተለየ መልኩ የጥምቀት በዓል በጠባብ አዉድ ዉስጥ ሳይሆን በአደባባይ የሚከወን ሕዝባዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓል ነዉ፡፡ በመሆኑም ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል፣ የዉጭ ሃገር ዜጎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ምዕመናን እንዲሁም ወጣቶች፣ ሴቶችና ወንዶች ኢአማንያንና የሌሎች እምነት ተከታዮች ጭምር ይታደሙበታል፡፡

እነዚህ አካላት ልዩ ልዩ ፍላጎቶቻቸዉን ለማሟላት የሚታደሙበት በመሆኑ ወቅታዊ የሆኑ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አተኩረዉ የሚቀነቅኑ ቃላዊ ግጥሞች ለሐይማኖታዊ በዓሉ ማድመቂያና ማጀቢያ ሆነዉ በኹለቱም ዓመታት የበዓሉ አከባበሮች ላይ ልዩ ትኩረትና ጫና ቢኖርባቸዉም በተለይ ወጣቶች ለጫናዉ ሳይንበከኩ በልባቸዉ የሰነቁት ወኔና ተልዕኮ በመበረታታት በርካታ ቃል ግጥሞችን አዚመዋል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዉስንነት

አዲስ አበባ ከተማ በርካታ ባህልና ቋንቋ ያላቸዉ በርካታ የሀገሪቱ ብሄረሰቦች የሚኖሩበት፣ ከተማ በመሆኑ በራካታ ቡድኖች በተለያዩ ቋንቋዎች በክወና አጋጣሚዉ ላይ በመገኘት በዘፈንና ጭፈራ ተሳትፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ በክፊለ ከታማዉ ዉስጥ ክዋኔዉ በተመሳሳይ ጊዜ የሚከናወን በመሆኑ ሁሉንም የበዓሉን አከባበር ሁነት በመመልከትና ከዚህ በላይ መረጃዎች መሰብሰብ አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት መረጃ በየካ ክፍለ ከተማ ሦሥት የታቦት ማደሪያዎች እና ሦሥት አብያተ ክርስቲያናት ጥምቀተ ባሕር ሲወርዱና ወደ መንበራቸዉ ሲመለሱ በአማርኛ ቋንቋ የተዜሙ ቃላዊ ግጥሞችን ብቻ በመሰብሰብ የተደራጀ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በሌሎችም የከተማይቱ ክፍሎች የሚዜሙትን ቃል ግጥሞች ሰብስቦ ማጥናት ቢቻል ጥናቱን ሁለንተናዊ ሊያደርገዉ ይችል ነበር፡፡

ሆም ግን ብዙሃኑ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያ፣ ታሪካዊ፣ ስነልቦናዊ እና ፖለቲካዊ ፍልስፍና፣ አኗኗር፣ አመለካከት፣ ፍላጎት እና ጥያቄ ያለዉ ከመሆኑም ባሻገር ቃላዊ ግጥሞች በባህሪያቸዉ በተወሰኑ ሰዎች፣ ቡድኖች፣ በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በተወሰኑ አካባቢዎች በቃል

ተፈጥረዉ ከአንዱ ሰዉ ወደሌላዉ ሰዉ፣ ከአንዱ ቡድን ወደሌላዉ ቡድን እና ከአንድ አካባቢ ወደሌላዉ አካባቢ በቃል የሚተላለፉ በመሆናቸዉ በሁሉም የከተማይቱ አካባቢና ማህበረሰቦች ተመሳሳይ ቃል ግጥሞች ሊዜሙ የሚችሉበት እድል ሰፊ በመሆኑ የጥናቱ ዉስንነት ጉልህ እንዳልሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

በታሪካዊ አጋጣሚ ይህ ጥናት እየተጠና ያለበት ወቅት የእርስ በርስ ጦርነት ድባብ ያጠላበት፣ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት የራቀበት እና የኑሮ ዉድነቱ ጣራ ነክቶ ህዝቡ በዘርፈ ብዙ ችግሮች የተሰቃየ ያለበትና ፍትህ ለማግኘት ድምጹን ባገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ እያሰማ ያለበት ነዉ፡፡ ስለሆነም በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ ቃል ግጥሞች እነዚህን የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ የሕይወት ገጽታዎች፣ ስሜትና አመለካከት የሚያንፀባርቁ በመሆናቸዉ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. የተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች በአግባቡ ተሰንደዉ እንዲቀመጡ በማድረግ በሥነቃል ጥናት ዉስጥ ቋሚ ሀገራዊ ሀብት ሆነዉ እንዲቀመጡ ለማድረግ እና የተዜሙበትን ዘመን መንፈስ ለማመላከት ያገለግላል፡፡
2. ሀገር በቀል ማህበረ ባህላዊ እሴቶቻችን ለዘላቂ ሰላም፣ ልማት፣ ለጠንካራ ሀገረ መንግስት እና ለህብረ ብሄራዊ አንድነት ግንባታ ለመጠቀም ያላቸዉን ፋይዳ ለማመላከት ሁነኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡
3. ጥናቱ ለሥነጽሑፍ፣ ለታሪክ፣ ለፖለቲካ፣ ለማህበራዊ ጉዳዮችና ለባህል፣ ተመራማሪዎች የማህበረሰቡን ሥነልቦና፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ ሕይወት፣ ወቅታዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የቃል ግጥም ፈጣሪዎችን ጥበባዊ የፈጠራ ብቃት እና ምናብ ለማጥናት የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
4. የሕዝቡ ባህላዊ፣ ስነልቡናዊ፣ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበረ ፖለቲካዊ ስሜት፣ አመለካከትና ጥያቄ በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ስለሚንፀባረቅ የሚመለከታቸዉ አካላት የማህበረሰቡን ጥያቄ፣ አመለካከት፣ ፍላጎት እና ችግር ተረድተዉ ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዉስጥ ጥናቱ ጠቃሚ ግብአት በመሆን የራሱ ሚና ይኖረዋል፡፡

5. በዘፈን፣ በሆታና በጭፈራ ዉስጥ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ከበዓል አከባበር፣ ከጭፈራና ከጨዋታ ማድመቂያ ባለፈ የማህበረሰቡን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን አጉልቶ በማሳየት ሕብረተሰቡ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለዉጥ እንዲያመጣና ስርዓታዊ ጫናዎችን በኪነጥበብ ሞሽሮ መቃወም እንደሚቻል ያስተምራል፡፡

## 1.7. የጥናቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአምስት አበይት ምዕራፎች እና በበርካታ ዝርዝር ንዑሳን ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕራፍ ዉስጥ የተዳሰሱ ነጥቦች እንደሚከተለዉ ተዘርዝረዉ ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ፡- የጥናቱ መግቢያ የቀረበበት ሆኖ በዉስጡም የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ ዐቢይና ዝርዝር አላማዎች፣ ወሰን፣ ዉስንነት፣ ጠቀሜታዎች፣ አደረጃጀት፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሂ አቅጣጫዎች፣ የመስክ ተሞክሮ እና የቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት ብያኔ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ኹለት፡- ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን የያዘ ሲሆን ክለሳ ድርሳናቱ የጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎችን እና የንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎችን ዳሰሳ የያዘ ነዉ፡፡ ምዕራፍ ሦሥት፡- የጥናቱን ንድፍ የያዘ ሲሆን የጥናቱ አይነት፣ ሥነ-ዘዴ የመረጃ ምንጭ፣ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና መሳሪያዎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ አራት፡- በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ እና የተሳበሰቡ የአማርኛ ቃል ግጥሞችን አደረጃጀትና ትንታኔን ይዟል፡፡ ምዕራፍ አምስት፡- የጥናቱን ማጠቃለያ ሐሳብና የአጥኚዉን አስተያየት (ይሁንታ) አጠቃሎ የያዘ ነዉ፡፡

## 1.8. ያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሔ አማራጮች

ይህ ጥናት እየተጠና ያለበት ወቅት በትግራይና በአማራ ክልል የታዩትን የእርስ በእርስ ጦርነቶች ተከትሎ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት የጠፋበት በመሆኑ የጸጥታ ኃይሉ በመሰል የክወና አጋጣሚዎች ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ወቅት ነዉ፡፡ ስለሆነም በከተራ፣ ጥምቀትና በቅዱስ ሚካኤል በዓላት ላይ ወጣቶች ድምጻቸዉን በዜማና በግጥም ለማሰማት ሲሞክሩ የጸጥታ አካላቱ ዘፈንና ጭፈራዎችን ለማስቀምና ወጣቶቹን የመበተን እና የጸጥታ ቁጥጥር ስራዉን በተደራጀ ሁኔታ ተጠናክሮ

ቀጥሏል፡፡ ስለሆነም ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮች መፍትሄ ሆነዉ ያገለገሉ አቅጣጫዎች እንደሚከተለዉ ተመላክተዋል፡፡

### 1.8.1. ያጋጠሙ ችግሮች

- የጥናት ስራዉ ከተጀመረና መረጃዎች ከተሰባሰቡ በኋላ በተፈጠረዉ የኩላሊት ጠጠር ህመም ምክንያት አጥኚዉ ሆስፒታል ገብቶ ኦፕሬሽን እንዲሰራ በሃኪሞች በመወሰኑ በተፈጠረዉ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ጥናቱን በተፈለገዉ ጊዜና ጥራት ለመጨረስ መስተጓጎሎች አጋጥመዉ ነበር፡፡
- የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ለማድረግ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሚገነዉ የጥናትና ምርምር ተቋም ደብዳቤ ከኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ በማጻፍ ዉስን ጥናቶችን መዳሰስ ቢቻልም በእድሳት ምክንያት ስራ በማቆሙ የተፈለገዉን ያህል ጥናት ለመዳሰስ አልተቻለም፡፡
- የጸጥታ አካላት በበዓሉ ላይ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸዉ ግጥምና ዜማዎችን በሚያዜሙ ወጣቶችና ቡድኖች ላይ ክልከላ፣ አፈሳና እስር በማካሄዳቸዉ ግጭቶች እያጋጠሙ ዘፈንና ጭራዎች ተቆራርጠዋል፡፡ በዚህም የመረጃ ቀረጻዉ ተስተጓጉሎ ነበር፡፡
- የክወና አጋጣሚቹ የሚገኙበት ቦታ ሰፊ በመሆኑ ባሉት ዉስን ቀናት በተመሳሳይ ሰዓትና ቀን ከሁሉም የክወናና የከበራ አዉዶች ላይ ተገኝቶ መረጃዉን ለማሰባሰብ የጊዜ፣ የቦታ፣ የቴክኖሎጂ እና የሰዉ ሃይል መጠነኛ ችግር አጋጥሟል፡፡
- በረዳት መረጃ ሰብሳቢዎች የተቀረጹ የተንቀሳቃሽ ምስልና የድምጽ መረጃዎችን ሰብስቦ ወደ ጽሑፍ ለመቀየር ሲሞከር አንዳንድ ግጥሞች የድምጽ ጥራት፣ የሐሳብ ግልጽነት ያለመኖርና ግጥሞቹ የተነገሩበትን አዉድ ለመረዳት አስቸጋሪ ሁኔታዎች አጋጥመዋል፡፡
- አንዳንድ አቀንቃኞ ጠንካራ ማህበረ ባህላዊና ፖለቲካዊ አንድምታ ያላቸዉ ቃል ግጥሞች መደርደር ሲጀምሩ ልዩ ተልዕኮ ወይም የእኔ ግጥም ከሌላዉ ቀድሞና በልጦ ሊሰማ ይገባል የሚል ስሜት ያላቸዉ የሚመስሉ አቀንቃኞች "ላግዘዉ ላግዘዉ ወንድሜን ላግዘዉ፣ ምነዉ እርሱን ብቻ ፍቅር ወዘወዘዉ" የሚለዉን ተለምዷዊ ጣልቃ አገባብ ስልት በመጠቀም በማቀንቀን ላይ ያለዉን ሰዉ የማቋረጥ እና የአቀንቃኝነቱን ቦታ የመረከብ ስራ በመስራት የመረባበሽ እና በቡድኖች

መካከል የመገፋፋት ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ይህም የመረጃ አሰባሰቡ ላይ ችግርና አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረዉ፡፡

## 1.8.2. የመፍትሄ አማራጮች

ከላይ የተጠቀሱት በርካታ ችግሮች አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይሰፉ ለማድረግ የሚያሥችሉ የመፍትሂ ሃሳቦች፣ አማራጮች እና አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተቀምጠዉ ችግሮችን ለማቃለል ተችሏል፡፡

- ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎችን ወደ እድር ሜዳ እና ጃንሜዳ ታቦት ማደሪያች በመላክ አጥኚዉ ብዙ ሰዎች በሚያዉቁትና ችግር ቢፈጠር እንኳን ማንነቱን አዉቀዉ ሊያሥረዱለት የሚችሉ ሰዎች በሚገኙበት በመኖሪያ አካባቢዉ ማለትም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አካባቢ በሚገኘዉ አርሴማ ታቦት ማደሪያ በመገኘት በልዩ ትኩረት የኦዲዮ ቪዥዋል ቀረጻ ለማድረግና የጽሑፍ ማስታወሻ ለመያዝ ጥረት ተደርጓል፡፡
- የሃኪምና የመስሪያ ቤት ፈቃድ በመዉሰድ የጤና ችግሩን በማስታመም በቤት ዉስጥ ቆይታ ጥናቱን ልዩ ትኩረት በመስጠት ለማጠናቀቅ ጥረት ተደርጓል፡፡
- የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ለማድረግ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘዉ ጥናትና ምርምር ተቋም በእድሳት ምክንያት ስራ ቢያቆምም በክፍያና በነጻ ከኢንተርኔት በማዉረድ በቂ ጥናቶችን ለመዳሰስ ተችሏል፡፡
- በተመሳሳይ ሰዓትና ቀን በሦሥቱም የክወናና የከበራ ቦታዎች ላይ ተገኝቶ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ስለማይቻል በአፈጻጸሙ ላይ ማብራሪያ ሰጥቶ ግንዛቤያቸዉን በማሳደግ ኹለት ረዳት መረጃ አሰባሳቢዎችን በክፍያና በነጻ በማሰማራት መረጃዎችን ቀርጸዉ እንዲመጡ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ድምጽና ምስል በጥራት መቅረጽ የሚችል፣ ከፍተኛ መረጃ የመያዝ አቅም ያለዉ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ማዘጋጀት፣ በጥራት መቅረጽ፤ በጥንቃቄ ማስቀመጥ እና በረዳት ሰብሳቢዎች የሚገኙ የተንቀሳቃሽ ምስልና የድምጽ መረጃዎችን በጆሮ ማዳመጫ በጥንቃቄ ደጋግሞ በማዳመጥ ወደ ጽሑፍ የመቀየርና ከመነሻ መረጃዎች ጋር የማገናዘብ ስራ በመስራት ችግርና ዉስንነቶችን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.9. የመስክ ተመክሮ

በዚህ ጥናት ላይ የተጠቀሱት የመስክ ተሞክሮዎች በመስክ ጊዜ ባጋጠሙ ተሞክሮዎች እና በተወሰዱ ወቅታዊ መፍትሄዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ይህም አንድ መስከኛ በመስክ ላይ እያለ ያልጠበቃቸው ገጠመኞች ሲከሰቱ በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ላይ ችግር እንዳያጋጥም እንዴት ማለፍ እንደሚችል ተሞክሮ ለማጋራት ከማሰብ የተነሳ የቀረበ ነው፡፡

የ2016 ዓ.ም የጥምቀት በዓል አከባበር በጸጥታ ስጋት፣ በመንግስትና በቤተክርስቲያን መካከል በተከሰተዉ አለመግባባት እና በጸጥታ ኃይሉ ስምሪት አወዛጋቢነት የተነሳ ገና ከዋዜማዉ አስቀድሞ የዉጥረት ድባብ የነገሰበት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በጥምቀት በዓል ላይ ከሚታደሙና በዓሉን ለማድመቅ በዘፈንና በጭፈራ ከሚሳተፉ አቀንቃኞች ግጥሞችን በመሰብሰብ ጥናት ለማድረግ ማሰብ ፈታኝ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡

የከተራና ጥምቀት በዓል ላይ የቁጥጥር ስራ ለመስራት ዕቅድ አውጥቶ ወደ ሥራ መግባቱን የገለጸዉ የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል “ፀረ-ሰላም ኃይሎች የበዓሉን አከባበር ድባብ ለማደፍረስ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ግጭት ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው መረጃዎችን እያሰራጩ ነው፡፡ ሰላም ጠል የሆኑ ቡድኖች አለን ለማለት ያላቸውን አቅም በመጠቀም ጉዳት ለማድረስ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ በበዓሉ አከባበር ብሄርን ከብሄር፣ ሐይማኖትን ከሐይማኖት፣ የሚያጋጩ ጭፈራዎች፣ አልባሳቶች፣ ጽሑፎች እና ግጭት ቀስቃሽ ተግባራትን አንታገስም” የሚል መግለጫ በማዉጣት ከፖሊስ፣ ከመከላከያና ፌደራል ፖሊስ በተጨማሪ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር በመዲናዋ የከተራና የጥምቀት በዓል ላይ ከጸጥታ ኃይሎች ጋር የሚሰሩ 15 ሺ.ሕ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ዝግጁ መሆናቸውን በመግለጽ ሂደቱን አክርሮታል።

ቅድስት ቤተክርስቲያንም የጸጥታ አካላትን በተመለከተ የጸጥታው አካላት የሀገራችንን ሰላም ባስጠበቀ መንገድ በዓሉን በማክበር የሀገራችንን መልካም ገጽታ ማሳየት ይቻል ዘንድ ከማንኛውም ቅሬታ ነፃ በሆነ መልኩ ኃላፊነቱን መወጣት ይገባዋል። በጠቅላይ ሚንስትሩ ላይ ዛቻ ያቀረቡትን ጳጳሥ ካላወገዛችሁ ግን እኛም በትብብር ለመሥራት እንቸገራለን በማለት የገለጹት ሀሳብ ከጥምቀት በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ መነሣቱ

አግባብነት የለውም ብለዋል። አዲስ አበባ፣ ጥር 08/2016 (ኢ.ዜአ)፦ የሊቃነ ጳጳሳቱ መግለጫ፡፡

በዚህ መልኩ ተልዕኮ የተሰጣቸዉ የጸጥታ አካላት 11/5/2016 ዓ.ም ከካራ አርሴማ ታቦት ማደሪያ ወደየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚመለሱትን የመድኃኒዓም፣ እና የሥላሴ ታቦት አጅበዉ የሚሄዱ ወጣቶች ካራ አደባባይ ላይ ሲደርሱ በበዓሉ ላይ እየዘፈኑ ይጨፍሩ የነበሩ ወጣቶችን ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸዉ ግጥምና ዜማዎችን አዚማችኋል በሚል ወጣቶችን በሰበብ አስባቡ ክልከላ በማድረግ መበተንና ማባረር ጀመሩ፡፡ በዚህም በበዓሉ ላይ ለማቀንቀን ለማጀብና ለመመልከት የተሰበሰበዉ ሰዉ ሁሉ ትዕይንቱን በግራ መጋባትና በጥጣሬ መከታተል ጀመረ፡፡

ዘፈንና ጭፈራ ለመጀመርም መፈራራት ጀመረ፡፡ ዘፈንና ጭፈራዉን ለማስጀመር አጥኚዉ ያዘጋጀቻዉ አቀንቃኞች ገራገሩን ተራ የፍቅር ጨዋታ እንዲጀመሩ በማድረግ ተመልካች ሆነዉ የቆሙትን የቱባ ባሕል ባለቤትና የጥበቡ ባለቤት የሆኑትን ወጣቶች ስሜት በመቀስቀስና በማደፋፈር ወደክዋኔዉ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከገቡ በኋላም የተዘጋጁት የአጥኚዉ ሰዎች በችሎታ የተበለጡ መስለዉ አጃቢና ከፊል ተሳታፊ በመምሰል መድረኩን ለባለቤቶቹ በማስረከብ አጥኚዉ የጥናት ስራዉን ለመስራት የሚያስችለዉን በቂ ቃል ግጥም ከማግኘት አልፎ ማንንም ሳይፈሩና ሳይጠረጥሩ በድፍረት የተቃዉሞና የዘለፉ ቃል ግጥሞች ጭምር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ሌላዉ በእድር ሜዳ ታቦታት ማደሪያ መረጃ ለማሰባሰብ የገብርኤልን ታቦት ተከትዬ ከሄድኩ በኋላ በክወናዉ ወቅት የፎቶና ቪዲዮ ቀረጻ ለማድረግ ተንቀሳቅሸ ስልኬን ሳወጣ ሁኔታዉን በጥጣሬ የሚመለከቱና የሚቃወሙ ጨፋሪ ወጣቶች ቀረጻዉን በመቃወም ቅጥ የለሽ ጭፈራ መገፋፋትና መከላከል ጀመሩ፡፡ ለተወሰነ ጊዜም ዘፈንና ጭፈራዉን አቋርጠዉ መበታተን ጀመሩ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ፖሊሶች የኔን ሞባይል ተቀብለዉ ከወሰዱ በኋላ ወጣቶቹን መልሳችሁ እንዳትሰባሰቡ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተዉ በታተኑን፡፡ ደግነቱ ቀድመዉ የተቀዱትን መረጃዎች በመገልበጥ ስለሰረዝኳቸዉና አዲስም ስላልቀረጽኩ ብዙ ችግር እንደማያጋጥመኝና ስልኬንም እንደሚመልሱልኝ ተስፋ አድርጌ ተለያየን፡፡

ዘፋኝና ጨፋሪ ወጣቶች ግን ይህን ሁኔታ ተመልክተዉ አጥኚዉን እንደሰላይ እና ቀረጻዉንም ለጸጥታ ቁጥጥር የሚዉል መረጃ አድርገዉ አስበዉ ስለነበር እንደገና ሲሰባሰቡ የግጥሙን ይዘት ቀይረዉ የምስጋናና ዉዳሴ፣ የፍቅር ዘፈኖችን መዘፈንና መጨፈር ጀመሩ፡፡ ይህኔ የተወሰኑ አግባቢ ሰዎችን በመጠቀም ማንነትና ለምን እንደምቀርጽ የማስረዳት እድል አግኝቼ ተነጋግረን ተግባባን፡፡ ነገርግን ሞባይሌ በፖሊስ የተያዘ ስለነበር በአካባቢዉ ሰዎች የተለየ አላማ እንደሌለኝና ማንነቴን ለፖሊስ አስረድቼ እንዲያዉም ወጣቶች የፖሊስ ሰላይ ነዉ በሚል ችግሩ እንደተፈጠረ ተግባብተን ስልኬን መለሱልኝ፡፡ የቀረጻ ስራዉንም በስኬት አጠናቀቅኩ፡፡

## 1.10. የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ

2. ሆታ፡- በህብረት የሚካሄድ በእስክስታ ሳይሆን ዱላ (በትር) ወዳላይ አቁሞ በመያዝ በፈጣን እንቅስቃሴ የሚደረግ የወንዶች የጭፈራና የዘፈን ክዋኔ ነዉ፡፡
3. ሞረሽ፡- የስም ምትክ፣ ስምን ወክሎ የሚገባ ህቡዕ መጠሪያ ነዉ፡፡ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አንድ ሰዉ በጭለማ፣ በዝናብና በአደጋ አጋጣሚ ዉስጥ ሲጠፋ በስሙ ቢጠራ ጠላት ወይም ሊያጠቃ የሚፈልግ ሰዉ ስሙን አዉቆ እንዳይከተለዉና እንዳያገኘዉ በዚህ ህቡዕ መጠሪያዉ ስም በሚፈልጉት ወገኖቹ ተራራ ላይ በመቆም ሞረሽ እየተባለ ይጠራል፡፡
4. በለስ ቀናዉ፡- አገኘ፣ ተሳካለት፣ ሆነለት፣ ጥሩ እድል አጋጠመዉ; ግዳይ ጣለ ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ ምሬ ወዳጆ የሚፈልገዉን እንዲያገኝ፣ የሚያስበዉ እንዲሳካለትና ጥሩ እድል እንዲገጥመዉ በዚህም ሰላሙ እንዲረጋገጥ ስለመመኘቱ ይነግረናል፡፡
5. በራይ፡- አበራዬ ከሚለዉ ግስ የሚወጣ ስም ነዉ፡፡ ትርጉሙም ወቃ፣ እህልን በከብት ማበራየት፣ በውድማ ላይ ጥሎ መውቃት። የሚለዉን ፍች ይይዛል፡፡ በፍካሬያዊ ትርጉሙ ግን ደበደበ፣ አብዝቶ መታ፣ በጦርነት አደቀቀ፡፡ የሚለዉን ፍች ይይዛል፡፡
6. አመክንዮ፡- ምክንያትን ወይም ምሳሌን ዐረቦንን መስጠት ሲሆን (በግዕዝ አመክነየ አመኻኘ) የሚለዉን ትርጉም ይወስዳል።
7. አስተምህሮ፡- በተወሰነ የዕዉቀት ዘርፍ ዉስጥ ያለ መሰረታዊ ሀሳብ፣ ትምህርታዊ ዉይይት፣ መርህ፣ እምነትና ቀኖና ማለት ነዉ፡፡

8. አረንዛ፡- ውስጣውስጡ ረግረግነት የሚሰማው፣ ውኀማ መሬት ማለት ነዉ። በግጥ ዉስጥ ካለዉ አዉዳዊ ትርጉም አንጻር ጠላትን በገባበት የሚያስቀር ጀግና፣ ኃይለኛና ኀበዝ የሚለዉን ያመለክታል፡፡
9. አንድምታ፡- አንድን ቃል፣ አባባልና ሃሳብ በተለያዩ መንገድ አብራርቶና ዘርዝሮ ትርጉምና ምስጢሩን መተርጎሚያ ስልት፣ የአተረጓጎም አዉድ ነዉ፡፡
10. አዉድ፡- ቃሉ በቁሙ ያለዉ ፍች አደባባይ፣ ሸንጎ፣ የህዝብ መሰብሰቢያ አጋጣሚ፣ ሁነትና ቦታ ሲሆን በጥናቱ ዉስጥ አውድ የክዋኔ ገፅታ ወይም ድባብ ነው ስለሆነም ድርጊቱ የሚከናወንበት ሁኔታ፣ ጊዜና ቦታ ወይም መቼት የሚያሳይ ነው::
11. እሴት፡- በሥነ ልቦና፣ በማህበራዊ፣ በሥነ ምግባራዊ ወይም በውበት ግምት ምክንያት አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰበው ማንኛውም ባህሪ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አንድ ነገር የሚገባውን ባህርይ መያዙን፣ የአንድ ነገር አስፈላጊነት፣ ዋጋ ወይም ጥቅም የሚያመለክት ጸጋ ነዉ፡፡
12. ዶለተ፡- በደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሰበሰበ፣ አደመ፣ ከንቱ አሳብ አሰበ፣ ክፉ ምክር መከረ፣ አሴረና ነገር ቋጠረ ማለት እንደሆነ ያስረዳል፡፡
13. ጃሎ፡- በስም ምትክ የሚገባ፣ ልጅ የሚለዉን ቃል የሚወክልና ጦረኛ፣ አርበኛ፣ ጀግና የሀገሩን ድንበርና ሕዝቡን የሚጠብቅ ህዝቡም በተስፋ የሚጠብቀዉ ወጣት ነዉ፡፡
14. ጋሜ (ጋሞቹ)፡- የሚለዉ ቃል ጥሬ ትርጉሙ ልጆች፣ ጓደኞቹ፣ ወጣቶች የሚለዉን እሳቤ የሚያመላክት ነዉ፡፡ ጋሜ ከጸጉር አለጫጨት ጋር የተያያዘ ስያሜና አጠራር ነዉ፡፡ የአንበሳ ጋማ እንዲሉ:: መሃሉን ተላጭቶ ዳድዳሩ ያደገ ጸጉር ያለዉ ልጅ፣ አሽከር ማለት ነዉ፡፡ ጸጉሩ ሲያድግ ይጎነጎናል፡፡ ይህም የጀግንነት መገለጫ ይሆናል፡፡ አያችሁት ቢያ ይህንን እብድ፣ ሁለት ጋሜ ሆኖ ጉራምባ ሲወርድ ተብሎ ለዳግማዊ ዓጼ ቴወድሮስ እንደተዘፈነ ልብ ይሏል፡፡
15. ዘገር፡- ንጉሥ፣ መስፍን፣ መኰንን ወደ ውጭ ሲወጣ ጋሻ ዣግሬው ከኋላ ከኋላ ሲከተል የሚሸከመዉ ከብረት የተሠራ ትልቅ ጦር፣
16. ርሽርሽ፤- ጥጋብ፣ ጸጋና በረከት የሞላበት ሞልቶ የተረፈዉ፣ አዝዕርት በየዓነቱ የሚመረትበት አካባቢ ነዉ፡፡

# ምዕራፍ ኹለት

# ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ስር ክለሳ ድርሳናት እና በርሱም ስር የተዳደሱት ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎች እና ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፎች ሲሆኑ በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተዉ የምሁራንን አስተሳሰብና እና ብያኔ መሰረት በማድረግ ሰፊ ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር በሌሎች ተመራማሪዎች የተጠኑና ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ተመሳስሎ እና ተቀራራቢነት ያላቸዉን ጥናቶች ዳሰሳ በማድረግ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸዉን ተመሳስሎና ልዩነት፣ ድክመትና ጥንካሬ፣ እንዲሁም የተወሰደባቸዉን ተሞክሮ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2.1. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎች እና ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፎች ማብራሪያ የሚሰጥ ሲሆን ከጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎች የቃል ግጥም ምንነት፣ ባህርያት፣ ዓይነቶችና ፋይዳዎች፤ የቃል ግጥም መሰረታዉያን፤ የክብረ በዓላት ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያትና ፋይዳዎች እንዲሁም ከክብረ በዓላት ዉስጥ የጥምቀት በዓል ምንነት፣ አጭር ታሪክ እና ፋይዳዎች እንዲሁም ከንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፎች ዉስጥ ተግባራዊና የክዋኔ ንድፈ ሃሳቦች የምሁራንን ብያኔ መሰረት በማድረግ ተብራርተዋል፡፡

### 2.1.1. የጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ የሆኑት የቃል ግጥም ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያት፣ ፋይዳና የቃል ግጥም መሰረታዉያን፤ የክብረ በዓል ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያና ፋይዳ፣ የጥምቀት በዓል ምንነት፣ አጭር ታሪክ፣ ወቅታዊ አከባበርና ፋይዳዎች በዝርዝር ይቃኛሉ፡፡

#### 2.1.1.1. የቃል ግጥም ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያት እና ፋይዳዎች

ከስነቃል ጥናት ጋር ተያይዞ በተፈጠረው አጋጣሚና ምቹ ሁኔታ የዚህ ጥናት ዋነኛ ማጠንጠኛ የሆነዉን የቃል ግጥም ለይተው ለማጥናት የሞከሩት የሙዚቃ ባለሙያዎች ሲሆኑ እነዚህ ተመራማሪዎች በርካታ የዘፈን ግጥሞችን መሰብሰብና ማጥናት

በመጀመራቸው ትኩረት ያላገኘውን የስነቃል ዘርፍ የማጥናት ተነሳሽነት በወቅቱ ታይቷል፡፡ (Finnegan 1970:42) ስለቃል ግጥም በበቂ ሁኔታ ያለመጠናትና ስለዘርፉ ያላቸውን ስሜት በሌላዉ መፅሀፋቸው መቅድም ውስጥ መስኩ በጣም የበለጸገ እና አስደሳች ነገር ግን የተረሳ /የተተወ/ መስክ በመሆኑ ምሁራን በራሳቸው ቋንቋ በሚያደርጉት የተሟላ የጥናት ሁኔታ የቃል ግጥምን ጥናት ወደተሻለ ደረጃ ሊያደርሱት ይችላሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡ (Finnegan 1977፡ x-xii)

### 2.1.1.1.1. የቃል ግጥም ምንነት

የቃል ግጥምን ምንነት አስመልክቶ ድንጋጌ ለመስጠት በርካታ ምሁራን ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች እንደሆነ ጠቅሰዉ ቃላዊ ግጥም በአንዳንድ የስነቃል ተመራማሪ ስራዎች ውስጥ ብያኔ የተለያየ ሆኖ ይገኛል በማለት ለአብነት የሦሥት ምሁራንን እይታ አመላክተዋል፡፡ (ፈቃደ አዘዘ 1991፣ 84)

Ben Amos (1982፡ 20-22) "ሥነጽሑፍና ሀገረሰባዊ ስነጽሁፍ" በማለት ባቀረቡት ገለፃ ውስጥ "ከሰለጠኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር የሀገረሰብ ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግጥም ነው"

Finnegan ቃል ግጥም የሰው ልጅ በአምዕምሮው የሚያስበዉን፣ በአይኑ አይቶና በጆሮዉ ሰምቶ የተገነዘበዉን፣ በአካባቢና በህይት ዘመኑ ያጋጠመዉን ሁሉ የሚገልጽበት እና ለሌላዉም የሚያስተላልፍበት በመሆኑ በቃል ግጥም ሀሳብን ለማስተላለፍ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ልጅ አዋቂ የሚል ውሳኔ የለም፡፡ የሰው ልጅ ሀሳቡን ለሌሎች በቃል ማስተላለፍ ተፈጥሯዊና የዕለት ተዕለት ኑሮዉ ፍልስፍና አካል ስለሆነ ዘወትር ከሰው ልጅ የማይነጠል ተግባር እንደሆነ፤

ስራን ለማቀላጠፍ፣ ራስንና ታዳሚን ለማዝናናት፣ ባህልና ታሪክን ለማቆየት፣ ድጋፍና ተቃውሞን ለማንጸባረቅ፣ ስሜትና ፍላጎትን ለመግለጽ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር፣ እንዲሁም ለማስተማር፣ ለመተቸት፣ ስርዓትን ለመገንባትና ለማፍረስ፣ መልዕክትን ለማስተላለፍ፣ የህይወት ፍልስፍናቸዉን የሚገልፁበት የሕይወታቸው፣ የኑሯቸዉና የማንነታቸው መገለጫ እና ተዝቆ የማያልቅ ሀብታቸዉ ስለመሆኑ፤

እንዲሁም በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት የሚታዩ በደሎችን፣

ጭቆናዎችን፣ ለማንፀባረቅ፣ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችና አስተዳዳሪዎች አስፈሪ በሚሆኑበት ጊዜ ስሜትን እና ፍላጎትን እንዲሁም ብሶትን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ:: በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሚፈጠሩ አለ-ታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን በአደባባይ አውጥቶ መናገር በማይቻልበት ሁኔታ ቃላዊ ግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል በማለት ይገልጹታል፡፡ (Finnegan 1977፡ 223-227)

የሐገራችን ምሁራን ብርሃኑ፣ ፈቃደ፣ ሰለሞንና መስፍን በበኩላቸዉ ስለ ቃላዊ ግጥም የራሳቸዉን ብያኔ በሚመለከት ተቀራራቢ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ለምሳሌ ቃላዊ ግጥምን "ቃላዊ ግጥም ሙዚቃዊነት በሚሰማባቸው በዘፈን፣ በቀረርቶ፣ በእንጉርጎሮ፣ ወ.ዘ.ተ. የሚከወኑ ጥበቦችን የሚያጠቃልል ነው" በማለት እጅጉን የሚዘወተር፣ በጣሙን ደግሞ ልዩ ልዩ መልኮች ያሉት ጥበብ በመሆኑ እያንዳንዱን ዘፈን፣ እንጉርጉሮ፣ ቀረርቶ፣ ከሌላው ጋር ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ እንደሆነና ቃላዊ ግጥምን ለመመደብ መሰረታዊ የሚሆኑት መንገዶች ቀያዊ ስያሜዎች፣ ጭብጦች እና አውዶች ስለመሆናቸዉ ይገልጻሉ፡፡ (ብርሃኑ፣ 1995፣ 31)

ፈቃደ በበኩላቸዉ "ቃላዊ ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮ እና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው" በማለት "ህዝባዊ ግጥም" የሚለው ቃላዊ ግጥምን ማንኛውም የዚያ ቡድን ወይም ማህበረሰብ አባል የሆነ ሁሉ፣ ችሎታው እስከፈቀደለት ድረስ እያስታወሰ፤ እየጨመረ፤ እየቀነሰ ሊያዜመው እንደሚችል የሚያመላክት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ህዝባዊ ባህሪ ሊኖረው የሚችለው በተስተላልፎው እና በክዋኔው እንደሆነና ፈጠራው ግን ግለሰባዊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ (ፈቃደ፣ 1992፣ 84-86)

የቃል ግጥሞች በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡ የሥነቃል ዓይነቶች ሲሆኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ስነልቡናዊ ሁኑቶች የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ቃልግጥም የማህበረሰብ ክፍል (በሰለጠነዉም ሆነ ባልሰለጠነዉም) ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን በድሮም ሆነ በአሁን ጊዜ የማህበረሰቡን ማንነት በማሳየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት የጥበብ አይነት ነዉ፡፡ የቃል ግጥም የማህበረሰቡን ባህል መሰረት በማድረግ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በግለሰብም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በዕለት ከዕለት የህይወት እንቅስቃሴዉ

ወቅት የሚያስተውላቸውን ገጠመኞች፣ ከተፈጥሮ ጋር ባለዉ ግንኙነት ምክንያት የሚከሰቱ ገጠመኞችን፣ ያለውን ፍልስፍና፣ ዕዉቀት፣ አስተሳሰብ ወ.ዘ.ተ በቃል ግጥሙ አማካኝነት ለትዉልድ ያስተላልፋል፤ በወቅቱ የተሰማውንም ስሜት ይገልጽበታል፡፡ (ሰለሞን፣ 2011፣ 129)

የቃል ግጥም ከሠው ልጅ ታሪክ ጋር የተቆራኘና ባህላዊ የመረጃና የእውቀት መግለጫ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡ አንዳንዶች ቃል ግጥሞች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ እንደ ወቅቱና ሁኔታው የሚፈጥሩና ይዘታቸውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዬችን የሚዘረዝሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ቃል ግጥሞች አንድን አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የጋራ እሴቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ (መስፍን፣ 2000፣)

የቃል ግጥምን ምንነት አስመልክቶ ድንጋጌ ለመስጠት በርካታ ምሁራን ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች እንደሆነ ጠቅሰዉ ቃላዊ ግጥም በአንዳንድ የስነቃል ተመራማሪ ስራዎች ውስጥ ብያኔ የተለያየ ሆኖ ይገኛል ፡፡ (ፈቃደ አዘዘ 1991፣ 84) በማለት ዶክተር ፈቃደ እንደገለጹት ከላይ ለአብነት ከተጠቀሱት ከነዚህ ምሁራን እይታና ብያኔ የምንረዳዉ የቃል ግጥምን ምንነት፣ ባህርያትና ፋይዳ ከመረዳት አንጻር ምሁራን ያላቸዉ ግንዛቤ የተለያየና ለጥናት ከተነሱበት ዓላማና ግብ ጋር የተያያዘ አሉታዊና አዎንታዊ ብያኔ ተሰንዝሮ እናገኛለን፡፡

ለአብነትም Finnegan ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል የተባለዉን የአፍሪካ ሥነቃልና ቃል ግጥም ጠለቅ ብለዉ ያጠኑ በመሆናቸዉና እዉነታዉን በሚገባ ለመገንዘብ በመቻላቸዉ፣ አወንታዊ ብያኔ ለመስጠት እና የተገነዘቡትን እዉነታ ለመጻፍ መቻላቻዉን እንረዳለን በአንጻሩ ደግሞ Ben Amos "ከሰለጠኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር የህገረሰብ ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግጥም ነው" በማለት አሉታዊና የቃል ግጥምን ባህርይ እና ፋይዳ ያላገናዘበ ብያኔ ሰጥተዉት እንገኛለን፡፡

"የአፍሪካ ተመራማሪዎች ሌሎች አውሮፓውያን ተመራማሪዎች ሳያስተዉሉት የቀሩትን ጉዳይ መመርመር በመቻላቸው ገለፃቸውና ትንተናቸው ስፋትና ጥልቀት ያለዉ ለመሆን ችሏል፡፡ (Finnegan 1970፡ 43) በማለት ያስቀመጡት ብያኔም ይህንኑ የሚያመላክትና በተለይም የሃገራችን ምሁራን የቃል ግጥም አይነቶች ከሚቀርቡበት

ማህበራዊ አውድና አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ የፍቅር፣ የምርቃት፣ የሰርግ፣ የልቅሶ፣ የእንቁጣጣሽ፣ የሥራ፣ የፉከራ፣ የእሰጥ አገባ፣ የቀረርቶ፣ የዕረኛ፣ የበገና፣ የክብረ በዓል፣ የአዉሎና የጌርጌርሳ ወ.ዘ.ተ በሚል የተሻለ ብያኔና የዓይነት አደረጃጀትና ምደባ አድርገዋል፡፡ ይህም Okpewho (1992፡ 127-138) የቃል ግጥምን “ዘፈኖችና መዝሙሮች” በሚል በጥቅሉ ካስቀመጡት ብያኔ ሰፋ ያለና ጥልቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም ሆኖ ግን በሀገር ዉስጥ ምሁራን የተሰጠዉ ብያኔም ሰፊ ልዩነት እንዳለዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ይህንን ልዩነት በማጥበብ ብዙሃኑ የሚስማሙበት የቃል ግጥም አይነትና ብያኔ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነዉ፡፡

#### 2.1.1.1.2. የቃል ግጥም ዓይነቶች

የቃልግጥም አይነቶች የሚባለት፣ ኤፒክ፣ ባሊድ፣ እና ሌሪክ ናቸው:: ኤፒክና ባላድ ረጃጅሞችና በተወሰነ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ሲሆኑ፣ ሌሪክ ግን በአንፃራዊነት አጭርና ተራኪ ያልሆነ፣ በሰው ልጅ ባህል ውስጥ በስፋት ተሰራጭቶ የሚገኝ፣ ምናልባትም ዓለማቀፋዊ ቅርፅ (አይነት) ነው:: ሌሪክ ከዓለማቀፋዊነቱ በተለየ፣ አፍሪካ ውስጥ በሰፊው እንደሚገኝ እንዲህ በማለት ይገልጹታል “ከስሀራ በታች ባሉት የአፍሪካ አገሮች ምናልባት በብዛት የሚገኘው የግጥም ቅርጽ ሌሪክ ነው። ሌሪክ አጭርና የሚዘፈን ሆኖ፣ ከአፍሪካ የስነቃል አይነቶች አንዱና በጣም ጠቃሚው ነው” (Finngan 1970፡ 241)

እንደነዚህ አይነት ቅርፆች በኛ ሀገር በጥቅሉ ይገኛሉ ተብሎ ስለማይታሰብ ስለቃል ግጥም አፈጣጠርና ስርጭት ስናስብ ከራሳችን አውድ ጋር የተገናዘበ ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ በእኛ ሐገር እያንዳንዱ አጋጣሚና ክስተት፣ የየራሱ ቃልግጥም ይገጠምለታል ወይም ይገጠምበታል፡፡ በየዘመኑ የሚገኙት ገጣሚዎች አዉዳዊ ክስተቱን፣ በአጠቃላይ የዘመኑን መንፈስ፣ መነሻ አድርገው ቃልግ ጥሞችን ይፈጥራሉ:: እንደነዚህ አይነት የዘመን አሻራ ያረፈባቸው ወይም የሚንፀባረቅባቸው ቃል ግጥሞች ለታሪክ ማጣቀሻነት ያገለግላሉ፡፡ (አማረ 2009፣ 46)

በቃል ግጥም ስር የሚመደቡ ጥበቦች በአብዛኛዉ በቃል ተደርሰዉ በተለያዩ የአከዋወን ስርዓች ታጅበዉ በቃላዊ ተስተላልፎ በአጭር የግጥም ቅርጽ ከትዉልድ ወደትዉልድ የሚተላለፉ ናቸዉ፡፡ በዚህ ዘርፍ ስር የሚመደቡ ሎሮች በርካታ ናቸዉ፡፡ እነዚህንም የቃል ግጥም አይነቶች ከሚቀርቡበት ማህበራዊ አውድና አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ

የፍቅር፣ የምርቃት፣ የሰርግ፣ የልቅሶ፣ የእንቁጣጣሽ፣ የሥራ፣ የፉከራ፣ የእሰጥ አገባ፣ የቀረርቶ፣ የዕረኛ፣ የበገና፣ የክብረ በዓል፣ የማሰ፣ የአዉሎና የጌርጌርሳ ወ.ዘ.ተ. በሚል መመደብ ይቻላል፡፡ (ሰለሞን 2011፣ 129)

Okpewho (1992፡ 127-138) የቃል ግጥምን ሁኔታ በሰፊው የመረመሩበትን ክፍል ስናየው ስያሜያቸው "ዘፈኖችና መዝሙሮች" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይሁን እንጂ የሀገራችን የቃል ግጥም ዓይነቶች እርሳቸዉ ከጠቀሱት በተጨማሪ ሙሾ፣ ቀረርቶና ፉከራ፣ ሆታና እንጉርጉሮ የሚሉትን የሚጨምር በመሆኑ ሰፊ ልዩነት አለዉ፡፡ ይሁን እንጂ ከእርሳቸዉ ብያኔ ጋር የተጣጣሙና ከክብረ በዓላት ዉስጥ አንዱ በሆነዉ የጥምቀት በዓል ላይ በዘፈን መልክ የተዜሙት ቃላዊ ግጥሞች ተሰብስበዉ ከተተነተኑ በኋላ ይዘትና ፋይዳቸዉን ለማመላከት ተሞክሯል፡፡

የሰው ልጅ ሁለት አይነት ሀብት አለው። ቁሳዊ እና መንፈሳዊ። የሚዳሰስና የማይዳሰስ፤ ሁለቱም ካላቸው ጥቂት አገራት መካከል ደግሞ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። የሚዳሰሱም የማይዳሰሱም ቅርሶች አሏት፤ ለዛውም የትየለሌ። አጥኚዎች "ፀጋ" ሲሉ የሚጠሩትም ይህንኑ ሰብአዊና ማህበራዊ ሀብት ነዉ። ከእነዚህ ከፈጣሪ ለሰዉ ልጅ ከተሰጡትና ለትዉልድ ከሚያወርሳቸው የማንነቱ መገለጫዎች እሴቶቹ አንዱ መንፈሳዊ ሀብቱና ጥበባዊ ጸጋዉ የሆነው ቃላዊ ግጥም የሕዝብ ነው፤ ሲወርድ ሲወራረድ በሕዝብ ቅብብሎሽ እዚህ ዘመን የደረሰ:: የአንድ ደራሲ ብቸኛ ውጤት አይደለም፤ የሕዝብ ስሜት ነው:: የየዘመኑን የሕዝብ ስነ ልቦና ያሳያል፤ ስለዚህ ትክክለኛውን የማህበረሰቡን ስነ ልቦና ይወክላል ማለት ነው::

### 2.1.1.1.3. የቃል ግጥም ባህርያት

ቃል ግጥሞች የአንድ ማህበረሰብ ስሜት ውዴታና ጥላቻ፣ ሃዘንና ደስታ፣ ተስፋና ምኞት አይረሴ በሆነ ገለፃ የሚያፀባረቅባቸዉ የህዝብ ሃብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የህዘብ ሃብቶች ደግሞ በጋራ ተፈጥረው በጋራ የሚከወኑ ሲሆኑ የአከዋዎን ስልታቸው እንደ ሚከወንበት አውድ፣ ምክንያትና አጋጣሚ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የቃል ግጥሞች የራሳቸው የሆነ መገለጫ ባህርይ አላቸው፡፡ አይረሴ፣ ዘያዊ፣ ቁጥብና ፈጠራዊ የሆኑ፣ተከታታይነትና ተደጋጋሚነት እንዲሁም እንደሚከዎንበት አውድ ደግሞ የተለዋዋጭነት ባህርይ እንዳላቸው ይገለፃል፡፡ (ሀና፣ 2015፣ 24)

የቃልግጥም ቃላዊ ቴክስት አለው፡፡ ነገር ግን ወደተሟላ ደረጃ እንዲደርስ ከተፈለገ መከወን አለበት፡፡ ቴክስት ብቻውን ቃል ግጥሙን የተሟላ አያደርገውም፡፡ ይህ የቃል ግጥም ዐቢይ ገፅታ፣ ብዙዉን ጊዜ እየተረሳ መጥቷል ቃላዊ ባህሪያቱ ማለትም ስሌቱ፣ ይዘቱ፣ ምናባዊነቱ፣ ተስተላልፎው፣ ወሳኝ ቢሆኑም ክዋኔ ግን ከሁሉም በላይ ሙሉ ያደርገዋል፡፡ እንዳይጠፋና ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ እንደ አጠቃላይ ግን በቃል ግጥም ዉስጥ የከዋኙ ክሂልና ስብዕና፣ የታዳሚው አይነትና የክዋኔ አውዱ ጠቃሚ ናቸው፡፡ (Finnegan 1977፡ 28-29)

ቃል ግጥም በባህሪዉ ሳይጻፍ በህሊና ታስቦ በቃል የተፈጠረ፣ ሳይጻፍ በምልዓት እየኖረ ትውልድና እና ድንበር የሚሻገር የማኅበረሰብ ጥበባዊ ሀብት ነው፡፡ የጋራ ስለሆነም የጋራ ተቀባይት ያለው ተፈጥሮ አለው፤ በባህርይና በተፈጥሮዉ አያፈነግጠም፣ የትኛዉንም ከባድ ስሜትና አጋጣሚ ለመግለጽም አይደነግጥም፡፡ ባለማፈንገጡ ከማኅበረሰቡ እውነታዎች ውጭ አይዘልም፣ ባለመደንገጡ የማኅበረሰቡ የሆኑ እውነታዎችን ችላ ብሎ አያልፍም፡፡ ስለሆነም ታሪክን ቀርጾ ያስቀምጣል፣ የጋራ የሆነ ባህልን ያስቀጥላል፣ ትውልድን ከትውልድ ያጋምዳል፡፡ ቃል ግጥም የማኅበረሰብ ሀብት ነው፤ ስለዚህም የትም ተመስርቶ እስከየትም ሊጓዝ ይችላል፤ የጉዳይ ገደብ የለበትም፣ ስለዚህም የፈለገውን ነገር ሊያነሣ ይችላል፤ ነገር ግን የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡

## 2.1.1.1.4. የቃል ግጥም ፋይዳ

የቃል ግጥሞች ለከዋኝ ማህበረሰቡ እንደሚከውኑት ዓላማ የራሳቸው ፋይዳ አላቸው፡፡ ቃል ግጥም መረጃን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያቀብላል፡፡ ባህልን፣ ወግን ጠብቆ ለማቆየት ያገለግላል፡፡ ስነ ምግባርን ለማስተማር፣ ከአስቸጋሪ ሁኔታ ለማምለጫነት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ስንፍናን በመንቀፍ፣ የደከመ አእምሮን ለማበረታት ስራን ያለመሰልቸት ለመስራት ያስችላል፡፡ (finnegan 1977፡ 3-7)

በተጨማሪም ፖለቲካዊ ይዘት እና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች በአንድ ቡድን አባላት መካከል በሚከወኑበት ጊዜ የቡድኑን የጋራ ስሜትና አንድነት ከማጠናከር አልፎ ተቀናቃኞችን ለመቃወም ይረዳሉ:: ቡድናዊ ስሜትን እና አንድነት በማጠናከር ቡድናዊ ወገናዊነትን ለማንፀባረቅ ቃላዊ ግጥሞች ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ (Finnegan 1977፡ 217-221) በማለት የመግለጻቸዉም በተጨማሪ የቃላዊ ግጥምን

ፋይዳ ወይም ተግባር በሚመለከት (Finnegan in Bauman 1992፡ 126) ላይ ጠቅለል ባለ መንገድ የቃላዊ ግጥም ተግባር በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ እነሱም አመፅን መግለፅ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድረግ እና ለውጥን ማበረታታት ናቸው፡፡ በማለት ያብራራሉ፡፡

ሥነቃል በፖለቲካው መስክ በአንድ በኩል ገዢው ስርዓቱን የሚያስከብርበት፣ በአንፃሩ ደግሞ ተገዢው በገዢው ላይ ያለውን ብሶት የሚገልፅበትም ነው፡፡ ህዝብ ስልጣን ላይ ስላለው መንግስት አስተዲራዊና ፖለቲካዊ ስርዓት የተሰማውን ስሜት፣ የሚመኘውን አይነት አስተዳደር የሚገልጽበት ነው፡፡ ገዥው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ህዝብ ጥላቻውን ይገልፅበታል፤ መልካም ከሆነ ደግሞ ያወደስበታል፡፡ ስነቃል ከተለለያዩ የልማት ፖሊሲዎችም ጋር በማያያዝ የህዝቡን ፍላጎት በማጥናትና በህዝቡም ውስጥ የቅስቀሳ ስራ ለመስራት የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ በስራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችንም ለማጥናትና በጊዜ ለመፍታት መንገድም ይከፍታሉ፡፡ (ፈቃደ 1995፣ 17-20)

በዚህ ሂደትና እንቅስቃሴ የቃላዊ ግጥሞቹ ይዘት፣ ብዙ ጊዜ ሙገሳና ውደሳ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ድርጊቶች እና አስተሳሰቦች የሚተቹበት አጋጣሚ የሚፈጠርበት ይሆናል፡፡ የሙገሳና የውዳሴ ግጥሞች በተለይ በማህበረሰቡ ዘንድ፣ ማህበራዊ እውቅና ያላቸውና መልካም እና ደግ የሚባሉ እሴቶችን ለተላበሱ አባላት ማወደሻ እና ማሞገሻ ስለሆኑ የማህበረሰቡ አባላት እነዚህን ተግባራትና እሴቶች አውቀው እንደነሱ እንዲሆኑ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ እና እድል የሚፈጠርበት አጋጣሚም ይሆናል፡፡

ቃላዊ ግጥሞች ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማንፀባረቅም ይጠቅማሉ፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በሚታዩ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ይዘትና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገጠማሉ፣ ይዘፈናሉ:: ትኩረታቸውም ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፌጠርና፣ ለቅስቀሳ ሆኖ፣ የህዝብን አመለካከት ማንፀባረቅ ይሆናል፡፡ ስድብ አዘልና ምፀታዊ ቃላዊ ግጥሞች ለፖለቲካ ተግባር በሚውሉበት ጊዜ እንደ ጦር መሳሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: በአንፃሩም፣ ለፖለቲካዊ ግፊት መፍጠሪያ፣ ወ.ዘ.ተ. ይሆናሉ፡፡ (Finnegan 1970፡ 272-284)

ቃል ግጥሞች ፖለቲካዊ ይዘት እና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች በአንድ ቡድን አባላት መካከል በሚከወኑበት ጊዜ የቡድኑን የጋራ ስሜትና አንድነት ከማጠናከር አልፎ ተቀናቃኞችን ለመቃወም ይረዳሉ፡፡ ቡድናዊ ስሜትን እና አንድነት በማጠናከር ቡድናዊ ወገናዊነትን ለማንፀባረቅ ቃላዊ ግጥሞች ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ (Finnegan 1977፡ 217-221)

በማህበርሰብ ዘንድ የሚታዩ ልዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ይዘትና መልክ ያላቸውን ቃል ግጥሞች ይነገራሉ፣ ይገጠማሉ፡፡ ትኩረታቸው ትችት ለማቅርብ ፣ ጫና ለመፍጠር፣ ለቅስቀሳ ሆኖ የህዝቡን አመለካከት ለማንፀባረቅ ይሆናል፡፡ ስድብ አዘል ምፀታዊ ቃል ግጥሞች ለፖለቲካ ተግባር የሚውሉበት ጊዜ እንደ ጦር መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ በማለት (Finnegan 1970) ያብራራሉ፡፡ ፖለቲካዊ ይዘት እና መልክት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአንድ ቡድን አባላት መካከል በሚከወኑበት ጊዜ የቡድኑን የጋራ ስሜትና አንድነት ከማጠናከር አልፎ ተቀናቃኞችን ለመቃዎም ይረዳሉ፡፡ ቡድናዊ ስሜትና አንድነትን ለማጠናከርና ለማንፀባርቅ ቃል ግጥሞች ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ ቃል ግጥሞች በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ከግለሰቦች ወይም በቡድኖች መከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ አስተዳድራዊ ችግሮችን ፣ በደሎችን ጭቆናዎችን ለማንፀባርቅ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችንና አስተዳዳሪዎች አስፈሪ የሚሆኑበት ጊዜ ስሜትና ፈላጎትን እንዲሁም ብሶት በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ፡፡ በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚፈጠሩ አሉታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን አደባባይ አውጥቶ መናገር የማይቻላበት ሁኔታ ቃል ግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ (Finnegan 1970፡)

በአጠቃላይ ቃል ግጥሞች በማኅበርሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና ለወቅቱ ተስማሚና በጣም ጥሩ የሚባሉትን ባህሪያትና አስተሳሰቦች የማህበርሰቡ አባላት እንዲማሩባቸው የማድረግ ፋይዳ ወይም አላማ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ የቃል ግጥምን ፋይዳ ወይም ተግባር በሚመለከት (Finnegan in Bauman 1992፡26) ጠቅለል ባለ መንገድ እንዲህ ይዘረዝሩታል፡፡ የቃል ግጥም ተግባር በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን አልፎ አልፎ አመፅን መግለፅ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድርግ ወይንም ለውጥን ማበረታታት ናቸው፡፡

ብዙዉን ጊዜ የተለመዱ የፖለቲካና የተቃውሞ ዘፈኖች ቢሆኑም ቃል ግጥሞች በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል የሚታዩ ሐይማኖታዊ፣ ክብር ባህላዊ፣ ጥበባዊና ተዝናኖታዊ፣ ሁኔታዎች ውስጥ የራሳቸውን ሚና ይጫዎታሉ፡፡ ስለሆነም የቃል ግጥም አላማዎች ብዙ ሲሆኑ ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያክል ጥላቻን ወይም ፍቅርን ለመግለፅ ችግሮችን ለማቃለል ወይም ችግሮችን ለማብረድ፣ ለማስደሰት፣ ለማሳፍ፣ ለማዋረድና ለማቃለል፣ ለህዝባዊ ሁነቶች ክብርና ሙገሳ ለመስጠት ወይም ምናባዊ በተዋቡ ቃሎች ሸፍኖ ለማቅርብ ያገለግላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቃላዊ ግጥምን ፋይዳ ወይም ተግባር በሚመለከት (Finnegan in Bauman 1992: 126) ጠቅለል ባለ መንገድ እንዲህ ይዘረዝሩታል:: የቃላዊ ግጥም ተግባር በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ እነሱም አመፅን መግለፅ ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድረግ እና ለውጥን ማበረታታት ናቸው:: ብዙ ጊዜ የተለመዱ የፖለቲካና የተቃውሞ ዘፈኖች ቢሆኑም ቃላዊ ግጥሞች በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል በሚታዩ ሀይማኖታዊ፣ ክብረበአላዊ፣ ጥበባዊ እና ተዝናኖታዊ፣ ሁኔታዎች ውስጥ የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ::

ኢትዮጵያ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ በርካታ የሰዉ ልጅ የፈጠራ ዉጤቶች ባለቤት ናት፡፡ ለአብነትም ሥነቃልን ከዚህም ዉስጥ ቃል ግጥምን ብወስድ በተለምዶ አልተማረም የሚባለዉን የኅብረተሰብ ክፍል ልሂቅነት የምንገነዘብበት ትልቅ ጥበባዊ ሃብት ነዉ፡፡ ይህ ማኅበራዊ ዕዉቀትና ጥበብ ድሮም የነበረ አሁንም ያለና ወደፊትም በትዉልድ ቅብብሎሽ ከሰዉ ልጆች ጋር አብሮ የሚኖር ነዉ፡፡ የአንድን ኅብረተሰቡ ትክክለኛና አወንታዊ ስሜትና አመለካከት ዛይበረዝና ሳይከለስ እደወረደ የምናገኘዉ በዚህ ጥበብ ዉስጥ ነዉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ስሜትና አመለካከት ደግሞ አድርባይነትና ወገንተኝነት ስለማይታይት አስተማማኝና ጠቃሚነቱ የተረጋገጠ ነዉ፡፡

### 2.1.1.2. የቃል ግጥም መሰረታዉያን

ቃል ግጥሞች የማህበረሰቡን ህይወት እንዲያንጸባቁ፣ ትርጉም እንዲሰጡ፣ ቅርጽና ይዘታቸዉን ጠብቀዉ እንዲቀርቡ እና ተስተላልፏቸዉም ከአንዱ ትዉልድ ወደሌላዉ ትዉልድ፣ ከአንዱ ማህበረሰብ ወደ ሌላዉ ማህበረሰብ እና ከአንዱ አካባቢ ወደሌላዉ አካባቢ ቀጣይነት ባለዉ መንገድ እንዲከናወን ሊያደርጉ የሚችሉ ጽንሰ ሐሳቦች አሉ፡፡

እነሱም ድረሳ ክዋኔ አዉድ እና ተስተላልፎ ናቸዉ፡፡ ቃል ግጥ እስካልተደረሰ፣ እስካልተከወነ፣ ክዋኔዉም አዉዱን ጠብቆ ካልተከወነና ቃል ግጥሞቹ ከተከወኑበት ቦታ፣ ጊዜ፣ ትዉልድና ማህበረሰብ ወደሌላዉ ማህበረሰብ ካልተላለፉ ህልዉናቸዉ ያከትማል፡፡ ስለዚህ የነዚህ የቃል ግጥሞች መሰረታዊ የህልዉና ምንጮች የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች ባህርያት፣ ምንነትና ሚና እንደሚከተለዉ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 2.1.1.2..1. የቃል ግጥም ድረሳ፡-

የቃል ግጥም ድረሳ ከዋኙ ቃል ግጥሞቹን የሚያፈልቅበት ወይም የሚፈጥርበት ዘዴ ነው። የቃል ግጥም በተለያየ መንገድ ይደረሳል፡፡ የቃል ግጥም በዋናነት ቀድመዉ የተዜሙትን በማስታወስ፣ እዚያው በዚያው አጋጣሚውን ተጠቅሞና አውዱን ተከትሎ በመፍጠር እና ነባራዊ ሁኔታዉን ተከትሎ በተመስጦ ሊደረስ ይችላል፡፡ በማስታወስ መከወንን አስመልክተው Finnegan ሲያስረዱ "He is repeating from memory a piece which has been composed prior to the performance, either by himself or, more likely by others, perhaps years or generation earlier" (Finnegan 1977: 52) ይላሉ፡፡

ከጥቅሱ እንደምንረዳው የቃል ግጥም ከዋኙ ከክዋኔው እለት በፊት በራሱ የተደረሰ ወይም በሌሎች የተደረሰ ቃል ግጥም አስታውሶ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በአብዛኛው በሌሎች የቃል ግጥም ደራሲያን ከአመት ወይም ከትውልድ በፊት የተደረሰውን አስታውሶ ሊከውን ይችላል፡፡ እዚያው በዚያዉ የአደራረስ ስልት ከሆነ ግን ከዋኙ በወቅቱ የክዋኔው ድባብ በሚያሳድርበት ስሜት ተነሳስቶ ነባሩን ቃል ግጥም ከወቅቱ ጋር እንዲስማማ አድርጎ አዳዲስ ወቅታዊ ሃሳቦችን በመጨመር አሻሽሎ የሚያቀርብበት ነው፡፡ ከዋኙ ነባሩን ስነቃል የዜማ አወራረድ ስልት ሳይለውጥ ያንኑ ስልት በመከተል የራሱን አዳዲስ ሃሳቦች በመጨማመር ሊፈጥር ይችላል፡፡

በተመስጦ የአደራረስ ስልት ግን ከዋኙ ነባሩን የቃል ግጥም እንዳለ ሙሉ ለሙሉ ወይም ሽራርፎ በማዜም ሳይሆን አዲስ ቃል ግጥም የሚፈጥርበት አጋጣሚ ነው፡፡ ከዋኙ አውዱ በፈጠረለት አነሳሽ ሁኔታ ተነቃቅቶ የሚፈጥራቸውን ቃል ግጥሞች የሚመለከት ነው (Finnegan 1977፡ 52-87)

የቃል ግጥም ድረሳ በክዋኔ ወቅት የመደጋገምና የተለዋዋጭነት ባህርያት ይታይበታል። ቃል ግጥም ከክዋኔ ውጭ በሚነገሩ የመደጋገም ባህርይ ቢኖራቸውም ድግግሞሹ ጎልቶ የሚታየው በክዋኔ ወቅት ነው። ድግግሞሹ በቃል፣ በሀረግ፣ በስንኝ

እንዲሁም በይዘት ደረጃ ሊሆን ይችላል። የቃል ግጥም ድግግሞሽ ለከዋኙና ለታዳሚው የሚያስገኘው ጠቀሜታዎች አሉት።

"ለከዋኙ በራስ የመተማመን ስሜት ይሰጠዋል፤ ለተሳታፊዎች ደግሞ የቃል ግጥሙን መልዕክት በቀላሉ ለመያዝና ከከዋኙ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር ያስችላቸዋል።" (Finnegan 1977፡ 129) ከዋኙ ቀጣዩን ስንኝ ለማስታወስ ፋታ ያገኝበታል። የታዳሚዎችን ትኩረት ለመሳብም ያስችለዋል። በተጨማሪም "ክዋኔውን ለማርዘም ዋና ዋና ለሆኑ ጉዳዮች አጽንኦት ለመስጠት፣ የግጥሙን መዋቅር ወይም ምት ለማስጠበቅ ይጠቅማል።" (Okpewho 1992፡ 9)

### 2.1.1.2.2. የቃል ግጥም ክዋኔ፡-

ክዋኔ ለቃል ግጥም የህልውናው ምንጭ ነው። የቃል ግጥም መልእክት ከነሙሉ ለዛው ከቦታ ወደ ቦታ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ክዋኔ ወሳኙን ድርሻ ይይዛል፡፡ የቃል ግጥም ክዋኔ ሲነሳ ከዋኙን፣ በክዋኔ ወቅት የሚሳተፉትን ታዳሚያንን፣ በክዋኔ ወቅት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት፣ እንዲሁም ቃል ግጥሙ የሚከወንበትን መቼት አጣምሮ መመልከት ይገባል፡፡ ክዋኔ፡- ጉዳዩን (text) ብቻ ነጥሎ የሚያይ ሳይሆን የአጥኚውን ግለሰብ እውቀትና ግንዛቤ እንዲሁም የሚጠናውን ማህበረሰብ እውቀት የሚያስተሳስር ነው።

የፎክሎር ተመራማሪዎች፣ ክዋኔ የተለየውን የቃላዊ ግጥም ጥሬ መረጃ ማጥናት፣ ተጨባጭነት የሌለውና ነፍሱ የተለየው በመሆኑ ቃላዊ ግጥሞች ከቃል ከተደረሱ በኋላ በሚገባቸዉ የክወና አጋጣዎች ላይ በአቀንቃኙ እየተዜሙ፣ በአጃቢዎች ቅበላ እየተስተጋቡ ከአድማጭ ተመልካች ልቦና ዉስጥ እንዲደርሱ ተደርገዉ መከወን አለባቸዉ፡፡

"ክዋኔ ጥበባዊ ድርጊት ነው" (Deborah A. 1995፡ 479) "ክዋኔ በተግባር የሚገለፅና ተሳትፎን የሚሻ ተግባር ነው፡፡ ተሳታፊዎች እንዳላቸው ልምድና ክሂል ተሳትፎ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣል። ክዋኔ በትክክል እንዲከወን መቼት፣ ተሳታፊ እና ከዋኝ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡" (Sims and Stephens, 2005፡ 128-129) በማለት ክዋኔ ጥበብ መሆኑን ከዚያም ባሻገር ክዋኔ ለሁሉም ተሳታፊዎች እንደ አቅማቸውና እንደፍላጎታቸው እንዲሳተፉ እድል እንደሚሰጥ ያስረዳሉ።

የቃል ግጥም ዓይነቶች በርካታ እንደመሆናቸው መጠን አከዋወናቸውም እንደየባህርያቸው የተለያየ ነው፡፡ እያንዳንዱ የቃል ግጥም ዓይነት የሚከወንበት የራሱ የሆነ መቼት፣ ታዳሚ እንዲሁም ከዋኝ እንዳለዉ Finnegan፤ an oral poem is an essentially ephemeral work of art, and has no existence or continuity apart from its performance. The skill and personality of the performer, the nature and reaction of the audience the context, the purpose- these are essential aspects of the artistry and meaning of an oral poem. (Finnegan 1977: 28) በማለት ያስረዳሉ፡፡

ቃል ግጥም ያለ ክዋኔ ህልውና የለውም፤ ቀጣይነትም አይኖረውም፡፡ እንደሳቸው አገላለጽ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከቦታ ወደ ቦታ የመሸጋገር እድሉ ያለው በክዋኔ ላይ ተንጠልጥሎ ነው፡፡ ለቃል ግጥም ኪናዊ ውበትና ትርጉም ሰጪነት፣ የከዋኙ ችሎታ፣ የታዳሚው የተሳትፎ ብቃት እና አውዱ ወሳኝነት አላቸው፡፡ በአጠቃላይ ለቃል ግጥም መኖር ክዋኔ ወሳኝ ነው በማለት ገልጸዋል። አንድ የቃል ግጥም ክዋኔ የተሳካ እንዲሆን ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ መቼት /አጋጣሚና አውድ የጠበቀ ቁርኝት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ "ክዋኔ በተግባር የሚገለፅ ሥራ ነው። ክዋኔ ተሳታፊዎች እንደ ችሎታቸውና እንደ ልምዳቸው መሳተፍ እንዲችሉ እድል ይፈጥራል፡፡ ክዋኔ ዓላማውን እንዲያሳካ ከተፈለገ ክዋኔው የሚከወንበት መቼት፣ ታዳሚዎችና ከዋኞች ሊገኙ ይገባል" (Sims and Stephens 2005: 129)

ክዋኔ እንዲኖር ሰበብ ወይም ምክንያት ያስፈልጋል፡፡ ሥነ ቃልም ሆነ ሌላ የፎክሎር ዘርፍ የሚከወነበት ምክንያት ሊኖረው ይገባል ክዋኔ ሰበብ የሚያስፈልገው መሆኑን ለመግለፅ Jan Vansina, *Performances are not produced at random times. The occasions for performances are littered and can be observed in the field. ... Each sort of tradition has its appropriate occasions for performance, and that also determines the frequency of performance (*Jan Vansina *1985: 39-40).* በማለት ያብራራሉ፡፡

ለክዋኔ የተወሰነ ጊዜና ቦታ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የመከወኛ ምክንያትና ወቅትም ያስፈልገዋል፡፡ የመከወኛ ምክንያትና ወቅት የክዋኔውን ድግግሞሽ ይወስነዋል፡፡ የፎክሎር ተመራማሪ በክዋኔ ወቅት ሊያተኩርባቸው ከሚገባው የክዋኔ አላባውያን መካከል አንዱ ከዋኝ ነው። ከዋኝ የተማረውን ወይም በተሳትፎ ብዛት ያካበተውን ፎክሎራዊ እውቀት ጥበባዊ በሆነ ድርጊት የሚያስተላልፍ ባለሙያ ነው፡፡ የቃል ግጥም ከዋኝ፣ የቃል ግጥሙን በመሪነት የሚያቀነቅን ወይም የሚያቀርብ ነው፡፡ ቃል ግጥሙ

ከቦታ ወደ ቦታ ብሎም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ትልቁን ድርሻ ይጫወታል፡፡ ስነቃል ኪናዊነት ወሳኙን ቦታ የሚይዘው ከዋኝ መሆኑን *Finnegan "Oral literature is by definition dependent on a performer who formulates in words on a specific occasion- there is no other way in which it can be realized as a literary product." (Ruth Finnegan 2012: 4)* በማለት ያስረዳሉ፡፡

ለአውዱ የሚሆነውን ሥነ ቃል ከመቀመር አንስቶ ጥበባዊ እሴቱን የሚያስጠብቀው ከዋኙ ነው፡፡ እንደ Ruth አገላለፅ በጽሑፍ የተዘጋጁ ድርሰቶች እንኳ በቃል በሚከወኑበት ወቅት ከዋኙ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ የተለያዩ ችሎታ ባላቸው ከዋኞች ቢከወን ለተለያዩ ታዳሚዎች የሚሰጠው ስሜት የተለያየ ይሆናል፡፡ መቼቱ፣ የታሪኩ መዋቅርና ገፀባህሪያቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም በከዋኙ ችሎታ ምክንያት ልዩነት ሊመጣ ይችላል፡፡

ከዋኞች በሙያው የሰለጠኑ ወይም በልምድ ያገኙት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ “performance would be specialists or not, indeed, some persons were specialized in one particular type of tradition…” (Jan Vansina 1985: 36) በሀገራችን ከሚገኙ የቃል ግጥሞች፣ ከዋኞች ሙያውን በሥልጠና ከሚከውኗቸው መካከል ቅኔን መጥቀስ ይቻላል።

በክዋኔ ወቅት የመስክ ተመራማሪ ትኩረት ከሚቸራቸው አላባውያን መካከል ታዳሚያንም ይጠቀሳሉ። ታዲሚያን የቃል ግጥምም ሆነ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት አፍ ተልብ ሆነው የሚከታተሉና የፎክሎሩ ዓይነት በሚፈቅደው መሠረት ከዋኙን የሚያግዙ እንዲሁም ለክዋኔው መሳካት የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ ናቸው። (Finnegan 1977፡ 176, 177, Sims and Stephen 2005: 128-129) ታዳሚዎች የከዋኙን ብቃትና ክህሎት መሰረት አድርገው ክዋኔውን ይለካሉ፤ ይገመግማሉ። ክዋኔውን ከተረዱት ምላሽ ይሰጣሉ። ታዳሚዎች ክዋኔውን መረዳትና መተርጎም ካልቻሉ ክዋኔው ተሳክቷል ለማለት ያስቸግራል።

### 2.1.1.2.3. የቃል ግጥም አውድ

አውድ የክዋኔ ገፅታ ወይም ድባብ ነው እና ድርጊቱ የሚከናወንበት ሁኔታ፣ ጊዜና ቦታ ወይም መቼት ነው:: ክዋኔ ያለመቼት፣ መቼትም ያለክዋኔ፣ የማይታሰቡ በስነቃል ጥናት የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸው:: ቆየት ያለ የስነቃል ምርምሮች በስነቃል ቴክስት ላይ ብቻ የተመሰረቱ እንደነበር ይታወሳል:: እንዲህ አይነቱ የምርምር ተግባር በዚያን

ዘመን ተገቢነት ቢኖረውም አውዳዊ መረጃ ከሌለው ጥናቱ የተሟላ ሊሆን አይችልም በማለት የሚከራከሩ አሉ:: ለምሳሌ (Bascom 1954: 335) "ቴክስት በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፣ ያለክዋኔ እና ያለ አውድ ህይወት አልባ ሆኖ ይቀራል" ይላሉ፡፡

አውድ የስነቃል አይነቱ በሚከወንበት ጊዜ ለክዋኔው ተስማሚ የሆኑ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ተሟልተው መኖራቸውን የሚጠቁም ነው:: አውድ ለስነቃል መነገር ወይም መከወን ምክንያት የሆነው ክስተት ወይም አጋጣሚ፣ መቼ? የት? ማን? ለምን? ወዘተ. እንደፈጠረው ወይም እንደከወነው የሚያመላክቱ መረጃዎችን አካትቶ በማሳየት፣ ትርጉሙን በተብራራ መንገድ ለመረዳት ወሳኝና አጋዥ ይሆናል፡፡ "አውድ ቴክስቱንና ክዋኔውን አቅፈው የያዙትን ሁሉንም ነገሮች ይመለከታል:: የቡድኑ አባላት ስነቃልን የሚጋሩበት አካላዊ መቼት እና ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም በከዋኙና በተደራሲያኑ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ባንድ ላይ የክዋኔ አውድ ይመሰርታል" ይላሉ፡፡ (Sims and Stephens 2005: 137 )

በመሆኑም አውዳዊ የቃልግጥም ጥናት መሰረት ማድረግ ያለበት በተከወነበት ወይም በተፈጠረበት አካባቢ በሚሰበሰበውና በሚገኘው አውዳዊ መረጃ ላይ ይሆናል ማለት ነው:: ቃልግጥሞች አብዛኛውን ጊዜ የየዘመኑን መንፈስና ገጠመኝ ተመርኩዘው የመፍጠር ባህሪ ስላላቸው፣ ይዘታቸውም ይህንኑ ባህሪ ማለትም የተፈጠሩበትን ምክንያት ከነሁኔታውና ከነድርጊቱ፣ ቦታውንም ጭምር የሚያመለክቱ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

### 2.1.1.2.4. የቃል ግጥም ተስተላልፎ፡-

የቃል ግጥም ህልውና የተመሰረተው በቃል በሚደረግ ተስተላልፎ ነው፡፡ ተስተላልፎ ስንል ቃል ግጥሙ ተደርሶ ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ፣ ከትውልድ ትውልድ ከባህል ባህል የሚተላለፍበትን ዘዴ ነው። የቃል ግጥም ተስተላልፎ ቀድሞ የነበረውን በመሸምደድ በክዋኔ ወቅት አስታውሶ በመከወን፣ የራስን አዳዲስ ሃሳቦች እየጨመሩ አሻሽሎ በመከወን ሊሆን ይችላል። ቃል ግጥም ለመከወን የተወሰነ አጋጣሚ መኖር አለበት፡፡

የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚ ካላገኘ የመኖር ህልውናውን ሊያጣ ወይም ሊጠፋ ይችላል፡፡ ከዚህ ነጥብ ጋር በማያያዝ በጽሑፍ የሚገኙ ስነጽሑፎችን ከቃል ግጥም ጋር በማነጻጸር ስንመለከት ተስተላልፏቸው በጽሑፍ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ሳይበረዙና

ሳይለወጡ ከመዝለቃቸውም በተጨማሪ በማን፣ ለማን፣ መቼና የት እንደተጻፉ ማወቅ ይቻላል፡፡ ቃል ግጥምን ስንመለከት ግን በማን፣ ለማን፣ መቼና የት እንደተደረሱ በትክክል ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል፡፡

የከዋኙ የዜማና የቃል ግጥም አከዋወን እውቀት እንደዚሁም የማስታወስ ችሎታ ለቃል ግጥሙ ተስተላልፎ ወሳኝነት አለው፡፡ የቃል ግጥም ከላይ ወደታች በቃል ስለሚተላለፍ በተስተላልፎው መካከል የመዘንጋት ወይም የመረሳት እድል ያጋጥመዋል፡፡ በተጨማሪም ከአንድ ከዋኝ የተከወነ ቃል ግጥም በሌላ ከዋኝ በሚከወንበት ወቅት በርካታ ለውጥ ሊኖር ይችላል።

Finnegan ተስተላልፎን በተመለከተ "As it passes from singer to singer it is changing unceasingly. Old stanzas are dropped and new ones are added; rhymes are altered; names of the characters are varied…" በማለት (Finnegan 1977፡ 144) ተስተላልፎ በማያቋርጥ ሁኔታ በለውጥ የታጀበ መሆኑን ያስረዳሉ። እንደሳቸው አገላለጽ ነባር ስንኞች በአዲስ ሊተኩ ይችላሉ። በቀድሞዎቹ ስንኞቹ የነበሩ ገጸባህርያት ስሞች በሌሎች ስሞች ሊተኩ ዜማዎቹ ሊቀየሩ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

በባህል፣ በቦታ፣ በዘመን፣ በከዋኙ የግል ችሎታ እና በመከወኛ አጋጣሚዎች ምክንያት የቃል ግጥም ለውጥ ይከሰታል፡፡ ይህንንም በተመለከተ "በቃላዊ ግጥም ተስተላልፎ በቃል፣ በሐረግ፣ በስንኝ፣ በዋና ሐሳብና በመቢያ ጉዳይ ላይ ለውጦች ይከሰታሉ፡፡" በማለት ያስረዳሉ። (Finnegan 1977፡135) ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለውጡ አንዳንድ ጊዜ የቃል ግጥሙን ጭብጥ እስከማሳት ድረስ ሊዘልቅ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ የቃል ግጥሞች ይዘት በፖለቲካና በማህበራዊ፣ በዘመንና በቦታ እንዲሁም በእድገት ወይም በብልጽግና በመሳሰሉት ለውጦች ምክንያት ሊለዋወጡ ይችላሉ። እንደአጠቃላይ ቃላዊ ግጥም ህዝባዊ ባህሪ ሊኖረው የሚችለው በስርጭቱ (በተስተላልፎው) እና በክዋኔው ሲሆን በፈጠራው ግን ግለሰባዊ ነው ማለት ይቻላል:: አዉድ ግን ህዝባዊም ይን ግላዊ የተከወነበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያመላክት ነዉ፡፡

## 2.1.1.3. የክብረ በዓላት ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያትና ፋይዳዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የክብረ በዓላትን ምንነት፣ ዓይነቶች፣ ባህርያትና ፋይዳዎች በዝርዝር የምሁራንን ብያኔ በማካተት ቀርበዋል፡፡ በስራቸዉም የሚካተቱ ክሎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1.3.1. የክብረ በዓላት ምንነት

(ደስታ ተክለወልድ 1950፣ 636) በመዝገበ ቃላቱ የክብረ በዓልን ምንነት ሲገልጽ "የበዓል ክብር፣ ገናን፣ ጥምቀትን፣ ትንሳኤን፣ ጰራቅሊጦስን፣ መስቀልን፣ ፍልሰታን፣ ኅዳር ሚካኤል፣ ማዚያ ጊዮርጊስን፣ ለመሰለ በዓል የሚደረግ ማሕሌት፣ ዘፈን፣ ንግስ፣ እልልታና ደስታ፣ ሥራ አለመስራት፣ መንገድ አለመሄድ።" በማለት በይኖታል። ክብረ በዓል ሲባል በዓላቱ የሚታሰቡበት ቀናት ብቻ ሳይሆኑ ከበዓላቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑትንም ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለምሳሌ ማህሌት፣ ዝማሬ፣ ዘፈንና እልልታ ጭፈራ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

Sims & Stephen ክብረ በዓላት በአንድ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ የሚያከብራቸውና በርካታ የፎክሎር ዓይነቶች የሚከወንባቸው መሆናቸውን ይገልጻሉ። "Rituals are repeated, habitual actions, highly organized and controlled…bring together many types of folklore." (Sims & Stephen 2005:95)

ዘሪሁን "አንዳንዶቹ ክብረ በዓላት በእምነት ላይ የተመሠረቱ ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ አለማዊ ናቸው።" ክብረ በዓላቱ ሀይማኖታዊ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ እንደሆኑ ሁሉ በየክብረ በዓላቱ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችም መንፈሳዊና ዓለማዊ ሊሆኑ ይችላሉ። በጥምቀት በዓል ላይ የሚዜሙ ቃላዊ ግጥሞችም በሃይማኖታዊ በዓል ላይ የሚከወኑ ዓለማዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ናቸው በማለት ያስረዳሉ። (ዘሪሁን አስፋው 1992፣ 54)

የክብረ በዓላት ዘፈኖች አንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን በበዓላት ቀናት የሚከውናቸው ወይም የሚያቀነቅናቸው ቃል ግጥሞች ናቸው። የበዓሉ ተሳታፊዎች በዓሉን በዘፈንና በጭፈራ ማሳለፋቸው የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ያጠናክርላቸዋል፤ ማህበራዊ ህይወታቸው ይበልጥ የተሳሰረ እንዲሆን ያደርግላቸዋል። የሥነ ማኅበረሰብ እና የሥነ ሰብዕ አጥኚዎች ፈንክሽናል አጥሮችን መሠረት በማድረግ ከፍተኛ የኾነ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት እና በማኅበራዊ ጠቀሜታ ውስጥ የሚለካ ነው በማለት ክብረ በዓልን ከማኅበረሰብ ዕሳቤ ጋራ አያይዘው ይበይኑታል፡፡ የሳይኮ ናላይቲክ አጥሮችን ተከትለው በዘርፉ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ እንደነ Robertson Smith ያሉ የሥነ ልቡና ተመራማሪዎች ደግሞ "ክብረ በዓል ማለት ንቁ ያልሆነውን የአእምሮ

ክፍል የሚገራ እና ማኅበረሰባዊ ባሕርይን የሚቀርጽ ነው" በማለት በሥነ ልቡና መስፈሪያ ይለኩታል:: Cather Bell (2009፡ 12-29), Islam and Zyphur (2009: 6)

ክብረ በዓል ውስብስብ የኾነ የማኅበረ ባህል መግባቢያ ነው፡፡ ይህ የሚኾነው ክብረ በዓል በውስጡ በተለያዩ፣ ትውፊቶች፣ ልማዶች፣ የራስ ግንዛቤዎች ወይም አረዳዶች የተገነባ ተግባቦት መኾኑ ነው፡፡ የክብረ በዓል ተግባቦት መፍጠሪያው መንገድ ተመራጭና ተደማጭ መኾኑ በሰዎች መካከል ሥርዓታዊ ተግባቦት እንዲኖርና እንዲቀጥል ያስተምራል፤ ያሠርጻል፡፡ (Cather Bell 2009: 12)

ክብረ በዓል በውስጡ የሥነ ልቡና፣ የማኅበረሰባዊ ጉዳዮች፣ ባህላዊ ዕሳቤዎች እና ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ተዛንቀው የሚከወኑበት ዘውግ ነው፡፡ ክብረ በዓልን ከማኅበረሰባዊ ግንኙነቱ እና ሥሪቱ ባለፈ በየ ቡድኑ የሚለበሱት አልባሳት፣ የሚቀርቡት ባህላዊ ምግቦች፣ የሚጠጡት ባህላዊ መጠጦች፣ በቃላት እና በድርጊት የሚፈጸሙት ክዋኔዎች ኹሉ ተዳምረው የተለያዩ ዕይታዎች እንዲኖረው አስችሎታል (Rappaport in Bell 2009: 31)፡፡

የክብረ በዓል ስፋት እና ውስብስብነት የሚለካው በውስጡ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እና ሥነቃል በአንድ ተባብረው የሚቀርቡበት አዉድ በመኾኑ ነው፡፡ እነዚህ የክብረ በዓል ስፋት፣ ጥልቀት እና ውስብስብነት ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች አንዳች ማኅበራዊ፣ ባህሊዊ፣ ሰብአዊ እና ሥነልቦናዊ ፋይዳዎች የሚያስገኙ ናቸው፡፡ (ጋሻዉ 2013፣15)

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የተብራሩትን በዓላት ብያኔ ወስደን ስንመለከት ክብረ በዓላት በተለይ በሀገራችን ዘርፈ ብዙ ማህበረ ፖለቲካዊና ባህላዊ ፋይዳ ያላቸዉ ማህበረሰባዊ ክዋኔዎች ሲሆኑ በቤትና በግቢ ዉስጥ እንዲሁም በዓደባባይ ወቅትና አጋጣሚ ተብቀዉ የሚከበሩ ናቸዉ፡፡ በላዓቱ አንዱ ከሌላዉ የሚለዩባቸዉ ባህርያት፣ ቅርጽና ይዘት ቢኖራቸዉም የጋራ የሆነ ፋይዳ አስተምህሮና እሴት አላቸዉ፡፡ በመሆኑም ከሚከበሩበት አዉድ ባሻገር ህብረተሰቡን በማገናኘት፣ በማቀራረብና በማስተሳሰር ለሰላም፣ ለልማትና ለአንድነት እድሁም የማህበረሰቡን አመለካከት ለማንጸባረቅና ትልቅ ድርሻ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ ለአብነትም የዚህ ጥናት ዋነኛ የክወና አጋጣሚ የሆነዉ የጥምቀት በዓልን ወስደን ብንመለከት ከሃይማኖታዊ አስተምህሮና የዕምነት ከበራ ፋይዳዉ ባሻገር ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዉ የጎላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም በዓላቱ ባህላዊና ማህበራዊ

ለዛቸዉን ጠብቀዉ እንዲከበሩ በማድረግ እነዚህ ተያያዥ የሆኑ ፋይዳዎች እንዲያሳኩ አድርጎ መጠቀም ከሚመለከታቸዉ አካላት ሁሉ የሚጠበቅና ከክልከላ ይልቅ ማበበረታታን የሚሻ ክብረ በዓል ነዉ፡፡

### 2.1.1.3.2. የክብረ በዓላት ዓይነቶች

የክብረ በዓል ዘውጎች ባላቸው የማኅበረሰብ ፋይዳ፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካ አስተምህሮ፣ የዕውቀት ፍልስፍና፣ የባህል እና የልማድ፣ የጊዜ ለዉጥ እና መታሰቢያዎችን ምክንያት በማድረግ፡- የሕይት ዑደት፣ የዘመን መለወጫ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የባህል በሚሉ ዘዉጎች ተከፋፍለዉ ይዳሰሳሉ፡፡

**ሀ. የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል፡-**

የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል የሚባለዉ የክብረ በዓል ዓይነት ሰዎች በሕይት ዘመናቸዉ የሚያልፉባቸውን የሕይወት ዑደቶች ተከትሎ የሚከበር ነው፡፡ የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል በዋናነት በልደት፣ በጋብቻና በሞት የሚከወኑትን ክብረ በዓሎች ይመለከታል፡፡ የመጀመሪያ ከወሊድ ጊዜ ጋር ተያይዞ በአዋላጆች እና በጎረቤቶች የሚደረገውን ምርቃት፣ የገንፎ ዝግጅት፣ በሽልም ያውጣሽ፣ የአጥር ወፍ አትስማሽ፣ እልልታ እና ማርያም ማርያም የሚባልበትን ጨምሮ የገለብ፣ የጸሐይ ማሞቅ፣ የልደት፣ የክርስትና እና የግዝረት፣ ስርዓቶች የሚከናበት በዓል ነው፡፡

ኹለተኛዉ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚከበረዉ በዓል ሲሆን የልጅህን ለልጄ (ልመና)፣ እርክክብ፣ ፍጥጥም፣ ሰርግ፣ ምላሽ እና ቅልቅል (እወቁልኝ) በዓላት በወዳጅ ዘመድና በቤተሰብ፣ በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት የሚከበረዉን በዓል የሚመለከት ነዉ፡፡ ሦሥተኛዉ ተጠቃሽ የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል ከሞት ጋር ተያይዞ የሚከበረዉን ሥርዓት የሚያጠቃልል ነው፡፡ ሰው በዚህ ዓለም ከቆየ በኋላ በሞት ወደ ሌለኛው ዓለም፣ ከማኅበረ ሕያዋን ወደ ማኅበረ ሙታን የሚቀላቀልበት መንገድ ነው፡፡ በዉስጡም ህልፈተ ሕይወት፣ መርዶ፣ ሰለስት፣ አርባ፣ ሰማኒያ እና ሙት ዓመት መታሰቢያ የመሳሰሉትን በልቅሶና ድግስ የሚደረጉ የሐዘን ስርዓቶችን ያጠቃልላል፡፡

የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል ከሌሎቹ ክብረ በዓላት የሚለይበት ዋናው ምክንያት አንድ ሰው ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ የሕይወት ምዕራፍ ላይመለስ የሚያደርጋቸውን ሽግግሮች ይኹን የሕወት ጉዞዎች በሚመለከት የሚከበርና የሚታሰብ መኾኑ ነው፡፡ ይህን ሐሳብ አስመልክቶ በዘርፉ የተሰማሩ ምሑራን አጽንኦት ሰጥተዉ

ምንነትና ባህርይዉን በማብራራት እንደሚከተለዉ ያስረዳሉ፡፡ የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል በጋራ በመሆን በተውኔት መልክ የሚከበር ነው፡፡ እንደ ልደት እና የወንዶችን እና የልጃገረዶችን የዕድሜ መጨመር ተከትሎ የሚመጣን ጋብቻ እና ሞትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ አንዳንዴም "የሕይወት ውድቀት" ወይም "የሕይወት ዑደት" ተብሎ ይጠራል፡፡ የሕይወት ዑደት በኅብረተሰቡ ባህል የተገራ ሲኾን ግለሰቦች ከአንድ ማኅበረሳበዊ የሕይት ደረጃ ወደ ሌላዉ የሕይወት ደረጃ ሽግግር የሚያደርጉበት በዓል ነው" (*Bell 2009፡ 94)*

**ለ. የዘመን መለወጫ ክብረ በዓል፡-**

*የዘመን መለወጫ ክብረ በዓል ማኅበራዊ እና አዉዳዊ ሲኾን የብሥራት ባሕርይ አለው፤ ዓመታዊ ክብረ በዓል በታወቀ ቦታ እና ጊዜ እየተመላለሰ ስለሚከበር እንደ አዲስ ሕይወትን በማስጀመር ለማኅበረሰቡ ትልቅ የኾነ ሥጋዊና መንፈሳዊ ርካታ ያስገኛል፤ ዓመታዊ ክብረ በዓል በሃይማኖታዊና ሥጋዊ ይዘቱ ምክንያት ለአክባሪዎቹ አንዳች በረከትን እና ተስፋን ያስገኛል ተብሎ ይታመናል* (Bell 2009፡ 102-105)::

*የበጋ፣ የበልግ፣ የክረምትንና የጸደይን ወራት በማስታወስ ሰዎች በአዲስ መንፈስ ለስራ እንዲነቃቁ ያደርጋል፤ በተጨማሪም ስለ ክብረ በዓሉን ጊዜና ቦታ ቅዱስነት በማሰብ ሰዎች አካበቢያቸውን እንዲጠብቁና ለተፈጥሮ ያላቸው ግምት ከፍ እንዲል ያደርጋል* (Bell 2009, 105)፡፡ *ለአብነትም እንቁጣጣሽ፣ ፍቹ ጨምበላላ፣ ኢሬቻን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ገና* (*ክሪስማስ*) *የምዕራባዉያን አዲስ ዓመት ቢሆንም ከጊዜ ወዲህ በሀገራችን እየተዘወተረ የመጣ የመጤ ባህል ወረራ አካል ቢሆንም በድምቀት ሲከበር ይስተዋላል፡፡*

**ሐ. ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት:-**

*ሀይማኖት*/Religion *የምንለው ሰዎች በጋራ ተሰባስበው ሥርአተ አምልኮታቸውን የሚፈጽሙብት የተደራጀ ስርአት ወይም ተቋም ማለት ነው። በሌላ ጎኑ የግለሰቦች የተናጠል የእምነት ደረጃና ጽናት ወይም በግል የሚያደርጓቸው ተግባራት እና የህይወት ፍልስፍናቸው መንፈሳዊነት ክዋኔ በመባል ይገለጻል። በአንድ ሀይማኖት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ ጥንካሬ እና የእምነት ደረጃ አላቸው። ለዚህም ነው መንፈሳዊነት የግለሰብ ጉዳይ ሲሆን ሀይማኖት ግን የቡድን ወይም የጋራ ጉዳይ የሚሆነው። ነገር ግን ሁለቱን ሙሉ ለሙሉ ነጣጥለን ማየት አንችልም። የሀይማኖት* (*የተቋሙ*) *ጠንካራ መሆን ወይም መድከም በስሩ ባሉ ግለሰቦች ህይወት እና መንፈሳዊነት ላይ እንደሁኔታው*

አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ አረኛው ጠንካራ ካልሆነ በጎች በተኩላ እንደሚበሉ ሁሉ አንድ ሀይማኖት እንደ ተቋም ጠንካራ አደረጃጀት ከሌለው በግለሰቦች መንፈሳዊ ስኬት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡ በተቃራኒው በተዘዋዋሪ መንገድ የግለሰቦች የእምነት ደረጃና እንቅስቃሴ በጥቅሉ የተቋሙ ተልእኮ ውጤታማ እንዲሆን ወይም እናዳይሆን በማድረግ ረገድ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህም በሁለቱ መካከል የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዳለ እንረዳለን፡፡ ለዚህ ነው ለሁለንተናዊ ስኬት ሲባል ግለሰቦች በምነታቸው ሲደክሙ ሀይማኖቱ መዋቅሩን ወይም ቀኖናውን ተጠቅሞ ምዕመኑን እንደሚያፀናና ችግሩን እንደሚፈታለት ሁሉ በግለሰቦች ወይም በሀይማኖት አባቶች ስህተት ምክንያት ተቋሙ ችግር ውስጥ ሲዘፈቅም ምዕመናን እንዲሁ እየተከታተሉ ሊተቹ እና ብልሽቱን ሊያርሙ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን መጨረሻው አብሮ መጥፋት ነው፡፡

ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል የእምነቱ ተከታዮች የሆኑ ምእመናን አንድ ላይ በመኾን በአደባባይ ወይም በግቢና በቤት ውስጥ የሚያከብሩት የክብረ በዓል አይነት ነው፡፡ ይህ ክብረ በዓል በአብዛኛው ሃይማኖታዊ ይዘት ያለዉ ነው፡፡ ይህ ክብረ በዓል ምድራዊ በረከትን፣ ረጅም እድሜን፣ ጤናና ሀብትን፣ ዘርቶ መቃምን እና ወልዶ መሳምን ያድል ዘንድ እየተደጋገመ በየዓመቱ ይከበራል፡፡ የፈጣሪን እና የማርያምን፣ የጻድቃን እና የሰማዕታትን፣ የሐዋርያት እና የነብያትን እንዲሁም የመላዕክቱን ረድኤትና በረከት፣ ይቅርታና ምህረት፣ ተራዳኢነትና አማላጅነት በማሰብ የሚከበር በዓል ነዉ፡፡ ለአብነትም በኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት የዚህ ጥናት ዋና የክዋኔ አጋጣሚ የሆነዉን የጥምቀት በዓልን ጨምሮ፣ መስቀል፣ የገና፣ የፋሲካ፣ የደብረ ታቦር፣ ፍልሰታ፣ አስተርዮ እና ቃና ዘገሊላ በእስልምና አስተምህሮ ደግሞ መዉሊድ፣ ኢድ፣ አረፋ የመሳሰሉትን በዓላት መጥቀስ ይቻላል፡፡

***መ. ፖለቲካዊ ክብረ በዓላት፡-***

ፖለቲካ ማለት በአንድ ቡድን ውስጥ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ቡድኖች/ሀይሎች መካከል ውሳኔ ለመወሰን እና ለማስፈጸም የሚደረግ ሂደትና ትግል ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የተለያየ አመለካከት ባላቸው ግለሰቦች ፣ቡድኖችና ሀገራት መካከል ሀይል ወይም ሥልጣን ለማግኘት የሚደረግ ፍትጊያ ፖለቲካ ነው፡፡ የተለያየ አተያይ (አመለካከት) ባለበት ቦታ ሁሉ ፖለቲካ አለ፡፡ ሰው ደግሞ የተለያየ ባህሪ ያለው ፍጡር እንደመሆኑ መጠን ይህን ተከትሎ የሚመጣ የፍላጎት አለመጣጣምና ፍትጊያ አለ፤ ይህ ሚጠቁመን ሰው ባለበት ቦታ ሁሉ ፖለቲካ እንዳለ ነው፡፡ በቤተሰብ፣ በእድር ፣በማህበራት፣በሀይማኖት ተቋማት፣በፓርቲና

መሰል ስብስቦች ውስጥ ሁሉ ፖለቲካ አለ። በምንም አይነት መለኪያ የሀይማኖት ተቋማትና አማኞች ከፖለቲካ ነጻ ናቸው ማለት አንችልም። ፖለቲካ ጥላ ነው። ሰው ባለበት ሁሉ ፖለቲካ አለ። ሸሽተን (ፖለቲካና ኤሌክትሪክ በሩቁ ነው ብለን) አናመልጠውም። ምናልባት ቃሉን በትክክለኛው መንገድ ለመረዳት እንቅፋት የሆነብን ፖለቲካ የሚለው ቃል ባዕድ መሆን ከሆነ በእውነትና ሀሰት ወይም በተለያየ አመለካከቶች መካከል የሚደረግ ፍትጊያ ብለን ለኛ በሚገባን መንገድ መግለጽ እንችላለን።

የፖለቲካ በዓላት ከፖለቲካ ልሂቃን እና መሪዎች ፍላጎትና ዉሳኔ ጋር ተያይዞ የሚከበር ነው፡፡ በዚህ በክብረ በዓል ወቅት ስለነገሥታቱ፣ ልዑላኑ፣ መንግሥታቱ፣ ስለመሪ ድርጅትና ፓርቲ ተጋድሎ፣ ቅድስና፣ በዓለ ሲመት፣ የድል ቀን፣ የነጻነት ቀን፣ የሰንደቅ ዓማ ቀን፣ የመከላከያ ቀን፣ የሰማዕታት ቀን ወ.ዘ.ተ. በሚል ስያሜ የዓመት በዓል ተብለዉ የሚከበሩ ናቸዉ፡፡ እነዚህ በዓላት ወቅት በመንግስት ፈቃድ፣ አስገዳጅነትና አስተባባሪነት ምልዓተ ሕዝቡ ወጥቶ እንዲያከብራቸዉ የሚያስገድዱ ናቸዉ፡፡

የድል እና ነጻነት፣ የመንግስት እና የፓርቲዉ ዝናና ክብር፣ ጀግንነት እና መስዋዕነት እንዲሁም የስርዓቱ ዴሞክራሲያዊነት፣ ልማታዊነትና ህዝባዊነት የሚተረክባቸዉ ናቸዉ፡፡ በእነዚህ ትረካዎች ባለሥልጣኑ በሕዛቦች ዘንድ መፈራትንና አብዛቶ መከበርን ስለሚሰብክ ሥልጣነ ሲመቱ እንዲራዘም እና ሕዛቡ አሜን ብሎ እንዲገዛ የማድረግ አለማ እና ግብ አላቸው፡፡

**ሠ. ባህላዊ ክብረ በዓላት፡-**

ባህላዊ ክብረ በዓላት የሚባሉት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩ የኀብረተሰብ ክፍሎች ባህላቸዉን፣ ማንነታቸዉን፣ አካባቢያዉን፣ ተፈጥሯቸዉን፣ አምላካቸዉን፣ ታሪክና አኗኗራቸዉን ለመዘከር በየዓቱ ቀን ቆጥረዉ፣ በጎና ክፉዉን አስበዉ፣ ድግስ ደግሰዉ፣ በህብረትና በተናጠል የሚያከብሯቸዉ ናቸዉ፡፡

አከባበራቸዉም በልዩ ልዩ አልባሳት አጊጠዉ፣ ባህላዊ ቁሳቸዉን ተጠቅመዉ፣ በጭፈራ፣ በዘፈን፣ በመዝሙር፣ በትግል፣ በዉድድር፣ በፈረስ ጉግስ፣ በፉከራና በቀረርቶ (ሽለላ) የሚያከብሯቸዉ ሲሆኑ በዚህ ዘርፍ ስር የሚጠቀሱት በዓላት እንቁጣጣሽ፣ ሆያሆዬ፣ አበባየሆሽ፣ መስቀል፣ ግጫ ነቃላ (ሚጊራ ጉራ)፣ አሸንዳ፣ አሸንድዬ ሶለል፣ ዮ መስቀላ፣ ኦዳ ዮዮ መስቀላ፣ ጊፋታ፣ መሰላ፣ ያሆዴ፣ የአገዉ ፈረሰኞች ቀን ወ.ዘ.ተ.

ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ በዓላት የማህበረሰቡን ባህል ከመጠበቅና ለትዉልድ ከማስተላለፍ ባሻገር ሁለንተናዊ ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

### 2.1.1.3.3. የክብረ በዓላት ባህርያት

በብዙ አጥኚዎች ዘንድ እንደሚታመንበት የክብረ በዓል ተብለዉ የሚወሰዱት ሥርዓታዊነት፣ ትውፊታዊነት፣ አይለወጤነት፣ በህግና ደንብ መመራት፣ ክዋኔ እና ትዕምርት የሚሉት ናቸዉ፡፡

**ሀ. ሥርዓታዊነት:-**

የክብረ በዓል ሥርዓታዊ መኾን የክብረ በዓሉን የክዋኔ ልዩነት እና የአከባበር ኹኔታ ለመገምገም፣ ለማወቅና ለመረዳት ወሳኝነት እንዳለው (Bell 2009: 139) እና Rappaport (1999: 46) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ስርዓታዊነት የክብረ በዓሉን ክዋኔ፣ መነሻና መድረሻ፣ በቅደም ተከተል ፖለቲካዊ፣ በሃላዊ፣ ማህበራዊና ሥነልቡናዊ ዕሴቱን ጠብቆ እንዲከወን ያደርጋል፡፡ ከተለመደዉ ሥርዓት ተዛንፎ ሲገኝ የተፈጸመውን ግድፈት ለመረዳትና ለመተቸት ያስችላል፡፡

**ለ. ትውፊታዊነት:-**

አንድ ክብረ በዓል በየወቅቱ አመራርና ግለሰቦች ስለፈለጉ ብቻ የሚከወን ሳይኾን ረጅም ዘመናትን ተሻግሮ እየተከበረ የመጣና ለወደፊቱም የሚቀጥል ሀይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ትውፊት ነው፡፡ በተለይም ሃይማታዊ እና ባህላዊ ክብረ በዓላት የቀደሙና በብዙ ሽሕ የሚቆጠሩ ዘመናትን የተሻገሩና የሚሻገሩም ናቸው" (Bell (2009፡ 145)

በሌላም በኩል (Candace S. Alcorta 2006፡5) and Cather Bell (2009፡ 6) በጥንት ዘመናት ለቅዱሳን ነገሥታት ይደረግ የነበረውን ክብረ በዓል ጠቅሰው ለፎክለር እና ለሥነ ጽሑፍ እንደ ምንጭ ኾኖ አገልግሏል በማለት ስለክብረ በዓል ትውፊታዊነት ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡ የክብረ በዓል ቀደምትነት ያለፈዉን፣ የአሁኑንና የሚመጣውን ትዉልድ በባህል፣ በታሪክና በፍልስፍና የሚያስተሳስሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ ለትዉልድ ጥያቄ መልስ ሰጪዎችም ናቸው፡፡ በተለይ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት እንደ ከየትመጤነት፣ ልደት፣ ሞት፣ ምኞት፣ ተስፋና ፍርሃት የመሳሰለትን ሥነ ልቡናዊ እሳቤዎች በማንሳት መልስ ለመስጠት ጥረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ክብረ በዓል

የቀድሞውን፣ የዛሬውን እና የነገውን ትዉልድ የማቀራረብ፣ የማስተዋወቅ እና የማስተሳሰር አቅም አለው (Bell 2009: 143)::

**ሐ. ቋሚነት/ አይለወጤነት:-**

ከክብረ በዓል አይለወጤነት ባሕርያት አንጻር በተመራማሪዎች ሁለት ዓይነት አተያዮች ይስተዋላሉ፡፡ ከእነዚህ አተያዮች መካከል ለአብነት እንደ (Rappaport 1999: 37) አተያይ "የተለያዩ ተመራማሪዎች ክብረ በዓልን አይለወጥም በሚለው ባሕርይ መበየን አለበት የሚል ማጠንጠኛ ያነሣሉ፡፡ በተቃራኒዉ ደግሞ ክብረ በዓል አይለወጥም የሚለው ጉዳይ እንደ ዋና ባሕርይ ተደርጎ መወሰድ የለበትም የሚል መሞገቻ ያቀርባሉ" ካሉ በኋላ "ክብረ በዓላት ይብዛም ይነስም የማይለወጥ ባህርይ አለው" በማለት የራሳቸውን የሙግቶች ማንጸሪያ ሐሳብ ይሠነዝራሉ::

እዚህ ላይ ገገር ሐሳብ የሚሆነው ክብረ በዓል ፍጹም ተለዋዋጭ አይደለም የሚል ድምዳሜ ከመያዝ ይልቅ የክብረ በዓል የተለዋዋጭነት መጠን አነስተኛ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ መገንዘብ ተገቢነት አለዉ፡፡ የክብረ በዓል ቋሚነት የሚለካው ዋና የሚባሉትና ለክብረ በዓሉ መፈጠር ምክንያት የሆኑት ምሰሶ ቁም ነገሮች ቀጣይ እና ዘመን ተሻጋሪ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ በተለይ የሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ዋና ዋና የመከበሪያ ጉዳዮች፣ ትዕምርቶች እና አስተምህሮዎች ጊዜና ቦታን ተሻጋሪዎች ናቸው (Bell 2009፡ 150፤ Rappaport (1999, 37)፡፡

**መ. በሕግና ደንብ መመራት:-**

ክብረ በዓል በሕግና በደንብ መመራቱ ሌላው ተጠቃሽ ባሕርይው ነው፡፡ ክብረ በዓል የተፈጠረበት ሕግ እና ደንብ በሚያዘው ህግና ደንብ መሰረት እንዲከበሩ በእንቅስቃሴ፣ በዜማዎች(መዝሙርና ዘፈን)፣ በንግግሮች፣ በጭፈራዎች እና በክዋኔዎች ላይ ገደብ ይጥላል፡፡ ለምሳሌ በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ከበራ ውስጥ ሐራም ተብለው የተወገዙ ድርጊቶችን ይከለክላል፡፡ ክብረ በዓሉ በሕግና በደንብ በመመራቱ ምክንያት የክብረ በዓሉ ከዋኝ፣ የክብረ በዓሉ ተሳታፊዎች፣ እና ታዳሚዎች ለክብረ በዓሉ ሥርዓት እና ደንብ እንዲገዙ ያደርጋል፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ የሚመራበት ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ማኅበራዊ ሕጎች መኖራቸው ከበራዎች በሥርዓት እንዲከወኑ ከማድረጋቸው ባሻገር የክብረ በዓሉ መገለጫዎችም ናቸው፡፡

**ሠ. ክበራ (ክዋኔ):-**

ከክብረ በዓላት ባሕርያት መካከል አንዱና ዋነኛው ክዋኔ ነው፡፡ ክብረ በዓላት ያክዋኔ ሊከበሩ፣ ሊቀጥሉም ኾነ ሊኖሩ አይችሉም (Rappaport 1999፡ 37 እና Bell 2009፡ 161)፡፡ የአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ እንደ ክብረ በዓሉ አይነትና ኹኔታ ለአዋቂዎች፣ ለሕፃናት፣ ለሴቶችና ለወንዶች ህግና ደንቡ በሚፈቅደዉ ልክ ክፍትና ዝግ፣ ፍቁድና ክልክል ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ክዋኔ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ የክብረ በዓሉን ህልውና መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ክብረ በዓሉ ለማን? ለምን? በማን? እንደትና መቼ እንደሚከዎን ለማሳወቅ እና የክብረ በዓሉን ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች ለመረዳት ያስችላል፡፡ (Bell 2009፡ 161)፡፡

**ረ. መንፈሳዊ አዉድ፡-**

ዓለማዊም ይሁኑ መንፈሳዊ ክብረ በዓላት ክዋኔያቸው እና ተስተላልፏቸው በአውድ አማካኝነት ነው፡፡ አዉድ የክብረ በዓሉ ተሳታፊ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ቤተኛዎች እና ወሰንተኞች የሚሳተፉበትን ጊዜና ቦታ፣ እንቅስቃሴን እና አጋጣሚንና ሁኔታን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ክብረ በዓሉ ከጊዜ አኳያ በወርና በዓመት፣ በሰርክ እና በጽባሕ ተደጋግመው በሚመጡና በሚታወቁ ቀናት ይወከላሉ፡፡

አልፎ አልፎ ማኅበረሰቡ አደጋና ሥጋት ሲገጥመው በአጋጣሚና በድንገት፣ ባልተጠበቀ እና ባልታሰበ ጊዜ ክብረ በዓ ሉያደርግ ይችላል፡፡ ክብረ በዓል ከቦታ አንጻር ደግሞ በወንዝ ዳር፣ በተራራ ጫፍ፣ በቤተ ክርስቲያን አጸድ፣ በታቦት ማደሪያ ስፍራ፣ በዛፍ ሥርና በመሳሰሉት ግርማ ሞገስ ባላቸው ስፍራዎች ይከበራሉ፡፡ ሁሌጊዜም ቢኾን የክብረ በዓላቱ ጊዜና ቦታ ከዘወትሩ ጊዜና ቦታ በተለየ መልኩ ስለሚከበሩ የክብርና ሞገስ፣ የቅድስናና ልዕልና ባለቤት ናቸዉ፡፡ (Sims and Stephen 2005:105)፡፡

የክብረ በዓል አዉድ ከቦታና ከጊዜ ባለፈ አጠቃላይ የክዋኔውን ድባብ የሚጨምር በመኾኑ እንደ ሥነ ቃሎች፣ ልማዶች እና ትውን ጥበባት የመሳሰለትን ኹሉ ያጠቃልላል፡፡ በዚህም የክብረ በዓሉ አዉድ የማኅበረሰቡን እሴት፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ አስተሳሰብ እና ፍላጎት የመግለጽ አቅም አለው (Bell, 2009: 191-194)፡፡

ሰ. ተግባቦት ፈጣሪነት:-

ከክብረ በዓል ባሕርያት መካከል አንዱ በቡድኖች መካከል ተግባቦትን መፍጠር ነው፡፡ የሰው ልጆች በዙሪያቸው ካሉ ከሚያውቋቸው እና ከሚረዷቸው ነገሮች ይልቅ እንግዳና ባይተዋር የሚኾኑባቸው ጉዳዮች ይበዛሉ፡፡ ሰዎች ስለዛሬው እንጂ ስለነገው ሊያውቁና ሊረዱ አይችሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ሰዎች በክብረ በዓል አማካኝነት ስለአካባቢያቸው፣ ስለማንነታቸው፣ ስለማኅበራቸው፣ ስለተፈጥሮና በዙሪያቸው ስላሉ ክሥተቶች እውናዊና ምናባዊ ተግባቦትን ያገኛሉ፡፡

ሸ. ትዕምርታዊነት:-

እንደ Bell (2009: 42) ገለጻ ትዕምርታዊነት የክብረ በዓል አንድ ባሕርይ ሲኾን በሰዎች አእምሮ ውስጥ ሠርጾ በመግባት ተግባቦት መፍጠሪያ መንገድ በመኾን ያገለግላል የክብረ በዓል ትዕምርት በአንደበት የሚነገሩትን፣ በድርጊት የሚከወኑትን እና በቁስ የሚወከሉትን የበዓላት ማክበሪያዎች ይመለከታል፡፡ በክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ የክብረ በዓሉ አዉድ፣ አልባሳት፣ አመጋገብ እና አጊያጋጥ የየራሳቸው ፎክለራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ሥነልቦናዊ ውክልና አላቸው፡፡ ይህም የክብረ በዓሉ ክዋኔ መለኪያ አንዱ ትዕምርታዊነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ትዕምርት በክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ የውክልናዎቹን አንድምታ፣ የረቀቁ እና የራቁ ዕሳቤዎችን ሥግው በማድረግ ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች ተግባቦትን ይፈጥራል፡፡

### 2.1.1.3.4. የክብረ በዓላት ፋይዳዎች

ክብረ በዓል ከሃይማኖት፣ ከልማድ እና ከማኅበራዊ መዋቅር ጋር ያለው መስተጋብር ጠንካራ በመኾኑ የክብረ በዓሉ ባለቤቶች ባህላቸውን፣ ሃይማኖታቸውን እና ዕሴታቸውን በድንጋጌና በሥርዓት ያስቀጥሉበታል (Green 1997: 734)፡፡

ክብረ በዓል ለመከበር ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ መንሥኤዎችን እና ምክንያቶችን ይፈልጋል፡፡ በመከበሪያ ሰበቦች ምክንያት እየተመላለሰ እና እየተደጋገመ ይከበራል፡፡ በዚህ እየተደጋገመ እና እየተመላለሰ በመከበር ሊደት ውስጥ የሰዎች ማኅበራዊ ልማድ፣ ግብረ ገብነት እና ተግባቦት ቀጣይ እንዲሆን በማስቻል ሚናው የጎላ ነው (Kyalo 2013፡ 35 and Watts 2013: 1-25)፡፡ የክብረ በዓል ፋይዳ ሲነሳ ከግላዊነት ይልቅ ማኅበራዊነትን፣ ከተናጠል ይልቅ አንድነት ባለው ማኅበረሰባዊ ዕሴት፣ ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ሃይማኖት፣ ተግባቦት እና አምልኮታዊ አዘክሮት ላይ ይጸናል

### ሀ. ማኅበረሰባዊ ፋይዳዎች፡-

የክብረ በዓል ተግባር ከሚመዘንባቸው እና ከሚለካባቸው ጠንካራ ነጥቦች መካከል አንዱ ማኅበረሰባዊ ፋይዳው ነው፡፡ በማኅበረሰባዊ ተግባቦት፣ በዝምድና መፍጠር እና በዕርቀ ሰላም ማውረድ የሚለኩ በርካታ ማኅበራዊ ተግባራት አሉት፡፡ እንዲሁም የማኅበረሰቡን ጸጥታ በመጠበቅ እና የአካባቢን ሰላም በማስፈን በኩል ሁነኛ ፋይዳ አለው

### ለ. ሥነምኅዳራዊ ፋይዳዎች፡-

ክብረ በዓል ከማኅበራዊ ተግባቦት በተጨማሪ የአካባቢን ሥነ ምሕዳር ለመጠበቅ የራሱ አስተዋጽኦ አለው፡፡ Kay Milton (2005፡ 22) ይህን በተመለከተ ክብረ በዓል የአካባቢን ሥነምኅዳር ለመጠበቅ ስለሚጠቅም የባህሉን ባለቤቶች ዕሴቶች እና ሀገረሰባዊ እምነቶች መንከባከብ እና ማክበር እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥተዉ ይከራሉ፡፡ በክብረ በዓሉ ባለቤቶች ዘንድ የክብረ በዓሉ ቦታና ጊዜ ከተራው ጊዜና ቦታ በተለየ መልኩ የተቀደሱና የተባረኩ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በዚህ የቅድስና ቅቡልነት ምክንያት በማክበሪያው ቦታ የሚገኙ ዕጽዋት፣ አዕዋፋት፣ አራዊት እና እንስሳት እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓል ሥነምኅዳርን በማስጠበቅ ማኅበረሰቡ ከአካባቢ እና ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ እንዲኖር ያስቺላል፡፡

ለአብነትም በሐገራችን ለጉብኝት በተንቀሳቀሰባቸዉ አካባቢዎች ሁሉ ተራሮችና ሸለቆዎች በደን ደምቀዉ፣ እድሜ ጠገብ ዕጽዋት ሽበታቸዉን አንዠርግገዉ አራዊቱና የዱር እንሰሳቱ ሲቦርቁባቸዉ የተመለከተ አንድ የፈረንጅ ቱሪስት ይህ ቦታ ምንድነዉ ሲል ቤተክርስቲያን መባሉን ተከትሎ የግብርናን በጀት ለቤተክርስቲያን መስጠት አለባችሁ አለ የለበትን አስተዉሎት ልብ ማለት ይገባል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች እንኳን ሰዉና ካህናቱ ነብርና ጉሬዛዉም መነኩሴና ጻድቅ እንዲሁም የቤተክርስቲያናት ጠባቂ ተደርገዉ እንደሚከበሩና ዛፎችም የጻድቃንና መላዕክት መሰወሪያ ተብለዉ ስለሚታሰቡ እንኳን መጥረቢያ እጁን የሚሰድባቸዉ እንደማይኖር በኢትዮጵያን የደንና አብያተ ክርስቲያናት ተዛምዶ ማወቅ ይገባል፡፡

### ሐ. የቱሪዝም ፋይዳዎች፡-

ክብረ በዓል ለቱሪዝም መስሕብነት ያገለግላል ሲባል ክብረ በዓል ባሉት ባህላዊና ሃይማኖታዊ ተዋህዶ ምክንያት የማኅበረሰቡን ማንነት፣ ዕሴት፣ አኗኗር እና ፍልስፍና ማሳየት መቻሉ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች፣ ሀገረሰባዊ

ቅርሶች እና ታሪኮች የሚታዩበት ነው፡፡ እንደ ጥምቀት እና መስቀል፣ ያሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ባላቸው የአከዋወን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ሥርዓት ምክንያት ከሐገሬዉ ሕዝብ እና ከባለቤቶቹ አልፎ የእንግዳን ቀልብ የመሳብ ኀይል አላቸው፡፡

በዚህ ምክንያት የውጭ ታዳምሚች፣ እንግዶችና ቱሪስቶች ሐገር አቋርጠው፣ ባሕር ተሻግረው በመምጣት በየዓመቱ በዓሎቻችንን ይታደማሉ፡፡ እነዚህ በአላት በቱሪዝም መስሕብነት፣ በምጣኔ ሀብት ዕድገት፣ በማኅበረሰባዊ ግንኙነት እና ሀገርን በማስተዋወቅ በኩል ከፍተኛ ሚና ያላቸው ድንቅ የዓለማችን ሐብቶች በመሆናቸዉ በዩኔስኮ (የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት) በሰው ልጅ ወካይ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስነት ተመዝግበዉ ከሐገር አልፎ የዓለም ሐብት ሆነዉ ተዋዉቀዋል፡፡

**መ. ተግባቦታዊ ፋይዳዎች፡-**

ከክብረ በዓል ክዋኔ ጠቀሜታዎች መካካል አንዱ በአክባሪዎቹ ዘንድ ተግባቦት መፍጠር ማስቻሉ ነው፡፡ ለነገሩ እንኳን በሐገሬዉ ሕዝብ በዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብም ዘንድ የተግባባንባቸዉ ክብረ በዓሎቻችን እጅግ ውስብስብ የኾኑ የባህልና የሃይማኖት ክዋኔዎችን በመግለጥ ዘርፈ ብዙ ተግባቦቶችን ፈጥረዉ እየተመለከትን አይደል፡፡ ክብረ በዓል በሰዎችና በሰዎች፣ በማኅረሰብና በማኅበረሰብ፣ በሰው እና ተፈጥሮ መካከል መልካም የሆነ ተግባቦትን ይፈጥራሉ፡፡ እንዲሁም የተደበቁ እና የታፈኑ ማኅበረሰባዊ ምስጢራት፣ ባህሊዊ እና ትዕምርታዊ ፍልስፍናዎች እንዲገለጡ እና ሥግው እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 2.1.1.4. የጥምቀት በዓል ምንነት፣ አጭር ታሪክ እና ፋይዳ



*ከእድር ሜዳ የየካ የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ሽንት ጥር 11/2016 ዓ.ም*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሰብአዊ ጉዳዮችን አቅፋ ይዛለች፡፡ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎቿ በተጨማሪ የሀገር በቀል ዕውቀቶች፣ ትውፊቶችና ቅርሶች እና ኪነጥበባት ባለቤትም ናት፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዕውቀት ሲመረመር ከማኅበራዊ ዕሴቶች እና ከፎክለራዊ ዕውቀቶች ጋር የተሸመነ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የማኅበረሰቡ ዕሳቤዎች፣ ባህልና ልማድ፣ ትውፊቱና ቅርሱ እንደ ድር እና ማግ አብረው የተሸመኑበት  ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ በመኾኑም የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እና የኢትዮጵያ ባህል አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚገለጹ እና የሚከሰቱ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሏት ረጃጅም ታሪኮች ውስጥ ትምህርትን ስታስፋፋ፣ ቅርስና ታሪክን ስትጠብቅ፣ አንድነት፣ ሰላም እና መቻቻልን ለማጽናት ስትሰራ ቆይታለች፡፡ ይህ የትምህርት፣ የታሪክ፣ ቅርስ የአንድነት እና የሰላም ባለቤትነቷ በዓለም ውስጥ፣ በተለይም በአፍሪካ የተለየ ቦታ እንዲኖራት አስችሏታል (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ 2000፣ 60)፡፡

እስካሁንም ድረስ ቤተክርስቲያኗ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የኾነ የክብረ በዓል፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የቅርስ እና የትውፊት ባለቤት ናት፡፡ ከነዚህ ብርቅና ድንቅ ሀብቶቿ ዉስጥ  የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነዉ በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት እና በልዩ ትኩረት እየተከበረ ከኢትዮጵያም አልፎ የዓለም የሰው ልጅ ወካይ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ሆኖ የተመዘገበዉ የጥምቀት በዓል አንዱ እና ዋናዉ ነዉ፡፡

### 2.1.1.4.1. የጥምቀት በዓል ምንነት እና አከባበር




*ካራ አርሴማ የሥላሴ፣ የመድሃኔ ዓለምና የጊዮርጊስ ታቦታት ሽንት ጥር 11/2016 ዓ.ም*

ጥምቀት የሚለው ቃል "አጥመቀ" (አጠመቀ) ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም በተከማቸ ውሃ ውስጥ መነከር፡ መዘፈቅ፡ ገብቶ መውጣት ማለት ነው። ጥምቀት በፅርዕ ቋንቋ ኤጲፋኒ፣ በግእዝ አስተርእዮ፣ በአማርኛ መገለጥ ይባላል፡፡ ቃሉ በቀጥታ ሲተረጎም በውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት፣ መነከር፣ መዘፈቅ፣ መጥለቅ ማለት ነው፡፡ ምሥጢረ ጥምቀት በምሥጢራዊ ፍቺው በተጸለየበት ውሓ (ማየ ሕይወት) ውስጥ በሥላሴ (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ) ስም ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ የመውጣት ሂደት ነው (ማቴ ፳፰፡፲፱)። (በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ፤ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2015) ለበዓለ ጥምቀት የተዘጋጀ ያልታተመ ጽሑፍ፡፡

የጥምቀትን በዓል ካህናቱ በማኅሌትና በመዝሙር፣ በቅዳሴና በልዩ ልዩ ውዳሴ፤ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በተለያዩ መዝሙራትና ሽብሸባዎች፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ ደግሞ ወንድ ሴት ሽማግሌና ወጣት ሕፃናትም ሳይቀሩ ሀብት ያለው አዲስ ልብስ ገዝቶ፣

አቅም የሌለው ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን አጥቦና አጽድቶ፤ ነጭ በነጭ ለብሶና አሸብርቆ እጅግ በደመቀና ባማረ ሁኔታ ታቦታቱን በማጀብ በዝማሬ፣ በሆታና በእልልታ፣ በከበሮ፣ በበገናና በእምቢልታ በታላቅ ዝግጅትና ሰልፍ በባሕረ ጥምቀቱ አካባቢና ታቦታቱ በሚያልፉባቸው መንገዶች ሁሉ በታላቅ ድምቀት የሚያከብረው በዓል መሆኑ ነው፡፡ (ሊቀ ብርሃናት ኢሳይያስ፣ 2008) "በዓለ ጥምቀት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቀ)

በኢትዮጵያ ዉስጥ ጥምቀት እየተባለ የሚጠራዉ በዓል ሌሎች ሃገራት ኢፒፋኒ (Epiphany) ከሚሉት በዓል ጋር የሚጋራዉ ባህርይ ቢኖርም የሚከበርበት አላማ፣ ቀንና የአከባበር ሥርዓቱ ግን ፍጹም የተለየ ነዉ፡፡ ሌሎች ሀገራት ኢፒፋኒ የሚሉት በዓ በኢትዮጵያ ‹‹ዘመነ አስተርዮ›› የሚለዉን የሚወክል እንጂ ጥምቀት የሚለዉን በዓልና ጽንሰ ሃሳብ ሊወክል አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ጥምቀት እየተባለ የሚከበረዉ በዓል የኢፒፈኒ አንድ አካል (በኢፒፈኒ ከሚከበሩ በዓላት አንዱ) እንጂ ኢፒፈኒ የሚለዉን ጽንሰሃሳብና በዓል ሙሉ ለሙሉ የሚወክል አይደለም፡፡

ስለሆነም የጥምቀትና የኢፒፈኒ ዝምድና (በስመ ህደሪ ይጸዋዕ ማህደር) እንዲሉ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የፈረንጆቹን አስተሳሰብና ፍላጎት ተከትሎ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ኢትዮጵያን ኢፒፈኒ እያሉ የሚጽፉና የሚያስተምሩ ኢትዮጵያዉያንም አሉ፡፡ ዘመነ አስተርዮ ከሚከበሩት በዓላት አንዱ የሆነዉ ቃና ዘገሊላም የጥምቀት በዓል አካል ተደርጎ የሚታሰበዉ "የዉሃን በዓል ከዉሃ ጋር ለማገናኘት" ሲባል ከጥምቀት ጋር በከተራ ሰሞን ስለተከበረ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጥምቀት ሌሎች ኢፒፈኒ እንደሚሉት "ዘመነ አስተርዮን" የሚወክል ቢሆን ነበር፡፡ ምክንያቱም ቃና ዘገሊላ "በዘመነ አስተርዮ" ከሚከበሩት በዓላት አንዱ ነዉና፡፡ (Abebaw Y. 2006:1)

ከአበባዉ ጥናት እንደምንረዳዉ ገናን ከክሪስማስ ጋር ጥምቀትን ኢፒፋኒ ጋር በማያያዝና አንዱ የሌላዉ መገለጫ አድርጎ በማሰብ የባህል እና የሃይማኖት ተላዉጦ የሚያሥከትል እንደሆነ ካለመረዳት የሚመጣ በመሆኑ የሚመለከታቸዉ አላት ትኩረት ሰጥተዉ ሊሰሩበት እንደሚገባ የሚያመለክት ነዉ፡፡

በተለያየ የእድሜ ክልል ዉስጥ ያሉ የበዓሉ ታዳሚዎች በቡድን በቡድን ሆነዉ የተለያዩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ህብረ ዝማሬዎችን እና ጭፈራዎችን በተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅበዉ ልዩ ልዩ ጭፈራዎችን ያከናዉናሉ፡፡ በለያይም በአዲስ አበባ የተለያዩ ብሔረሰብ አባላት የተዉጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመወከል፤ በሃይማኖት በኩል ካህናት፣ ዲያቆናትና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ በባህልና ዘፈንና ጭፈራ ወጣቶች የግንባር ቀደምነቱን ሚና ይዘዉ ይታደማሉ፡፡

በዓሉ ደማቅ፣ ዉብና ማራኪ በመሆኑ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆኑ የሌሎችም እምነት ተከታዮች፤ ኢአማንያንና እና የዉጭ ሀገር ዜጎች (ጎብኚዎች) ደስታ እና እርካታ ሊያስገኙላቸዉ የሚችሉ የተለያዩ የክወና አጋጣሚዎችን በመሻት የበዓሉ ታዳሚዎች ይሆናሉ፡፡ በከበራዉ ላይም ሁሉም እንደችሎታና ፍላጎቱ ዜማ እያዜመ፣ ጭፈራ እየጨፈረ፣ እልል እያለ ክወናዉን ያሞቃል፡፡ በዓሉን ያከብራል፡፡ መንፈሱን ያድሳል፡፡ በተለይም ቀደም ባሉት ዓመታት የጥምቀትን በአል ያላከበረ፣ ታቦት ያልሸኘም እንዲህ እየተባለ በዜማ በግጥም ይወረፋል፣ ይነቀፋል!

ዳቢሎስ ሞተ አሉ ከነሚስቱ፣
ዳቢሉስ ሞተ አሉ ከነሚስቱ፣
ተስካሩን ያዉጡለት ከዚህ ያልመጡቱ! ።



*የካራ አረሴማ ምዕመናን በጥምቀተ ባሕር ተገኝተዉ ሲጠመቁ*

በጥምቀት ታቦት ማንገሱ ከሃይማኖት ሌላ የጥምቀት መድረክ ፍቅረኛ ማግኛም በመሆኑ ያገቡ ሴትና ወንድ ወጣቶች በዘፈን በእስክስታ፣ በአለባበስ፣ በጌጣጥ የሌላዉን ትኩረት ለመሳብና ለመታጨት ጥረት ያደርጉ ነበር። በበዓሉ ላይ ያልተገኙ ቆነጃጅት እና ጉብሎች እንዲህ እየተባሉ ይተቻሉ፡፡

ለጥምቀት በአል ያልዘፈነች ቆንጆ፣

ቆማ ትቀራለች እንደዘላን ጎጆ! ።

ከቤት ይዉላልሞኙ፣

ከቤት ይዉላልሞኙ፣

እናት እና ልጁ በጥምቀት ሲገኙ!

መልካም ገበያ ገበይን፣

መልካም ገበያ ገበየን፣

እናት እና ልጁን፣ በአንድ ላይ አየን፣

በበዓሉ ላይ ተገኝዉ ነጫጭ ልብስ ለብሰዉ በኩራት ተኮፍሰዉ ከሚጨፍሩት ጋር ሳይላቀሉ ዳር ዳሩን የሚሄዱትን ደግሞ በሞት እያስፈራሩ ለፈጣሪ ክብርና ለጥምቀት በዓል ያሆነ ማንነትና ልብስ ለምኔ እያሉ ወደ ጭራዉ እንዲቀላቀሉ ያደርጓቸዋል፡፡

ያሁኑ ኩራት ለምንድን ነዉ፣

ያሁኑ ኩራት ለምንድን ነዉ፣

ሁሉም የተሰራዉ ላፈር ነዉ!

እሱ አይደለም ወይ ባለቤቱ፣

እሱ አይደለም ወይ ባለቤቱ፣

ቀጭን ኩታ ለብሶ ምንድ ነዉ ኩራቱ!

በበዓሉ ላይ በዘፈን በጭፈራ፣ በመዝሙርና በምስጋና የማይሳተፉ ምዕመናንን ብቻ ሳይሆኑ እነ እማሆይም ለበዓሉ ድምቀት የድርሳቸዉን ካተወጡ እንዲህ እየተባሉ ይወቀሳሉ፣ ይተቻሉ።

ምነዋ እማሆይ ዝም አልሽ፣

ምነዋ እማሆይ ዝም አልሽ፣

ዋንጫ ጠላ ቦሆን፣ አይለፈኝ ባልሽ፣

ጠላዉማ ቢሆን ይበቃል ባላልሽ!

ኸረ ተይ እማሆይ ተነሽ፣

ኸረ ተይ እማሆይ ተነሽ፣

*መድሃዓለም ቆሞ ምነዋ ዝም አልሽ፣*

(Azeb Tadesse 2002) **የጥምቀት በአል ባህላዊዉ ወጉና ፍችዉ በሚል ርዕስ በማህበራዊ ሚዲያ ያቀረበችሁ ጽሑፍ፡፡** https://www.dw.com/am/

*ከነዚህ ግጥሞችና ከገለጻዉ የምንረዳዉ ቀደም ባሉት ዓታት የጥምቀት በዓል በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ ወጣቶች ሁሉ ከእረኝነትና ከመሳሰሉት አድካሚ ሥራዎች ሁሉ ነፃ ሆነው የሚዝናኑበትና የወጣትነት ስሜታቸውን በዘፈን፣ በጭፈራ በእስክስታና በጨዋታ የሚገልጡበትና የኑሮ ጓደኛ የምትሆናቸውንም ኮረዳ በሎሚ ዉርዋሮ የሚመርጡበትና የሚያጩበት ወቅትና ባህል ተወዳጅ ሆኖ ቆይቶአል፡፡ በከተሞች ለአብነትም በአዲስ አበባ ደግሞ ወጣቶች በአርሞኒካና በማሲንቆ እንደ ጃንሜዳ ባሉ የታቦታት ማደሪያዎች በወጣቶች ጭፈራ በድምቀት ይከበር ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለይ የከተሞች አካባቢ እንዲህ አይነት ከበራዎች እየተዘነጉና አሁን አሁን ደግሞ ክልከላ እየተደረገባቸዉ ከመሆኑም ባሻገር ተወዳጅ ባህሎቻችን በመጤ ባህሎች እየተበረዙ መምጣታቸዉ በግልጽ እየተስተዋለ በመሆኑ የሚመለካታቸዉ አካላት ትኩረት ሰጥተዉ ሊሰሩበት ይገባል፡፡*

## 2.1.1.4.2. የጥምቀት በዓል ታሪካዊ አመጣጥ



*የታቦታት ሽኝት ወደ ጃንሜዳ ጥምቀተ ባሕር ጥር 10/2016 ዓ.ም*

በ2006 ዓ.ም ለበዓለ ጥምቀት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በተዘጋጀው ልዩ ዕትም መጽሔት ላይ የጥምቀት በዓልን አጀማመር እና ታሪካዊ ጉዞ አስመልክቶ እንዲህ የሚል ሃሳብ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡

በአፄ ገብረ መስቀል ዘመን፡- የበዓለ ጥምቀት አከባበር የተጀመረው የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ በብሉይ ኪዳን ሥርዓት መሠረት "የበዓለ መጸለት (የዳስ በዓል)" በሚባል ስያሜ ሲከበር የኖረ መሆኑ ቢታመንም ታቦታትን ወደ ጥምቀተ ባሕር ማውረድ የተጀመረው ግን በ328 ዓ.ም በጣና ቂርቆስ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በሀገር ዐቀፍ ደረጃ ግን ከዛሬ 1,484 ዓመታት በፊት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (በ530 ዓ.ም) የጥምቀት በዓል በሜዳና በወንዝ ዳር እንዲከበር ተወስኗል፡፡ በወቅቱ የበዓሉ አከባበር እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአጥቢያቸው በሚገኝ ሜዳና ወንዝ ተሰባስበው ለየብቻቸው ያከብሩ ነበር። በዚህ ዘመን ማኅሌታዊው ቅዱስ ያሬድ በሥጋ በምድር የነበረበት ዘመን በመሆኑ ቅዱሱ የበዓሉን አከባበር መንፈሳዊ ሥርዓት እና ዝማሬ ከንጉሡ አፄ ገብረመስቀል ጋር በመሆን ወስኗል፡፡

በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት፡- ከዛሬ 874 ዓመታት በፊት ከአንድ ዐለት መቅደሶችን በመፈልፈል የሚታወቀው ንጉሡ ቅዱስ ላሊበላ (ቅዱሱ አርኪቴክት) ዘመነ መንግሥቱ (በ1140 ዓ.ም.) በዓለ ጥምቀት በየአድባራቱ ለየብቻ በየአካባቢው በተናጠል መከበሩ ቀርቶ በአንድ ላይ ተሰባስበው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ጥር 11 ቀን ወርደው እንዲያከብሩ እና እለቱኑ ወደማደሪ መቅደሳቸው እንዲመለሱ ሥርዓት ተሠርቷል፡፡ በዚህ ዘመን ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅደስ የኖሩበት ዘመን ስለነበር ቅዱስ ላሊበላን የበዓለ ጥምቀት አከባበሩን ለመወሰን በምክር እና በጸሎት ረድተዋቸዋል፡፡

በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት፡- ከዛሬ 769 ዓመታት በፊት ደግሞ በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት (በ1245 ዓ.ም) በዓለ ጥምቀት ጥር 11 ቀን ወደ ጥምቀተ ባሕር መውረዳቸው ቀርቶ በዋዜማው ጥር 10 ቀን (በከተራ) ወደ ጥምቀተ ባሕር በመውረድ እንዲያድሩ እና በነጋታው ጥር 11 ወደ ማደሪያ መቅደሳቸው እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡ የዚህ ሃሳብ አመንጪ የሆኑትም በዘመኑ የነበሩት ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ናቸው፡፡

በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት፡- በመንፈሳዊነታቸውንና በደራሲነታቸው የሚታወቁት አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከዛሬ 588 ዓመታት በፊት ታቦታቱ ወደ ወንዝ ወርደው ሀገርን በኪደተ እግራቸው (በእግር በመኼድ) እንዲባርኩ፣ በኼዱበት መንገድም እንዳይመለሱ ሥርዐት ሠርተዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ "ታቦት እና ሙሽራ በኼደበት መንገድ አይመለስም" የሚባል አነጋገር በሀገራችን ተለምዷል።

በአፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት፡- ከዛሬ 528 ዓመታ በፊት በአፄ ናዖድ ዘመን(1486 ዓ.ም.) ምእመናን ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚወጡትን ታቦታት አጅበው ወደ ጥምቀተ ባሕሩ በመውረድ እያከበሩ እንዲያድሩ እና በነጋታውም አጅበው እንዲመለሱ ዐውጀዋል። በዚህም አዋጅ መሠረት በዓሉ ይበልጥ ህዝባዊ ሆኗል፡፡ ምእመናን ከልጅ እስከ ዐዋቂ በዐጸደ ቤተ ክርስቲንና ታቦታቱ በሚያልፉባቸው መንገዶች "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" እንደሚባለው ያማረ ልብሳቸውን ለብሰው በዓሉን ይበልጥ ማድመቅ ጀምረዋል፡፡ (የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ፣ 2006፣ 39-45)

በአሁኑ ወቅት የጥምቀት በዓል በመላዉ የሃገራችን ክፍሎች በ50 ሐገረ ስብከቶች፣ አርባ ሽህ አብያተ ክርስቲያናት፣ በድምቀት የሚከበር ሲሆን በአዲስ አበባ ብቻ በዓት ከአስራ ሰባት ሽህ በላይ በሚሆኑ በጎ ፈቃደኞች አስተባባሪነት በዋናነት በአዲስ አበባ ጃንሜዳ፣ በጎንደር በአጼ ፋሲል መዋኛ ገንዳ፣ በአክሱም በንግሥተ ሳባ መዋኛ (ማይ ሹም)፣ በላስታ የላሊበላ መዋኛ፣ በሰሜን ሸዋ (ደብረ ብርሃን) በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አደባባይ በድምቀት እየተከበረ ነዉ፡፡ በአንጻሩ ግን የመንግስት ህግአስከባሪ አካላት ለክበረ በዓል የተገኘዉን ሰዉ በአለባበሱ፣ የሚያዜመዉን በግጥሙ ይዘት፣ የሃይማኖት አባቶችን በሚያስተላልፉት መልዕክት እየነቀፉ እና ለእስርም እየዳረጉ በዓሉ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ለዛዉን ሳያጣ በመንፈሳዊ ቀናኢነት ታጅቦ መከበሩን ቀጥሏል፡፡ Yimrhane Kirstos, January 15, 2019 Hintset: https://hintset.org/articles/epiphany

ይህም የሚያሳየን የጥምቀት በዓል በሀገራችን ከዘመናት በፊት የተጀመረና በርካታ የአከባበር ለዉጦችና ሂደቶችን አልፎ ዛሬ ካለበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ እገነዘባለን፡፡ በዚህም ጥምቀት ከሃይማኖታዊ ፋይዳዉ በተጨማሪ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያ ፋይዳዎች እንዳሉት ለአብነትም ወጣቶች የሚተጫጩበት፣

ህብረተሰቡ ቅሬታና ተቃዉሞዉን የሚያሰማበት፣ የቱሪዝም፣ የገበያና የመዝናኛ ትዕይንቱ የሚደራበት የክወና አጋጣሚ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

### 2.1.1.4.3. የጥምቀት በዓል ሁለንተናዊ ፋይዳዎች

"ከከተራ እስከ ቃና ዘገሊላ" በተከታታይ የሚከበረው የጥምቀት በዓል ከሕዝቡ ባህል ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ ከሃይማኖታዊ በአልነቱ ባሻገር ባሕላዊ ፋይዳውም የጎላ ነዉ፡፡ ይህ ታላቅ ሃይማኖታዊ በዓል ከሕዝበ ባህል ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ ከሃይማኖታዊ በዓልነቱ ባሻገር ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ታላቅ ክብረ በዓል ነው፡፡ ለሁለት ቀናት ያህል (ከተራ እና ጥምቀት) በሚከበረው በዚህ ታላቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ላይ መንፈሳዊ መዝሙሮች፣ የተለያየ ስልት ያላቸው ያሬዳዊ ዜማዎች ይመጣሉ፡፡

በበዓሉ ላይ የየአካባቢው አገረሰባዊ ዘፈኖች፣ ጭፈራዎች፣ ውዝዋዜዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡ የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችም ይደረጋሉ፡፡ በዓሉም እነዚህን የትውን ጥበባትና የሥነ ቃል ሀብቶች ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ በዓሉ ሕዝቡን በሰፊው የሚያሳትፍ በመሆኑ ታቦታቱን ለመሸኘት እና በዓሉን ለማክበር በተሰባሰበው የአካባቢው ነዋሪ መካከል ማኅበራዊ ትስስርን ይፈጥራል፡፡ ለሰላምና ለዕርቅ፣ ለአገር የመልካም ገጽታ ግንባታ፣ ለአንድነትና ለመከባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በተጨማሪ በዓሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ቱሪስቶች ከሁሉም ዓለማት ወደ አገራችን ማለትም ወደ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ጣና፣ አዲስ አበባ ጃንሜዳና ሌሎች የታሪክና የተፈጥሮ መስህቦችን ያሉባቸው ቦታዎች መጥተው እንዲጎበኙ በማድረግ ለአገሪቱ የመልካም ገጽታ ግንባታና ለቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት ጠቀሜታ አለው፡፡

የጥምቀት በዓል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም የጎላ ነው፡፡ በዓሉ በሚከበርባቸው ዋና ዋና ሥፍራዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች ይታደማሉ፡፡ ይህም በአካባቢው የንግድ እንቅስቃሴ ላይ በተለይም በአገልግሎት ዘርፉ ሰፊ እንቅስቃሴ ይፈጥራል፡፡ ሆቴሎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የመጓጓዣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የተለያዩ የምግብ እና የመጠጥ፣ የመጻሕፍት፣ የቅዱሳት ሥዕላት፣ የመዝሙር ሕትመቶች፣ ባህላዊ አልባሳትና የዕደ ጥበብ ውጤቶች አምራቾችና ነጋዴዎች ወ.ዘ.ተ. ሰፊ የሥራና የገቢ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ"

በሚለው ብሂል አብዛኛው ሰው ለበዓሉ አዳዲስ የአገር ባህል ልብሶችን ይገዛል፡፡ ይህ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎችም ከፍተኛ የገቢያ እና የሥራ ዕድል ዕድል ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡ ስጦታዎች፣ ቁሳቁሶችን በማቅረብና በመሸጥ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችም ከፍተኛ የገቢያና የሥራ ዕድል ይፈጥራላቸዋል፡፡

ዩኔስኮ በበኩሉ ጥምቀትን በዓለም ቅርስነት ለምዝገባ ያበቁት ዋና ዋና ነጥቦች ሲዘረዝር "የበዓለ ጥቀት አከባበር ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሥርዓት ቢሆንም ማኅበራዊ እሴትን በመላበሱ ለኢትዮጵያውን ማኅበራዊ ትስስር በማጠንከር የሀገሪቱ ሰላም ለማጽናት አስተዋጽኦ ያለው ነው፡፡ በዓሉ አንድነትን እና መከባር ሥር እንዲሰድድ አግዟል፤ የተለያዩ ቋቋንቋዎችን የሚናገሩ ልዩ ልዩ ነገዶች በመገናዘብ አብረው እንዲኖሩ ከማስቻሉም በላይ የማንነት ስሜትን እና ማኅበረሰባዊነትን አዳብሯል" የሚል ምስክርነቱን ሰጥቷል። (አዜብ ታደሰ 2009) https://www.dw.com/am/

## 2.1.2. የንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ዳሰሳ

ይህ ጥናት ተግባራዊ እና የክዋኔ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ የተጠና ነዉ፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ የቃላዊ ግጥሞቹን ይዘት እና ፋይዳ ተንትኖ ለማሳየት እና የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ደግሞ ቃላዊ ግጥሞቹ የክብረ በዓሉን አዉድ ጠብቀዉ የማህበረተሰቡን ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ዉበትና ሥርዓት ሳይለቁ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊ እና ሥነልቡናዊ ጣያቄአቸዉን ለማስተጋባት በሚችል አግባብ እንደት እንደተከናወኑ ለማሳየት አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡

### 2.1.2.1. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የተቀነቀነው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሐሳብ የዝግመተ ለውጥ እና የሥርጸት ንድፈ ሐሳቦችን ተቃውሞ የመጣ ነው፡፡ ንድፈ ሐሳቡ የማኅበረሰቡን መዋቅር፣ የክብረ በዓል ተግባራትን እና ባህላዊ ትዕምርቶችን በአውድ ለመመልከት አስቻይ ነው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ብቅ ያለውና እና ትግበራ ላይ የዋለው ከ1950ቹ ዘግየት ብሎ እና ከ1960ቹ ቀደም ብሎ እንደኾነ Bell (2009፡ 42) ያስረዳሉ፡፡ አክለውም ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን፣ የክብረ በዓል ክዋኔን እና የባህላዊ ትዕምርትን ተዛምዶ ለማየት የሚያስችል

ነው በማለት አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡ (Elliot Oring 1976፡ 78) በበኩላቸው "ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ባለፉት ጊዜያት ለሥነ ሰብዕ፣ ለፎክሎር፣ ለሥነ ጽሑፍ እና ለሥነ ልሳን የትምህርት መስኮች የተሻለ መመልከቻ በመኾን አገልግሏል" በማለት የንድፈ ሐሳቡን ኹለ ገብነት ያስተነትናሉ፡፡

የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ዋና አቀንቃኝ ከሚባሉት መካከል (William Bascom, Bronsilaw Malinowski and A.K Radcliffe Brown) ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራን ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን መሠረት በማድረግ የፎክሎርን ተግባራት፡- የማምለጥ፣ የመትከል፣ የማስተማር እና የመቆጣጠር ተግባሮች እንዳሉት ይገልጻሉ (William R. Bascom (1965: 239), Sims and (Stephen 2005: 175)፡፡ እንደዚሁም Radcliffe Brown የፎክሎርን ተግባር ከተፈጥሮ እና ከአልሰለጡኑ ማኅበረሰቦች ጋር አያይዘው ይመለከቱታል (Bell 2009, ይህ የWilliam Bascom በአራት ክፍሎች ወስኖ መመልከት እና የA.K Radcliffe Brown ተፈጥሮአዊ እና ያልሰለጠኑ ማኅበረሰቦች ጉዳይ ነው የሚለው ማጠንጠኛ ሐሳብ ትችት ገጥሞታል፡፡

የትችቱ ማጠየቂያ ደግሞ የፎክሎርን ፋይዳ አስተሳሰብ ከፎክሎሩ ባለቤት ይልቅ በምሁራኑ አይን ለማየትና ለማጠቃለል መሞከር ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ ከሞጋቾቹ መካከል (Sims and Stephen 2005: 176) የባህል ክዋኔዎች የተለያዩና ውስብስብ ከመኾናቸው የተነሣ አንዳች ፎክለራዊ ፋይዳን ለመመርመርና ለማወቅ በመጀመሪያ ለምን እንደሚከወኑና ክዋኔውን መረዳት ተገቢ ነው ካለ በኋላ አንድ የፎክሎር የዘውግ ክዋኔ በተጠኚዎቹ አይን በመመርመር እና በመተርጎም ፋይዳውን ማወቅ ተገቢነት አለው የሚል ማጠየቂያ ያነሣሉ፡፡ በተጨማሪ (Dorson 1972: 167) ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ የፎክሎር ተግባር የሚለካው እንደየ ባህሉ እና ኹኔታው፣ እንደ ክዋኔው እና አጋጣሚ፣ እንደ አውዱ እና አሐዱ በባህሉ ውስጥ ተገብቶ መኾን አለበት በማለት ያብራራሉ፡፡

Dan Ben Amos (1982፡ 46) and (Shoe Maker 1990, 86) Sims and Stephen (2005: 175) የተባሉ የዘርፉ አጥኚዎች ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በማኅበራዊ፣ በሥነ ልቡናዊ እና በባህሊዊ ፋይዳዎች በሚሉት ነጥቦች ላይ መመርኮዝ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ ተመራማሪዎቹ አክለውም ፎክሎራዊ ተግባር የሚለካው በሚከወንበት ባህል ውስጥ በመግባት በአውድና በክዋኔው ሚዛን ልክ መኾን አለበት የሚል የነ Dorson (1972: 167) አይነት ጠንካራ አቋም አላቸው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ

ሐሳብ በአንድ የፎክሎር ቡድን ውስጥ መጠነ ሰፊ የኾነ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳን ለመረዳት ሚናው የጎላ ነው፡፡ ስለኾነም አንድ የፎክሎር አጥኚ የፎክሎር ቡድኑ የሚጋራቸው ክብረ በዓሎች፣ ሥነ ቃሎች ትውፊቶች፣ ልማዶችና እምነቶች ለምን? እንዴት? መቼና የት? እንደሚከወኑ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በባህሉ ውስጥ ገብቶ መረዳት ግድ ይለዋል፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ከአውድ እና ክዋኔ ጋር የጠበቀና የጠነከረ ግንኙነት አለው፡፡ በዚህ ቁርኝት ውስጥ የፎክሎር ተግባር በክዋኔ አውድ ላይ በመመሥረት ማኅበራዊ፣ ባህሊዊና ኹለንተናዊ መስማማትን በማስገኘት በፎክሎሩ ባለቤቶች መካከል የተረጋጋ ማኅበረሰብ እንዲመሠረት ያደርጋል:: (Elliot Oring (1976: 72) የፎክሎር ተግባር ጠቅለል ባለ ኹኔታ ሲታይ የማኅበረሰቡን መዋቅር በማስቀጠል፣ ሥርዓትና ሕግን በመደንገግ፣ በማጽናት እና በማስከበር የማኅበረሰቡን የሕይወት በተሻለ ሁኔታ ያስቀጥላል፡፡ እንደዚኹም ማኅበረሰቡን በማረጋጋትና የተደላደለ ኑሮ እንዲቀጥል በማድረግ ትልቅ ሚና አለው፡፡ የፎክሎር ዘርፍ የኾነው ክብረ በዓል በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በርካታ የአክባሪዎቹ ጉዳዮች አደባባይ የሚወጡበት ነው፡፡

ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ እና ሰብአዊ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ማጠንጠኛዎች ናቸው፡፡ እንደ አጠቃላይ የክብረ በዓል ፋይዳ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በ2015 እና 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተዜሙ የቃል ግጥሞች ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዎች ለመመርመር ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት መመልከቻ (መታገጊያ) በመሆን አገልግሏል፡፡ ይህም ማለት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ቃል ግጥሞቹ ተሰብስበዉ ሲተነተኑ ለማህበረሰቡ፣ ለዘፈኑና ለሆታዉ አቀንቃኝና አጃቢዎቹ እንዲሁም ማህበረሰቡን ለሚያስተዳድሩትና በቀጣይ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች ሊኖራቸዉ የሚችለዉን ፋይዳ (ተግባር) መሰረት ያደረገ የመመልከቻ መነጽር እንደሆነ መገንዘብ ይባል፡፡

### 2.1.2.2. የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ

ፎክሎር ከሚጠናባቸው በርካታ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፎች መካከል አንዱ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ንድፈ ሐሳቡ እንደ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ኹሉንም የፎክሎር መከሠቻዎች ለመመርመር በማስቻሉ ለዘርፉ እጅግ ተመራጭ እየኾነ መጥቷል፡፡

(Bauman 1977፡ 190) እንደሚሉት የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ አውድን፣ አጋጣሚን፣ አሐድን፣ ከዋኔን፣ ተሳታፎን እና የክዋኔውን ትውን ጥበባት በአንድ አስተባብሮ የሚያስገኝ በመኾኑ ለፎክሎር ጥናት መመልከቻ ከፍ ያለ ፋይዳ አለው የሚል አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ (Goldstein 1962፡ 95) በበኩላቸው ፎክሎር በክዋኔ፣ በዕውቀት፣ በጥበብ፣ በትርጉም እና በትውፊት የተሞላ የትምህርት መስክ ነው ካሉ በኋላ ፎክሎርን በክዋኔ ንድፈ ሐሳብ መመልከት አዋጭነት ይኖረዋል በማለት ስለ ንድፈ ሐሳቡ አስፈላጊነት ያስረዳሉ፡፡

እነ Mccarmik C.T and White, K.K (20011: 96) በበኩላቸው ክዋኔ ለማህበራዊ ቡድኑ አንዳች የጋራ ውጤትን በማስገኘት እና በቡድኑ ውስጥ ተግባቦትን በመፍጠር ከዋኝ፣ ተሳታፊ እና ዕውቀት በጋራ የሚገናኙበት አውድ ነው ይላሉ፤ እንደዚሁም በክዋኔ ግንኙነት ወቅት በአውድ ዛፍ ጥላ ሥር፣ አዉድ፣ ከዋኝ እና ተሳታፊ የሚተዋወቁበት፣ አንድነት የሚፈጥሩበት እና የክዋኔው ባለቤት የኾኑት ማኅበረሰቦች ዕሴታቸውን የሚያስቀጥሉበት የግንኙነት ማዕቀፋቸው ነው በማለትም ያስረዳሉ፡፡

Yankah, Kwesi and Peek, Philip (2004: 670) በበኩላቸው የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በ1970ዎቹ አካባቢ ጀምሮ ለሥነ ሰብእ፣ ለፎክሎር፣ ለሶሽዮሎጂ እና ለመሳሰሉት የትምህርት መስኮች አዋጭ መመልከቻ መኾኑን ያረጋግጣሉ፡፡ እንደነ Sims and Stephen (2005: 133) and Bauman (1977: 195) ዕይታ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የቅርብ ጊዜ የጥናት መስክ ቢኾንም ለፍክሎር፣ ለሥነ ሰብዕ፣ ለዘውግ እና ለባህል ጥናት ወሳኝና ዘመነኛ ንድፈ ሐሳብ ነው የሚል ምልከታ አላቸው፡፡

በአንድ የፎክሎር ዘውግ ውስጥ የሚታዩት የክዋኔ ዘውጎች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ዳንሶች፣ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎች፣ ፌከራዎች እና ልማዶች ለየብቻ ተነጣጥለው የቆሙ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የሚሰናሰሉ፣ የሚተጋገዙ እና የሚተረጎሙ ናቸው:: (Richard Bauman 1975: 77) የእነዚህ ፈርጀ ብዙ የፎክሎር ዘውጎች ህልውና እና ተስተላልፎ የሚጸናው በክዋኔ ደምሥር ነው፡፡ በመኾኑም የፎክሎር ዘውጎችን ለመረዳት እና ለመተርጎም የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አስፈላጊ ነው፡፡

የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ ያለውን ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ማኅበራዊ መዋቅር፣ የክዋኔውን ጥበባት፣ ስሜት እና ትርጉም ለመረዳት ያስችላል፡፡ ይህን ሐሳብ በተመለከተ Peek and and (Yankah 2004: 797) "የክብረ በዓል ክዋኔ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮችን ትርጉም የሚሰጥ ወይም የተለያየ ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች እና

ግለሰባዊ ተግባራት የሚገለጹበት ነው፡፡ ከአውድና ከቴክስት አኳያ የክብረ በዓል ክዋኔ የሚጠበቅ ስሜት ወይም ትውን ጥበባት በሥዕል መልክ የሚታዩበት አጋጣሚ ነው" በማለት ያትታሉ፡፡

እንደዚሁም Finnegan (1992፡ 93) ከነ Peek and Yankah ሃሳብ ጋር በሚስማማ መልኩ ክዋኔ የክብረ በዓል ዋና ማስኬጃ ሲኾን በክብረ በዓል ውስጥ የሚከወኑትን የሥነ ቃል ዘውጎች ለመረዳት ትልቅ ፋይዳ አለው ይላሉ፡፡ (Bauman 1977፡ 14) በበኩላቸው አንድ የክብረ በዓል ክዋኔ በክዋኔው ወቅት ለማኅበረሰቡ ፍቃድን፣ ነጻነትን፣ መከወንን እና መሳተፍን የሚፈቅድ ነው፡፡ በነጻነት እና በመሳተፍ የሚደረግ ክዋኔ ደግሞ የማኅበረሰቡን ዕሴት፣ ፍልስፍናና የሕይወት ተሞክሮ ለመረዳት ያስችላል የሚል ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

እንደነ (Sims and Stephen 2004፡ 141) ማረጋገጫ ደግሞ የክብረ በዓል ክዋኔ በአንድ በታወቀ ስፍራና ጊዜ የከዋኝ፣ የአሐድ፣ የአውድና የተሳተላልፎን ተራክቦ በመፍጠር የፎክሎር ትውን ጥበባት እውን የሚሆንበት አጋጣሚ ነው በማለት የክዋኔ ንድፈ ሐሳብን መጠነ ርዕይ ይገልጻሉ፡፡ (Bauman 2002፡ 72) በበኩላቸው የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የክዋኔ አላባውያን የኾኑትን ከዋኝን፣ አሐድን፣ አውድን፣ ትዕምርትን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ በአንደበትና ከአንደበት ውጭ የሚገልጹትን ኹሉ የሚያጠቃልል ነው በማለት የንድፈ ሐሳቡን አስፈሊጊነት ይገልጻሉ፡፡

የክብረ በዓል ክዋኔ አንድ ማኅበረሰብ ዕውቀቱ እና ዕሴቱን በአንድ ኹነኛ አውድ ውስጥ ለትዕይንት የሚያበቃበት አጋጣሚ ነው፡፡ በዘህ የክዋኔ ትዕይንት ውስጥ የማኅበረሰቡ ዕሴቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ሕጎች፣ ዕውቀቶች፣ ግብረ ገብነቶች እና ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች እንዲታዩ እና እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካን፣ ማኅበራዊ እና ባህሊዊ ጉዳዮችን አደባባይ በማውጣት ግለሰቦችን ከማኅበረሰቡ፣ ዕውቀትን ከለማጁ ጋር የማገናኘት አቅም አለው፡፡ (Peek M. and Yankah 2004፡ 797-800) የክብረ በዓል ክዋኔ በአብዛኛው ቡድናዊ በመኾኑ ማኅበረሰባዊ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው፡፡ በክብረ በዓል ክዋኔ ማኅበረሰቡ በሚችለው መልኩ ወይም ክብረ በዓሉ በሚያዘው ልክ እየተሳተፈ ወይም ሳይሳተፍ በክዋኔው ውስጥ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ከዋኝ እና ተሳታፊው በእስክስታ፣ በቀረርቶ፣ በፉከራ፣ በዝማሬ፣ በሽብሻቦ እና በመሳሰሉት ተሳትፎ ውስጥ የደስታ ስሜት እንዲያገኝ እና ለአንጻፍታም ቢኾን

ከችግሮቹ እንዲነጠቅ እና እንዲያመልጥ ያስችለዋል፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ የትዳር ጓደኛ፣ አበልጅ፣ የጡት አባት፣ የነፍስ አባት የመሳሰለትን ዝምድናን በመፍጠር ቁሳዊ ወይም ሥጋዊ የኾነ ጥቅምን ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች ያስገኛል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ መመሰጥን፣ ከአምላክ ጋር መገናኘትን፣ ይህን ዓለም መርሳትን፣ ይኾንልኛል ብሎ ማሰብን በማለምለም የተጠኚዎቹን ኅሊና ይገዛል፡፡ ክብረ በዓል በአንደበት፣ በምልክት፣ በትዕምርትና በተምሳሌት አማካይነት ማኅበራዊ እና ሰብዓዊ ተግባቦቶችን ይፈጥራሉ፡፡ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ለመረዳት ከዘወትራዊው ውክልና በተጨማሪ ፍካሬያዊ ውክልናዎቹን፣ ትዕምርቶቹን እና ተምሳሌቶቹን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የክብረ በዓል ክዋኔ በከዋኙ፣ በተሳታፉዎቹና በተመልካቾቹ ዘንድ ማኅበራዊ ግንኙነትን በመፍጠር እና ማኅበራዊ ዕሴቶች ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ በኩል ላቅ ያለ ሚና አለው፡፡ በመኾኑም የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት መመልከቻ አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ የጥምቀት በዓል የአደባባይ በዓል ከመሆኑም በላይ ሰፊ ማህበረ ባህላዊ የክዋኔ አዉዶችን አጣምሮ በደማቅ የአከባበር ሥነሥርዓት ለሦሥት ተከታታይ ቀናት ማለትም በጥምቀት ዋዜማ አብያተ ክርስቲያናቱ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ወርደዉ በሚያድሩበት የከተራ፣ በዕለተ ቀኑ በሚከበረዉ የጥምቀትና በማግስቱ በሚከበረዉ የቅዱስ ሚካኤል በዓላት ላይ ልዩ ልዩ ክዋኔዎች የሚስተዋሉበት ነዉ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በተደረገዉ የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ ቃላዊ ግጥሞችን በመሰብሰብ ወቅታዊ ከሆነ ፋይዳቸዉ ጋር ተያይዘዉ የተጠኑ ጥናቶች አልተገኙም፡፡ ይኹን እንጂ ጥምቀትን ጨምሮ በሌሎች በሃይማኖታዊ እና ማህበረ ባህላዊ በዓላት የክወና አጋጣሚዎች ላይ በመገኘት በምልከታ፤ እና ህብረተሰቡ የሚያዉቃቸዉን አሁን የማይከወኑ ቆየት ያሉ ቃላዊ ግጥሞችን በቃለመጠይቅ በመሰብሰብ ከፋይዳ እና ይዘት ትንተና አንጻር በተጠኑ አራት ጥናቶች ላይ ቅኝት ተደርጓል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ተናጠላዊ ይዘት እና ጭብጥ ላይ ሳይሆን የተዜሙበትን ኅብረተሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ነባራዊ ሁኔታ በሚያንጸባርቅ መልኩ የተጠኑ ጥናቶች በመሆናቸዉ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው በመሆናቸዉ ዳሠሣ ተደርጎባቸዋል፡፡

ከላይ በተቀመጠዉ መስፈርት መሰረት የተመረጡት ለሦስተኛ ድግሪ መመረቂያ የተሰሩ ኹለት ጥናቶች እና ለኤምኤ ድግሪ መመረቂያ የተሰሩ ሌሎች ኹለት ጥናቶች በአማርኛ ፊደል ተራ ቅደም ተከተል እንደሚከተለዉ ተቃኝተዋል፡፡

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በርካታ ጥናቶች የተዳሰሱ ሲሆን ለዶክትሬት ድግሪ መመረቂያ  አማረ ሞላ በ2009፣ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ምደባ፣ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎና Getie Gelaye 2001 Contemporary Amharic Oral poetry from Gojjam: Classification and sample analysis የሚሉት እንዲሁም ለማስተርስ ድግሪ መመረቂያ መኮንን አስማማው፣ በ2007 ዓ.ም በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኽኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ እና በደብረወርቅ ሞላ በ2010 ዓ.ም. የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና በሚል ርዕስ የተደረጉት ጥናቶች ይዘትና ፋይዳ ትንተና ላይ ስለሚያተኩሩ ተመርጠዉ በሰፊዉ ዳሰሳ ተደርጎባቸዋል፡፡

በአማረ "የአማርኛ ቃል ግጥሞች ምደባ፣ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ" በሚል ርዕስ በ2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በዶክትሬት ድግሪ ለመመረቅ የተደረገ ጥናት መነሻ ምክንያቶች የሆኑት፣ ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ በተለያዩ ጊዜያት ብሶቱንና ቁጭቱን፣ ጥላቻውንና ተቃውሞውን ወ.ዘ.ተ የሚገልጽባቸውን ቃል ግጥሞች እስከ ትንታኔያቸዉ ሰንዶ በማስቀመጥ ለሌሎችም አጥኝዎች መረጃ እንዲሆን በማሰብ የተጠና እንደሆነ ገልጧል፡፡

መረጃዉን የሰበሰበዉ በሰሜን ወሎ ዞን የሚገኙት ቆቦ፣ ጉባላፍቶና ሀብሩ ወረዳዎች ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማ፣ በተመረጡት አካባቢዎች የሚገኙትን ቃል ግጥሞች መሰብሰብ፣ መመደብና መተንተን እንደሆነ ገልጿል፡፡ እነዚህን አላማዎች ለማሳካትም ከ1500 በላይ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ 650 ቃል ግጥሞች በስምንት ዋና ዋና ምድቦች በመመደብ 400 ያህል ቃልግጥሞችን መተተኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ቃልግጥሞቹን ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ሰነዶች ዳሰሳ ሲሆኑ ከተሰበሰበው የቃል ግጥም መረጃ በመነሳት የተገኙት የአማርኛ ቃል ግጥም አይነቶችን ቃል ግጥሞቹ፣ የሙገሳና የውዳሴ፣ የትችት፣ የጀግንነትና የፈሪነት መግለጫዎች፣ የቁንጅናና የፍቅር መግለጫዎች፣ ብሶትንና ቁጭትን፣ እንዲሁም ጥላቻንና ማንኳሰስን የሚያመለክቱ በማለት በስምንት ዋና ዋና ምድቦች አደራጅቶ ተንትኗል፡፡

በመሆኑም ከፖለቲካና ከእርስ በርስ ጦርነቶች፣ ከድርቅና ከርሃብ እንዲሁም በሽታን፣ ስደትን፣ ቤት ማፍረስን፣ የሚመለከቱ ቃልግጥሞች ተተንትነዋል። በአጠቃላይ ቃልግጥሞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ፤ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ባህላዊ ገጠመኞች የሚያሳዩ ስለሆኑ የሚመለከታቸው የማህበረሰብ አጥኝዎች፣ የታሪክና የሥነ ሰብ ተመራማሪዎች፣ የስነጽሑፍ ባለሙያዎች፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሰዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች ወ.ዘ.ተ. ይህንን ጥናት እንደመነሻ በመጠቀም ማህበረሰቡን ለማስተዳደርም ሆነ ለእድገትና ለልማት እቅድና ለስራ ቢገለገሉበት የተሻለ ይሆናል የሚል ጥቆማ በመስጠት ተጠቃሏል።

የአማረ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ ጥናቱ በነጠላ ጭብጥ እና ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑና የተጠኚን አካባቢ እና የማህበረሰቡን አጠቃላይ (ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሥነልቡናዊ) የህይወት ገጽታዎች የሚያንጸባርቁ ቃላዊ ግጥሞችን ሰብስቦ ትንታኔ ያቀረበ መሆኑ፤ ማኅበረሰቡ በተለያዩ የክወና አጋጣሚዎች ላይ የሚያዜማቸዉን ቃል ግጥሞች ሰብስቦ እና አደራጅቶ ይዘትና ፋይዳቸዉን በመተንተን ለትዉልድ ከማስተላለፍም ባሻገር ለማህበራዊ ለዉጥ የሚበጅ ማጠቃለያ ማስቀመጡ፤ ለምን በሁለት ዙር እንደሰበሰበ እና ከመቼ እስከ መቼ እንደሰበሰበዉ ባይጠቅስም ቃላዊ ግጥሞቹን በሑለት ዙር መሰብሰቡ ነዉ፡፡

በልዩነት የታየዉ መረጃ አሰባሰብ እና የጥናት ወሰኑ በተተኳሪዉ ማህበረሰብ እና አካባቢ በታሪካዊ አጋጣሚ የተከሰቱ ሁነቶች ላይ ከዱሮ እስከ ዘንድሮ የሚመለከት መሆኑ፤ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ የቃል አቀባዮችን ዘያዊ አገላለጽ እንደወረደ መጠቀሙና ወደመደበኛዉ ቋንቋ አለመመለሱ፤ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸዉን በጅምላ አንድ ማብራሪያ ለመስጠት መሞከሩ እና የግጥሞቹን አይነት ባህርይ፣ ፋይዳ፣ መነሻና መድረሻ ተንትኖ ለማሳየትና ለመተርጎም አለመሞከሩ ይጠቀሳሉ፡፡

እንደ ድክመት የታየዉ እና በዚህ ጥናት እንዳይደገም ትምህርት ይሰጣል ተብሎ የታሰበዉ ደግሞ የተሰበሰቡትን የቃል ግጥሞች ፋይዳ በተመለከተ በማጠቃለያዉና አልፎ አልፎ በቡድን ያደራጃቸዉን የቃል ግጥሞች የነበራቸዉን ፋይዳ ለማሳየት ከመሞከር ባለፈ እያንዳንዳቸዉንም ሆነ በጅምላ ያደራጃቸዉን ግጥሞች ለማህበረሰቡ፣

ለስርዓቱ እና ለሶስተኛ ወገን አካላት ያላቸዉን ፋይዳ በብቃት ዘርዝሮ ለማሳየት አለመሞከሩ በዚህ ጥናት ይህንን መሰል ችግር እንዳያጋጥም አስተማሪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በጥንካሬ በኩል በተለያዩ ጊዜ የተዜሙ (የተገጠሙ እና የተከወኑ) 1500 ቃል ግጥሞችን መሰብሰቡ፣ የተሰበሰቡበትን በክዋኔ እና የመከወኛ ስልቶች ለይቶ ማደራጀቱና ከማህበራዊ ፋይዳቸዉ አንጻር በሰፊዉ መተንተኑ እንዲሁም ለጥናት የመረጠዉን አካባቢ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያ፣ ስነልቡናዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች እና መፍትሄዎችን ለማመላከት መሞከሩ እና ቃላዊ ግጥሞችን ቀርጾ ለማስቀመጥ ያደረገዉን ጥረት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሌላዉ በዳሰሳዉ ምልከታ የተካሄደበት Getie Gelaye: 2001 **Contemporary Amharic Oral poetry from Gojjam: Classification and sample analysis** በሚል ርዕስ ያቀረበዉ ጥናት ነዉ፡፡ ጥናቱ በኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ ወዲህ የምስራቅ ጎጃም አርሶ አደሮች የገጠሟቸውን፣ ያዜሟቸውን፣ ያንጎራጎሯቸውን የሀዘን፣ የብሶት፣ ፍትህ ማጣት፣ መበደል፣ ቁጭት፣ ድህነትና ፖለቲካዊ ግጥሞች የተመለከቱ ናቸው፡፡ መጣጥፉ የመሬት ሽግሽጉን የደገፉትም ሆነ የተቃወሙት አካላት ድጋፍም ሆነ ተቃውሟቸውን እንዴት በቃል ግጥማቸው አማካይነት እንደገለፁ ያሳያል፡፡

ጌቴ መረጃውን ከምስራቅ ጎጃም ወረዳዎች ደጅ ማሪያምና ገደብ-ጊዮርጊስ ከ32 መረጃ አቀባዮች 2000 ቃል ግጥሞችን እንደሰበሰበና ወደ እንግሊዝኛ እንደተረጎማቸው ገልጿል፡፡ መረጃውንም በሁለት ገበሬ ማህበረሰቦች ውስጥ በተከሰቱ 6 ልዩ ልዩ የክዋኔ አጋጣሚዎች ላይ ተገኝቶ ቃል ግጥሞቹን በመቅዳት ሰብስቧል፡፡ እነዚህ የክወና ማህበራዊ አጋጣሚዎችም የግብርና ስራዎች፣ ህዝባዊ በዓላት፣ የልቅሶ ስርዓት፣ ሰርግ ስርዓት፣ የከብት እገዳ ወቅትና ዓመታዊ የሀይማኖት በዓላት ለአብነትም ጥምቀት መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡ አጥኝው መረጃውን ያሰባሰበው በሁለት ዙር ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ምልከታ በማድረግና ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ቃል መጠይቁንም ያደረገው በተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ሁኔታዎች ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ቄሶች፣ የዕድሜ ባለጸጎች እና ህጻናት እንደሆነ ገልጿል፡፡ የሰበሰባቸውን ቃል ግጥሞች ከሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር በስድስት ክፍሎች መድቦ እና ተንትኖ አቅርቧቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ለገበሬው የሚሰጡ ስያሜዎች (ቢሮክራት፣ ፊውዳልና ጪቃኝ) የሚመለከቱ፣ የመሬት ሽግሽግ ፖሊሲውን

የሚደግፉ ግጥሞች፣ የመሬት ሽግሽግ ፖሊሲውን የሚቃወሙ ግጥሞች፣ የአካባቢውን ባለስልጣናት ሙስና፣ ኢፍትሃዊነትን የሚመለከቱ፣ ዘመኑን የሚቃወሙ፣ በገበሬውና በአገዛዙ መካከል ያለውን ግጭት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የጌቴ ጥናት በገበሬዎች ቃል ግጥም ላይ ማተኮሩ፣ ግጥሞቹን በሰበሰባቸው ማህበራዊ አጋጣሚዎች፣ በሰበሰባቸው ቃል ግጥሞች ብዛትና አቀራረብ እንዲሁም ቃል ግጥሞቹን መቼ፣ እንዴት፣ እና ለምን እንደሚገጥሙና እንደሚጠቀሙባቸዉ በማሳየቱ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ የመረጃ አሰባሰቡ በኹለት ዘመን የተገደበና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና መዛግብት ዳሰሳ መጠቀሙ፣ የይዘት እና ፋይዳ ትንተና ማድረጉ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

የአማርኛ ግጥሞችና ዜማዎች በገበሬው የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ከመዝናኛና ከማስተማሪያነት ተግባራቸው በተጨማሪ የገጠሩን ህብረተሰብ አሳሳቢ ችግሮች እና ወቅታዊ ጉዳዮችን በማንፀባረቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። የገበሬውን ሃሳቦች፣ አስተያየቶች፣ አመለካከቶች እና ግንዛቤዎች፣ እንዲሁም የሽሹትን ደስታ እና የደስታ ስሜት፣ ሀዘናቸውን እና ቅሬታቸውን በተለያዩ የግል እና የቡድን ትርኢቶች እና አውዶች ይፋ የሚወጡባቸዉ እና የሚገለጡባቸዉ ብቸኛ መንገዶች እንደሆኑ ይጠቁማል።

በጥንካሬ ከህብረተሰቡ ታሪካዊ የኪነጥበብና የቃል ግጥም አደራረስ፣ ክወና እና ተስተላልፎ ታሪካዊ ዳራ በመነሳት የአማርኛን የቃል ግጥሞችን ዘዉጋዊ ምደባ ማሳየት እና በርሱም ጥናት ዉስጥ ተግባራዊ ማድረጉ ለአብነት የሚጠቀሱ መልካም ተመክሮዎች ናቸዉ፡፡

በሦሥተኛ ደረጃ ዳሰሳ የተደረገበት በመኮንን አስማማው 2007 ዓ.ም በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ ለምኤ ድግሪ መመረቂያ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰራዉ ጥናት ነዉ፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዋና ትኩረቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው የትኩረት ነጥብ በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች እንዴትና መቼ እንደሚከወኑ ማሳየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቃል ግጥሞቹን ይዘት መተንተን ነው። ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ቦታና ጊዜ በመገኘት ለዚህ ጥናት የሚጠቅሙ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ነው። በምልከታና በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኙ

መረጃዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና የተሟላ መረጃ ለማግኘት የቡድን ውይይት ተደርጓል። በጥናቱ የሰባት በዓላትን የቃል ግጥሞች ክዋኔ ተመልክቷል።

የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች መከወኛ አጋጣሚ ክብረ በዓላት ናቸው። በጥናቱ ህዳር 21 ቀን የማሪያም ታቦትን ንግሥ አስመልክቶ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች እንደሚጀምሩና እስከ ፋሲካ በዓል ድረስ በሚከበሩ ዓውደ ዓመቶችና የንግስ በዓላት እንደሚቀጥሉ ይገልጻል።

እንደ አጥኚዉ ገለጻ ቃል ግጥሞቹ በፆታ ልዩነት ላይ ተመሥርተው የሚገጠሙ ናቸው። የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ሴቶችን ብቻ ለማወደስና ለመሳደብ የሚገጠሙ ሲሆን የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ደግሞ ሴቶችን በማወደስ በአብዛኛው ወንዶችን የሚሳደቡና በጥቂቱ የሚያሞግሱ መሆናቸው ያሳያል። በሁለቱ ቃል ግጥሞች መካከል የአከዋወን ሂደት ልዩነትም እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል። የአበሹቴና የኧኸይቦሌ የቃል ግጥሞች አከዋወን የተለያየ ቢሆንም የሁለቱም ቃል ግጥሞች አጠቃላይ ይዘት የደላንታ ወረዳን ህብረተሰብ ባህል መጠበቅና ማንነቱን ማንጸባረቅ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

በጥናቱ የቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ድግግሞሽ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል። ለዘመናት በዓመት አንድ ጊዜ በፋሲካ በዓል ብቻ ይከወኑ የነበሩት እነዚህ ቃል ግጥሞች አንድ ትውልድ ሳያልፍ በአንድ ቀበሌ ውስጥ በዓመት ከስድስት ጊዜ በላይ በመከወን ላይ መሆናቸውን ጥናቱ ያስረዳል። በገና፣ በጥምቀት እና በፋሲካ በዓላት ጨዋታዎቹ በሚከወኑባቸው ሁሉም ቀበሌዎች ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑ ሲሆን በንግስ በዓላት ግን በተወሰኑ የታቦት ንግስ ባለባቸው ቀበሌዎች ብቻ የሚከወኑ መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል። ከክዋኔው ጋር ተያይዞ ድግግሞሹ (የሚከወኑበት አጋጣሚ) የጨመረ ቢሆንም በከተማ እና በከተማ ዙሪያ በሚገኙ ቅርብ ቀበሌዎች ጨዋታዎቹ እየቀሩ መሆኑን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ሴቶችን የአንድ ቡድን አባል በማድረግ ግንኙነታቸው የጠነከረ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና አላቸው። በተጨማሪም በየመንደሩና በየጎጡ ያሉ ሀሜቶችን ይፋ በማድረግ መረጃ ከመለዋወጥ ባሻገር የሚታሙት ሴቶች ከስህተታቸው እንዲታረሙና ማህበረሰቡ መልካም ሥነ ምግባር የሚላቸውን እሴቶች እንዲከተሉ ዕድል ያገኛሉ። የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ሁለቱም በገጠር አካባቢ የሚከወኑ ናቸው። በመሆኑም ጥናቱ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስር የጠነከረ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች የክዋኔ ቦታና የክዋኔ ድግግሞሽ ለውጥ እየታየባቸው እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። ቀደም ባለው ጊዜ ጨዋታዎቹ የሚከወኑት በፋሲካ ዕለት ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በገና፣ በጥምቀትና ታቦት በሚነግስባቸው የገጠር ቀበሌዎች ይከወናሉ። በሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች ይከወኑ የነበሩት እነዚህ ጨዋታዎች በአሁኑ ጊዜ ከከተማ ራቅ ባሉ ቀበሌዎች ብቻ እየተከወኑ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

የመኮነን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያለያየዉ በመጀመሪያ ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ሳይሆን ክዋኔያዉ ላይ ትንተና በማድረግ ፋይዉን በማስተዋወቅ ላይ ማተኮሩ፣ ስድብና ምስጋና ተኮር ቃላዊ ግጥሞች ብቻ መቀንቀናቸዉ፣ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞቹ በሴቶች ስለሴቶች ለሴቶች የሚዜሙና መሆናቸዉ እና በሰባት በተለያዩ ወቅቶች በሚከወኑ የክዋኔ አጋጣሚዎች ላይ የሚቀርቡ መሆናቸዉ ነዉ፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ ደግሞ ቃላዊ ግጥሞቹ በሃይማታዊ በዓላት ለአብነትም በጥምቀት በዓል ላይ የሚከወኑ መሆናቸዉ፣ በይዘታቸዉ ላይ ትንተና በማድረግ ፋይቸዉን ለማሳየት ትረት ማድረጉ፣ መረጃዎቹ በኹለት ዙር መሰብሰባቸዉ እና የማህበረሰቡን ማንነትና ፍላጎት የሚያላክቱ መሆናቸዉ ነዉ፡፡

በጥንካሬ የሴቶችን አንድነት፣ መተሳሰብና መቀራረብ የሚያጠናክሩ ቃላዊ ግጥሞችን ሰብስቦ በመተንተን ፋይዳቸዉን በአጭሩም ቢሆን ማሳየቱ ክዋኔዉም ያለዉን ፋይዳ አብሮ ለማመላከት መሞከሩ የሚጠቀስ ሲሆን በድክመት ቃላዊ ግጥሞቹና ክዋኔዉ ያቸዉን ፋይዳ በጥልቀት ተንትኖ ለማሳየት መሞከር አለመቻሉ እና ለአጥኚዎች እና ለሌሎች ለሚመለከታቸዉ አካላት ምክረ ሃሳብ እና ጥቆማ ሳያሰጥ ጥናቱን በማጠቃለያ መቋጨቱ ይጠቀሳሉ፡፡

በመጨረሻ ምልከታ የተደረገበት ጥናት በደብረወርቅ ሞላ በ2010 ዓ.ም የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና በሚል ርዕስ የተደረገዉ ጥናት ነው፡፡ ለጥናቱ መነሻ ምክንያቶች የሆኑት ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ የኖረ በመሆኑ፣ ብሶቱን፣ ጭንቀቱን፣ ጥላቻውንና ተቃውሞውን ወ.ዘ.ተ የሚገባቸውን ቃል ግጥሞች እየፈጠረ ስሜቱን ሲያንፀባርቅ እንደቆየና

እነዚህ የፈጠራቸው ቃል ግጥሞች ተሰብስበው ትገልጻለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ባሉት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸው ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች እየተለወጡና እየቀሩ በመሆናቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፉ የነበሩ ቃል ግጥሞች እየተረሱ፣ እየተለወጡ፣ በሂደትም እየጠፉ የመሄድ አጋጣሚዎች ሰፊ እየሆነ እንደመጣ ታስረዳለች፡፡

በዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጡ አካባቢዎች በአምባሰል ወረዳ የሚገኙ ቀበሌዎች ሲሆኑ የጥናቱ ዋና ዓላማ በተመረጡት አካባቢዎች የሚገኙትን የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞችን ፋይዳ መተንተን ሲሆን፣ ይህን ለማሳካት መስክ ላይ የተሰበሰቡት 61 ግጥሞች ናቸዉ፡፡ ቃል ግጥሞቹም በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ሲሆን የሙገሳ፣ የነቀፌታና የፍቅር በሚሉ ጭብጣዊ መከፋፈያዎች ከተግባራዊ ፋይዳቸዉ አንፃር ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ በሙገሳ ቃል ግጥሞች ስር አካባቢንና ወጣቶችና ጎልማሶችን የሚያሞግሱ፣ ልጃገረዶች እርስ በርሳቸው የሚሞጋገሱበት፣ የፍቅር ስሜትን የሚገልፁ ሲሆን በነቀፌታ ቃል ግጥሞች ስር ደግሞ ወንዶችን ብቻ የሚተቹና ልጃገረዶቹ እርስ በርሳቸዉ የሚነቃቀፉበት በሚል የቀረቡ ሲሆን ፍቅር ደግሞ ራሱን ችሎ ቀርቧል፡፡ በእያንዳንዱ ምድብ በተደረገው ትንተና መሰረት፣ ጥናቱ ከደረሰባቸው ግኝቶች መካከል የሙገሳና የውዳሴ ቃል ግጥሞች አካባቢዎችንና ሰዎችን የሚያሞግሱ ናቸው፡፡ በሚል ግኝት ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

በአጠቃላይ ቃል ግጥሞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ባህላዊ ገጠመኞች የሚያሳዩ ስለሆነ የሚመለከታቸው የማህበረሰብ አጥኝዎች፣ የታሪክና የስነስብ ተመራማሪዎች የስነ-ፀሁፍ ባለሙያዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሰዎች ወዘተ ይህንን ጥናት እንደመነሻ በመጠቀም ለማህበረሰቡ ለማስተዳደርም ሆነ ለእድገትና ለልማት ቢገለገሉበት የተሻለ ይሆናል የሚል ጥቆማ አቅርባለች፡፡

የደብረወርቅ ጥናት ከአማረ ጥናት ጋር በይዘት ልዩነት ይኑረዉ እንጂ በቅርጽ ተመሳሳይ ነዉ፡፡ በተጠኑበት ዘመን የአማረ ጥናት ቀዳሚ በመሆኑ ለደብረወርቅ ጥናት መነሻ ብቻ ሳይሆን መዳረሻም ይመስላል፡፡ በተጨማሪም የጥናት ወሰኑ የአምባሰል ወረዳ ቀበሌዎች የሚል በመሆኑ እጅግ ሰፊና በዚህ መልኩ ሊዳሰስ የማይችል መሆኑ፣ በወረዳዉ ቀበሌዎች ሁሉ በተደረገዉ ዳሰሳና መረጃ ስብሰባ 61 ቃል ግጥሞች ብቻ መሰብሰባቸዉ እና ማደማደሚያዉ ወንዶችን በትችትና በማህበራዊ ዉክልናቸዉ

የሚገልጹ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዉ ቢተነተኑም በልጃገረዶቹ ባህላዊ ጭፈራ እና አገልግሎቱ ላይ ብቻ የሚያተኩር በመሆኑ የጥናቱን ድክመቶች የሚያመላክቱ ችግሮች ናቸዉ፡፡ የደብረወርቅ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ በከፊልም ቢሆን ቃል ግጥሞችን ከጥምቀት በዓል ላይ በምልከታ የተሰበሰቡ መሆናቸዉ፣ የቃል ግጥሞችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ ትንታኔ በማድረግ እና ፋይዳቸዉን ለማመላከት በመሞከሩ ነዉ፡፡ ከዚህ ጥናት የሚለየዉ ደግሞ በልጃገረዶች የዘፈን ክዋኔ ላይ ተመስርቶ በጥምቀት፣ በሰርግ እና በእንጨት ሰበራ የክወና አጋጣሚዎች ላይ የተዜሙት ቃል ግጥሞች ያላቸዉን ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ነዉ፡፡

በዳሰሳዉ የሀገራችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የድፕሎማሲና የዉህድ ማህበረ ፖለቲካዊ ማንነት ማዕከል በሆነችዉ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለዉን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ ሆነዉ አልተገኙም፡፡ በመሆኑም በጥምቀት በዓል ላይ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በሦሥት ታቦታት ማደሪያዎች የተዜሙ የሕዝቡን አመለካከት፣ ስሜትና ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ቃላዊ ግጥሞች ሰብስቦ በመተንተንና በማህበረ ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ዉስጥ ያላቸዉን ሁለንተናዊ ፋይዳ እና አስተምህሮ በመጠቆም እንደ ጥናት በዘርፉ የተፈጠረዉን ኀዶሎ ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሦሥት

## የጥናቱ ዘዴ

የሥነቃል አጠናን፣ ቴክስት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስለሆነ ጥናቱ ባለሶስት ደረጃ ሞዴልን ተከትሎ የሚሰራ እንደነበርና፣ ደረጃዎቹም መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መመደብ እና መተንተን የሚባሉት ናቸው በማለት (Ben Amos 1982፡16) ይገልጻሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ጥናት አውዳዊ መረጃዎችን ስለማያካትት ኋላ ቀር ነው ቢባልም መስከኛው መስክ ላይ በሚቆይባቸው ጊዜያት አውዳዊ መረጃዎችን እየተመለከተ እና ግልጽ ያልሆነለትን እየጠየቀ መሰብሰብ ከቻለ ሞዴሉ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል::

ይህ በጥምቀት በዓል አከባበር ላይ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም የተዜሙ ቃል ግጥሞች ይዘትና ፋይዳ ትንተና በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የተከናወነ ነዉ፡፡ የቃል ግጥም ጥናት የሥነቃል ጥናት አካል እንደመሆኑ Ben Amos የተቀሱትን ሞዴል መከተል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ቃል ግጥምን ያጠኑ ምሁራን ሲገልጹ "በአፍሪካ ስነቃል ጥናት ውስጥ አካባቢያዊ ግጥሞችንና ዘፈኖችን ሰዎች ወይም ቡድኖች በሚገጥሙበት፣ በሚደረድሩበት እና በሚከውኑበት ጊዜ ተገቢ የሆነው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ እና የገለጻው ትኩረት መሆን ያለበት የክዋኔውን ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ አውዶችን ከመግለጽ ላይ ነው" (Getie 2001፡19)

እንደ አጠቃላይ ይህ ምዕራፍ የምርምሩን የአጠናን ዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ሲከናወን ምን ዓይነት የጥናት ዓይነት፣ ምን ዓይነት የጥናት ሥነዘዴ እና እንደ መታገጊያ ምን አይነት ንድፈ ሐሳቦች ጥቅም ላይ እንደዋሉ፤ የጥናት ዘዴዉን ተከትሎ ምን ዓይነት የናሙና አመራረጥ ዘዴ ጥቅም ላይ እንደዋለ፤ መረጃዎች በምን የመተንተኛ ስልት እንደተፍታቱ፣ እንዲሁም መረጃዎች ከየት፣ ከነማን፣ በምን ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እንደተሰበሰቡ እና አጥኚው የተከተለው ሥነምግባር ምን እንደሆነ የሚያሳይ ክፍል ነው፡፡

ጥናቱ በአዲስ አበባ የጥምቀት በዓል ላይ የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በማደራጀት ይዘት እና ፋይዳቸዉን ተንትኖ መመርመር በመሆኑ ሙሉ በሙሉ በምልከታ፣ ቀረጻና በመዛግብትና ማስታወሻ፤ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ በነዚህ ዘዴዎች ቃል ግጥሞቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በጥናትና ምርምሩ የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካትም

ዓይነታዊ ጥናት ዓይነት እና እንደ ጥናት ሥነዘዴ ገላጭ ሥነዘዴ የተመረጡ ሲሆን ለጥናቱ ማብራሪያና ማስተንተኛ (መታገኒያ) ተግባራዊ እና የክዋኔ ንድፈ ሐሳቦች ተመርጠዋል፡፡

## 3.1. የጥናቱ ዓይነት

በፎክሎር መስክ ጥናቶች የሚደረጉት በአብዛኛው የመጠን (የስሌት) ሳይሆን ዓይነታዊ፣ ሀተታዊ (የጥራት) የጥናትና ምርምር ዓይነትን በመጠቀም ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት ዓይነታዊ (ሀተታዊ) የምርምር አቀራረብ ባህርይን የተከተለ ነው። ይህም ማህበረሰቡን የሚመለከቱ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተገኙት የሥነቃል መረጃዎችን በማሰባሰብ የሚብራራበት አቀራረብ ነው። የዚህ ጥናት ስልት ተፈላጊነቱ እየጎላ የመጣው በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚካሔዱ ጥናቶች በመስክ በሚገኙ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸውና ዘዴውም ተፈጥሯዊ፣ አሳታፊ፣ በአውድ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እና የሚገለጽ መሆኑን ምሁራን እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> *Qualitative research geners have become increasingly important modes of inquiry for the social sciences and applied fields such as education, regional, planning, nursing, social work, community development, and management. Qualitative research a) is naturalistic, b) draws on multiple methods that respect humanity of participants in the study, c) focuses on context, d) is emergent and evolving, and e) is fundamentally interpretive.(Marshal & Rossman 2006:1)*

## 3.2. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ

ለዚህ ጥናት የተመረጠዉ የጥናትና ምርምር ሥነ-ዘዴ ገላጭ የምርምር ሥነ-ዘዴ ሲሆን ገላጭ ምርምር ሥነዘዴ የአንድን ጉዳይ ወይም ክስተት ወቅታዊ ሁኔታን በግለጽ በማሳየት ላይ ያተኩራል፣ ገላጭ ምርምር መላምቶችን መቅረጽና መፈተሽን ያካትታል፡፡ ገላጭ ምርምር ቋሚና አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት ክስተቶችን በአሉበት ተፈጥሮአዊ አካባቢ ይመረምራል ተጨባጭ መረጃዎች ላይ በመመስረት ትክክለኛ መደምደሚያዎችን ይሰጣል፡፡ እውነታን በመፈለግ ላይ ብቻ ሳይሆን ጠቃሚ የሆኑ የዕውቀት መርሆዎችንና ለችግሮችም መፍትሔ በመፈለግ ላይ ያተኩራል፡፡ መረጃ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን መለካት፣ መመደብ፣ መተንተን እና  መተርጎምን ያካትታል፡፡

## 3.3. የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

(Bernard, H. R. 2005፡ 189-192) እንዳለው በጣም ታወቂና ተተግባሪ የናሙና አወሳሰድ ቴክኒኮች መካከል ግምት የማይሰጥ ናሙና በመጠቀም በዚህ ዘርፍ ውስጥም ዓላማ ተኮር ናሙና የተባለው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ይህ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በሁሉም ዓይነታዊ ጥናት ዘዴ ለመጠቀም የሚያስችል፤ ትክክለኛ፣ እውነተኛ እና ተዓማኒ መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ነው፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥናት ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመራጭ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሆኖ ተመርጧል፡፡ አላማ ተኮር የናሙና ዘዴን በተመለከተ (ያለው 2004፣ 36) ሲገልፁ፡- "አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የምፈለገውን መረጃ ለሲጡኝ ይችላሉ፡፡ የሚሉትን ለመመለስና ለማሳካት ሲባል ዓላማ ተኮር ዘዴ ይመርጣል፡፡" በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዚህን ጥናት ዓላማ ማሳካትና ጥናቱን ውጤታማ ለማድረግ ሲባል፣ ቃላዊ ግጥሞቹ በዘፈንና ጭፈራ የሚከወኑ በመሆናቸዉ እና ክዋኔዉ በጉዞ የሚደረግ በመሆኑ አድካሚና ሞራላዊ ተነሳሽነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ለስርዓት ከበራና ለአዉዱ ጉልህ ሚና የሚኖራቸው ቡድኖች እና ወጣቶች ተመርጠዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች

የስነቃል መረጃ ለመሰብሰብ ወደመስክ በሚወጣበት ጊዜ የመስክ ሁኔታውና የሚሰበሰበው የስነቃል አይነት ወሳኝ ይሆናል:: መስከኛው የሚሰበሰበውን የስነቃል አይነት መቼ? የት? በምን አይነት ሁኔታ? ወዘተ. ሊያገኝ እንደሚችል ቀደም ብሎ ማሰብ ይገባዋል:: ምንም እንኳ የመስክ ላይ እንቅስቃሴው የተመቼ ይሆናል ተብሎ ባይታሰብም በተቻለ መጠን የመስክ ተግባርን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በጥበብና በትዕግስት ማለፍ የመስከኛው ሃላፊነትና ብቃቱም የሚወሰንበት ይሆናል፡፡

ከዚህ አንፃር መስክ ላይ የስነቃል መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል ተብለው የታመነባቸው የመስክ መቼቶች፣ ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሰራሽ (አርቲፊሻል)፣ እና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች ናቸው፡፡ (ፊቃደ 1991፣ 122-124) ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው የስነቃል አይነቱ በባህል ወይም በተለምዶ የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ሲሆን የቃል ግጥም ተፈጥሯዊ መቼቶች ሊሆኑ ከሚችሉት መካከል የሰርግ፣ የስራና ክብረ በአላቶች ልዩ

ልዩ መዝናኛ ቦታዎች፣ ጥቂቶቹ ናቸው:: በእነዚህ ቦታዎች መስከኛው እየተገኘ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ቃልግጥሙ በተፈጥሯዊ መቼቱ ከነሙሉ ክዋኔው እና ከታዳሚዎቹ አኳያ እየታየ የተሟላ መረጃ ለመያዝ ያስችላል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል መስከኛው የስነቃል አይነቱ በተፈጥሯዊ መቼቱ ሲከወን ባልተገኘበት ጊዜ ወይም አጋጣሚ፣ ወይም ደግሞ የስነቃል አይነቱ ከክዋኔ ውጪ ሆኖ እየተረሳ፣ እየተለወጠ በሚሄድበት ሁኔታ ያለን ስነቃላዊ አይነት ቅርስ የማስቀረትና የመሰነድ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ ሲፈጠር የሚሰበሰብበት መቼት ሰው ሰራሽ መቼት ይሆናል፡፡ ሰው ሰራሽ መቼት ባንድ በኩል፣ ከዚህ በፊት ይከወን የነበረ፣ ዛሬ ግን ያለፈን የስነቃል አይነት ክዋኔውን እያስታወሱና እያስመሰሉ የሚከወኑበት መቼት ሲሆን፣ በሌላ በኩል አንድን የስነቃሉ አይነት ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ቦታና ጊዜ መስከኛው እየጠየቀ ስነቃልን የሚሰበስብበት መቼት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ (ፈቃደ 1991፣ 123)

በመሆኑም ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ የጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ ቃል ግጥሞችን በመሰብሰብ እና በማደራጀት ይዘት እና ፋይዳቸዉን በመተንተን ላይ ያተኮረ በመሆኑ ተፈጥሯዊ መቼቶትን በመጠቀም በዋናነት በምልከታ የቃል ግጥም መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለጥናት የተመረጠው አካባቢ በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ የጥምቀት በዓል አከባበር ላይ በአማርኛ ቋንቋ በተለይም በወጣቶች የተዜሙ ቃል ግጥሞች ናቸዉ፡፡ ወጣቶች የተመረጡበት ምክንያት ወቅቱ የጸጥታ ሃይሉ በመሰል የክዎና አጋጣሚዎች ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሥርዓትና አመራሩን የሚተቹ ቃል ግጥሞች እንዳይዜሙ ክልከላ የሚያደርግበት በመሆኑ ክልከላወና ጫናዉን ተቋቁመዉ የማህበረሰቡን ችግር ለማንጸባረቅ የሚችሉት ቃል ግጥሞችን የሚያዜሙት ወጣቶች ይሆናሉ የሚል የአጥኚዉ ግምት በመኖሩ ነዉ፡፡

በተጨማሪም አካባቢዉ የተመረጠዉ የአጥኚዉ መኖሪያ ሰፈር የካ ወረዳ 12 በመሆኑ አብያተ ክርስቲያናቱን፣ ማኅበረሰቡን፣ ወጣችቶን እና ካህናቱን በከፊልም ቢሆን ለማወቅና የትብብር መንፈስ ለመፍጠር የሚያስችል እድል ስለሚሰጥ ነዉ፡፡

በአካባቢዉ ከሚታወቁ እና ቅርበት ካላቸዉ ጓደኞች በተጨማሪ ችግርና አፈጻጸሞችን በቅርበት ለመከታተልና ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎችን ለማሰማራትም ምቹ ነዉ፡፡ አካባቢዉ ከመሃል ከተማ ወጣ ያለ በመሆኑ ከክልል የመጡ ሰዎች ተከራይተዉ

የሚኖሩበትና የቱባ ባህል ባለቤቶች እና አቀንቃኞች በስፋት የተገኙበት ነዉ፡፡ ከአጎራባች አካባቢዎች የሚመጡ ወጣቶችም በስፋት የሚሳተፉበት ከመሆኑም ባሻገር በ2015 ዓ.ም በተመሳሳይ ቦታና አዉድ የተወሰኑ ቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ ጥረት በተደረገበት አጋጣሚ ለዚህ ጥናት የሚሆኑ ቃል ግጥሞች በብዛት ሊገኙ የሚችሉ ስለመሆኑ አመላካቾች መሆናቸዉ አካባቢዉ ተመራጭ ሆኗል፡፡

## 3.5. የመረጃ ምንጭና መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት በዋናነት እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለዉ ምልከታ ሲሆን በክዋኔ ወቅት አቀንቃኞች በክዋኔ ላይ በጭፈራ፣ በዘፈን፣ በሆታ የሚያወርዱቸውን ቃል ግጥሞች የሚሰበሰቡበትን ሁኔታ የሚመለከት ይሆናል፡፡ ምልከታ ከውጭ ሆኖ የተመለከቱትን መግለፅ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የስሜት ህዋሳት አማካይነት የሚሰማውንና የሚታየውን እስከ ማካተት የሚደርስ መሆኑን (Goldstein፣ 1964፡ 77) ያመለክታሉ፡፡

ምልከታ መስክ ላይ እንደሚገኘው አጋጣሚና ምቹነት እየታየ የሚካሄድ የመስክ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም፣ መስክ ላይ አጥኚዉ የተገኘባቸው አጋጣሚዎች የከተራ፣ ጥምቀትና የሚካኤል ዕለት በአላት ናቸዉ፡፡ በዚህ የክዋኔ አጋጣሚ ላይ በመገኘት ለዚህ ጥናት መረጃ የሚሆኑ ቃል ግጥሞችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡

መረጃዎቹ አጥኚዉ በአካል በተገኘባቸዉ አካባቢዎች በአሉን ለማክበር ከታደሙና በቡድን ተደራጅተዉ ከሚጨፍሩ ወጣቶች የምስል፣ የቪዲዮና የድምጽ መረጃዎችን በመቅረጽ የተሰበሰቡ ናቸዉ፡፡ የጨፈራው ቡድኖች ቁጥር ብዙ ከመሆኑም ባሻገር በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በጉራጌኛ፣ ወላይተኛ እና በአማርኛ ወ.ዘ.ተ. የሚጨፍሩ ስለነበሩ በአማርኛ ቱባዉን ባህል መሰረት ይዘዉና ጠብቀዉ የሚጨፍሩትን አስር ቡድኖችን በመምረጥ የሚያዜሟቸዉ ቃል ግጥሞች በምልከታ፣ በቀረጻና በማስታወሻ ተሰብስበዋል፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥናት የሚሆነዉ መረጃ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ሊቃነ ጳጳሳትን ጨምሮ በርካታ ቱሪስቶችና በርካታ ሕዝብ የሚታደምበትን ጃንሜዳ ጨምሮ ሦሥት የታቦታት ማደሪያ ስፍራዎች (ጥምቀተ ባህሮች) በተጨማሪ የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የዳግማዊ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤልና የየካዉ የቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት ከመንበራቸዉ ወደ ጥምቀተ ባህር ሲወርዱና

ከጥምቀት በኋላ ወደመንበራቸዉ ሲመለሱ በባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ታቦታቱን ከሚያጅቡ አስር ቡድኖች የተሰበሰበ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ውስጥ ምልከታ (ቀረጻ እና ማስታወሻ) የተመረጡ ሲሆን ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የጥናት እና ምርምር ስራዎች፣ መጽሐፎችና መጽሔቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ተመርጠው መረጃ ተሰብስቦባቸዋል፡፡

## 3.5.1. ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች፡-

ይህ የመረጃ ምንጭ ናሙና ከሆነው ግለሰብ ወይም ቡድን ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት የምንፈልገውን መረጃ በምልከታ፣ መረጃ የምናገኝበት ስለሆነ በዓይናችን የተመለከትናቸውን ብቻ ሳይሆን በአፍንጫችን ያሸተትናቸውን፣ በዕዝነ አዕምሯችን የተመለከትናቸውን፣ በምላሳችን የቀመስናቸውን እና በመዳፎቻችን የዳሰስናቸው ነገሮችን እንደሚያካትት (Goldstein, 1964፡79) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ከቃል ግጥም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዘፈን፣ ጭፈራ እና ሆታ፣ ከመሳሰሉ ክዋኔዎች ሙሉ መረጃ ለማግኘትና ለማሳየት ምልከታ ተግባር ላይ ይዉላል፡፡ በዚህ ጥናት ከምልከታ ዓይነቶች ውስጥም ተገቢና አስፈላጊ የሆነው ከፊል ተሳትፏዊ ምልከታ ይተገበራል፡፡ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱም በተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ከሦሥቱ የታቦት ማደሪያዎች (ጥምቀተ ባህሮች) ከአስር የባህላዊ ጭፈራ ቡድኖች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ምልከታ ከቀዳማዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ እና ቀዳሚዉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነዉ፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ እንደመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ ሲውል በክዋኔ ወቅት በሆታ፣ በጭፈራና በዘፈን በክዋኔ ላይ የሚያወርዷቸውን ቃልግጥሞች እየሰበሰቡ፣ ያለውን ሁኔታ በሚመለከት መረጃ መሰብሰብን የሚመለከት ይሆናል፡፡ ምልከታ ከውጭ ሆኖ የተመለከቱትን መግለፅ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የስሜት ህዋሳት አማካይነት የሚሰማውንና የሚታየውን እስከ ማካተት የሚደርስ መሆኑን (Goldstein፣ 1964፡ 77) ያመለክታሉ፡፡

ምልከታ መስክ ላይ እንደሚገኘው አጋጣሚና ምቹነት እየታየ የሚካሄድ የመስክ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የጥምቀት በዓል የሚከበረዉ በጥር ወር በመሆኑ በከተራ፣ የጥምቀት እና በሚካኤል በአላት መረጃዎች በሁለት ዙር የተሰበሰቡ ናቸዉ፡፡

የመጀመሪያው ዙር ጥር 10፣ 11 እና 12/ 2015 ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን በዚህ ዙር 50 ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ ሁለተኛው ዙር የመስክ እይታ ጥር 10፣ 11 እና 12/ 2016 ዓ.ም. የተደረገ ሲሆን በዚህ ዙር 300 ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ በሁለቱ ዙሮች የመስክ ቆይታዎችም በሦሥት ታቦት ማደሪያች እና ሠላሣ አብያተ ክርስቲያናት እና ታቦታት በሚታደሙባቸዉ ጥምቀተ ባሕሮች ላይ በመገኘት በአዲስ አበባ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ 350 ቃል ግጥሞችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ከምልከታ የተገኙትን ትዕይንቶች የዘፈን ሆታና ጭፈራ ክዋኔዎች በተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ካሜራ ተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) ምስል አልባ ድምጽ እና ፎቶ በመቅረጽ፣ ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዮችንና የቀረጻ ክልከላ (ተቃዉሞ ሲያጋጥም) ማስታወሻ በመያዝ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የክዋኔ አጋጣሚዎች ላይ በጃንሜዳ፣ አርሴማ፣ ስጋሜዳና ጃንሜዳ ታቦት ማደሪያ እና ጥምቀተ ባህር ላይ በመገኘት በአሉን ለማክበር በቡድን በቡድን እየሆኑ ከሚጨፍሩት ወጣቶች ጋር ከፊል ታዳሚ በመሆን የአማርኛ ቃልግጥሞች ከሚቀርቡባቸው ባህላዊ ዘፈኖች እና ባህላዊ ጭፈራዎች ለዚህ ጥናት መረጃ የሚሆኑ ግጥሞች ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ በምልከታ ላይ መረጃ የሚሰበሰበዉ በቀረጻና በማስታወሻ ነዉ፡፡ የስነቃል ጥናት መረጃ አሰባሰብ በምልከታ ወቅት የተመለከቱና የሰሙትን በማስታዎሻ ከመጻፍና ፍቶ ከማንሳት በተጨማሪ ተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) በመቅረጽ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በዚህ ጥናትም በሰፊዉ ስራ ላይ ዉሏል፡፡

## 3.5.2. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች፡-

ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ሁለተኛዉ የመረጃ ምንጭ ሲሆን ይህ የመረጃ ምንጭ ስለሚጠናው ጉዳይ የተጻፉ መጽሐፎችን፣ መጽሔቶችን፣ ደብዳቤዎችን፣ ጋዜጣዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ መግለጫና የአከባበር መርሃ ግብሮችን፣ የጥናት ወረቀቶችን እና የጥናት መድረኮች የመወያያ ሰነዶችን እና መሰል የመረጃ ማግኛ ስልቶችን ተጠቅመን ከቤተ መጻሕፍት፣ ከኢንተርኔትና ከግለሰቦች መረጃ የምናገኝበት ነው፡፡ የዚህ የመረጃ ምንጭ ደካማ ጎኑ ከጉዳዩ ባለቤት ጋር የቀጥታ ግንኙነት ሳናደርግ በተጻፉ ሰነዶች ላይ ብቻ በመመስረት የምንሰበስበው በመሆኑ ተመራጭነቱንና የመረጃው ጤነኝነት ዝቅ ማድረጉ ሲሆን፣ ነገር ግን ጉዳዩን ለማጥናት ያለው አማራጭ በዚህ ብቻ የተወሰነ ከሆነ በቀጥታ የማይገኙ መረጃዎችን በማስገኘትና ጥናት እንድንሰራ ማስቻሉ በጎ ጎኑ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በክወና አጋጣሚዎች ላይ በቀረጻ ለመሰብሰብ ያልተቻሉ መረጃዎችን በተለይም ጥምቀትን ጨምሮ የክብረ በዓላትን ምንነት፣ ዓይነት፣ ባህርያትና ፋይዳ በተመለከተ ከበይነ መረብ (ኢንተርኔት) ከአዲስ አበባ ኬኔዲና የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የጥናትና ምርምር ስራዎችን፣ መጻሕፍትን፣ ያልታተሙ ጽሑፎችን፣ መጽሔቶችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ መግለጫና የአከባበር መርሃ ግብሮችን እና የጥናት መድረኮች የመወያያ ሰነዶችን ወ.ዘ.ተ ማሰባሰብና በማደራጀት መተንተን ተችሏል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የተሰበሰቡ መረጃዎች ትርጓሜ (ትንታኔ) ተስማሚ ከሆኑ ቲወሪዎች አንጻር የሚከናወን መሆን አለበት። በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየፈርጁ ተደራጅተው ተስማሚ ከሆኑ ቲዮሪዎች አኳያ መተንተን እንዳለባቸው Marshal & Rossman (2006: 156) እና Creswell 2007:161) ይገልጻሉ። በአንድ ጥናት ውስጥ ከመስክ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተለይተው ለአንባቢ ግልጽ የሆነ ትርጉም እንዲሰጡ በልዩ ልዩ ቲዮሪዎች መተንተን እንደለባቸው በጥናትና ምርምር ስልቶች ላይ የጻፉ ምሁራን እነ (Dundes 1980); (Marsha and Rossman 2006) እና (Creswell 2007) ይገልጻሉ። ከዚሁ አንጻር ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ የመተንተኛ ቲዮሪዎች ተዳሰዋል።

በዚሁ መሠረት በልዩ ልዩ መንገዶች የተሰበሰቡት የቃል ግጥም መረጃዎች በዓይነታቸዉና በይዘታቸው ተለይተው ተደራጅቷል። ይሁን እንጂ በየርዕሳቸው ተለይተው የተደራጁ መረጃዎች በራሳቸዉ ገላጭ አይደሉም። በመሆኑም ምንነታቸውን፣ በማብራራት ፋይዳቸውንና ያላቸውን ትርጉም ከተለያዩ ቲዮሪዎች አኳያ መተንተን አለባቸው።

በዚሁ መሠረት ዓውዳዊ እና ይዘት ትንተና ስልቶች ተሰብስበዉ የተደራጁት ቃል ግጥሞች አዉድና ይዘታቸዉን ጠብቀዉ ተተንትነዋል፡፡ በዓዉዳዊ ትንተናዉ ቃል ግጥም ሁለገብ በመሆኑ የማህበረሰቡን ገጽታ ከተለያዩ ጉዳዮች ማለትም ማህበራዊ፣ ወቅታዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ አኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች አንጻር መዳሰስ አለበት። ስለሆነም ቃል ግጥም ሲጠና ትንታኔዎቹን ከተለያዩ አቅጣቻዎች ማየት የግድ ይሆናል። ሥነቃል በአውዳዊ ቲዮሪ የሚተነተን ከሆነ ይዘት ትንተና የግድ መነሳቱ አይቀርም። ምክንያቱም ያለይይት ትንታኔ አዉድ ብቻውን የለምና ነዉ።

አዉዳዊ ትንተና ቲወሪ አቀንቃኞች (Bascom 1954 and Ben Amos 1993) ዋነኛ ትኩረት አንድ የፎክሎር ዘውግ የተከናወነበትን አውድ ማጉላት ነው። ስለዚህ የፎክሎር ጥናትና ምርምር አውድን መሠረት ያደረገ ነው ሲባል በተለይም የሥነቃል መረጃዎች ሲሰበሰቡ የሥነቃሉ ዓይነት ምሳሌያዊ ንግግር፣ ቀልድ ተረት ዘፈን ወ.ዘ.ተ የዓይነቱ ውስጣዊ ሁኔታ ወይም የቋንቋው ትርጉም እና ሥነቃሉ የተነገረበት (የተከወነበት) አውድ (Context) ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (Dundes, 1980, Ben Amos, 1993: 210)።

በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን የሚያካትት መሆኑን Ben Amos 2102: 11) ያስረዳል። ይህንኑ በማጠናከር አውድን ከሥነቃል አንጻር ሲገልጽ ከሦስት ቁልፍ ጉዳዮች ማለትም ከከዋኙ ስብእና፣ ከመከወኛው ድባብ፣ ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ አኳያ ይመለከታል:: (Okepewho, 1992: 105) የክዋኔው ድባብ ማለት ከከዋኙ አንደበት የሚወጡትን ቴክስቶች (የሥነቃል ዓይነቶች)፣ ቴክስቱን ለመግለጽ የተጠቀማቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ከዋኙን ከበው ያሉ ታዳሚዎችና ተጽዕኗቸውን እንዲሁም በከዋኙ ስኬት ወይም ውድቀት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ያካትታል።

ባህላዊ ዓውድ፡- ባህላዊ ዓውድ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔን ከሶስት ገጽታዎች አኳያ መመልከት ማለት ነው። እነርሱም ትዕምርታዊ ትርጉም፣ ባህላዊ ተቋም ትርጉምና የተግባቦት ሥርዓት ደንቦች ናቸው። ይህ ማለት በባህላዊ ዓውድ ውስጥ ከሚካተቱት ገፅታዎች አንዱ የባህላዊ ክዋኔው "ትዕምርታዊ ትርጉም" ነው። የባህላዊ ዓውድ ትንተና የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ትዕምርታዊ ትርጉም ምን እንደሆነ ይገልጻል። ሁለተኛው የባህላዊ ዓውድ ገጽታ "የባህላዊ ተቋም ትርጉም" ሲሆን የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ባህላዊ ተቋማትና ባህላዊ መዋቅር ውስጥ ያላቸው እሴትና ስምረት ምን እንደሆነ ማብራራት ማለት ነው።

ሦስተኛው የባህላዊ ዓውድ ገጽታ ደግሞ "የተግባቦት ሥርዓት ደንቦች" መሆናቸውን (Bauman 1977); (Okepewho 1992) እና (Ben Amos 1993) ይገልጻሉ። በመሆኑም ዓውድን መሠረት አድርጎ የተካሔደው የዚህ ጥናት ትንተና ዋናው ጉዳይ የሥነቃል ዓይነቶቹ እንዴት የመግባቢያ ሥርዓትና ስልት ሆነው እንደሚያገለግሉና እንዴት ከሌሎች የፎክሎር ቅንጣቶች ጋር እንደሚዛመዱ ማሳየት ነው።

ማህበራዊ ዓውድ፡- እነዚሁ ምሁራን ማህበራዊ ዓውድ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔን ከሦስት ገፅታዎች አኳያ መተንተን ማለት መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያው የሥነቃል ዓይነቶቹ ከግለሰብ ህይወትና የኑሮ መሰረት ጋር የሚገናኙበትን መንገድ ሆኖ ይህም በውስጥ የተካተቱ ኢኮኖሚን፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው። ሁለተኛው የማህበራዊ ዓውድ ገፅታ የሥነቃል ዓይነቶቹ ባለቤት ማን እንደሆነ መለየትና ይህም እድሜን፣ ጾታን፣ አከባቢን፣ የኑሮ ደረጃን ወዘተ.. መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ክፍፍል ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ የሚብራራበት ነው።

ሦስተኛው የማህበራዊ ዓውድ ገፅታ ወቅታዊ ሁኔታ ሲሆን ይህም ማህበረረሰቡ አሁን በዚህ ዘመን የሚገኝበት ማህበራዊ ሁኔታ የሚመለከት እና ዘመኑን ተከትለው በሚከሰቱ ተለዋዋጭ ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔ ማህበራዊ ፋይዳ ከዘመኑ ፍላጎት አንጻር ያለበት ሁኔታ የሚተነተንበት ነው (Bauman, 1977); (Okepewho, 1992;) (Ben Amos, 1993) በዚህ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ከላይ የተዘረዘሩትን ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታዎችን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ባህላዊ እና ማህበራዊ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ታሪካዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ካላቸዉ ፋይዳ አኳያ የተተነተኑ ናቸው። ከዚሁ አንጻር ይህ ቲዮሪ ለዚህ ጥናት በዋናነት የተሰበሰቡትን መረጃዎችም መተንተኛ ሆኖ አገልግሏል።

በጥናቱ ከክወና አዉዱ ላይ በአካል በመገኘት በተደረገ ምልከታና ዳሰሳ በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በድምጽና በማስታወሻ 350 ቃላዊ ግጥሞች ተሰብስበዉ ከነዚህም ዉስጥ 150 ያህሉን በሰባት ንዑሳን ክፍሎች በማዋገንና አዉዳዊ ትንተና በመከተል ተተንትነዋል፡፡ ትንተናዉ ቃል ግጥሞቹ በማህበረ ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ዉስጥ ያላቸዉን ፋይዳና አስተምህሮሯቸዉን ማመላካት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ምደባ፣ አደረጃጀት እና ትንተና

ይህን ጥናት ለማካሄድ በ2015 እና በ2016 ዓ.ም የጥምቀት በዓል አከባበር የክወና አዉድ ላይ በመገኘትና ምልከታ በማድረግ፣ የድምጽና የተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) ቀረጻ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በበዓሉ ላይ የሚታደሙ ቡድኖች፣ አቀንቃኝና አጃቢዎቹ ፈቃደኛ ባልሆኑባቸዉ አጋጣሚዎች ዘፈኖችን እያዳመጡ ማስታወሻ በመያዝ 350 ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ በዚህ መልክ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ዉስጥ 150 ያሉን ከተቀረጹት ቪዲዮዎች በጥንቃቄ በማዳመጥ፣ ማስታወሻዎችን በማንበብ፣ ልየታ በማድረግና በዘዉግ በማደራጀት ከተዜሙበት አዉድ፣ ይዘት እና ፋይዳ አንጻር ተተንትነዋል፡፡ ግጥሞቹን ለመተንተን ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ መተንተኛ ስልቶች የይዘት ትንተና እና አዉዳዊ ትንተና ናቸዉ፡፡

## 4.1. የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ምደባ እና አደረጃጀት

ምደባ ማለት የተሰበሰበን ሥነቃል ለአብነትም ቃላዊ ግጥምን ለመተንተን ስናስብ መረጃዎችን የምናደራጅበትና የምንከፋፍልበት ስልት መሆኑን ተከትሎ የዘርፉ ምሁራን ለአብነትም (Finnegan 1992: 143-145) and (Ben-Amos 1982: 38-46) ዘውጎችን በጭብጣቸው አጠቃሎና በተግበራቸው ከፋፍሎ መመደብ ይቻላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

የሥነቃል አመዳደብን በሚመለከት ሁለት ሞዴሎች አሉ። እነሱም ሥነቃል መከፈል ያለበት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጠው አገልግሎት (ማህበረሰቡ ሥነቃሉን ከተጠቀመበት ጉዳይ) እና ከሥነቃሉ ታሪካዊ አመጣጥ አኳያ መሆን እንዳለበት በመጥቀስ ይህም አካባቢያዊ ንድፈ ሃሳብን መሠረት ያደረገ መሆኑን (Ben Amos, 1975a: 168) ይገልጻሉ። ሌላው ሥነቃልን በአካባቢ ንድፈ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ መክፈል አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ ለአብነትም አንድ ግጥም ሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ የተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊገኝ እንደሚችል ይገልጻሉ። (Okepewho 1992፡ 27)

ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ ሁሉንም የሚያስማማ የምደባ ስልት የለም። ይህ ደግሞ ከፎክሎር ብያኔ ወጥ አለመሆን ጋር የታያያዘ ነው። ስለሆነም ምደባን ለማከናወን ስልታዊ ገጽታዎችን፣ ርዕሰ ጉዳይን፣ የመከሰቻ አጋጣሚን፣ ተግባርን፣

አውድን፣ እንዲሁም ሀገራዊ ስያሜዎችን የአከፋፈል መስፈርቶች መሠረት አድርጎ መውሰድ የተሻለ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያብራራሉ። (በጅጋ 2008፣ 175)

ስለሆነም በወቅቱ ያለዉን የማህበረሰቡን ስሜት፣ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ አስተያየትና ምክር የሚገልጹ፤ ከዚህም ከፍ ብሎ ቅሬታ፣ ተቃዉሞና ተግሳጹን የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ ለማደራጀት ይህንኑ የማህበረሰቡን ልማድና ሥነቃላዊ የምደባ ስልት መሰረት በማድረግ ለማደራጀት ተሞክሯል፡፡

በዚህ ጥናት ተሰብስበዉና ተደራጅተዉ ትንተና የተደረገባቸዉ ቃል ግጥሞች በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የጥምቀት በዓል ላይ በተለይም በየካ ክፍለ ከተማ በሦሥት የታቦታት ማደሪያ ስፍራዎች በታደሙ አስር ቡድኖች በአማርኛ ቋንቋ የተዜሙ ናቸዉ፡፡ የቃል ግጥሞቹ በሰባት አበይት ክፍሎችና እንደ አስፈላጊነቱም በሌሎች ንዑሳን ክፍሎች የተደራጁ ናቸዉ፡፡ አደረጃጀቱ ቃል ግጥሞቹ ያላቸዉን ይዘት፣ ፋይዳ እና የሚያስተላልፉትን መልዕክት መሰረት በማድረግ ተከናዉኗል፡፡

በዚህም መሰረት የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ምስጋናና ዉዳሴ፣ ምክርና ማስጠንቀቂያ፣ ቅስቀሳና ማነቃቂያ፣ ባህልና ማህበራዊ፣ ተቃዉሞና ቅሬታ፣ ዉግዘትና ነቀፌታ እንዲሁም ፍላጎትና ምኞት የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች በሚሉ ሰባት አበይት ክፍሎች ተደራጅተዉ በዚሁ መሰረት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

## 4.2. ተሰብስበዉ የተደራጁ ቃል ግጥሞች ትንተና

ትንተና ማለት በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለሌላው ግልጽ እንዲሆኑ ወይም በተራው ከሚታዩት በበለጠ ልዩ ልዩ ገጽታዎችን የምናሳይበትና የምናመለክትበት ስልት ነው። በትንተና ወቅት ሦስት ነገሮች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ይከናወናሉ። ይህም የተገኙትን መረጃዎች በማቅረብ መግለጽ፣ መተንተንና መተርጎምን ያካትታል። በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ ትንተና መረጃን ወደ ግኝት የምንቀይርበት መንገድ መሆኑን (Marshal & Rossman 2006:154) ይገልጻሉ። ትንተና ከገለጻ በላይ በመሆኑ የሁሉንም መረጃዎች ግንኙነት የሚመለከት ዘዴ ነው።

በመሆኑም አንድ አጥኚ መረጃ በሚተነትንበት ወቅት በዋናነት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የመረጃውን ሀሳብና ጭብጥ መጠቆም መሆኑን (Ben Amos, 1993) ይገልጻሉ። ስለዚህ ትክክለኛ ትንተና የሚባለው ዘውጉን በአውዱ ውስጥ የተነተነ

በመሆኑ አንድን የፎክሎር ዘውግ ለመተንተን የተሰበሰበውን የመረጃ ዓይነት (text)፣ የዓይነቱን ውስጣዊ ሁኔታ ወይም የቋንቋ ትርጉም (Texture) እና ሥነቃሉ የተነገረበት ሁኔታ ወይም የመረጃውን አውድ (Context) ትኩረት ተሰጥቷቸው በዝርዝር መታየት እንዳለባቸው (Dundes 1973: 26) (Ben Amos 1993: 210) ያብራራሉ።

የሀገራችን ተመራማሪዎች በበኩላቸዉ ትንተና ማለት በተሰበሰበው መረጃ ላይ በመነሳት ማብራሪያ የመስጠት፣ ፍች የመፈለግ፣ ትርጉም የመስጠት፣ ተግባር ነው:: ትርጎማም እንዲሁ መረጃው የቀረበበትን ቋንቋና ይዘት መሰረት አድርጎ፣ ከባህልና ከልምድ ጋር እያዛመዱ፣ በአንድምታ ጭምር፣ ማብራራት፣ ማፍታታት፣ ወዘተ ይሆናል:: ስለዚህ፣ ትንተናና ትርጎማ ተያያዥነት አላቸው ማለት ነው በማለት ያሥረዳሉ፡፡ (አማረ 2009፣ 92-93)

በ2015 እና 2016 ዓ.ም በጥምቀት በዓል የክወና አጋጣሚ ላይ በዘፈን፣ ሆታና ጭፈራ የተዜሙና የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች የሕብረተሰቡን ስሜት፣ ፍላጎት፣ ጥያቄ እና አመለካከት የሚያንጸባርቁ፣ የዘመኑን መንፈስ፣ የሕዝቡን ሥነልቡና፣ የሀገርና የሕዝቡን ወቅታዊ ገጽታ የሚያመላክቱና ሀገረሰባዊ እሴታችንን፣ ባህላችንንና ታሪካችንን እምርታ የሚያመላክቱ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ሕዝቡ የተሰማዉን ቅሬታና ተቃዉሞ የሚያንጸባርቁ ለልዩ ልዩ አካላት ያስተላለፉዉን ዉግዘት፣ ቅስቀሳ፣ ምክርና ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ቁመንልሃል ለሚላቸዉ አደረጃጀቶችና ግለሰቦች የቀረቡ ምስጋናና ዉዳሴዎችን የያዙ ናቸዉ፡፡

## 4.2.1. የማመስገንና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



*በ2016 ዓ.ም በጃንሜዳ ጥምቀተ ባሕር በራያ አለባበስ የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት*

የሙገሳና የውዳሴ ግጥሞች በተለይ በማህበረሰቡ ዘንድ፣ ማህበራዊ እውቅና ያላቸውና መልካም እና ደግ የሚባሉ እሴቶችን ለተላበሱ አባላት ማወደሻ እና ማሞገሻ ስለሆኑ የማህበረሰቡ አባላት እነዚህን ተግባራትና እሴቶች አውቀው እንደነሱ እንዲሆኑ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ እና እድል የሚፈጠርበት አጋጣሚም ይሆናል:: (Finnegan፣ 1970፡ 272-284)

በዚህ የመጀመሪያዉ አብይ ክፍል ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች በህወሓት እና በፌዴራሉ መንግስት መካከል በተካሄደዉ እና በአሁኑ ሰዓት በአማራ ክልል እየተደረገ ባለዉ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተሳትፎ ያደረጉና እያደረጉ ያሉ አካባቢዎች፣ አደረጃጀቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦችን ጀግንነት የሚያድወሱ ቃል ግጥሞች ናቸዉ፡፡ ጀግንነትን በሚመለከት ዶክተር አስቴር በጥናታቸዉ *"ጀግና ማለት ከሰዎች መካከል የተሻለ አቅም፣ ብርታትና ዕውቀት ያለው ግለሰብ በመሆኑ ማንኛውም ማኅበረሰብ በራሱ መስፈሪያ ሰፍሮ ጀግና ሲል የሚሾማቸው ግለሰቦች ሊሉት" እነዚህ ግለሰቦች የሚለኩበት መስፈሪያም ባህል እንደሚባል ያስረዳሉ፡፡*(አስቴር፡ 1991፡81) በዚህ ምድብ ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች ያላቸዉ ይዘት፣ ፋይዳ እና የሚያስተላልፉት መልዕክትም ለህዝብ ጥቅምና ክብር እየታገሉ ያሉ፣ ታግለዉ የወደቁና ጠላቴ የሚሉትን አካል ጥለዉ ለመዉደቅ ለተዘጋጁ ጀግኖች እዉቅናና ክብር

ለመስጠት እንዲሁም አርዓያነታቸዉ ለቀሪዉ ሕዝብና ትዉልድ እንዲተላለፍ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡

ሀ. የአማራን ሕዝብ እንደ ሕዝብ የማወደስ ፋይ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና

1. እየፎከረበት ያባቶቹን ገድል፣
   የዘመተ ለታ ይመለሳል በድል፡፡
2. አማራ አሳረኛዉ ግፍ የሚሰራበት፣
   ዋልታና ማገር ነዉ ለኢትዮጵያዊነት፡፡
3. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ፣
   ሞትን አይፈራዉም አማራዉ መብረቁ፡፡
4. ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣
   አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ፡፡
5. አሁን ያማራን ልጅ ማን ይለዋል ፈሪ፣
   ነፍጠኛ ነዉ እንጂ ሐገር አስከባሪ፡፡
6. እኔ ከአማራ ልጅ ፈሪ ቢገኝብኝ፣
   ሦሥት ዓመት እስራት ሞት ይፈረድብኝ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስድስት የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች በተራ ቁጥር ስድስት ከተጠቀሰዉ ዉጭ ሁሉም ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎችን መሰረት አድርገዉ እንደ አዲስ የተደረሱ ናቸዉ፡፡ ቃል ግጥሚቹ ጠቅለል አድርገዉ የአማራን ህዝብና የአያት የቅድመ አያቶቻቸዉን ጀግንነት የሚጠቁሙ እና ይህ ትዉልድም የአያት ቅድመ አያቶቹን ገድል እንዲደግም የሚያበረታቱ ናቸዉ፡፡ አማራ ጠላቴ የሚለዉ ሕዝብና አካባቢ እንደሌለና በተሳሳተ የጠላትነት ስሜት ተነስተዉ ሊያጠቁት የሚፈልጉትን አካላት ታግሶ ትዕግስቱን ሲጨርስ እየፎከረና እያቅራራ በጀግንነት ወኔ ድባቅ እንደሚመታ ይጠቁማሉ፡፡ ሕዝቡ ጀግኖችን እያወደሰ ፈሪዎችን የሚያወግዝበት በዘፈን በሆታና ጭፈራ የሚገለጽ ባህልና የትየለሌ ቃላዊ ግጥሞች አሉት፡፡ በተራ ቁጥር ስድስት ቀረበዉ ነጠላ ግጥም ከትዉልድ ወደትዉልድ እየተላለፈ የመጣ እና በዚህ የከወና አጋጣሚ አቀንቃኙ ***"እኔ ከአማራ ልጅ ፈሪ ቢገኝብኝ ሦሥት ዓመት እስራት ሞት ይፈረድብኝ"*** እያለ በማቀንቀን የአማራን ጀግንነት በኩራት የሚያወድሰዉም ለዚህ ነዉ፡፡ አቀንቃኙ በአማራ ሕዝብ ጀግንነት ስለሚታማመን

ሕይወቱን አስይዞ ለመወራረድ ያበቃዉ የአሸናፊነት መንፈስና መተማመን የመጣም ከዚሁ ከህዝቡ ማንነትና ታሪካዊ ዳራ የመነጨ ነዉ፡፡

ይህ ሕዝብ በዚህም ከአያት ከቅድመ አያት በወረሰዉ ጀግንነት፣ ቆራጥነት እና ሞት አይፈሬ ባህርይዉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የስልጣን መንበሩን የተቆጣጠሩ ብሄረሰብ ተኮር ፖለቲከኞች ነፍጠኛና ትምክህተኛ ነዉ በሚል ይፈሩታል፣ የሥልጣናቸዉ ተቀናቃኝ አድርገዉም ይጠረጥሩታል፡፡ ይህ ብቻም አይለም እነዚህ የሥርዓቱ መሪዎች ሁሉም ብሄረሰቦች ይህንን አስተሳሰባቸዉን እንዲቀበሏቸዉና የጥላቻ አስተሳሰባቸዉን እንዲጋሯቸዉ ስራዬ ብለዉ ይቀሰቅሱበታል፡፡

ይሁን እንጂ ሀገር ስትወረር፣ ድንበር ሲደፈር፣ ሌላዉ ቀርቶ የእርስ በርስ ግጭት ሲፈጠር እንኳን ቀድሞ በመዝመት የሀገርን አንድነት፣ ሉአላዊነትና ሰላም ለማስጠበቅ ራሱን መስዋዕት ለማድረግ ባለዉ ፍላጎት ከፊት ያሰልፉታል፡፡ አባቶቹ የፈጸሙትን ገድል እያሰበና እየፎከረበት ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር በመሰለፍ ድል አድርጎ ይመለሳል፡፡ ***"አሁን ያማራን ልጅ ማን ይለዋል ፈሪ ነፍጠኛ ነዉ እንጂ ሐገር አስከባሪ"*** የሚለዉ ቃል ግጥምም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡

ይህ ሕዝብ እርሱ አይወደኝ መከራዉ አይሰደኝ ሆኖበት እየተጠላም እየተጠረጠረም ለትግል ዘምቶ እየታገለ ለሀገሩ ዋልታና ማገር ሆኖ ኖሯል፡፡ ለዚህም አንድ አብነት ለመጥቀስ ያህል አርበኛ በላይ ዘለቀ ንጉሱ በሌሉበት ከወገኖቹ ጋር ሆኖ አምስት ዓመት ከወራሪዉ የጣሊያን ጦር ጋር ሲዋጋ ኖሮ እርሳቸዉ ወደሀገር ሲመለሱ በስቅላት እንዲሞት እንደፈረዱበት ይታወሳል፡፡ ***"ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣ አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ"*** የሚለዉ ቃል ግጥም አንድምታም ይህንኑ ለሀገሩ ያለዉን ቀናኢነት እና አመድ አፋሽ አድርጎ የሚያስቆጥዉን ጀግንነት እና መስዋዕነቱን የሚጠቁም ነዉ፡፡

ስለሆነም እነዚህ ቃል ግጥሞች Finnegan "ቃላዊ ግጥሞች በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት የሚታዩ በደሎችን፣ ጭቆናዎችን፣ ለማንፀባረቅ፣ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችና አስተዳዳሪዎች አስፈሪ በሚሆኑበት ጊዜ ስሜትን እና ፍላጎትን እንዲሁም ብሶትን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ:: በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሚፈጠሩ አሉታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን በአደባባይ አውጥቶ መናገር በማይቻልበት ሁኔታ ቃላዊ ግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ" (Finnegan፣ 1977፣ 223-227)

በማለት ያስቀመጡትን ብያኔና የቃል ግጥም ፋይዳ መሰረት አድረግን ስንመረምራቸዉ እዉነትም ቃል ግጥም የሕዝብ እስትንፋስ እና መደበቂያ ዋሻ መሆናቸዉን ያመለክቱናል፡፡

**ለ. የሸዋን ሕዝብ የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና**

1. አትንኩኝ ነዉ እንጂ ከልክ አትለፉ፣
   አሁን ሰሜን ሸዋን ማን ይለዋል ክፉ፣
2. አይንኩት እንጂ ከነካኩት፣
   የሸዋ ልጅ ነዉ ሰደድ እሳት፡፡
3. አይታሰስም ምጣድ ባሸዋ
   የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ሸዋ፡፡
4. ሸዋ ሞት አይፈራም ደንዳና ነዉ ቀልቡ
   መገዘዝ ተራራ እመጓ ነዉ ልቡ፡፡
5. መገን የሸዋ ልጅ አይጨበጥ እጁ፣
   ላገሩ የሚሞት አባትና ልጁ፡፡
6. ሸዋ ባላመጠ ይዉጣል ባመቱ ፣
   ጠላት አይፈታዉም ቅኔ ነዉ ብልሃቱ ፡፡

በዚህ ንዑስ ምድብ ስር ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስድስት የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በተራ ቁጥር አምስት ከተጠቀሰዉ ዉጭ ነባርና በትዉልድ ቅብብሎሽ በቃል እየተዜሙ የመጡና የሸዋን ሕዝብ ባህላዊና ማህበራዊ ማንነትና ጀግንነት ሚመሰክሩ፣ የሚያወድሱ፣ የሚያሞግሱና የሚያደንቁ ናቸዉ፡፡ በተራ ቁጥር አምስት የተጠቀሰዉ ግን የእሸቴ ሞገስ ከወራሪዉ የጁንታ ሰራዊት ጋር ሲታገል ከነልጁ በጀግንነት መሰዋቱን መሰረት በማድረግ በአዲስ መልክ የተፈጠረ ነዉ፡፡ በጠቅላላዉ ግን በቀረቡት ቃል ግጥሞች የሸዋ ሕዝብ እስካልነካኩት ድረስ በማንም ላይ የማይደርስ፣ ከነኩት ግን የማይመለስ፣ ለነገርም ሆነ ለጠብ የማይቸኩል፣ ቀድሞ እርምጃ ለመዉሰድ የማይነሳ፣ ከነካኩት ግን እንደ ሕዝብ መክሮና ዘክሮ ምስጢሩን በሆዱ ደብቆ ጠላቱን በአደባባይ ገጥሞ የሚያደባይ መሆኑን ለማሳየት የተደረሱና የተዜሙ ናቸዉ፡፡

እነዚህ የሸዋን ሕዝብ ጀግንነት ለማወደስ የቀረቡ ቃል ግጥሞች (መስፍን መሰለ፣ 2000፣) ላይ አንዳንዶች ቃል ግጥሞች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ እንደ ወቅቱና ሁኔታው የሚፈጥሩና ይዘታቸውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዬችን የሚዘረዝሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ቃል

ግጥሞች አንድን አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የጋራ እሴቶች ተደርገው ይቆጠራሉ። በማለት ከሰጡት ብያኔና ማብራሪያ ጋር የሚጣጣሙ ናቸዉ።

በተራ ቁጥር አምስት የተጠቀሰዉ ቃል ግጥም በዚህ የጀግንነት ታሪክ ዉስጥ ህወሓት የአማራ ክልልን በመዉረር ማዕከላዊ መንግስቱን ለመቆጣጠር ባደረገችዉ ጦርነት ብቻዉን በራካታ ጠላቶቹን ረፍርፎ የጀግንነት ክብሩን እንደጠበቀ ከልጁ ጋር የተሰዋዉ እሸቴ ሞገስ ለአብነት ተጠቅሶ ላበረከተዉ አስተዋፅኦ፣ ለከፈለዉ መስዋዕትነት ዉዳሴና ምስጋና በቃል ግጥሙ ሲበረከትለት እናያለን፡፡ አጼ ቴወድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ባደረጉት ጦርነት ከጠላት ጋር ተናንቀዉ የራሳቸዉን ሽጉጥ ጠጥተዉ እንደሞቱ ሁሉ እሸቴ ሞገስም "መገን የሸዋ ልጅ አይጨበጥ እጁ፣ ላገሩ የሚሞት አባትና ልጁ" በሚል በተገለጸዉ ቃል ግጥም የታጠቀዉን ጥይት እስኪጨርስ የቻለዉን ያህል ጠላት ገድሎ በአይበገሬነት እስከ ልጁ የተሰዋ ጀግና ስለመሆኑ ይነግረናል፡፡

**ሐ. የጎንደርን ሕዝብ የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና**

1. እኔስ ያኮራኛል ጎንደር መወለዴ፣
   ሴቲቱ ሁመራ ወልቃይት ጠገዴ፡፡
2. አይታሰስም ምጣድ በዘገር፣
   የጀግኖች ሀገር እንዴት ነዉ ጎንደር፡፡

3. አገራችን ጎንደር መልሶ አገራችን
   ጓያችን ይሰብራል እንኳን ጥይታችን፣
4. ሲሆን አንሸሽም ብንሸሽም ተጓደን
   ከጎበዞች አገር ጎንደር ላይ ተወልደን፡፡
5. ሰሜን አርማጭሆ ወልቃይት ጠገዴ፣
   ማረሻዉ ምንሽር መጎልጎያዉ ጓንዴ
6. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር፣
   በርስትና በእምነት የማንደራደር፡፡

በዚህ ንዑስ ክፍል ዉስጥ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አምስት የቀረቡት ቃል ግጥሞች ነባርና በቃል እየተነገሩ ለዚህ ትዉልድ የተላለፉ ሲሆኑ በተራ ቁጥር ስድስት የተገለጠዉ ግን ወቅቱን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ እንደ አዲስ የተገጠመ ነዉ፡፡ ሁሉም

ግን የጎንደርን እና የህዝቡን ጀግንነትና የሚያኮራ ባህልና ማህበራዊ ዉርስ ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ናቸዉ፡፡ ይህ ባህላዊና ማህበራዊ ዉርስ ግለሰቦችን ለጀግንነት የሚያነሳሳ፣ ፍርሃትን የሚያወግዝና ለተሰለፈበት ዓላማ በጽናት ቁሞ ለድል መብቃትን እንደ ኩራት የሚቆጥር ሥነልቦና ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ፡- ***"ሲሆን አንሸሽም ብንሸሽም ተጓደን ፣ ከጎበዞች ሀገር ጎንደር ላይ ተወልደን"*** የሚለዉ ቃል ግጥም ማህበረሰቡ ከቅድመ አያቶቹ በክብር ያወረሱትን ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴት የጀግንነቱ ምንጭና የድሉ መሰረት ስለመሆኑ ይጠቁማል፡፡ ***"ጓያችን ይብራል እንኳን ጥይታችን"*** እና ***"ማረሻዉ ምንሽር መጎልጎያዉ ጓንዴ"*** በሚል የተገለጹት ስንኞች ደግሞ የሀገርና የህዝቡን ጀግንነት እና ዝና የሚመሰክር ጎንደር እንኳን ሰዉ ሳር ቅጠሉ ሁሉ ለጠላት የማይተኛ፣ አራሽ፣ ተኳሽ፣ ቀዳሽ ሕዝብ በመሆኑ ለወደደዉ ማር ለጠላዉ ኮሶ መሆኑን የሚጠቁም ነዉ፡፡

አማረ "በእኛ ሐገር እያንዳንዱ አጋጣሚና ክስተት፣ የየራሱ ቃልግጥም ይገጠምለታል ወይም ይገጠምበታል:: በየዘመኑ የሚገኙት ገጣሚዎች አዉዳዊ ክስተቱን፣ በአጠቃላይ የዘመኑን መንፈስ፣ መነሻ አድርገው ቃል ግጥሞችን ይፈጥራሉ:: እንደነዚህ አይነት የዘመን አሻራ ያረፈባቸው ወይም የሚንፀባረቅባቸው ቃል ግጥሞች ለታሪክ ማጣቀሻነት ያገለግላሉ::" (አማረ፣2009፣46) በማለት እንደገለጹት ቃል ግጥሞቹ በብዛት የጎንደር እርስትና ጉልት የሆኑት ሰቲት ሁመራ፣ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ዳንሻና አርማጭሆ በብሔር ተኮር ፖለቲካ ሀገሪቱን ከፋፍሎ የአማራን መሬት ለፈለገዉ አካል ሲደለድል የራሴ ድርሻ በማለት ከትግራይ ክፍለ ሀገር ጋር ያጣመራቸዉ የጎንደር አጽመ እርስት የሆኑ አካባቢዎች መሆናቸዉን ይጠቁማሉ፡፡

ይህ ሕዝብ ለብርታትና ጀግንነት እንዲያበቃዉ በአባቶቹ ገድል እያሰበ እየፎከረና እየሸለለ ከጠላት ጋር ተናንቆ ይወድቃል ጠላቱን ይጥላል፡፡ ፎክሮ መሸሽ ግን ታሪክ ያበላሻልና እንኳን ሊያደርገዉ አያስበዉም፡፡ ለድል የሚያበቃዉም ይሄዉ አስተሳሰብ እና አቋሙ ነዉ፡፡ "ብንሸሽም ተጓደን" የሚለዉ ሀረግም የሚያመለክተዉ ነባራዊ ሁኔታዉ ለትግል የማይመችና ራስን ለጥቃት የሚያጋልጥ ሆኖ ካገኘዉ ስትራቴጂያዊ ማፈግፈግ በማድረግ የተሻለ ቦታና አጋጣሚ ይዞ እንደገና በመግጠም ማሸነፍ እንደሚችል ብቻ ሳይሆን የትግል ስትራቴጂ አዋቂ መሆኑንም ይጠቁማል፡፡

በአዲስ መልክ ቅታዊ ችግርና አጋጣሚዉን መሰረት አድርጎ የተደረሰዉ ***"ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር በርስትና በእምነት የማንደራደር"*** የሚለዉ አዲስ ቃል ግጥም

(አማረ፣2009፣46) ላይ እንደጠቆመዉ ታሪካዊ መሰረት ያለዉና ወልቃይት፣ ጸገዴ፣ ዳንሻ፣ ሁመራና ሰቲት ሁመራ አጽመ እርስቱ ሆናቸዉን እና ድንበሩም የተከዜ ወንዝ መሆኑን የሚጠቁም የታሪክ ምስክር ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል ነዉ፡፡

**መ. የወሎን ሕዝብ የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና**



*ወደ ጃንሜዳ ታቦት ማደሪያ በነበረ ጉዞ ላይ የነበረ የባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ክዋኔ*

1. የወሎ ልጆች ቀጫጭኖቹ፣
   ይናደፋሉ እንደንቦቹ፡፡
2. አይታሰስም ምጣድ ባለሎ፣
   የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ወሎ፡፡
3. የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ
   ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ፡፡
4. ራያና ቆቦ ዙሪያዉ በራበሩ
   እንኳን ሰዉ ቁሞበት ያሥፈራል ግራሩ፡፡
5. ከመቃብር በላይ ስም ይዉላል ብሎ፣
   ፍቅርና ጀግንነት ያዉቅበታል ወሎ፡፡
6. ሀገራችን ደሴ ስማችን ወሎዬ፣
   በነካኩንና ጉዳችን በለዬ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስድስት የቀረቡት ቃል ግጥሞች ነባር ቃል ግጦች ሲሆኑ እንደ ሸዋ እና ጎንደር ሁሉ የወሎ አካባቢና ሕዝብም የጀግንነት እሴት ባለቤት በመሆኑ ተመሳሳይ ስነልቦና እና ታሪካዊ ጀግንነት እንዳለዉ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡ በተራ ቁጥር አንድ የቀረበዉን ብንመለከት በተነጻጻሪ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት የቀረበ ነዉ፡፡ በመሆኑም ወሎየዎች አካላቸዉ ቀጫጭን ቢሆንም ጀግንነት አባት አደርና ማህበራዊ እሴታቸዉ በመሆኑ ልክ እንደ ንቦች ጠላትን እንደሚናደፉ ያሳያል፡፡ ግጥሙ ሌላም አብነት አለዉ፡፡ ንቦች ከነኳቸውና የኔ የሚሉትን ነገር ከወሰዱባቸዉ ራሳቸዉን ለመጠበቅ እና ለመከላከል በጋራ ቆመዉ ጠላታቸውን እንደሚናደፉና እንደሚያጠቁ ሁሉ ወሎም የፍቅርና የሰላም ባላቤት ብቻ ሳይሆን ለጋራ አላማና ግብ በጋራ ተሰልፎ የሚታገል ጀግና ሕዝብ መሆኑን ያመለክታል፡፡

***"የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ፣ ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ"*** የሚለዉ ስንኝ በበኩሉ በታሪክ እንደሚታወቀዉ እና አማረ 2009፡3 ላይ ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያ በሰራዉ ጥናት እንደጠቆመዉ ወሎ፣ ከመሀል አገር ወደ ሰሜን እና ከሰሜን ወደ መሀል ሀገር ለተደረጉ የእርስ በርስ እና ራስን የመከላከል ጦርነቶች ሁሉ የመሸጋገሪያና የጦርነት ቀጠና እየሆነ የኖረ አካባቢ ነው:: ስለሆነም ወልድያና ቆቦ አካባቢ የሰዉ ልጅ አስከሬን በየጊዜዉ ወድቆ የሚገኝበት አካባቢ እንደሆነና ህብረተሰቡም ወደቆላ ወርዶ ጠላቴ የሚለዉን አካል ታግሎ እየጣለ ለክብሩ የሚወድቅ መሆኑን የሚጠቁም ነዉ፡፡

ሰሜን ወሎ በተለይ የጢነኞች ምድር ራያና ቆቦ አንድም ከአፋር ጋር ተጎራባች በመሆኑ በየጊዜዉ በግጦሽ ሳር ምክንያት ወደግጭት ይገባል፡፡ በሌላም መልኩ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ለዘመናት የጦርነት መናኸሪያ አካባቢ ነዉ፡፡ እንደባህልም ጀግንነት የሚበረታታና ፍርሃት የሚወገዝበት አካባቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም እንኳን ሰዉ አካባቢና ዛፎችም የጀግና መጠለያና መሸፈቻ በመሆናቸዉ እንደሚፈሩና እንደሚከበሩ፤ ***"ራያና ቆቦ ዙሪያዉ በራበሩ እንኳን ሰዉ ቁሞበት ያሥፈራል ግራሩ"*** የሚለዉ ቃል ግጥም ይመሰክራል፡፡ በተራ ቁጥር ስድስት ***"ከመቃብር በላይ ስም ይዉላል ብሎ ፍቅርና ጀግንነት ያዉቅበታል ወሎ"*** የሚለዉ ቃል ግጥም ወሎ እንኳን ለክብሩ፣ ለርስትና ለጉልቱ ለስሙም የሚጨነቅ ገራገር፣ ጀግናና ቸር ሕዝብ መሆኑን ይተቁማል፡፡ በመሆኑም የፍቅርና የጀግንነትን ወኔ ተላብሶ ለሀገር፣ ለወገንና ለትዉልድ አርዓያነት ያዉ ስራ የሚሰራ ሰዉ በዘመኑ ክብርና ዝናን እንደሚጎናጸፍና ሲሞትም ስሙ ከመቃብር በላይ ሆኖ በስራዉ ሲጠራ እንደሚኖር የሚጠቁም ነዉ፡፡

በተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሰዉ ***"ሀገራችን ደሴ ስማችን ወሎዬ በነካኩንና ጉዳችን በለዬ"*** የሚለዉ ቃል ግጥም ስንመለከተዉ ወሎ በታሪክም በተግባርም እንደምናዉቀዉ ሰላም አብሮ መኖር፣ ፍቅርና መቻቻል የሚታይበት አካባቢ ቢሆንም ሀገርና ሕዝቡን ለማስተዳደር እድሉ የገጠማቸዉ ቡድንና ግለሰቦች አካባቢዉንና ሕዝቡን በፍቅር በማታለልና በአብሮነት ስም የጭና ቀንበራቸዉን ጭነዉበት በድህነት አረንቋ ዉስጥ ተዘፍቆ የኖረ ነዉ፡፡ በዚህም በዓጼዎቹ ጊዜ ስልጣኑን፣ በደርግ ጊዜ መብቱን በህወሓት ጊዜ እርስቱን በብልጽግና ጊዜ ማንነቱን የተዘረፈ ሕዝብ ነዉ፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ግን በፍቅር የቀረባቸዉ ፍቅር እንጂ ጀግንነት የማያቅ አድርገዉ የሚቆጥሩት ወዳጆቹ በገዛ እጃቸዉ ነካክተዉ፣ ነካክተዉ፣ አዉሬ አድርገዉታል፡፡ የነካኩት ሁሉም "ሳይደርሱባቸዉ እየደረሱ ይመለሳሉ እየቀመሱ" እንዲሉ አበዉ የክንዱን ብርታት እየቀመሱ ይገኛሉ፡፡

### ሠ. የጎጃምን ሕዝብ የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና

1. የዓባይ ውሃ ቀመስ አያዉቅም ሽሽት
   አስተምሮት በላይ ለእምነቱ መሞት፡፡
2. አይታሰስም ምጣድ በአጋም፣
   የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ጎጃም፡፡
3. ትጥቁ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ
   በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ፡፡
4. ደብረ ኤልያስን የነካት ሰዉ ማነዉ፣
   እንኳንስ ልጆቹ ምድሩም ተዋጊ ነዉ፡፡
5. ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሀገርህ፣
   አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ፡፡
6. አረንቋ ነዉ ጎጃም ዝናቡ እየናጠዉ፣
   እየዋጠዉ አስቀረዉ እየሰለቀጠዉ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስድስት ድረስ የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች በአመዛኙ ከሕዝቡ ታሪካዊ ዳራና ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ አዲስ የተገጠሙና የጎጃም ክፍለ ሀገርና የሕዝቡን ጀግንነት፣ ቆራጥነትና ልበሙሉነት የሚጠቁሙና የሚያሞግሱ ናቸዉ፡፡ አርበኛዉ በላይ ዘለቀ እና የዓባይ ወንዝና በረሃ ደግሞ የጎጃም የጀግንነትና የወንድነት ልክ፣ የድፍረትና የቆራጥነት ሥነልቦና መገለጫና ምንጮች ናቸዉ፡፡

ለዚህም ነዉ *“የዓባይ ዉሃ ቀመስ አያዉቅም ሸሸት አስተምሮት በላይ ለእምነቱ መሞት”* የሚለዉ ቃል ግጥም የጎጃም ሕዝብ የበላይን ዘመን ተሻጋሪ ዓርዓያነትና ጠላትን ታግሎ የጣለበትን የዓባይ በረሃን የጀግንነት ምንጭ አድርጎ ላመነበት ነገር ከመግደልና ከመሞት ወደኋላ እንደማይል አብነት ሆኖ የተጠቀሰዉ፡፡

አማረ፣ 2009፣ 46 ላይ በእኛ ሐገር እያንዳንዱ አጋጣሚና ክስተት፣ የየራሱ ቃል ግጥም ይገጠምለታል ወይም ይገጠምበታል፡፡ በየዘመኑ የሚገኙት ገጣሚዎች አዉዳዊ ክስተቱን፣ በአጠቃላይ የዘመኑን መንፈስ፣ መነሻ አድርገው ቃል ግጥሞችን ይፈጥራሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት የዘመን አሻራ ያረፈባቸው ወይም የሚንፀባረቅባቸው ቃል ግጥሞች ለታሪክ ማጣቀሻነት ያገለግላሉ:: በማለት ያብራሩትም ይህንን ሀቅ የሚያሥረዳ ነዉ፡፡

ከታሪካዊ ዳራዉ እንደምንረዳዉ በላይ ጠላትን አርበድብዶ ተፈርቶና ተከብሮ ከኖረ በኋላ በንጉሱ በፍርሃትና በጥርጣሬ አይን ስለታዬ በገመድ ታንቆ እንዲገደል ተደርጓል፡፡ ለዚህም ይመስላል ጎጃም ወቅታዊዉን ትጥቅ የማስፈታት ዘመቻ ተከትሎ የታጠቅኩትን ከምፈታ እንደበላይ ታንቄ ብሞት ይሻለኛል በማለት አይበገሬነትና ኩራቱን የገለጸዉ፡፡ *“አረንዛ[1] ነዉ ጎጃም ዝናቡ እየናጠዉ እየዋጠዉ ቀረ እየሰለቀጠዉ”* የሚለዉ ቃል ግጥም በበኩሉ የሚያመለክተዉ አሁን ባለንበት የታሪክ አጋጣሚ በአማራ ክልል መንግስት ሕን ለማስከበር በሚል በከፈተዉ ጦርነት ከላይ በድሮንና በአዉሮፕላን ከታች በከባድ መሳሪያና በእግረኛ ጦር የሚወርድበትን የጥይት ዶፍ ተቋቁሞ እንደ ረግረግ መሬት እየዋጠ በማስቀረት ጠላቴ ብሎ በሚጠራዉ አካል ላይ ያደረሰዉን ዉድመት የሚያመለክት ነዉ፡፡ አንድም ደግሞ የጎጃምን ፋኖ አደራጅቶና አሰልጥኖ ወደትግል ጎራ ያስገባዉ ሻለቃ ዝናቡ ልንገርህን ጀግንነት በገደምዳሜ የሚነግር ነዉ፡፡

*“ትጥቄ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ”* እና *“ደብረ ኤልያስን የነካት ሰዉ ማነዉ እንኳንስ ልጆቹ ምድሩም ተዋጊ ነዉ”* የሚሉት ኹለት መንቶ ቃል ግጥሞች ወቅታዊዉን የጎጃም ችግርና ተጋድሎ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ ጎጃም የወቅቱ የትጥቅ ትግል በስፋት የተቀጣጠለበትና መንግስት

---

[1] አረንዛ የሚለዉ ቃል ትርጉም ረዘረዝ ውስጣውስጡ ረግረግነት የሚሰማው ውኅማ መሬት ማለት ነዉ። በግጥ ዉስጥ ካለዉ አዉዳዊ ትርጉም አንጻር ጀግና፣ ኃይለኛና ጎበዝ የሚለዉን ያመለክታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ እስክንድር ነጋን እይዛለሁ በሚል ደብረኤሊያስ ላይ በገዳማትና በመነኮሳት ላይ ታሪካዊ ጥፋት ያጠፋበትና ሕዝቡ በቁጣ የተቀሰቀሰበት አካባቢ ነዉ፡፡ ይንንም ተከትሎ መንግስት ፋኖና ልዩ ሃይል ትጥቅ ይፍታ ማለቱን ለመቃወምና በዚሁ አካባቢ ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር በተደረገ ተጋድሎ የተገኘዉን አኩሪ ድል እንድሁም የሕዝቡን አቋም ለመጠቆም የተገጠሙና በሀገሪቱ መዲና እንደማስጠንቀቂያ ለስርዓ የተነገሩ ናቸዉ፡፡ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ ተከትሎ ነዉ ***"ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሀገርህ አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ"*** በሚል ሕዝቡ የተቃጣበትን ጥፋት በክንዱ እንዲመክትና ለትግል እንዲሰለፍ በሕዝባዊ ግጥሙ ሕዝባዊ ጥሪ የተላለፈለትና አሁን ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ የምንመለከተዉ፡፡

ረ. ማህበራዊ ቡድኖችን የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና

1. ምንጨነቀኝ ብዬ ይሳሳል ገላዬ፣
   ያሳምነዉ ሚዜ ካለ ከኋላዬ፡፡
2. የሐገር አርበኛ የድል ችቦ ለኳሽ፤
   አመጸኛዉ ፋኖ አራሽ ቀዳሽ ተኳሽ፡፡
3. አሳምነዉ ጽጌ ደረሰ አዝመራህ፣
   አጨደዉ ከመረዉ ያዉ ፋኖ ልጅህ፡፡
4. ዛሬ እሞት ነገ እሞት እያልኩኝ ስከሳ
   ያማራዉ ልጅ ፋኖ ደረሰልኝሳ፡፡
5. ይዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
   ፋኖ ቁሞ አያይም ስትፈርስ ሀገሩ፡፡
6. ተወረረ ሲባል ሐገር ተደፈረ፣
   አመለኛዉ ፋኖ ወጣ እየፎከረ፣

ፖለቲካዊ ይዘት እና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች በአንድ ቡድን አባላት መካከል በሚከወኑበት ጊዜ የቡድኑን የጋራ ስሜትና አንድነት ከማጠናከር አልፎ ተቀናቃኞችን ለመቃወም ይረዳሉ፡፡ ቡድናዊ ስሜትን እና አንድነት በማጠናከር ቡድናዊ ወገናዊነትን ለማንፀባረቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ (Finnegan፣ 1977፣ 217-221)

ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስድስት የቀረቡት ቃል ግጥሞች በሙሉ ከላይ ከቀረበዉ ብያኔና የቃል ግጥም ፋይዳ ጋር የሚጣጣሙና ከወቅታዊ ችግርና ማህበራዊ ቡድኖች ማሕበራዊ ድርሻ ጋር ተያይዘዉ አዳዲስ የተገጠሙ ለሀገር እና ለማኅበረሰቡ

*ሰላምና ደህንነት በሚደረገዉ ተጋድሎ ዉስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸዉን ቡድኖች ለማመስገንና እና ለማወደስ የቀረቡ ናቸዉ፡፡ በኢትዮጵያ እና በአማራ ህዝብ የተጋድሎ ታሪክ ዉስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ ካላቸዉ ህብረተሰባዊ አደረጃጀቶች ዉስጥ አርበኞች፣ ፋኖዎች፣ ልዩ ሃይል እና ሚሊሻዎች በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ፡፡ አሁን በአማራ ክልል ያለዉን የእርስ በርስ ግጭትና ደም አፋሳሽ ጦርነት ተከትሎ ከነዚህ በቡድኖች መካከል ጎልቶ የወጣዉ የፋኖ አደረረጃጀት ነዉ፡፡ የዚህ ምክንያት ደግሞ የአማራ ልዩ ሀይል በመንግስት እና በክልሉ መንግስት ዉሳኔ እንዲፈርስ[2] በመደረጉና ትጥቅ ለማስፈታት በተወሰደዉ እርምጃ የሕዝቡን ተጋርጦብኛል ከሚለዉ የህልዉና አደጋ ለመታደግ በፋኖ ስም ስለተደራጀ ምስጋናና ዉዳሴዉም እርሱን የሚመለከት ነዉ፡፡*

*ፋኖ አንድ ማህበራዊ ማንነት እና መታወቂያ ያለዉ የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተዉጣጣ በመሆኑ* ***"የሀገር አርበኛ የድል ችቦ ለኳሽ፣ አመጸኛዉ ፋኖ አራሽ፣ ቀዳሽ፣ ተኳሽ"*** *እየተባለ ይዘፈንለታል፡፡ በዚህ ነጠላ ግጥም ኹለተኛ ስንኝ ዉስጥ የቀረቡት ሀረጋት ሆነኝ ብለዉ የተደረሱ፣ በቅደም ተከተል የተቀመጡና የፋኖን ማንነት አሳምረዉ የሚገልጹ ናቸዉ፡፡ ፋኖ በሰላሙ ቀን እንደሚያርስና እንደሚነግድ፣ በሰንበት ቀን ቄስ ሆኖ እንደሚቀድስና ችግር ሲያጋጥም ደግሞ ለሀገር፣ ለሕዝባና ለሰለማሙ ዘብ ቆሞ እንደሚታገል የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡* ***"የድል ችቦ ለኳሽ"*** *የሚለዉም በተለይ ወቅታዊ ከአማራ ክልል የርስ በርስ ጦርነት ጋር ተያይዞ ህዝቤ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ ብሎ ቀደም ሲል ከህወሓት ጋር አሁን ከሀገር ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ያደረገና እያደረገ ያለዉን ተጋድሎና የስመዘገበዉን ድል ለማሳየት የቀረበ ነዉ፡፡*

*ህብረተሰቡም የታጠቀና ያልታጠቀዉን የህብረተሰብ ክፍል ሳይለይ በጅምላ በመጨፍጨፍ የሚደርስበትን ጥቃትና ሞት ፈርቶ ሲሸማቀቅ አለኝታና መከታየ የሚለዉ ፋኖ እንደደረሰለት ይገልጻል፡፡ ይህንንም ለመረዳት ከላይ በተራ ቁጥር አንድ እና አራት የቀረቡትን* ***"ምንጨነቀኝ ብዬ ይሳሳል ገላዬ ያሳምነዉ ሚዜ ካለ ከጓላዬ"*** *እና*

[2] ኢሰመኮ ዓመታዊ ሪፖርት በአማራ ክልል በተለይም ከየካቲት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ የክልሎችን ልዩ ኃይሎች መልሶ ለማደራጀት በመንግሥት እርምጃዎች መወሰድ ከጀመረ በኋላ በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋል የጸጥታ ችግር አሳሳቢ ነው። ለምሳሌ ግንቦት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ዞን በሀገር መከላከያ ሠራዊት በተወሰደ የኃይል እርምጃ ምክንያት በሸዋሮቢት አካባቢ ቢያንስ 5 ሲቪል ሰዎች፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ልዩ ቦታው ራሳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መሣሪያ ማስፈታት በሚል በወሰደው እርምጃ አንድ ቄስን ጨምሮ 7 ነዋሪዎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል።

*"ዛሬ እሞት ነገ እሞት እያልኩኝ ስከሳ፣ ያማራዉ ልጅ ፋኖ ደረሰልኝ እሳ"* የሚሉትን ቃል ግጥሞች ማየት ብቻ በቂ ነዉ፡፡ ከቃል ግጥሞቹ አጠቃላይ ይዘት የምንረዳዉ ሕዝቡ ሀገርና ሕዝብ ያስተዳድራል ብሎ የመረጠዉ ወይም ሕዝቡ መርጦኛል የሚለዉ መንግስት የሕዝቡን ሰላምና ፍትህ ማረጋገጥ ባለመቻሉና ከህልዉና ስጋቱ ሊታደገዉ ባለመቻሉ ፋኖን ብቸኛ አዳኝና አማራጭ አድርጎ መያዙንና በመንግስት ላይ እምነት ማጣቱን ነዉ፡፡

በተራ ቁጥር ሦሥት፣ አምስትና ስድስት የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች በበኩላቸዉ ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነዉ ጽጌ የአማራ ሕዝብ የህልዉና አደጋ እንዳለበት ጠቅሶ መደራጀትና መታገል እንዳለበት በጠቆመዉ መሰረት የርሱን ፍለግ ተከትሎ የተቋቋመዉ ፋኖ የሕልዉናዉ ስጋት የሆነዉን አካል ባልቤን በመዉዜሩ አጭዶ እየከመረዉ እንደሆነና ሀገሩ ስትፈርስ ቁሞ እንደማያይና ተደፈረችና ተወረረች ሲባል አመለኛዉ ፋኖ ቆሞ ማየት ስለማያስችለዉ እየፎከረ እንደወጣ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡

## ሰ. ታዋቂ ግለሰቦችን የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና

1. አሳምነዉ ፅጌ ሞተ ያለዉ ማነዉ?
   ሰፍቷል እንደ ዋርካ ቀንዘሉ[3] ብዙ ነዉ፡፡

ስም ከመቃብር በላይ ይዉላል የሚል በጎ አድራጎትን የሚያበረታታ ዘመን ተሻጋሪ አስተሳሰብ እና ይህንን አስተሳሰብ የሚያጎላ የአማርኛ ብሂል አለ፡፡ ይህ ቃል ግጥምም የአማራ ክልል ሰላም እና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ የነበረሩት ብርጋደር ጄኔራል አሳምነዉ ፅጌን ስም ከመቃብር በላይ የሚያዉል እና በያዙት አቋም፣ በሰጡት አመራርና በወጣቱ በነበራቸዉ ተቀባይነት ብዙ ተከታይና ደጋፊዎችን ማፍራታቸዉን የሚዘክር[4] ነዉ፡፡ የጄነራሉ አሟሟት በኹለት ተጻራሪ ሐይሎች እይታ የተለያየ አንድምታ ያለዉ ሆኖ እደጠላትና እንደ ወዳጅ የሚያሥቆጥራቸዉ ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ እይታ መንግስት እና የመንግስት ሚዲያዎች ክልሉን በማተራመስ ስራ ላይ ተሰልፈዉና የአማራን ክልል

---

[3] **ቀንዘል**፡- የሚለዉ ቃል የዛፍ ቅርንጫንፍ የሚያመለክት ሲሆን በግጥሙ ዉስጥ ባለዉ አንድምታ ደጋፊ፣ ተከታይ፣ አድናቂ የሚለዉን ትርጉም ይይዛል። አንዱ ዛፍ ብዙ ቅርንጫፍ ማዉጣቱንና ጥላዉ ለህዝቡ እንደሚጠቅም ሁሉ ጄነራል አሳምነዉ ፅጌም ለህዝቡ ጥላ ከለላ የሚሆን ተከታይ ማፍራታቸዉን የሚጠቁም ነዉ።

[4] **ዘከረ** አሰበ፣ አስታወሰ ማለት ሲሆን ብ/ጄነራል አሳምነዉ ፅጌ ለአማራ ሕዝብ በዋሉት ዉለታና በከፈሉት መስዋዕነት ሲታወሱ ሲመሰገኑ እና ሲከበሩ እንደሚኖሩ የሚጠቁም ነዉ ።

አመራሮችን ገድለዉ በጸጥታ ሃይሉ የተገደሉ ናቸዉ የሚል ነዉ፡፡ ኹለተኛዉ እይታ ደግሞ ከራሳቸዉ ክብርና ጥቅም ይልቅ ለሀገርና ለሕዝብ ክብርና ጥቅም የሰሩና በፌዴራሉ መንግስት መሪዎች የተቀናጀ የሴራ ገመድ ተጠልፈዉ ከወደቁ በኋላ ሽህ ተከታይና ወዳጆችን ለማፍራት የበቁ የዘመናችን ጀግና መሆናቸዉን የሚጠቁምና ግብራቸዉን የሚያወድስ ነዉ፡፡

በኹለተኛዉ ብያኔ መሰረት በ2015 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ላይ የተዜመዉ ቃል ግጥም ጄኔራሉ በአመራር ብቃት እና በመስዋዕትነታቸዉ በአምሳላቸዉ በቀረጿቸዉና ባፈሯቸዉ የተግባር ልጆቻቸዉ ስማቸዉ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተላለፈ ሲጠራ እንደሚኖር የሚያመላክት ነዉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ሕዝቡን ለማንቃት፣ ለማደራጀት እና ለማስታጠቅ ያደረጉት ጥረት መክኖ አለመቅረቱንና የሞቱለት ዓላማ በሽዎች ልቦና ዉስጥ የሰረጸና ዛሬ ለሚደረገዉ ህዝባዊ ተጋድሎ መሰረት ስለመሆኑ የሚጠቁም ነዉ፡፡

በአማራ ሕዝብ እይታ አሳምነዉ ጽጌ የሞት መድሃኒቱ መዉለድ ነዉ እንዲሉ ፋኖን በአምሳላዉ ቀርጸዉ የወለዱ በመሆናቸዉ ሞቱ ሳይሆን ረቡ ተራቡ የሚል እይታ እንዳለዉና ከሰዉ መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት እንዲሉ እርሳቸዉን በታላቁ የአድባር፣ የአዛዉንትና የንጉስ ተምሳሌት በሆነዉ በዋርካ መስሎ ሰፊ ቅርንጫፍና ቀንዘል እንዳለቸዉ ሕያዉ ተምሳሌት አድርጎ ያምናል፡፡ ይህም ዋርካ ከዛፎች ሁሉ ረጅም ዘመን እንደሚኖር የርሳቸዉ ስምና ስራም ከትዉልዱ ጋር አብሮ እንደሚኖር ያሳያል፡፡

2. ማን ሊኖርበት ይሰራል ጎጆ፣
   በለስ ካልቀናዉ[5] ምሬ ወዳጆ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በካራ አርሴማ ታቦት ማደሪያ ህዝቡ ጀግና ነዉ ብሎ የሚያስበዉን ግለሰብ ለማወደስ በቃል ተደርሶ የተዜመ አዲስ ቃል ግጥም ነዉ፡፡ የራያ አካባቢ በታሪክ ለዘመናት በሰሜን በኩል ለተፈጠሩ ጦርነቶች መቆራቆሻ ከመሆኑም ባሻገር ሕዝቡ በጅምላ እየተፈናቀለና እየተሳደደ ወደሌሎች አካባቢዎች ሲጎርፍ የኖረ ነዉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በህወሓት የዘዉግ (የጎሳ) ተኮር የሴራ ፖለቲካ ርስቱን

---

[5] **በለስ ቀናዉ፡-** አገኜ፣ ተሳካለት፣ ሆነለት፣ ጥሩ እድል አጋጠመዉ; ግዳይ ጣለ ማለት ነዉ። ስለሆነም ህብረተሰቡ ምሬ ወዳጆ የሚፈልገዉን እንዲያኝ፣ የሚያስበዉ እንዲሳካለትና ጥሩ እድል እንዲገጥመዉ በዚህም ሰላሙ እንዲረጋገጥ ስለመመኘቱ ይነግረናል።

ተነጥቄ በቀየዬ ላይ ተረጋግቼ እንዳልኖር ተደርጌ ነበር አሁን ላይ በግፍ የተነጠቅኩትን ርስቴን በልጆቼ አስመልሼ ነጻነቴንም አዉጃለሁ ሲል ይሰማል፡፡ በግጥሙ ዉስጥ በለስ ቀናዉ የሚለዉ ቃል ፍቺ አገኘ፣ ተሳካለት፣ ሆነለት፣ ጥሩ እድል አጋጠመዉ; ግዳይ ጣለ ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ ምሬ ወዳጆ የሚፈልገዉን እንዲያኝ፣ የሚያስበዉ እንዲሳካለትና ጥሩ እድል እንዲገጥመዉ በዚህም ሰላሙ እንዲረጋገጥ ስለመመኘቱ ይነግረናል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ሃሳቡ እና ፍላጎቱ በመንግስት አካላትና በህወሃት አመራሮች ተቀባይነት ስላላገኘ የቀደመ ታሪክና እጣ ፋንታዉ ተጠናክሮ በመቀጠሉ ህብረተሰቡ ቅሬታዉን ሲገልጽ ይሰማል፡፡ በመሆኑም ሕዝቡ በህወሓት ከሚደርስበት ጥቃት መንግስት ሊታደገዉ ስላልቻለ ተስፋ ቆርጦ ታጥቀዉ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖችን ተስፋ ማድረግ እንደጀመረ ይገልጻል፡፡ ከነዚህ ታጣቂ ኃይሎች መካከል አንዱ በምህረት ወዳጆ የሚመራዉ የምስራቅ አማራ ፋኖ አደረጃጀት አንዱ ነዉ፡፡

ሥለሆነም ቃል ግጥሙ እንደሚነግረን ሕዝቡ ምህረት ወዳጆ እና እርሱ የሚመራቸዉ ታጣቂ ሃይሎች ከጸጥታ ኃይሉ ጋር በሚደረገዉ የእርስ በርስ ጦርነት የማሸነፍ እድል እንዲቀናቸዉ ለማሰብ፣ ለመመኘትና ለመጸለይ መገደዱንም ያመላክታል፡፡ ካልሆነ ግን የሰራዉ ጎጆና የሚኖረዉ ኑሮ ሁሉ በህወሓት አገዛዝ ስር ወድቆ መና ሆኖ እንደሚቀርና ሕዝቡም መልሶ ለስደት፣ መፈናቀልና ለስቃይ እንደሚዳረግም ይጠቁማል፡፡

3. የለበሰዉ ልሚል የታጠቀዉ ልሚል፣
   የምሬ ወዳጆ የፋኖዉ ባለሚል፡፡

የራያ ህዝብ በኢሕአዴግ የስልጣንና የአመራር ዘመን ራያ አላማጣ፣ ኮረም፣ ኦፍላ ዛታና ባላ አካባቢዎች ከወሎ ተወስደዉ በትግራይ ክልል እንዲካለሉ ተደርጎብኛል በሚል በሰላማዊ እና በትጥቅ ትግል ጥያቄዉን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ኢህአዴግ በሕዝባዊ ትግል ተሸንፎ ስልጣኑን ለለዉጡ መንግስት እንዲያሥረክብም የራሱን ድርሻ አበርክቷል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ህወሓት በፌደራሉ መንግስት ላይ ክህደት በመፈጸም እና የስልጣን ኮርቻዉን ዳግም ለመቆናጠጥ ያረገዉን በጦር ሃይል የታገዘ ሙከራ ለማክሸፍም የራሱን ድርሻ እንዳበርከተ የጸጥታ ኃይሉ አመራሮች ጭምር ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ጋር ሆኖ ከህወሃት መንጋጋ

በትግል የተረከበዉን ርስቱን ዳግም ለህወሃት ለማስረከብ እቅድ በመኖሩ ህብረተሰቡ ቅሬታ እንዳለዉ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ስለሆነም ርስቱን ለመጠበቅ፣ ወራሪዎችን ለመከላከል እና መንግስት የሚያሳድርበትን ጫና በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ለመመከት የምስራቅ አማራ ፋኖን በማደራጀት እና በትጥቅና በስንቅ በማጠናከር የሕዝቡን እንባ እንዲያብስ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ከነዚህ ልጆቹ ዉስጥ ምሬ ወዳጆ አንዱና ትግሉን እየመራ ያለ የህዝብ ባለዉለታ ወጣት እንደሆነም ይነገራል፡፡ ለዚህ ነዉ ‹‹የታጠቀዉ ልሟል የለበሰዉ ልሟል›› በሚል በትግሉ ዉስጥ ያለዉን ሚና፣ የደረሰበትን ልፋትና መንገላታት ለመዘከር፣ እዉቅና ለመስጠትና ለማመስገን በጥምቀት በዓል ላይ በዘፈንና በጭፈራ በአደባባይ የተዜመለት፡፡

4. አሳምነዉ ጽጌ ሙቶ አይቀርምና፣
   ሐገሩ ሲደፈር ሆዱ አይችልምና፣
   አፈር አታብዙበት ይበቃል ሦስት ቁና፡፡
5. ስጋዉን ላይበሉት ደሙን ላይጠጡት
   አሳምነዉ ጽጌን ለምን ገደሉት
6. ብረቱ መዉዜር ነዉ ጥይቱ ዘጠና፣
   ደስ ሲለዉ ቆቦ ሲከፋዉ ጎሊና፣
   ምሬ አባ ድፈቅ የትግሉ ፋና ፡፡
7. የወሎዉ ጀግና ምሬ ወዳጄ፣
   የቁርጥ ቀን ልጅ አለ ቀኝ እጄ፡፡
8. ፍርድ ቤት ፍለጋ ለምን እለፋለሁ፣
   ለምሬ ወዳጆ እነግርብሃለሁ፡፡
9. በአምስት አቦ ናቸዉ በሰባት ሥላሴ፣
   የአሳምነዉ ምትክ ልጅ ዘመነ ካሴ፡፡
10. ነፍሱን የሰጠዉ ከልጁ ጋራ፣
    እሸቴ ሞገስ ሸዋ ላይ በራ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አራት እስከ አስር የተዘረዘሩት ቃል ግጥሞች ከትግራይና ከአማራ ክልል የእርስ በርስ ጦርነቶች ጋር በተያያዘ ግለሰቦች በጦነቱ ላይ ባላቸዉ አስተዋጽዖ እና በአማራ ሕዝብ ዘንድ እዉቅና፣ ክብርና ዝና የተሰጣቸዉን ግለሰቦች ለማመስገንና

ለማወደስ በአዲስ መልክ ተደርሰዉ የቀረቡ ቃል ግጥሞች ናቸዉ፡፡ በቃል ግጥሞቹ ምስጋናና ዉዳሴ ከተቸራቸዉ ግለሰቦች መካከል ብ/ጄኔራል ሳምነዉ ጽጌ፣ ምህረት ወዳጆ፣ ዘመነ ካሴ እና እሸቴ ሞገስ ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ግለሰቦች እዉቅና፣ ዝናና ክብር የተቀዳጁት ከመንግስት ጎን በመሰለፍ የህወሓት ወያኔን ወረራ ለመመከት ባደረጉት ሀገር ዓቀፍ ተጋድሎ ነዉ፡፡ አሁን ላይ ግን የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር አቋም በመያዛቸዉ የለዉጡ መንግስት በጥርጣሬ ተመልክቶና በጽንፈኛ ኃይልነት ፈርጆ ስላሳደዳቸዉ ዱር ቤቴ ብለዉ ቀደም ሲል በወያኔ ሲመታ አለንልህ ካሉት ከሀገር መከላከያ ሰራዊቱ ጋር በትጥቅ ትግል ጦርነት የገጠሙ ጀግንነታቸዉን በአደባባይ ያመሰከሩ ግለሰቦች ናቸዉ፡፡

በተለይ አሳምነዉ ጽጌ ከአማራ ክልል አመራሮች ግድያ ጋር ተያይዞ የተራገበዉ አሉቧልታ እንዳለ ሆኖ በርሱ አስተሳሰብ የአማራ ሕዝብ እየደረሰበት ያለዉን የህልዉና አደጋ ቀድሞ በመረዳት እንዲደራጅና በጋራ እንዲቆም በመቀስቀስ ቀዳሚዉን ቦታ የሚወስድ ነዉ፡፡ ለዚህም ይመስላል "***ስጋዉን ላይበሉት ደሙን ላይጠጡት አሳምነዉ ጽጌን ለምን ገደሉት***" በማለት በዜማና በግጥም የተቀኙለትና ሕዝባዊ ወገንተኝነትና ባለዉለታነቱን በአደባባይ የመሰከሩለት፡፡ ይህንንም ተከትሎ በምትኩ ዘመነ ካሴን ለማፍራት መቻሉን ጭምር ቃላዊ ግጥሞቹ ያስረዳሉ፡፡

***"አሳምነዉ ጽጌ ሙቶ አይቀርምና አፈር አታብዙበት ይበቃል ሶስት ቁና"*** የሚለዉ ቃል ግጥም አሳምነዉ ጽጌ ለአማራ ሕዝብ በዋለዉ ዉለታና በከፈለዉ መስዋዕትነት ምድራዊ ትንሳዔዉን እስከመመኘት ያደረሰ ፍቅርና አክብሮት በህዝቡ ዉስጥ እንደዘራና እንዳበቀለ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ሕዝቡ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አፈሩን አራግፎ፣ ሙስና መቃብርን ድል ነስቶ እነሆ ተነስቷል የሚል የምስራች እንደሚጠብቅና አፈር ሳይጫነዉ መቀበር እንደነበረበት በቃል ግጥሙ የተቀነቀነዉ ሕሕባዊ ስሜት ያመላክታል፡፡

በቃል ግጥሞቹ ሌላዉ ሰፊ ምስጋናና ዉዳሴ የተቸረዉ ምሕረት ወዳጆ ነዉ፡፡ በቅጽል ስሙ ምሬ በራያና በአካባቢዉ የሚንቀሳቀሰዉን የምስራቅ አማራ ፋኖ የሚመራ ጀግና ወጣት ነዉ፡፡ ምሬ ሀብትና ንብረቱን ጥሎ፣ ጥሩ ኑሮዉን በቃኝ ብሎ ለራያ ህዝብ ሰላም እና ነጻነት ራሱን መስዋዕት በማድረግ የደረሰበትን መንገላታት ለመግለጽ ***"የለበሰዉ ልሟል የታጠቀዉ ልሟል፣ የምሬ ወዳጆ የፋኖዉ ባለሟል"*** ተብሎ ተገጥሞለታል፡፡

ምህረት ህወሓትን ለመጣልና የራያን ህዝብ ፍትህ ለማረጋገጥ ከሌሎች አጋሮቹ ጋር ቀደም ብሎ ትግል የጀመረ ፋኖ ነዉ፡፡ ቡድኑ በኋላ የአማራ ክልልን በመዉረር ለፌዴራሉ መንግሰት ስጋት መሆን ሲጀምር ከጓደኞቹ ጋር በአደረገዉ ተጋድሎ ወያኔን ረፍት የነሳ ጀግና ነዉ፡፡ ዛሬም የምስራቅ አማራ ፋኖን እየመራ ተበድሏል ለሚለዉ ሕዝብና አካባቢ ዱር ቤቴ ብሎ በትጥቅ ትግል መስዋዕነት እየከፈለ በመሆኑ ሕዝቡ ***"ፍርድቤት ፍለጋ ለምን እለፋለሁ፣ ለምሬ ወዳጆ እነግርብሃለሁ"*** በማለት የራያ ሕዝብ የሰላምና የፍትህ አለኝታና መከታነቱን መስክሮለታል፡፡ ቃል ግጥሙ ግን ከምስጋናም ያለፈ ፋይ አለዉ፡፡ ምክንያቱም መንግስት እና የአካባቢዉ አመራር አካላት የሕዝቡን ሰላም፣ የአካባቢዉን መረጋጋትና ፍትህና መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ ባለመቻላቸዉ ሕዝቡ ከመንግስት ተስፋ እየቆረጠ በአካባቢዉ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚታገሉ ቡድንና ግለሰቦችን አሌኝታነት ወዶና ፈቅዶ መቀበሉንም ያመላክታልና ነዉ፡፡

ሸዋ ላይ ለሐገርና ለህዝቡ ሰላምና መረጋጋት ከህወሓት ጋር ታግሎ ከልጁ ጋር በክብር የወደቀዉ እሸቴ ሞገስም ***"መገን የሸዋ ሰዉ አይጨበጥ እጁ፣ ለሀገሩ የሚሞት አባትና ልጁ"*** ተብሎ የተገጠመለት የዘመናችን ስመጥር ጀግና መሆኑንም ወጣቶች በዘፈናቸዉ አመላክተዋል፡፡ ቃል ግጥሙ ከስመጥሩ ጀግና እሼቴ ሞገስ ባለፈ የሸዋን ሕዝብ ጀግንነትና እንደ አጼ ቴወድሮስ ክንዱ የማይጨበጥ የጀግና ህብብ ሀገር መሆኑንም ይመሰክራል፡፡

በተጨማሪም ***"በአምስት አቦ ናቸዉ በሰባት ሥላሴ፣ የአሳምነዉ ምትክ ልጅ ዘመነ ካሴ"*** በሚሉ ስንኞች የጎጃምን ሕዝብ አደራጅቶ የትጥቅ ትግል ያስጀመረዉ ዘመነ ካሴ የአሳምነዉን ዓላማ ለማሳካት አማራ መታጠቅ መደራጀትና መታጠቅ እንዳለበት የሰበከና የአሳምነዉ ምትክ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ዘመነ በአሁኑ ሰዓት የጎጃም ፋኖ መሪና ሕዝቡ ለህልዉናዉ ታግሎ መብቱን በክንዱ እንዲያሥከብር ግንባር ቀደሙን ሚና እየተጫወተ ያለ አርበኛ ታጋይ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ የምስጋና ዜማ የተቀነቀነላቸዉ ጀግኖች የሕዝቡ ባለዉለታ፣ አለኝታና መከታ እንዲሁም የነጻነት ተስፋና የድል ችቦ ለኳሽ እንደሆኑ ቃል ግጥሞቹ ይጠቁማሉ፡፡

## 4.2.2. የመምከርና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



*በ2016 ዓ.ም በጃንሜዳ ጥምቀተ ባሕር በባንዲራ አለባበስ የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት*

ቃላዊ ግጥሞች ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማንፀባረቅም ይጠቅማሉ:: በማህበረሰቡ ዘንድ በሚታዩ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ይዘትና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገጠማሉ፣ ይዘፈናሉ:: ትኩረታቸውም ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፍጠርና፣ ለቅስቀሳ ሆኖ፣ የህዝብን አመለካከት ማንፀባረቅ ይሆናል:: ስድብ አዘልና ምፀታዊ ቃላዊ ግጥሞች ለፖለቲካ ተግባር በሚውሉበት ጊዜ እንደ ጦር መሳሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: በአንፃሩም፣ ለፖለቲካዊ ግፊት መፍጠሪያ፣ ወ.ዘ.ተ. ይሆናሉ (Finnegan፣ 1970፣ 272-284)

ስለሆነም በዚህ ኹለተኛ ዐብይ ክፍል ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች የሕዝቡን ሰላምና መረጋጋት፣ እኩልነትና ፍትህ፣ ልማትና መብት የሚጻረሩ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ አካላትን፣ አመራርና ሥርዓቱን የማሥጠንቀቅና የመምከር ፋይዳ ያላቸዉ ሲሆኑ ይህ ካልሆነ ግን ምላሹ እንደሚከፋ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡

1. እየነገርናቸዉ እያረጉት ዋዛ፣
   የሚፈናቀለዉ የሚሞተዉ በዛ፣
   መንግስትን የሚንቅ የሚጠላዉ በዛ፡፡
2. ህዝብ እንዲያስተዳድር  ቢሰጡ ሀገር፣
   እንደ ልጅ አማረዉ መጫወት ባፈር፡፡

በዚህ በኹለተኛ አብይ ክፍል ስር ከላይ በተራ ቁጥር አንድና ኹለት የቀረቡት ቃል ግጥሞች አመራሩ፣ ሕዝቡና የሚመለከታቸዉ አካላት የሕዝቡን ምክር መስማትና መቀበል ባለመቻላቸዉ እየተከፈለ ያለዉን ዋጋ ለመጠቆም በአዲስ መልክ ተደርሰዉ የተዜሙ ናቸዉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሀገራዊ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ፣ ጥላቻና ቅሬታ እየነገሰ መጥቷል፡፡ በዚህም ሰላምና መረጋጋት ስለጠፋ ሕዝቡ ሁሉን እያየና እየሰማ ደስታና ሀዘኑን፣ ቅሬታና ወቀሳዉን በቃል ግጥሙ በተገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ በማንጎራጎር እየገለጸ ይገኛል፡፡

ምሁራን፣ አዝማሪዎች፣ እረኞች፣ አባቶችና ተመራማሪዎች በግጥምና በምክር የሚያቀርቧቸዉን አስተያየቶች መንግስት ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ ለፖሊሲና ስትራቴጂ መረጃ ግብአት፣ ለችግሮች መፍቻና የህዝቡን ስሜትና ፍላጎት ለማወቅ ሊገለገሉበት ይገባል፡፡ አለበለዚያ ሕዝብ ታግሶ፣ ችሎ መክሮ ዘክሮ የሚሰማዉ ሲያጣ ቅሬታና ተቃዉሞ ያሰማል፣ ተስፋ ሲቆርጥ ግን የሆዱን በሆዱ አድርጎ መናገርም ያቆማል፡፡

የሕዝብን  ዝምታ ከፍርሃት መቁጠር ሞኝነት ነዉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮው ቻይ፣ በባህርይው ታጋሽ፣ በሕልውናዉ ከመጡበት እንደ አራስ ነብር ቁጡ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱን ሕዝብ ለማስተዳደር መብቱን መጠበቅና ባህሪዉን ማወቅ ይጠይቃል፡፡  የታሪክ ስህተቶችን ላለመድገም ከታሪክ መማር ብልህነት ነው፡፡ ለአብነትም ከግብፅና ከሊቢያ ክስተቶች መማር ይገባል፡፡ ካልሆነ “መካሪ የሌለው ንጉስ ያለ አንድ ዓመት አይነግስ” እንዲሉ የሥርዓትና የአመራሩ እድሜው ያጥራል፡፡ ስለሆነም የህዝብን የልብ ትርታ በማዳመጥ የተጠላውን የአገዛዝ አካሄድ ማሻሻል ተገቢነቱ አያጠራጥርም፡፡ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞችም ይህንኑ የሕዝብ ስሜት፣ አመለካከትና ድርጊት የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡

***"ግን ማንስ አዳምጦ ኧረ ማንስ ሰምቶ፤ ሁሉም እጀሮዉ ላይ በሆዱ ተኝቶ"*** እንዲል ደራሲ[6] የታላላቅ ሰዎችን፣ የአዝማሪዎችንና የሕዝቡን ምክር ጆሮ የሚነሳዉና ዳባ ልበስ የሚለዉ፣ የሚንቀዉ እና የሚተቸዉ በዝቷል፡፡ ሰዉ እንደልቡ ወጥቶ መግባት፣ ሰርቶ መብላት፣ ዘርቶ መቃም እና ወልዶ መሳም ባለመቻሉ ሁሉም የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆን ጀምሯል፡፡ በተራ ቁጥር አንድ በቀረበዉ ቃል ግጥም ለማስተላላፍ የተሞከረዉም ሕዝቡ ከየአካባቢዉ መጤና ሰፋሪ እየተባለ ሃብትና ንብረቱን እየተቀማ፣ እየተዘረፈ፣ እየተሰደደ የሞት ድግስ ፍሪዳ መሆን ጀምሯል የሚል አንድምታ ያለዉ ምክር ነዉ፡፡

ሕገወጥ ዘራፊና ቀማኛ ቡድኖች ኬላ እያቆሙ ሕዝቡን መዝረፍ፣ ሰዎችን አግተዉ ገንዘብ መቀበል፣ የሚጠሉትን ብሔረሰብ አባል ወደመጣህበት ተመለስ፣ ማለት ጀምረዋል፡፡ ሕዝብ መርጦናል የሚሉት አመራሮችም የሕዝብን ሰላም፣ ደህንነትና መረጋጋትን ማስጠበቅ፣ እንዲሁም ፍትህና ሕግን ማስከበር ባለመቻላቸዉ ከሁሉም ጋር ሳይነካኩ መንበራቸዉን በጦር ሃይል ማስጠበቅ ጀምረዋል፡፡ በተራ ቁጥር ኹለት የቀረበዉ ግጥምም ይህንኑ የመንግስት አስፈጻሚ አካላትን የሚጠበቅባቸዉን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት አለመቻላቸዉን የሚያመላክትና የተሰጣቸዉን ኃላፊነት ህዝብን በብቃት ሊያገለግሉበት እንደሚገባ የሚመክር ነዉ፡፡

3. አመለ ልስልሱን የዋህ ገራም በሬ፣
ነካክተዉ ነካክተዉ አደረጉት አዉሬ፡፡
4. አይተነዉ አይተነዉ ካላማረ ቀኑ፣
እኛም አዉሬ እንሁን እነሱም ያድኑ፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ሦሥት እና አራት በተጠቀሱት ባለመንቶ ቃል ግጥሞች ሊተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት ሰላም ወዳዱ ሕዝብ በተለይም አርሶ አደሩ በደል ጭቆናና ግፍ ሲጠናበት የሚሰጠዉን የከፋ ምላሽ የሚያመለከት ነዉ፡፡ በተራ ቁጥር ዘጠኝ ***"አመለ ልስልሱን የዋህ ገራም በሬ፣ ነካክተዉ ነካክተዉ አደረጉት አዉሬ"*** የሚለዉን ቃል ግጥም ለብቻዉ ስንመለከተዉ በተለዋጭ ዘይቤ የቀረበ ሲሆን በሬ ጫናና ግፍ

[6] ፈቃደ አዘዘ፡ ጥቅምት 29/1986 ዓ.ም እየሄድኩ አልሄድኩም በሚል ባሳተሙት መድበለ ግጥም ገጽ 34 ላይ ከበዳ ወደበዳ, በሚል ርዕስ ይጮሃል አዝማሪ፣ ይጮሃል ከያኒ፣ ይጮሃል ደራሲ፣ ግን ማንስ አዳምጦ ኧረ ማንስ ሰምቶ ሁሉም እጀሮዉ ላይ በሆዱ ተኝቶ። የሚል ግጥ አላቸዉ፡፡

ካልበዛበት አይዋጋም ቀንበሩንም አይሰብርም፡፡ ሰዎችም ቀንበር ጭነዉ፣ በማነቆ ጠፍረዉ በጅራፍ እየገረፉ ሞፈር እያስጎተቱ እርሻ ያርሱበታል፡፡

የዚህ አይነቱ በሬ ለየዋሃን፣ ትዕግስተኛና ገራም ሰዎች ምሳሌ ሆኖ የቀረበ ነዉ፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች ታግሰዉ፣ ችለዉ፣ የመከራና የግፍ ቀንበር ተጭኖባቸዉ ትዕግስታቸዉ እስካላለቀ ድረስ ትንፍሽ አይሉም፡፡ ለባለቤታቸዉ በቅንነት ያገለግላሉ፡፡ ግፉ የበዛና ትዕግስታቸዉ ያለቀ ዕለት ግን አዉሬ ይሆናሉና ቀንበሩን እስከ አራሹ ሰባብረዉ ከመጣል ወደኋላ አይሉም፡፡ በግጥሙ የተመላከተዉ ቀንበር የጭቆና ተምሳሌት ነዉና በጭና ቀንበር ስር ያሉ ሕዝቦችም ግፉ ጠንቶ ትዕግስታቸዉ ያለቀ ዕለት አዉሬ ይሆናሉና ቀንበሩን እስከ አራሹ ሰባብረዉ እንደጣሉት በሮች ሥርዓቱን ከነአመራሮቹ ሰባብረዉ ከመጣል ወደኋላ አይሉም የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

ሕዝብ ታግሶ፣ ችሎ መክሮ ዘክሮ የሚሰማዉ ሲያጣ ቅሬታና ተቃዉሞ ያሰማል፣ ተስፋ ሲቆርጥ ግን መናገር ያቆማል፣ ልቡ ይሸፍታል፣ የሰላሙን መንገድ ትቶ የኃይል እርምጃ ዉስጥ ይገባል፡፡ ይህ ቃል ግጥምና የታየዉ የክዋኔ አዉድም ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ሕዝብ ዝም ሲል ጠቢባን ይናገራሉ፡፡ ገጣሚዎች ደግሞ ጠቢባን ናቸዉ፡፡ የሕዝቡን ስሜት መከራና ስቃይ በግጥማቸዉ ይናገራሉ፡፡ ለህሊናቸዉና ሕዝብ ለጣለባቸዉ አደራና እምነት ኃላፊነታቸዉን ይወጣሉ፡፡ በተለይም የቃል ግጥም ደራስያን የግላቸዉን እምነትና ስሜት ሳይሆን የሀገርና የሕዝብ ድምጽ ሆነዉ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮችን እየደረሱ ሕዝብ በተሰበሰበባቸዉ የክወና አጋጣሚዎች ሁሉ በመገኘት ሕዝብንም መንግስትንም ያስጠነቅቃሉ፤ ይወቅሳሉ፤ እንደ እረኞች፣ እንደ አዝማሪዎችና እንደ አዋቂዎች ሁሉ የመካሪና የዘካሪነት ሚናቸዉን ይወጣሉ፡፡

የተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች በተለይ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በገጠሩም ሆነ በከተማዉ ማኅበረሰብ ዘንድ እየተባባሰ የመጣውን መንግሥትን የመጠራጠር፣ የእርስበርስ ጥላቻና ተቃውሞ፣ የምግብ እጥረት፣ የምርት ማሽቆልቆል፣ ድህነት፣ አፈና፣ እገታ፣ ስደትና በሰላም አብሮ የመኖር ተስፋ መጨለም በገሃድ ያሳያሉ፡፡ ይህም የተነገሩት ቃል ግጥሞች አንድምታ በድምሩ ሲመረመር የሥርዓት ውድቀት አስቀድሞ በሰዉ ልብ ውስጥ እንደሚፀነስ ያመላክታል፡፡

በተራ ቁጥር አራት የተጠቀሰዉ ግጥምም በተራ ቁጥር ሦሥት ከቀረበዉ ጋር ተመሳሳይ የቋንቋ አቀራረብ እና መልዕክት ያለዉ ነዉ ፡፡ ይዘቱ ግን “ሰነፍ እረኛ ከቅርብ ሲሉት ከሩቅ” እንዲሉ አይነት ነዉ፡፡ ታጋሽ፣ የዋህና ሰላማዊ የሆነን ሰዉ

ችግሩን እየፈቱ፣ ትዕግስቱ እንዳያልቅ ቀንበራቸዉን አለዝበዉ ማስተዳደር ሲችሉ በኋላ ትዕግስቱ አልቆ ተስፋ ከቆረጠ በኋላ ትግሉ የከፋ ሊሆን እንደሚችል የሚያስረዳ ነዉ፡፡ በጥምቀት በዓል ላይ የቀረቡት እነዚህ ግጥሞች የተዜሙበት የዘፈንና ጭፈራ ብሂል የአማራ በመሆኑና ታሪክና መልዕክቱ አሁን ያለዉን የአማራን ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ የሚያመላክት እንደሆነና ዱርቤቴ ብሎ ለትግል መሰለፉን የሚያመላክት እንደሆነ ይገመታል፡፡

5. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር፣
   በርስትና በእምነት የማንደራደር፡፡
6. ንቃ ራያ ቆቦ ንቃ ሰሜን ጎንደር፣
   ባገርና በርስት እንዳትደራደር፣
7. ጭናና ማይካድራ የፈሰሰዉን ደም፣
   ቁመህ እንዳትረሳዉ በድንህ ሳይጋደም፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አምስት እስከ አስራ ሰባት የቀረቡት ቃል ግጥሞች የዘመናችን እና የሃገራችንን የፖለቲካ ትኩሳት እና የግጭት ማዕከል የሆነዉን የወልቃይት አካባቢ እና የሰሜኑ ጦርነት ያስከተለዉን ሰቆቃ መሰረት አድርገዉ በአዲስ መልክ ተደርሰዉ የተዜሙ ናቸዉ፡፡ በታሪካዊ አጋጣሚ እና በተግባርም እንደሚታወቀዉ እስከ 1983 ዓ.ም ወልቃይት እና የራያቆቦ ዋና ከተማ አላማጣ የጎንደርና የወሎ ርስት እና ግዛቶች እንደነበሩ የሚታወቅ ነዉ፡፡

ኹለቱም አካባቢዎች ወደትግራይ የተካለሉት ህወሃት ደርግን አሸንፋ ወደመሃል አገር ከመምጣቷ በፊት በ1982 እና በ1983 ዓ.ም ነዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሕወሃቶች ቦታዎችን በሀይል ያዙ እንጂ መንግስትም ይሁን ሕገመንግስቱ ገና አልተቋቋሙም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ትግራይ ገና ክፍለ ሀገር እንጂ እንደ ክልል አልተቋቋመችም ነበር ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ሥልጣን በእጃቸዉ ሲይዙ ይህንን ስዉር ዓላማና የመሬት ወረራቸዉን በሕገመንግስታዊ የብሔር ማዕቀፉ አሳበዉ የራሳቸዉ ግዛትና ርስት እንደሆነ በማወጅ የአማራን ሕዝብ ከአካባቢዉ የማጽዳት ስራ ሰሩ፡፡

በህወሓትና በፌዴራሉ መንግስት መካከል በነበረዉ የ2013ቱ ጦርነት ከያዙት የወልቃይ አካባቢ የጦር ሃይላቸዉን ተከትለዉ ሲወጡ ጭናና ማይካድራ ላይ ሳምሪ

በተሰኘዉ ታጣቂ ቡድን በአማራ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ[7] በማድረግ ወደሱዳን መሻገራቸዉ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ***“ጭናና ማይካድራ የፈሰሰዉን ደም ቁመህ እንዳትረሳዉ በድንህ ሳይጋደም”*** የሚለዉ ቃል ግጥም አማራዉ ይህን ጅምላ ጭፍጨፋ እንኳን በሕይወት እያለ ሞቶም ሊረሳዉ አይገባም የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ ***“ንቃ ራያ ቆቦ ንቃ ሰሜን ጎንደር ባገርና በርስት እንዳትደራደር”*** የሚለዉ ቃል ግጥም ደግሞ የአማራና የትግራይ ክልል ድንበር ተከዜ ስለሆነ አማራዉ በርስቱና በቆመለት እምነት መደራደር የለበትም፡፡ ክንዱን ሳይንተራስ እርስቱን ለህወሓት አሳልፎ መስጠት የለበትም ካልሆነ እልቂቱ እንዲቀጥል እድል መስጠት ነዉ የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

8. ጎንደር ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ጎጃም ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ወሎ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ሸዋ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ለካስ ይዘነዋል በራበሩን ሁሉ፡፡

የዚህ ቃል ግጥም መልዕክት አንድም የአማራን ክልል ስፋትና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የሚያሳይ ሲሆን አንድም ደግሞ ክልሉ ለወገን ምቹ ለጠላት ፈታኝ ስትራቴጂያዊ ቦታ መሆኑን የሚጠቁም ነዉ፡፡ በተለይም አሁን ባለዉ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ክልሉ ዉስጥ በተጀመረዉ የእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት ራስን ለመከላከል ምቹ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለአብነትም ተዋጊ የሰዉ ሃይል ለመመልመል፣ የትጥቅና ስንቅ ድጋፍ ለማግኘት፣ የጠላት ሃይልን እንቅስቃሴ ለመከታተል፣ ሸሽቶ ለማምለጥና ጠላትን አባሮ ለመያዝም ምቹ መሆኑንም የሚያመላክት ቃል ግጥም ነዉ፡፡

---

[7] የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማይካድራ የደረሰውን ጅምላ ጭፍጨፋ የተመለከተ ተጨባጭ ማስረጃ ማደራጀቱን ገለጸ ሐምሌ 16 ቀን 2013 (ኢዜአ) የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማይካድራ የደረሰውን ጅምላ የዘር ጭፍጨፋ የሚያጋልጥና ለዓለም አቀፍ መንግስታትና ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የሚቀርብ ተጨባጭ ማስረጃ ማደራጀቱን ገለጸ። ዩኒቨርሲቲው ለአምስት ወራት ባካሄደው ጥናትና ምርምር ማስረጃውን እንዳደራጀ አመልክቷል። በዘር ጭፍጨፋው 1 ሺህ 563 ሰዎች በማንነታቸው ምክንያት ሲገደሉ 81 ሰዎች ደግሞ ለአካል ጉዳት መዳረጋቸውን አረጋግጧል። Ethiopian News Agency July 23/2021

9. ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፣
   ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፡፡
10. እንኳን በለዉ ብለዉ ልከዉ ሰደዉት ፣
   እንዳዉም አማራ አመል አለበት፡፡
11. አምናም አስሮኝ ነበር ዘንድሮም አጋዘኝ፣
   እንደማንላቀቅ ገብቶታል መሰለኝ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር ዘጠኝ እስከ አስራ አንድ የቀረቡት ቃል ግጥሞች ከአማራ ሕዝብ በተቃርኖ ለቆሙ ለሀገሪቱ ፀጥታ ሃይሎች፣ የቀረቡ የማስጠንቀቂያ የተግሳጽ፣ የዛቻና የማስፈራሪያ መልዕክቶችን ያዘሉ ናቸዉ፡፡ በአማራ ክልል በህግ ማስከበርና ራስን በመከላከል ስም በተጀመረዉ የእርስ በርስ ጦርነት በአንድ በኩል ሕዝቡ በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ አመራሮች እርምጃ እየተወሰደባቸዉ ነዉ፡፡ በተራ ቁጥር ዘጠኝ የቀረበዉ ቃል ግጥም ሃሳብም ይህንኑ የሚያጠይቅ ሆኖ ቅጥኛ እና ባንዳ በመሆን ሥርዓቱን እያገለገሉና ሕዝባቸዉን እያሰቃዩ ያሉት የብአዴን አመራሮች፣ ከመከላከያ ጋር ወግነዉ ሕዝባቸዉን የሚወጉ ሚሊሻና አድማብተናና በጥቅም ተገዝተዉ የዉስጥ አርበኛ ሆነዉ የሚያገለግሉ አማራዎች ወ.ዘ.ተ ርካሽ ተግባራቸዉ ካልተመለሱ የማያዳግም እርምጃ ይወሰድባችኋል የሚል አንድምታ ያለዉ ማስጠንቀቂያ ነዉ፡፡

በተራ ቁጥር አስር የቀረበዉ ቃል ግጥም በበኩሉ ***"እንኳን በለዉ ብለዉ ሰደዉ ልከዉት፣ እንዳዉም አማራ አመል አለበት"*** በሚል በመንግስት አመራሮች "እንኳን ትጥቁን ሱሪዉን እናስፈታዋለን" በሚል በተሳሳተ ስሌት የተከፈተበትን ክብረነክ ስድብና አዉዳሚ ጦርነት በአሸናፊነት ለመወጣት የሚያደርገዉ የትጥቅ ትግል በመንግስትና በመከላከያ ተንኳሽነት የተጀመረ እና አማራ ተገዶ የገባበት መሆኑን ይገልጻል፡፡

"መታፈር በከንፈር" እንዲሉ የአማራን ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት ለማስከበር በሚል መዝመት እና ሕዝቡንም ከጎን ማሰለፍ እየተቻለ የንቀት ቃል መሰንዘሩ ሕዝቡን ከፋኖ ጋር እንዲሰለፍ እና በመከላከያ ትጥቅ መፍታት በመጠናቀቅ ላይ እንደሆነ አስተያየቶች ይሰማሉ፡፡ አማራ እንደተባለዉም እንኳን በለዉ ተብሎ እንዲያዉም ሆድ የባሰዉ ነዉ፣ ማህበረ ፖለቲካዊና የመልካም አስተዳደር ችግር ያሥመረረዉ በመሆኑ ምላሹን የከፋ እንዳደረገዉ የጸጥታ ሃይሉን ለማስጠንቀቅ የቀረበ ይመስላል፡፡

*"እምናም አስሮኝ ነበር ዘንድሮም አጋዘኝ፣ እንደማንላቀቅ ገብቶታል መሰለኝ"* በሚል የቀረበዉ ቃል ግጥም በበኩሉ በመላዉ አማራና በአዲስ አበባ ከተማ ያለዉን የወጣቶች አፈናና ግዞት እሱም ያስከተለዉን ምላሽ በሚመለከት የቀረበ ይመስላል፡፡ ወጣቶች በዓሉን ለማድመቅና እገረ መንገዱንም የሕብረተሰቡን ስሜትና ቅሬታ ለማንጸባረቅ ሲሞክሩ ዘንድሮም ባለፈዉ ዓመትም ብዙ ወጣቶች ታስረዉ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ቃል ግጥሙም ይህንን በመቃወም ወጣቶች እስር ፈርተዉ ወደኋላ እንደማይሉ፣ ለሚያሳድዷቸዉ አካላት አንላቀቅም የሚል ማስጠንቀቂያ ያሥተላለፉበት ይመስላል፡፡ በተጨማሪም ቃል ግጥሙ በእነዚህ ወጣቶች እና በጸጥታ ኃይሉ መካከል ከሚታየዉ የበዓሉ የአሳዳጅ ተሳዳጅ ትሪኢት ባለፈ ጉዳዩ ወደለየለት ግጭትና መሄዱ እንደማይቀርና መንግስትና የጸጥታ ኃይሉ የመልካም አስተዳደር ችግር አለብን የሚሉ ጥያቄዎችን በሃይል ለመፍታት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ካላቆሙና ሰለማዊ ትግሉ ለዉጥ እስካላመጣ ድረስ የጥትጥቅ ትግሉ አይሬ መሆኑን የሚያመለክት ነዉ፡፡

12. ጠ/ሚኒስቴር ኬኛ ከንቲባዋ ኬኛ፣
    ኢታማጆር ኬኛ ደህንነቱም ኬኛ፣
    ብሔር ብሔረሰብ ተከናንበህ ተኛ፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር አስራ ኹለት የቀረበዉ ቃል ግጥም የጸጥታ ሀይሎች በሕዝቡ ላይ ጉዳት አድርሰዉ በነሱም ላይ በሕዝቡ ተመጣጣኝ ጉዳት በደረሰበት ከስጋ ሜዳ ታቦት ማደሪያ ወደ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በነበረዉ ጉዞ ጥር 11/2016 ዓ.ም የቀረበ ነዉ፡፡ ቃል ግጥሙ በሦሥት ስንኞች እና በአንድ አርኬ ዘመንኛዉን የቄሮ የኬኛ ፖለቲካ ተከትሎ ለብሔር ብሔረሰቦች የቀረበ የማስጠንቀቂያ መልዕክት የያዘ ይመስላል፡፡ የግጥሙ ጠቅላላ መልዕክት የተረኝነት ፖለቲካ ያስከተለዉን የተሳሳተ አመራርና ተጠቃሚነት ሊያመጣ የሚችለዉን ሃገራዊ ዉድቀት በማሳየት የማስጠንቀቂያ ደወል ለአመራርና ለሕዝቡ ማሰማት ነዉ፡፡

የዚህ ግጥም ጭብጥ የሃገሪቱ ዋና ዋና የስልጣን ወንበር በአንድ ብሄረሰብ ተጠቅልለዉ የተያዙ ስለሆኑ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሐገሪቱ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤቶች ናቸዉ የሚለዉ ሕገመንግስት ተሸሯል የሚል ነዉ፡፡ በዚህም የተጠቀሱት ብሔር ብሔረሰቦች የአሃዳዊ አስተዳደር እና የጥቂቶች

ተጠቃሚነት የፖለቲካ አደጋ ተጋርጦባቸዋል የሚል አንድምታና ማስጠንቀቂያ ያዘለ ነዉ፡፡

13\. እንኳንስ መታሰር መገደል ቢመጣ፣
ማንንም አልሰማ በፋኖ የመጣ፡፡

14\. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አስራ ሦሥት እና አስራ አራት የቀረቡት ቃል ግጥሞች ሕዝቡ ለፋኖ ያለዉን እምነት እና ወገንተኝነት በማመላከት ማንም አይንካብን የሚል ማስጠንቀቂያ እና ለፋኖ ያለዉን ድጋፍ የሚያመላክቱ ናቸዉ፡፡ ለፋኖ ያለን እምነትና ድጋፍ እንኳን መታሰር መገደልም ቢመጣ አናቆምም፣ ፋኖን አትደግፉ የሚል ፕሮፓጋንዳ፣ አዋጅና ማሳሰቢያ እንዲሁም አመራር ሆነ ሕግ አስከባሪ ምክር አንቀበልም የሚል አንድምታ ያለዉ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ኅብረተሰቡ የሚደርስበትን ችግርና በደልም ሕግ አስከባሪዉ ስለማይሰማዉ በሕግ አምላክ ማለትን እንደከንቱ ጩኸት በመቁጠር የመንግስትን ሚናና ኃላፊነት ለታጣቂ ኃይሎች መስጠቱንና በመንግስት ተስፋ መቆረጡን የሚያሳይ ማስጠንቀቂያ ነዉ፡፡

15\. ተዉ እርገጥ እርገጥ እርገጥ ባንድ ላይ፣
ተወልደህ አድገህ ሰሜን ሸዋ ላይ ፣
ተዉ እርገጥ እርገጥ እርገጥ ባንድ ላይ፣
ተወልደህ አድገህ ቤተ አማራ ላይ፡፡

ነባርና አዲሱ ማኅበራዊ ሚዲያዎች፣ መዛግብትና ምሁራን እንደሚነግሩንና በተግባርም እንደምናየዉ የዘዉግ ፌደራሊዝምና ፖለቲካ ህዝቡን በመከፋፈልና በጎጥ ማዕቀፍ ዉስጥ ታጉሮ እንዲበጣበጥ እና ሀገር እንዳትረጋጋ የሚያደርግ እንደሆነ ይናገራሉ[8]፡፡ በ1983 ዓ.ም ህወሓት ደርግን አሸንፋ ሀገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በ1987 ዓ.ም በጸደቀዉ ሕገመንግስት እዉቅና አግኝቶ በተደራጀዉ የዘዉጌ ፌደራሊዝምና የክልል

---

8 የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ኢትዮጵያ ፌዴራል የመንግስት መዋቅርን የምትከተል አገር መሆኗን በግልጽ ይናገራል፥ ሆኖም ዛሬ በተግባር እንደሚታየዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ኮንፌዴሬሺን እንጂ ፌዴራሊዝም የሚባል ነገር ያለም አይመስልም። ክልሎች ከፌዴራል መንግስቱ ጋር የሚገዳደር፥ ታማኝነታቸዉ ለፍትህና ለህግ የበላይነት ሳይሆን የኛ ነዉ ለሚሉት ክልል ብቻ የሆነ የታጠቀ ልዩ ሃይልና ፖሊስ አላቸዉ። በክልሎችና በፌዴራሉ መንግስት መካከል ያለዉ ግኑኝነት የላላ ነዉ፥ በዚህም ምንያ ግጭቶችና መገፋፋቶች ይጠራሉ። ኤፍሬም ማደቦ ኤፍሬም ማዴቦ ህዳር 12 2012 ዓ. ም

አደረጃጀት አጽመ ርስታችን የሆኑ ግዛቶች ለሌሎች ክልሎች እንዲከፋፈሉ ተደርጓል በሚል በአማራ ሕዝብና ምሁራን በኩል ቅሬታዎች ይሰማሉ፡፡ በዚህም አማራዊ አንድነቱን ሳይሆን መከፋፈሉን እያሰበ ተለያይቶ እንዲኖር ለማድረግ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎና ሸዋ እንጂ አማራ የሚባል አካባቢና ሕዝብ የለም የሚል የተሰራጨበት አስተምህሮም እንዳለ ይገልጻል፡፡

ስለሆነም ቃል ግጥሙ ህዝቡ ይህንን እኩይ አላማና ግብ ተረድቶ መለያየቱን አቁሞ በጋራ እንዲቆም፣ አንዱ ሌላዉን እዳይጠላ፣ አንዱ ሌላዉን እንዳይጠራጠርና፣ በስሁት ስብከትና ትርክት እንዳይደናገር የሚያስጠነቅቅ ነዉ፡፡ የሕዝቡ መለያየት ለገኘሮዎች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን ተረድቶ እርስ በርስ ከመናከስና ከመለያየት ይልቅ ጠላትና ወዳጁን አዉቆ ለጋራ አላማና ግብ በጋራ እንዲሰለፍ የሚመክር ነዉ፡፡

16. አዉድማዉም ይስፋ በሮችም አይራቁ፣

መናዱ የማይቀር ዉሽልሽል ነዉ እርቁ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በሰሜኑ የሐገራችን ክፍል የተከሰተዉ የእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት በድርድር እና በእርቅ ስም መጠናቀቁን ተከትሎ በ2015 ዓ.ም የጥምቀት በዓል የክወና አጋጣሚ ላይ ጥር 11 በካራ አርሴማ ታቦት ማደሪያ የተዜመ ነዉ፡፡ በግጥሙ ዉስጥ “በሮችም” የሚለዉ ቃል በሬዎችም የሚለዉን ስያሜ ገጣሚዉ ባለዉ መብት (poetic licence) የግጥሙ ዜማና ምት እንዳይሰበር ሆን ብሎ የተጠቀመበት ነዉ፡፡ ቃል ግጥሙ በበዓሉ ታዳሚ ወጣቶች በተምሳሌታዊ አገላለጽ፣ ቅርጽና ትርጓሜ ተዋዝቶ የቀረበ ነዉ፡፡ ይህም ሲባል አንድም በግብርና ሙያ ልማድ መሰረት አርሶ አደሩ ሰብሉን ከማሳዉ ላይ አጭዶ ወደ አዉድማ አግዞ ከከመረዉ በኋላ አዉድማዉ ላይ በአስቸኳይ ተንዶ ካልተወቃ በራሱ ጊዜ ሊናድ ወይ ባለበት ዝናብ ሊያበላሸዉ እንደሚችል ይጠቁማል፡፡ ለዉቂያ ለበራይ እና ምርቱን ከገለባዉ ለመለየት በሬዎችም ከአካባቢዉ መራቅ የለባቸዉም የሚል ትርጓሜ ይዞ እንደ ምስጢሩ ሽፋን ተደርጎና የቀረበ ሀሳብ አለዉ፡፡

አንድም ደግሞ በቃል ግጥሙ ሊተላለፍ የተፈለገዉ ማዕከላዊ ጭብጥ እና የግጥሙ ዋና መልዕክት ሆኖ የቀረበዉ በህወሓትና በፌደራሉ መንግስት መካከል የተደረገዉን የደቡብ አፍሪካና የናይሮቢ ድርድርና የሰላም ስምምነት ዘላቂ ሊሆን እንደማይችል የሚጠቁም ነዉ፡፡ ስምምነቱ ሕዝባዊ መሰረት የሌለዉ፤ መሰረታዊ ችግሮችን ሊፈታ የማይችል፤ ዘላቂ ሰላም፣ መረጋጋት እና ሀገራዊ አንድነት ሊያመጣ

የማይችል ነዉ፤ የፌደራል መንግስቱንና የህወሓት አመራሮችን ከተጠያነት ለማዳን የተሸረበ የሴራ ፖለቲካ ነዉ ተብሎ ይታማል፡፡ ከዚህም የተነሳ በሂደት በአፈጻጸም ችግር መፍረሱ የማይቀር ነዉ የሚል ስጋት በሕዝቡ ስሜት ዉስጥ እንዲፈጠር ያደረገ ስለመሆኑም ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በጊዜ መፍትሄ ተፈልጎለት መላ እንዲበጅለት ለአመራሩም ሆነ ለሕዝቡ ምክርና ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ነዉ፡፡

ሀገር ተወረረ ድንበር ተደፈረ የሚል ጥሪ ተቀብለዉ በጦርነቱ የተሳተፉና የተጎዱ አካባቢዎች እንዲሁም ነዋሪዎች (ለአብነትም አማራና አፋር) ለስምምነቱ ስላልተጋበዙ ሰላምና እርቅ ተፈጽሟል በሚል የእነዚህ ክልሎች ነዋሪዎች ሊዘናጉ እንደማይገባ ያስጠነቅቃል፡፡ የአማራ ታጣቂ ሀይሎቻቸዉ (ፋኖ፣ ፖሊስ፣ ሚሊሻና ልዩ ሃይል) ትጥቃቸዉን ሳይፈቱ፣ ከጦር አዉድማዉ ሳይርቁ፣ በሁሉም አካባቢ የሚመጣዉን ነገር ተዘጋጅተዉ እንዲጠብቁ የሚያስጠነቅቅ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት በሁለቱ ክልሎች መካከል ጦርነት እንደገና መከሰቱ የማይቀር መሆኑን የሚጠቁም ምጡቅ እና እምቅ የሕዝብ እይታና ማስጠንቀቂያ አዘል በዘፈን መልክ የተቀነቀነ ቃል ግጥም ነዉ፡፡

17. ጠላትን ሳይገድሉ ምን ያደርጋል አፍሮ፣
    መቀሱን ላኪልኝ ቁርጥ ነዉ ዘንድሮ፡፡

የዚህ ቃላዊ ግጥም የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ቅኔያዊ ነዉ፡፡ አሁን እየተዘነጋ መጣ እንጂ በራያ ባህልና ወግ ጠላቱን ያልገደለ ሰዉ ጸጉሬ አማረልኝ፣ ሰዉ ወደደልኝ፤ ፀሀይ ከለለልኝ ብሎ ጎፈሬዉን ማሳደግ እና ህዝብ በተሰበሰበበት መድረክ ላይ መንጎባለልና መፎከር አይችልም ነበር የሚለዉን ቱባ ባህላዊ እሴት ያስታዉሳል፡፡ አንድም ደግሞ የራያ መሬት ተወሮ፤ ህዝቡ በጦርነት እንደቅጠል እየረገፈ፤ ከሞት የተረፈዉ በስደትና በርሃብ እየተሰቃየ ስለሆነ ሕዝቡን ለዚህ መከራና ስቃይ የዳረገዉን ጠላት ሳይበቀሉ፣ ሳይገድሉና ወንድነትን ሳያረጋግጡ ማዉራት ከጀግንነት የተፋታ ድንፋታ ነዉ የሚዉል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ የዚህን አካባቢ ባህልና ወግ ለሚያዉቅ ሰዉ እንዲህ አይነቱ ተግባር ትዝብት ላይ የሚጥል ስለሆነ ጸጉሩን ቆርጦ እንደሚጥለዉ ሁሉ ፍርሃቱንም አዉጥቶ መጣልንና ጠላትን መበቀል ያሥፈልጋል የሚል ምክርና ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍ ቃል ግጥም ነዉ፡፡

18. እንጫዉት እንደሁ እንጫዉት ዛሬ፣
    ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡

የዚህን ቃል ግጥም አንድምታ በሁለት መንገድ ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያዉ ከማህበራዊ ጉዳይና ከባህላዊ ትዉፊት አንጻር ዛሬ የጥምቀት በዓል ስለሆነ እንጫወትና እንደሰት ነገ ግን ስራ ስለሆነ ይህንኑ አዉቀን ለስራ መዘጋጀት አለበን የሚል አንድምታ አለዉ፡፡ ሁለተኛዉ ስራ በሚል ጥቅል እሳቤ የተጠቀሰዉ ተጀምሮ ያለዉን የትጥቅ ትግል ነገ ተጠናክሮ መቀጠሉ አይቀርምና ለዚሁ መዘጋጀት አለብን የሚል አንድምታ ያለዉ ይመስላል፡፡ ይህንንም በተመሳሳይ አዉድና የክወና አጋጣሚ ላይ ከቀረቡት ሌሎች ግጥሞች ለአብነትም ከታች በተራ ቁጥር አንድ ***"በረቱን ከፍታችሁ በሮቹን ላኳቸዉ ሸገር ከተማ ላይ በራይ አለባቸዉ"*** ከሚለዉ ቃል ግጥም ይዘት፣ ጭብጥና አንድምታ ጋር በማነጻጸር መገንዘብ ይቻላል፡፡

19. ወይኔ አበቤ ወይኔ አበቤ፣

    አልወደደሽም ሂጂልኝ ቀልቤ፡፡

አዲስ አበባ የተማረ፣ በፖለቲካ የበሰለ፣ አስተዋይና ሕዝባዊ ወገንተኝነቱ የተረጋገጠ ለአመራርነት የሚበቃ የራሷ ተወላጅ ቢኖራትም ሀገሪቱ በቋንቋ ፌደራሊዝ መመራት ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ በራሷ ተወላጆች ተመርታ አታዉቅም፡፡ በዚህም ምክንያት በፖለቲካ መድረኮች ሁሉ በራሳችን ልጆች እንመራ የሚል ጥያቄ ቢነሳም አንድም የፌደራሉ መንግስት ከተማ ነች አንድም ደግሞ የብሔር ብሄረሰቦች ከተማ ስለሆነች በሚል ሰበብ አስባብ የኢሕአደግ አባላት በሆኑት የአማራ፣ ከትግራይ እና ከኦሮሚያ በመጡ (በተመረጡ) ፖለቲከኞች ስትመራ ቆይለች፡፡

አሁን ያለዉ ግን ከዚህ ሁሉ የተለየና በብሄር ተዋጽኦም ሆነ በድርጅት ዉክልና ሳይሆን አዲስ አበባ የኦሮሚያ ስለሆነች መመራት ያለባት በኦሮሞ ብቻ ነዉ በሚል የፖለቲካ ሽፍጥ በተደጋጋሚ ኦሮሞዎች ብቻ እየመሯት ይገኛሉ፡፡ ከ1983 ዓ.ም እስከ ዛሬ ከሦሥት አስርት ባልዘለሉ ዓመታት ዉስጥ ኩማ ደሜክሳ፣ ድሪባ ኩማ፣ ---- እና አዳነች አበቤ መርተዋታል፡፡

አዳነች አበቤ የወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሲሆኑ ዉክልናና አገልግሎታቸዉ ግን ለኦሮሚያና ለኦሮሞ ሕዝብ እንደሆነ አምነዉ፣ አዉቁና ፈቅደዉ እየሰሩ ያሉ አወዛጋቢ ባለስልጣን ናቸዉ፡፡ በዲስ አበባ ዜጎች በብሔር ማንነታቸዉ ቤታቸዉ ይፈርሳል፣ ይፈናቀላሉ፣ ይሳደዳሉ፣ ይታሰራሉ ይገደላሉ አድሎና መገለል

ይደረግባቸዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ይመስላል ቀልቤ አልወደደሽምና ሂጂልኝ ሲህ በስልጣናቸዉ ላይ መቆየታቸዉን እንዳልወደደዉ እየገለጸ ይገኛል፡፡ የግጥሙ ዜማና ክዋኔ እንደሙሾ ድርደራ እና የሞት ስንብት በሚመስል መልኩ የተከናወነ ሲሆን ይህም ወጣቱ ጥላቻ የጡን ያህ ከፍታ ላይ እንደደረሰ የሚጠቁም ነዉ፡፡

20. ወይኔ ቀጀላ ወይኔ ቀጀላ፣

መኖሩ ይብቃህ በኦነግ ጥላ፡፡

ቀጀላ መርዳሳ ከኦነግ ፖለቲከኞች እና አመራሮች አንዱ ሲሆኑ ከመሪዉ የፖለቲካ ፓርቲ ከብልጽግና ጋር ተስማምተዉ ዋናዉንና ታዋቂዉን የኦነግ መሪ የሆኑትን አቶ ሌንጮ ለታን በቁም እስር ዉስጥ በማዋል የኦነግ መሪነትን ከተረከቡ በኋላ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለመሆን የበቁ ሌላዉ አወዛጋቢ አመራር ናቸዉ፡፡ ባለስልጣኑ በፖለቲካ ወገንተኝነት እንጂ በአቅም ብቃት፣ በትምህርት ዝግጅታቸዉና በስራ ልምዳቸዉ ተመርጠዉ የተሾሙ ባለመሆናቸዉ ብቻ ሳይሆን በሚጠሏቸዉ ኢትዮጵያዊነትና ብሔረሰቦች ስም በፍቅርና ሕዝባዊ ወገንተኝነትት ሊመራ የሚገባዉን ተቋም በኦነግ አላማና ተልዕኮ እየመሩ በመሆናቸዉ የሚወቀሱ ሰዉ ናቸዉ፡፡

ለዚህምነዉ በእዉቀት፣ በቅንነትና በፍቅር ሊመራ የሚገባዉን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኦነግ የፖለቲካ ማዕቀፍ ስር መምራታቸዉን ለመቃወምና በኦነግ ጥላ ስር ተደብቀህ ህዝብና ተቋሙን መበደል ይቅርብህና ራስህን ሆነህ መታገል ካለብህ አቋም ይዘህ ከሕዝብ ተቋም ለቀህ በፖለቲካ መሰመርህ ታገል የሚል የመስጠንቀቂያና የምክር አንድምታ የሚል ቃል ግጥም ነዉ በ2016 የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተስተጋባዉ፡፡

21. ቢመችሽም ባይመችሽም

ሸገር ፊንፊኔ አይሆንልሽም፡፡

ይህ ቃል ግጥም ወጣቶች በተገነዉ አዉድና የክወ አጋጣሚ ሁሉ ከአፋቸዉ የማያወጡት የዘመናችን የአዲስ አበባ ሕዝብ እስትንፋስ፤ የህልዉና ጥያቄና የፖለቲካ ተቃዉሞ ድምጽ ነዉ፡፡ የቃል ግጥሙ ታሪካዊ መሰረት ኦነግ ለዘመናት ታግየለታለሁ የሚለዉና አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መዲና ሳትሆን የኦሮሞ በመሆኗ የህዝቡን አሰፋፈር ለመቀየር ሌላዉን ብሄራብ አባላት ከከተማዋ በልዩ ልዩ መንገድ በማሳደድና ኦሮሞን ከገጠር እያመጡ አዲስ አበባ ላይ በማስፈር የማብዛት ስራ እየሰራበት ያለ የኬኛ ፖሊካ አጀንዳ ነዉ፡፡

አጀንዳዉ ለአንድነትና የኢዮጵያዊነት ፖለቲካ እንታገላለን በሚሉ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቃዎሙት ቢሆንም የኦነግን እኩይ ተግባር ሊያስቆመዉ የቻለ አካል ባለመኖሩ ተግባርና አስተሳሰቡ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነዉ፡፡ በዚህም አሁን በስልጣን ማማ ላይ የተፈናጠጡት የኦነግ ስሪትና አስተሳሰብ ያላቸዉ የኦህደድ ፖለቲከኞች በህግም በጉልብም የሕዝቡን አሰፋፈር እየቀየሩ የኦሮሞ ከተማ ለማድረግ እየሰሩ የሚጨበጥ ለዉጥም እያስመዘገቡ ናቸዉ፡፡

እነዚህ አመራሮች የወጣቶች "ሸገር ፊንፊኔ አይሆንሽም" ዛቻና ማስፈራሪያ ሲሰለቻቸዉ  ቀደም ሲህ ፊንፊኔ ዙሪያ ወረዳ እያሉ የሚጠሩትን ከተማይቱን የዳርቻ ክፍሎች ከተማይቱን ብቻ ሳትሆን ስያሜዉንም እንፈልገዋለን ብለዉ ሸገር ከተማ ብለዉ በመሰየም አዲስ አበባን የማትጠቅምና ርባና ቢስ ከተማ እናደርጋታለን እንዳሉት ከጥቅም ዉጭ ለማድረግ እየሰሩ ነዉ፡፡

ለዚህ የፖለቲካ ስራና የብሄር ፌደራሊዝም አስተዳደር ስልት ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ ዉስጥ ለሚፈጠረዉ ለየትኛዉም ችግርና ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ሆነዉ የሚወቅሱትና የማስጠንቀቂያ መልዕክት የሚላከዉ የከተማይቱ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ ናቸዉ፡፡ የግጥሙ ጭብጥ በምንም አይነት መልኩ ሸገር ፊንፊኔ ልትሆን አትችልም የሚል በመሆኑ ይህንን ማድረግ እደማይቻል የተረዱት አመራሮች ስያሜዋን ወደሸገር የቀየረ አዲስ አበባን ዙሪያዋን አቅፎ መዉጫ መግቢ እየነሳ ሌላ ከተማ አቋቁመዋል፡፡ አዲስ በአባ ፊንፊኔ ባትሆንም ሰገር በማድረግ ሸገር ኬኛ እያሉን ነዉ፡፡

### 4.2.3. የመቀስቀስና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና




*በ2016 ዓ.ም በጃንሜዳ ጥምቀተ ባሕር በዉሁድ ማንነት የደመቁ የጭፈራ ቡድን አባላት*

በዚህ በሦሥተኛ አብይ ምድብ ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች በአፈና፣ በመፈናቀል፣ በጦርነትና በህልዉና ስጋት ዉስጥ ነኝ የሚለዉ የአማራ ሕዝብ ራሱን ከዉድቀት እንዲከላከልና በቀየዉ ላይ ሰፍሮ የሚገድለዉን ታጣቂ ሃይል፣ ባንዳና ተላላኪ ሁሉ ጥሎ ነጻነቱን እንዲያዉጅ የመቀስቀስና የማነቃቃት ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

ይህንንም ቃላዊ ግጥሞች ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማንፀባረቅም ይጠቅማሉ፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በሚታዩ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ይዘትና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገጠማሉ፣ ይዘፈናሉ፡፡ ትኩረታቸውም ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፌጠርና፣ ለቅስቀሳ ሆኖ፣ የህዝብን አመለካከት ማንፀባረቅ ይሆናል፡፡ ስድብ አዘልና ምፀታዊ ቃላዊ ግጥሞች ለፖለቲካ ተግባር በሚውሉበት ጊዜ እንደ ጦር መሳሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: በአንፃሩም፣ ለፖለቲካዊ ግፊት መፍጠሪያ፣ ወ.ዘ.ተ. ይሆናሉ (Finnegan፣ 1970፣ 272-284) በማለት Finnegan የገለጹትን የቃል ግጥም ፋይዳ አተገባበር በግልጽ የሚያመላክት ነዉ፡፡

1. በረቱን ከፍታችሁ በሮቹን ላኳቸዉ፣

   ሸገር ከተማ ላይ በራይ አለባቸዉ፡፡

የዚህ ባለመንቶ ቃል ግጥም የቋንቋ አቀራረብ ተምሳሌታዊ የትርጓሜ ስልት ሲሆን ጀግኖችና ጠንካራ ሰዎች በበሬዎች ጦርነቱ በበራይ ተመስለዉ የቀረቡበት ነዉ፡፡ የግጥሙን ይዘት ስንመለከትም ሕዝቡ ከየአቅጣጫዉ እየደረሰበት ያለዉን የመልካም አስተዳደር እና የህልዉና ችግር ተከትሎ በሰላማዊ መንገድ ላቀረበዉ ጥያቄ በጎ ምላሽ አልተሰጠኝም ብሎ እያማረረ ነዉ፡፡

ስለሆነም መብቱን በክንዱ ለማስከበር የትጥቅ ትግል ጀምሮ የጸጥታ ኃይሉን መገዳደር ጀምራል፡፡ ትግሉም ራስን ነጻ በማዉጣት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዳልሆነና ወደ አዲስ አበባ ያነጣጠረ ስለመሆኑ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜሙ የአማርኛ ዘፈንና ጭፈራ የቃል ግጥሞች ያመላክታሉ፡፡ በግጥሙ ***“በረቱን ከፍታችሁ በሬዎቹን ላኳቸዉ”*** የሚለዉ ስንኝ የጀግንነት ተምሳሌት በተሰጠዉ በሬ ስም የተወከሉት አካላት ትግሉን አጠናክረዉ ድንበር፣ ክልልና የማንነት ማዕቀፍ ተብሎ ከተሰጣቸዉ ክልል ወጥተዉ ወደፊት እንዲገፉ የሚቀሰቅስ ነዉ፡፡

ሁለተኛዉ ስንኝ በበኩሉ ከአሉበት ክልል ተፈትተዉ የሚለቀቁት በሬዎች ‹‹ሸገር ከተማ ላይ በራይ[9] አለባቸዉ›› በሚል ጀግኖቹ አዲስ አበባ ላይ እንዲያደርጉት የሚጠበቅ ከባድ ጦርነት እንዳለባቸዉና ሕዝቡም በተስፋ እደሚጠብቃቸዉ የሚያመለክት ነዉ፡፡ በኹለተኛ ስንኝ ከቀረበዉ መረዳት የሚቻለዉ ደግሞ የቃል ግጥሙ ይዘት በአማራ በተጀመረዉ የእርስ በርስ ጦርነትና በፋኖ ትግል ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት ሕዝቡ ፋኖዎች የጀመሩትን ጦርነት ከአማራ ክልል አዉጥተዉ ወደአዲስ አበባ እንዲያሥፋፉት የሚቀሰቅስና የሚገፋፋ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

2. ያገር ያለህ እያልን ዝም አላችሁ ምነዉ!?

   ያማራዉ በሽታ የናንተም ህመም ነዉ፡፡

3. ታምሚያለሁና ሁላችሁ ታመሙ፣

   ያንድ ሰዉ በሽታ ይበቃል ለሁሉ፡፡

---

[9] በራይ፡- አበራዬ ከሚለዉ ግስ የሚወጣ ስም ነዉ። ትርጉሙም ወቃ፣ እህልን በከብት ማረባየት፣ በዉድማ ላይ ጥሎ መዉቃት። የሚለዉን ፍች ይይዛል። በፍካሬያዊ ትርጉሙ ግን ደበደበ፣ አብዝቶ መታ፣ በጦርነት አደቀቀ። የሚለዉን ፍች ይይዛል።

ከላይ በተራ ቁጥር ኹለት እና ሦሥት የቀረቡት ቃል ግጥሞች ምንም የተደበቀ ምስጢር የላቸዉም፡፡ በአማራ ክልል የተጀመረዉን የመልካም አስተዳደርና የፍትህ ጥያቄ እንዲሁም የተቃዉሞ እቅስቃሴ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊቀላቀለዉ እንደሚገባ የመቀስቀስ ሚና ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ የአማራን ችግር ዝም ብሎ ማየት ግን በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለዉ ስቃይ፣ መከራ እና ችግር በናንተም ላይ መድረሱ የማይቀር ነዉና በጋራ እንታገል የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ "ያገር ያለህ" የሚለዉ ሃረግ ትርጉም የዕሪታ፣ የጩኸትና የድረሱልኝ ጥሪን የሚጠቁምና በሀገር ስም ሕዝቡን የሚቀሰቅስ ነዉ፡፡ የዋህ ከጥፋቱ ብልህ ግን ከሌላዉ ጥፋት ይማራልና አማራ ሀገር ይዳን ጥፋት ይብቃ፣ በእኔ የደረሰ ችግር፣ መከራና ስቃይ አይድረስባችሁ የሚል ይመስላል፡፡

4. እንኳንስ ጎጃም አይዞህ እያለዉ፣
   እንኳንስ ጎንደር አይዞህ እያለዉ፣
   እንኳንስ ወሎ አይዞህ እያለዉ፣
   እንኳንስ ሸዋ አይይህ እያለዉ፣
   እንዳዉም ፋኖ አመጸኛ ነዉ፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ስራ ላይ የዋለዉ የቋንቋ አጠቃቀም በስመ ሀደሪ በመሆኑ መኖሪያዉን ጠርቶ ነዋሪዉን የሚጠቅስ ነዉ፡፡ ስለሆነም እንኳንም ጎንደር፣ ጎጃም ወሎና ሸዋ አይዞህ እያለዉ ሲል የጎንደር፣ የጎጃም የወሎና የሸዋ ሰዉ አይዞህ በርታ እያለዉ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በፋኖ ስም የተጠራዉ ሕዝባዊ ሃይል ደግሞ አይዞህ በርታ የሚለዉ ጥላና ከለላ የሚሆነዉ አጋርና ወገን በማግኘቱ መበረታታቱን ያሳያል፡፡

በግጥሙ የተጠቀሱት አራቱ አማራ የሚኖርባቸዉ ክፍለ ሀገሮች (አሁን ዞኖች) ሲሆኑ የግጥሙ መልዕክት በነዚህ የአማራ ክፍለ ሀገሮች መካከል መረዳዳት፣ መተጋገዝ፣ መተሳሰብ መኖሩንና ለአንድ አላማ በጋራ መቆማቸዉን ያመላክታል፡፡ ፋኖ በበኩሉ እንኳን ወገኖቹ አይዞህ እያሉት እንዳዉም አመጸኛ፣ ሐይለኛ፣ ለጠብና ለጦርነት የማይለስ መሆኑን የግጥሙ ይዘት ያስረዳል፡፡ የግጥሙ መልዕክት ዘመድ ቢረዳዳ ችጋርም አይጎዳ እንዲሉ አበዉ፣ የአማራ ሕዝብ መረዳዳት፣ መተጋገዝና መተባበር አለበት የሚል የቅስቀሳ ጭብጥ የያዘ ነዉ፡፡

5. *ምን ያደርጋል ጎመን ስጋ ሳይታጣ፣*

*ተሰቅሎ እያለልን ያምስት ዓመት ቋንጣ፡፡*

6. *ኧረ ተዉ ተረኛዉ ግፉ አይብዛ በቃ!!*

*ፀሀይ ትጠልቃለች እንኳንስ ጨረቃ፡፡*

*ከላይ በተራ ቁጥር አምስትና ስድስት ላይ የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች ከረር ያለ መልዕክት እና ጭብጥ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ የቋንቋ አቀራረባቸዉ በተምሳሌታዊ የትርጓሜ ስልት የተገለጹ ሲሆን ሕዝቡ ርካሽና በቀላሉ የሚገኘዉን ጎመን ሳይሆን ዉድና ዘወትር የማያገኘዉን ሥጋ እንደሚፈልግና የዚህም ትርጓሜ የተሻለ ለዉጥ መሻትን የሚጠቁም ነዉ፡፡ በተራ ቁጥር አምስት የተገለጸዉ ተፈላጊ ስጋ እና አምስት ዓመት የተሰቀለ ቋንጣ በሚል የተገለጸዉ አካል በከፍታ ላይ ያለ፣ ለአምስት ዓመታት በክብርና በማዕረግ የኖረዉ አካል መሆኑን ይጠቁማል፡፡*

*ይህ ማለት ደግሞ የቃል ግጥሙ ትኩረት ገዢዉ ፓርቲና በስልጣን ላይ ያለዉ መንግስት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በሕዝብና በመንግስት መካከል ቅራኔና ተቃርኖ እንዳለና ትግላቸዉ በሥርዓትና መንግስት ለዉጥ ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ያሥረዳል፡፡*

*ይህንን በግልጽ የሚያመለክተዉ ደግሞ በተራ ቁጥር ስድስት የተገለጸዉ **"ኧረ ተዉ ተረኛዉ ግፉ አይብዛ በቃ!!"** የሚለዉ የግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ ነዉ፡፡ በዚሁ ግጥም **"ፀሀይ ትጠልቃለች እንኳንስ ጨረቃ"** የሚለዉ የቤት መምቻ ስንኝ ደግሞ መንግስትና ገዢ ፓርቲ በሕዝብ ለአምስት አመታት ዉክልና የተሰጠዉ ጊዜያዊ፣ የዉክልና ተቀባይ ሕዝቡ ግን ቋሚና፣ ዉክልና ሰጪ መሆናቸዉን ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ሕዝቡ በሰጠዉ ሥልጣንና ኃላፊነት በታማኝነትና በእኩልነት ማገልገል እንዳለበት ካልሆነ ግን ዉክልናዉን ሊነሳዉ እምቢ ካለም በመፈንቅለ መንግስት ሥልጣኑን ሊነጥዉ እንደሚችል የሚያስጠነቅቅ ነዉ፡፡*

7. *ሞቅ በል! ሞቅ በል! ሞቅ በል! ቀዝቃዜ፣*

*ያአማራዉ ነፍጠኛ የአሳምነዉ ሚዜ፡፡*

8. *መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ?*

*ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ፡፡*

*ከላይ በተራ ቁጥር ሰባትና ስምንት የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች አሁን ያለዉን ችግርና ወቅቱ የሚጠይቀዉን ተግባር ያልተገነዘቡ የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸዉን*

ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም በነዚህ አቀንቃኞ አማካኝት በዚህ የቃል ግጥም ለነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ትግሉን እንዲቀላቀሉ የሚጋብዝ ቅስቀሳና የጥሪ ደወል ለማሰማት የቀረቡ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ በተራ ቁጥር ሰባት በተገለጸዉ ግጥም ትግሉን በከፊል የሚደግፉ፣ ግን በያዝ ለቀቅና በመወላወል ዉስጥ ያሉ አካላትን የሚመለከት ሲሆን በቁርጠኝነት እንዲታገሉ የሚቀሰቅስ ነዉ፡፡ ***"መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ"*** የሚለዉ ሃሳብ አንድም ተረኞችን ታግሎ በመጣል ሌላ ተረኛ የማንገስ፣ አንድም ደግሞ ከኋላ ተነስቶ ዘመናይ እንደሆነዉ አካል ከፊት ቀድሞ ዘመናይ ለመሆን የሚደረግ ትግል እና እሽቅድምድም አሁን ያለዉን አክሳሪ የፖለቲካ አዙሪት የሚጠቁም ነዉ፡፡

9. በታጣፊ ክላሽ ክንዱን ካልሰበሩት፣
   ጠላት መች ይተዋል በሥላሴ ቢሉት፡፡
10. በል ጠመንጃ ግዛ በሬህን ሽጥና፣
   መሬትህን በታንክ አርሰዉ‌ታልና፡፡
11. ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሐገርህ፣
   አረንዛዉ[10] ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር ዘጠኝ እስከ አስራ አንድ የቀረቡት ባለመንቶ ቃል ግጥሞች በምስጢር፣ በቅኔና በተምሳሌት የቀረቡ ሲሆን ሕዝቡ ለትግል እንዲነሳ የዘመቻ ጥሪና ቅስቀሳ የሚያደርጉ ናቸዉ፡፡ የሚደረገዉ ትግልም በሰላማዊ ሰልፍ፣ በዉይይትና በድርድር ሳይሆን በትጥቅ መሆኑን ***"በታጣፊ ክላሽ ክንዱን ካልሰበሩትና" "በል ጠመንጃ ግዛ በሬህን ሽጥና"*** የሚሉት በተራ ቁጥር ዘጠኝና አስር በቀረቡት ግጥሞች የመጀመሪያ ስንኞች ያረጋግጣሉ፡፡

የአማራ ሕዝብ ከሚከተለዉ እምነት (ፈሪሃ እግዚአብሔር)፣ ማህበረ ባህላዊ አቃፊነትና ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት መርህ የተነሳ ያሳየዉ ትዕግስትና ዝምታ እንደፈሪ እንዳሥቆጠረዉ ያምናል፡፡ ለዚህም ምክንያት ነዉ ሕዝቡ የአስተሳሰብና የድርጊት ለዉጥ እንዲያመጣና ሰዉን ማመን ቀብሮ የሚል አቋም እንዲይዝ

[10] **አረንዛ፡-** የሚለዉ ቃል ፍቺ፡- ውስጣ ውስጡ ረግረግነት የሚሰማው አረንዛ ውኀማ መሬት። አንድም ደግሞ ለጎርፍ የማይበገር ድንጋያማ ለምጣ መሬት ሲሆን ሕዝብ ሲመሰልበት የገባበትን ዉጦ የሚያሥቀር፣ ሀይለኛ፣ የማይበገር ጠንካራ፣ ማህበረሰብ፣ የሚል ፍች ይኖረዋል።

እየተቀሰቀሰ ያለዉ፡፡ ***"በታጣፊ ክላሽ ክንዱን ካልሰበሩት፣ ጠላት መች ይተዋል በሥላሴ ቢሉት"*** የሚለዉ ቃል ግጥም ከዚህ አስተሳሰብ ጋር ተመሳሳይ አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

***"በል ጠመንጃ ግዛ በሬህን ሽጥና"*** የሚለዉ ሀረግም አርሶ አደሩ በፍትህና በህግ የበላይነት ላይ ተስፋ መቁረጡንና መብቱን በትግል ለማስከበር ***"እጅን የሚያጣዉ እጅ ነዉ እንግዲህ"*** ብሎ መነሳቱን የሚጠቁም ነዉ፡፡ መሬትህን በታንክ አርሰዉታልና የሚለዉም የተስፋ መቁረጡ አመክንዮ መነሻና መድረሻ እንደሆነም ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር አስራ አንድ የቀረበዉ ***"ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሀገርህ፣ አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ"*** የሚለዉን ቃል ግጥም አንድምታ ስንመረምር የአማራዉ የእርስ በርስ ጦርነት ጎጃም ላይ ከማንም በላይ የበረታ መሆኑን፣ የጎጃም ሕዝብም የማይበገር አረንዛ መሆኑንና ለጦርነት ታጥቆ እንዲነሳ የሚቀሰቅስ፣ የሚያበረታታና የሚያነቃቃ ነዉ፡፡

በዚህ ግጥም በተምሳሌታዊ የቋንቋ አቀራረብ በጎርፍ የተመሰለዉ ነገር የማያባራዉ ተከታታይ ጦርነት፣ በአረንዛ ተመስሎ የቀረበዉ ደግሞ የጎጃም ሕዝብ ጀግንነት ነዉ፡፡ በግጥሞቹ ይዘት ሦሥቱም ቃል ግጥሞች ከመልካም አስተዳደር ችግር አልፎ የህልዉና አደጋ ገጥሞኛል ብሎ የሚያስበዉን የአማራ ሕዝብ ተነስ፣ ዝመት፣ ታጠቅ የሚል ቅስቀሳ  የሚያደርጉ መስለዉ ይታያሉ፡፡

12. ኧረ ተይ እናቴ ፈሪ አታርጊዉ ልቤን፣
 እቤት እንድቀመጥ አጣጥፌ ክንዴን፣
 ማን ባቀናዉ ሃገር ላሳድግ ነዉ ልጄን?

በዚህ ቃል ግጥም እናቶች ለልጆቻቸዉ ደህንነት የሚያስቡ መሆናቸዉንና ሀገር ሲወረር፣ ሉአላዊነት ሲደፈር ልጆቻቸዉን መርቀዉ የሚሸኙትን ያህል በእርስ በርስ ጦርነት እና የወንድማማቾችን መገዳደል ግራ መጋባት ያመላክታል፡፡ ይህም ከፍርሃት የመነጨ ሳይሆን ችግሩ በሰላማዊ መንገድ ይፈታል፣ ይህም ቢቀር በመንግስት አስተዋይት በእረቀ ሰላም ሊፈታ ይገባል ብለዉ ስለሚያስቡ ከንቱ መስዋዕትነት እንዳሆይን በመስጋት ይመስላል፡፡

ይሁን እንጂ ወጣቶች የተጀመረዉን ትግል አዝማሚያና የታጋዮቹን የመንፈስ ጥንካሬ ግምት ዉስጥ በማስገባት ትግሉ በፋኖዎች አሸናፊነት ቢጠናቀቅ ነገ ጠዋት አንገት ደፍተን እንኖራለን የሚል ስጋት እንዳላቸዉ ያመላክታል፡፡ አንድም ደግሞ

ማቄን ጨርቄን በሚል ሰበባ ሰበብ ከትግሉ ወደኋላ የምትሉ አካላት ነገ ጠዋት ማን ባቀናዉ ሃገር ልጆቻችሁን ልታሳድጉ ነዉ? የሚል ማስፈራሪያም ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም ሰዉ በተለይም ወጣቶች ለትግል እንዲሰለፉ ለመቀስቀስና ለማነቃቃት ለማስጠንቀቅም ጭምር የቀረበ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

13. ዝም ሲል አማራ የሌለ መስሏቸዉ፣
ትዕግስቱ ሲበዛ የፈራ መስሏቸዉ፣
ሰበርነዉ ያሉትን እዩት ሲሰብራቸዉ፡፡

ይህ ቃል ግጥም የአማራን ዝምታና ትዕግስት መብዛትና ከልክ ያለፈ ትዕግስት በተቀናቃኝ ሃይሎች እንዲናቅ፣ እንዲደፈርና እንደሌለ እንዲቆጠር አድርጎታል የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ በዚህም ጠላቶቹ እንዲዘምቱበትና በቀላሉም እናሸንፈዋለን ብለዉ እንዲያስቡ እንዳደረጋቸዉም ይጠቁማል፡፡ አማራን እንኳን የታጠቀዉን መሳሪያ የታጠቀዉን ሱሪ እናስፈታዋለን[11] የሚለዉ የጸጥታ ሃይሉ ማስጠንቀቂያም የዚህ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

"ክፉ ተጣሪ ክፉ ወይ ባይ ያመጣል" እንደሚባለዉ ያልተሰበሩትን "ተሰበርን" ያልሰበሩትንም "ሰበርን" የሚል ፕሮፓጋንዳ በሕዝቦች መካከል ዘላቂ ጥላቻ እንዲሰፍን፣ በሀገር ዉስጥም አለመረጋጋት እንዲፈጠርና አንዱ በሌላዉ ላይ እንዲነሳ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ በህልዉና ስጋት ዉስጥ ወድቀናል የሚሉ አካላት ተፈጥረዉ ከሰላማዊ ትግል ይልቅ የትጥቅ ትግልን በመምረጥ ዛሬ የሚታየዉን የማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት ያቀጣጠሉት፡፡

"ዉሻ በቀደደዉ ጅብ ይገባል" እንዲሉ በክልል አመራሮች የተሰበከዉ ***"የሰበርነዉ"*** የሴራ ፖለቲካና ርካሽ ፕሮፓጋንዳ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁን በክልሉ የተፈጠረዉን የእርስ በርስ ጦርነት ተከትሎ በአማራ ክልልም ተንጸባርቋል፡፡ ለዚህ ይመስላል በግጥሙ የመጨረሻ (ቤት መድፊያ) ስንኝ ላይ እንደሚታየዉ ***"ሰበርነዉ ያሉትን እዩት ሲሰብራቸዉ"*** የሚል አስተሳሰብ የተንጸባረቀዉ እና ቃል ግጥሙ በአደባባይ ለዚያዉም በሐገሪቱ መዲና የጸጥታ ኃይሉን ቁጥጥርና ክልከላ አምልጦ በጭፈራ ታጅቦ የተዘፈነዉ፡፡

14. ምነዉ በሰማይ ላይ እንዳሞራ ልጅ፣

---

[11] የጦር ሃይሎች ኢታማጆር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በቀን ለፋና ብሮድ ካስት ኮርፖሬት በወቅታዊ ጉዳይ ላይ የሰጡት ምላሽ እና ማብራሪያ ይህንኑ የሚያመላክት ነዉ፡፡

ወርደህ በጠብመንጃ ይለይልን እንጅ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በንጽጽራዊ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት የቀረበ ነዉ፡፡ ለንጽጽር የቀረቡትም የአሞራ ልጅና የአየር ሀይሉ የዉጊያ ቴክኖሎጂዎች ናቸዉ፡፡ የግጥሙ ይዘትም የመከላከያ ሀይሉ በድሮን፣ በሚግና በሄሊኮፕተር የሚያርገዉን ዉጊያ ተከትሎ ወንድ ከሆንክ በምድር ላይ በሚደረግ ትግል ወንድና ሴቱ  ለምን አይለይም የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ ይህም ቴክኖሎጂ እንጂ ሰራዊቱ አልተዋጋንም ለማለት የቀረበ ሲሆን የማህበራዊ ትስስር ገጾችና የዉጭ ሐገር ሚዲያች እንደዘገቡት ድሮን በሕዝቡ ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል የሚሉ አስተያየቶች ከየአቅጣጫ ይሰነዘራሉ፡

በዚህ ጉዳት ሰፊዉን ቁጥር የሚይዙት መሳሪያ ያልታጠቁ ንጹሃን ዜጎች ሲሆኑ አዛዉንቶች፣ ሴቶችና ሕፃናት እንደሆኑ የኢሰመኮ መግለጫ[12] ያመላክታል፡፡ ሕግን ለማስከበርና ሰላምን ለማስፈን እየታገልን ነዉ የሚሉት የመንግስት አካላት የሚሰጡት ምላሽ ግን የተገደሉት ያልታጠቁ ጽንፈኛ ሐይሎች ናቸዉ የሚል ነዉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከመንግሰት ጎን ተሰልፎ ፋኖን የማይዋጋ አማራ ሁሉ ፋኖ ነዉ ስለዚህ የሚሞተዉ ሰዉ ሁሉ ያልታጠቀ ፋኖ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የሚሞተዉን ያልታጠቀ ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ እንዲሄድና በዚህም ምክንያት ህዝቡ እየተማረረ ከፋኖ ጎን እንዲሰለፍ አድርጎታል የሚሉ አስተያየቶች ይደመጣሉ፡፡

15. አሻቅበህ በለዉ ሰማዩን በእንቧይ፣

ጊዜዉ ካልደረሰ ሰዉ ይሞታል ወይ?

ይሄኛዉ ቃላዊ ግጥም በአንድምታ ትርጉሙ ሕዝቡን ከኹለት ሃያላን የሰማይና የምድር ገዢዎች ጋር የሚያፋጥጥና የሚያጋጭ ነዉ፡፡ በአንድ በኩል  ወይ ፍረድ ወይ ዉረድ ብሎ ፈጣሪን የሚሞግትና የመፈታተን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡን ሰላምና መረጋጋት በሀገራችን በታሪካዊ አጋጣሚ ስልጣን እጃቸዉ ላይ የወደቀ መሪዎች ስልጣናቸዉን ለልማት፣ ለሰላምና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሳይሆን ለአፈናና ስልጣናቸዉን ለማስጠበቅ ይለገሉበታል፡፡ በዚህም ምክንያት ሕዝቡ በመንግስታቱ ላይ ቅሬታ ወቀሳና ጥላቻዉን ባገኘዉ አጋጣሚ ያንጸባርቃል፡፡ ስለሆነም ግጥሙ በተግባርም

[12] ኢሰመኮ ሰኞ ጥቅምት 19/ 2016 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ በአማራ ክልል በቀጠለው የትጥቅ ግጭት ምክንያት ግድያ እና መድፈርን ጨምሮ መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እየተፈጸሙ ነዉ።

በትጥቅ ትግል እስከመፈታተን የሚያደርስ የትግል ጥሪና ቅስቀሳን የሚሰብክና የሚያነሳሳ ነዉ ሊባል የሚችል ነዉ፡፡

በመሆኑም ሰዉ ቀኑ ካልደረሰ እንኳን መንግስት ፈጣሪ ሊገድለዉ እንደማይችል የተፈጥሮን ህግና አመክንዮ በማጣቀስ ግፋ በለዉ ሲል ታጋዮችን ያደፋፍራል፡፡ የሕዝቡን ፍላጎት ለማስፈጸምና ደህንነቱን ለማስጠበቅ መሟገት፣ መታገልና ለቆመለት አላማ በክብር መዉደቅን መርህ አድርጎ ደረቱን ለጦር እግሩን ለጠጠር ሰጥቶ እንዲነሳም ያሳስባል፡፡

16. ሳንጃዉን አግለህ ከቂጡ ለኩሰዉ፣

መቼም አይነሳ ወኔ የሌለዉ ሰዉ፡፡

ሕዝብ እና ሀገር ሲቸገሩ ሉአላዊነተታቸዉ ሲደፈር እኔን ያስቀድመኝ በሚል ወኔ ለሕዝባዊ ትግል ግንባር ቀደም ሆነዉ ለፍትህ፣ ለሰላም እና ለነጻነት በመታገል ህይታቸዉን ለመገበር ቆርጠዉ የተነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ግለሰቦች ይኖራሉ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ከሕዝቡ ፍላጎት በተጻራሪ የቆሙትን አካላት ደግፈዉ ከቆሙት ባሻገር በፍርሃት፣ በመደናገርም ሆነ በቸልተኝት ትግሉን ከዳር ቆመዉ ለመመልከት የተዘጋጁ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ታሪክ ምስክር ነዉ፡፡

ስለሆነም ጉዳዩን አሁን በሀገራችን የተፈጠሩትን የእርስ በርስ ጦርነቶች ተከትሎ ቃል ግጥሙ ሕዝቡ በሁለት ተከፍሎ ሁለቱን ተጻራሪ ኃይሎችን ደግፎ የሚቆምበትን አመለካከት እና ባህርይ በመቃወም እንደ ትግል መቀስቀሻ፣ የሕዝብ ማነሳሻ፣ ፈርተዉ ከዳር የቆሙትን አካላት ማስጠንቀቂያ ሆኖ የቀረበ ይመስላል፡፡ በዚህም በጥቂቶች መስዋዕትነት ጥቅማቸዉን ለማስከበር የሚፈልጉ ግለሰቦችን በማስፈራራት የህዝባዊ ትግሉ አካላት እንዲሆኑ የማድረግ አንድምታ ያለዉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በሀገራችን እንዲህ አይነት ችግርና አጋጣሚዎችን ተከትሎ የሚነገሩ ሌሎች ነባር ቃል ግጥችም የዚህ ሃሳብ ተጋሪዎች ሆነዉ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ለአብነትም "ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻዉ፣ አተላ መሸከም ይችላል ትከሻዉ" የሚለዉ ቃል ግጥም ፈሪ የተጫነበትን የጭቆና ቀንበር፣ መከራና ችግሩን ችሎ እደሚኖርና ጀግና የጭቆና ቀንበሩን ለመስበር አሻፈረን ብሎ ታግሎ እንደሚወድቅ የሚጠቁም ነዉ፡፡

17. አይዟችሁ ጋሞቼ[13] ሆዳችሁ አይባባ፣

ይጋጠም የለም ወይ ሰባትና ሰባ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በጦርነት፣ በጠብና በቡድን ግጥሚያዎች ወቅት የቡድኑን አባላትን ለማበረታታት፣ ለማጀገንና የፍርሃት ስሜት እንዳይሰማቸዉ ለማድረግ በባህላዊ ጭፈራ መልክ ለዘመናት ያገለገለና አሁንም እያገለገለ ያለ የሕዝብ ሥነቃላዊ ሀብት ነዉ፡፡ ቃል ግጥሙ በኹለት ቡድኖች ተጋጣሚ የቡድን አባላት መካከል የቁጥር አለመመጣጠን ሲኖር የሚዜምና ድል የሚገኘዉ በርትቶ በጀግንነት በመከላከልና በማጥቃት እንጂ በተጋጣሚ ቁጥር ብዛት አይደለም ጥቂት ሁነንም ማሸነፍ እንችላለን የሚል አንድምታ አለዉ፡፡

በቅርብ ጊዜም በአማራ ክልል ፋኖ የተደራጀ ኃይል ሆኖ ከመዉጣቱ በፊት ሕዝብ ተበደለ፣ ፍትህ ተጓደለ ብለዉ ለትግል የተሰለፉ ጥቂት ወጣቶች በትጥቅ ትግል ለመታገል የጀመሩትን እንቅስቃሴ አጠናክረዉ እንዲቀጥሉ ለማደፋፈር በሚችል መልኩ የቀረበ ነዉ፡፡ በነገራችን ላይ በሸዋ ፋኖ ዕዝ ስር ሰባት ለሰባ የሚባል ብርጌድ መኖሩ፣ ቀደም ሲልም ህወሓት ሰባት ሆነን ደደቢት በረሃ ተትግል ወጣን የሚለዉ ትርክትና በጎላዌ ዮሴፍ የተደረሰዉ የብአዴን መዝሙርም[14] ይህንኑ ማህበራዊ ዕሴት እና ታሪካዊ ዳራ የሚያመላክቱ ናቸዉ፡፡

18. ጃሎ[15] መንገዱን እስኪ አለስልሰዉ፣

ቀድሞ ይመጣል ያልሞተ ሰዉ፡፡

የግጥሙ የቋንቋ አቀራረብ ተምሳሌታዊ በመሆኑ በሁለት መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡፡ በመጀመሪያ መንገዱ ይጠረግ፣ ጥርጊያዉ ይቅና ከዚያ ለነዋሪዎች ምቹ ጎዳና (ሐገር) ይፈጠራል የሚል ትርጓሜ በአንድ በኩል ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የትግል

---

[13] ጋሞቼ ፡- የሚለዉ ቃል ጥሬ ትርጉሙ ልጆች፣ ጓደኞቼ፣ ወጣቶች የሚለዉን የሚያመላክት ነዉ፡፡ ጋሜ ከጸጉር አለጫጨት ጋር የተያያዘ ስያሜና አጠራር ነዉ፡፡ የአንበሳ ጋማ እንዲሉ:: መሃሉን ተላጭቶ ዳድዳሩ ያደገ ጸጉር ያለዉ ልጅ፣ አሽከር ማለት ነዉ፡፡ ጸጉሩ ሲያድግ ይጎነጎናል፡፡ ይህም የጀግንነት መገለጫ ይሆናል፡፡ አያችሁት ቢያ ይህንን እብድ፣ ሁለት ጋሜ ሆኖ ጉራምባ ሲወርድ ተብሎ ለዳግማዊ ዓጼ ቴወድሮስ እንደተዘፈነ ልብ ይሏል፡፡

[14] ጎላዌ ዮሴፍ መስከረም 1975 ዓ.ም ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነዉ፣ ነገ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነዉ፡፡

[15] ጃሎ የሚለዉ ቃል በስም ምትክ የሚገባ፣ ልጅ የሚለዉን ቃል የሚወክልና ጦረኛ፣ አርበኛ፣ ጀግና የሀገሩን ድንበርና ሕዝቡን የሚጠብቅ ህዝቡም በተስፋ የሚጠብቀዉ ወጣት ነዉ፡፡

መስመሩ ይዘርጋ ከዚያ በኋላ ሕዝቡን ሊያደራጅና ሊመራ የሚችል ጀግና መሪ ሊፈጠር፣ ወይም ካለበት ቦታ ሊመጣ ይችላል የሚል አንድምታና ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

አማራ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በደቡብ ክልሎች እንዲሁም በራሳችን ክልል በሴራ ፖለቲካ እየተሳደድንና እየተጨፈጨፍን እንገኛለን የሚታደገንም አካል አላገኘንም የሚል ቅሬታ አለዉ፡፡ ስለሆነም ሕዝቡ በመንግስት እና በሕግ አስከባሪዎች ላይ ያለዉ እምነትና ተስፋ እየተሸረሸረ እንደሆነም ይገልጻል፡፡ በዚህም ምክንያ ቃል ግጥሙ ጀግኖች ከመካከላችን ተነስተዉ መንገዱን ያስተካክሉልናል፣ መሰናክሉን አስወግደዉ መስመሩን ይዘረጉልናል ከጥቃትና ጥፋት ይታደጉናል ብሎ እንደሚጠብቅም ያመለክታል፡፡

19. ዘንድሮ ጉልበቴ ዉለታ ዋለልኝ፣
 አንገቴን ስደፋ ቀና አደረገልኝ፡፡

ይህ የመጨረሻዉ የቅስቀሳ እና ማነቃቂያ ቃል ግጥም ወቅታዊ ሁኔታና የኅብረተሰቡን ንቃተ ህሊና ፍላጎትና ዉስጣዊ ስሜት የሚጠቁም ነዉ፡፡ ሕዝብ ታግሶ፣ ችሎ መክሮ ዘክሮ የሚሰማዉ ሲያጣ ቅሬታና ተቃዉሞ ያሰማል፣ ተስፋ ሲቆርጥ ግን መናገር ያቆማል፣ ልቡ ይሸፍታል፣ የሰላሙን መንገድ ትቶ የኃይል እርምጃ ዉስጥ ይገባል፡፡ በቃል ግጥሙ የታየዉ ጭብጥም ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ አንገቱን ሲደፋ በጉልበቱ ታግሎ ለማሸነፍ መነሳቱንና በድል ጎዳና ለመራማድ ጉልበቱ፣ ጀግንነትና ክንዱ እንደጠቀመዉ ያረጋግጣል፡፡

ሕዝብ ዝም ሲል ጠቢባን ይናገራሉ፡፡ ገጣሚዎች ደግሞ ጠቢባን ናቸዉ፡፡ በተለይም የቃል ግጥም አቀንቃኞች የሕዝቡን ስሜት መከራና ስቃይ በግጥማቸዉ ይናገራሉ፡፡ ለህሊናቸዉና ሕዝብ ለጣለባቸዉ አደራና እምነት ኃላፊነታቸዉን ይወጣሉ፡፡ የግላቸዉን እምነትና ስሜት ሳይሆን የሀገርና የሕዝብ ድምጽ ሆነዉ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞችን በዜማና በጭፈራ አለዝበዉ ሕዝብ በተሰበሰበባቸዉ የክወና አጋጣሚዎች ሁሉ በመገኘት ሕዝብንም መንግስትንም ያስጠነቅቃሉ፤ ይወቅሳሉ፤ እንደ እረኞች[16]፣ እንደ አዝማሪዎችና እንደ

16. በድሮ ጊዜ ‹‹እረኛ ምን አለ?›› ይባል ነበር አሉ። ይህን የሚለው መንግሥት ነው፡፡ በተለይም በነገሥታቱ ዘመን ልክ ዛሬ ‹‹ዓለም እንዴት አደረች›› ተብሎ የበይነ መረብ መረጃዎችን እንደሚዳሰሰው በጥንቱ ዘመን የመረጃ ምንጬ እረኞች ነበሩ። እረኛ ምን አለ? የሚባለው በሕዝቡ ውስጥ የነበረውን ስሜት ለማወቅ ነው፡፡እረኛ በተለየ የሚፈለግበት ምክንያት ልጆች ስለሆኑ ክፉ ደጉን ለይተው አያውቁም፤ ቤት ውስጥ ወላጆች በምሥጢር ያወሩትን ነገር በአደባባይ ሊያወጡት ይችላሉ። በድሮው ጊዜ የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች ስለሌሉ መንግሥት

አዋቂዎች መካሪ ዘካሪነት ሚናቸዉን ይወጣሉ፡፡ ስለሆነም የቃል ግጥሙ አስተምህሮ ሕዝብ ታግሶ፣ ችሎ መክሮ ዘክሮ የሚሰማዉ ሲያጣ ቅሬታና ተቃዉሞ ከማሰማት ባሻገር ከመሪዎቹ ተስፋ በመቁረጥ የሰላሙን መንገድ ትቶ የኃይል መንገድን መከተል እንዳለበት በመጠቆም እንደ ቅስቀሳና ማነቃቂያ ሆኖ የቀረበ ነዉ፡፡

### 4.2.4. ባህልና ማህበራዊ ጉዳዮችን የማጠናከር ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



*በ2016 ዓ.ም በካራ አርሴማ ጥምቀተ ባሕር በባህላዊ አለባበስ የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት*

የቃል ግጥሞች በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡ የሥነቃል ዓይነቶች ሲሆኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ስነልቡናዊ ሁኑቶች የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ቃልግጥም የማህበረሰብ ክፍል (በሰለጠነዉም ሆነ ባልሰለጠነዉም) ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን በድሮም ሆነ በአሁን ጊዜ የማህበረሰቡን ማንነት በማሳየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት የጥበብ አይነት ነዉ፡፡ የቃል ግጥም የማህበረሰቡን ባህል መሰረት በማድረግ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በግለሰብም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴዉ ወቅት የሚያስተውላቸውን ገጠመኞች፣ ከተፈጥሮ ጋር ባለዉ ግንኙነት ምክንያት የሚከሰቱ ገጠመኞችን፣ ያለውን ፍልስፍና፣ ዕዉቀት፣

[16] የሚወቀሰው በእሳት ዳር ጨዋታ ነው። ሰዎች ቤት ውስጥ ብሶታቸውን ሲያወሩ ልጆች ይሰማሉ፤ ያንን በእረኝነት ወሏቸው በእንጉርጉሮ ይናገሩታል። እረኛ ምን አለ የሚባለው ለዚህ ነው።

አስተሳሰብ ወ.ዘ.ተ በቃል ግጥሙ አማካኝነት ለትዉልድ ያስተላልፋል፤ በወቅቱ የተሰማውንም ስሜት ይገልጽበታል፡፡ (ሰለሞን፣ 2011፣ 129

ሥለሆነም በዚህ አራተኛ ዐብይ ክፍል ተሰብስበዉ የተተነተኑ ቃል ግጥሞች የሕዝቡን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳዮችን ለአብነትም ጀግንነትና ኩራቱን፣ ሰዉ አማኝና ታጋሽነቱን አዛኝና ርኅሩህነቱን የማወደስና የማሞገስ ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩልም እነዚህን የማህበረሰቡን ማህበረ ባህላዊ እሴቶችን የሚጻረሩ ድርጊት፣ አመለካከትና ይህንን የሚያደርጉ አካላትን የሚቃወሙና የሚያወግዙ ጭምር ናቸዉ፡፡

1. ሀገሬ ላይ ሁኜ ናፈቀኝ ሀገሬ፣
   ከማን ጋር ይዋላል ሁሉም ሆኗል አዉሬ፡፡
2. አትግፋኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ፣
   እንኳን የሰዉ ሀገር የኔንም ትቻለሁ፡፡

ኢትዮጵያዉያን የምንታወቅበት እና ከሌላዉ ዓለም የሚለየን ዉድና ብርቅ እሴታችን፣ እንግዳ ተቀባይነታችን፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ የመከባበር፣ አብሮ የመስራት እና አብሮ የመብላት ባህልና በአጠቃላይም ማህበራዊ ኑሯችን ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ህወሓት ኢህአዴግ በተከለዉ የዘዉግ ፖለቲካና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዉያን ይህንን ብርቅና ድንቅ እሴታችን ጥለን የማናዉቀዉን በመናፈቅ አንዳችን ሌላችንን በመግፋትና በመገፋፋት ሁላችንም እየተጎዳን እንገኛለን፡፡

ስለሆነም ለዘመናት ተዋዶና ተላምዶ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ፣ ተከባብሮና ተጣጥሞ አንድነትና ህብረቱን አጠናክሮ የኖረዉ ሕዝባችን “መጤና ሰፋሪ” “ባይተዋርና ተስፋፊ” በመባባል ሀብትና ንብረቱ እየወደመ፣ ካንዱ አካባቢ ወደአንዱ እየተሳደደ፣ እንዲኖርና አንዱ ሌላዉን እንዲጠላና እንዲጠራጠር የሚያደርግ የፖለቲካ ሸፍጥ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ይህ ቃል ግጥም ይህንን ለማመላከት በፍቅር፣ በደስታ፣ በመቻቻል እና በመከባበር የኖረባት ሀገሩን እንደወትሮዋ ሆና አለማግኘቱንና ሰዉ በጭካኔ አንዱ ሌላዉን ከማሳደድም አልፎ መግደል መጀመሩን ለማመላከት ከማን ጋር ይኖራል ሁሉም ሁኗል አዉሬ እና አትግፋኝ ወንድሜ ግፊ ጠልቻለሁ ሲል የሰዉን ክፋትና የነገሰብንን የመገፋፋት የሴራ ፖለቲካ አስከፊነትና የማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችንን መሸርሸር አመላክቶናል፡፡

3. እንብላ እንጠጣ ነዉ ለመጣ ለሄደዉ፣

ራያ ምድር ላይ ሰዉ መሆን በቂ ነዉ፡፡

ኢትዮጵያዉያን የምንታወቅበትና ከሌላዉ ዓለም የሚለየን ዉድና ብርቅ እሴታችን እንግዳ ተቀባይነታችን፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ የመከባበር፣ አብሮ የመስራት እና አብሮ የመብላት ባህልና በአጠቃላይም ማህበራዊ ኑሯችን ነዉ፡፡ ይህ ብርቅና ድንቅ ባህልና ዕሴታችን በፖለቲከኞች አስተሳሰብ እየተበረዘና እንደነዉር እየተቆጠረ መጥቷል፡፡ የሕዝቡን ባህልና ዕሴት፣ ቋንቋና ብሔረሰባዊ ማንነት መከለያና የግል ጥቅም ማስጠበቂያ እና የወንጀለኞች መደበቂያ ሆኖ እያገለገለ ከመደብዘዝ አልፎ እየጠፋም ይገኛል፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ለማስተላለፍ የተሞከረዉ መልዕክት እየደበዘዘና እየጠፋ የመጣዉን ባህልና ማህበራዊ ኑሯችንን ዛሬም የራያና ቆቦ ህዝብ ጠብቆት እየኖረ መሆኑን ማመላከት ነዉ፡፡ ወደራያ የመጣና የሄደዉን እንግዳ ሁሉ ዘር፣ ቀለም፣ ማንነትና መተዋወቅን ሳይጠይቅ ሲያበላና አብሮ ሲበላ የኖረና እየኖረ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ በራያ ሕዝብ እና ምድር ላይ አብሮ ለመብላትና ለመጠጣት፣ እንደሰዉ ለመከባበርና ለመረዳዳት ሰዉ መሆን ብቻ በቂ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡

ስለሆነም የራያ ሕዝብ ይህንን ባህሉን ጠብቆ እየኖና ሌሎችም እንዲማሩት በዚህ ቃል ግጥም በየዓመቱ በራያ ባህል ልብሳቸዉ ደምቀዉ በዓሉንም በሚያደምቁት ወጣቶች አዲስ አበባ ከተማ የጥምቀት በዓል ላይ ግዝፈት ነስቶ እየተዜመ ምልአተ ህዝቡን ሲያሥደምምና መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ዉሏል፡፡

4. እኔስ አራሽ ነበርኩ የገበሬ ልጅ፣

   ሰርቼ እንዳልበላ አደረጉኝ እንጂ፡፡

5. አዲስ አበባ ላይ ቁና ጤፍ አይገኝ፣

   ርሽርሹ ጎጃም ካንተ በፊት ያርገኝ፡፡

6. ሞፈሩን ቀንበሩን ክተቱት በጎታ፣

   እናርስበታለን ቀን የወጣ ለታ፡፡

7. ከዘንድሮዉ ችግር የከርሞዉ ይብሳል፣

   በሮቻችን ሞተዉ በምን ይታረሳል?

ከላይ ከተራ ቁጥር አምስት እስከ ሰባት የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች የአርሶ አደሩን ህይወትና በወቅቱ ሰርቶ ለመብላት የገጠመዉን ችግርና መሰናክል እንዲሁም

የተሰማዉን ስሜትና መሰናክለል ሆኖብኛ በሚለዉ አካል ላይ የወሰደዉን አቋም የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡ አርሶ አደሩ በተለይም የጎጃም አርሶ አደር፣ አርሶ አንደፋርሶ ማኛ ጤፉን እያመረተ ከራሱና ከቤተሰቡም አልፎ ለከተማዉ ህዝብ ምርቱን በሽያጭ ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ በአማራ ክልል በተፈጠረዉ የርስ በርስ ግጭትና ጦርነት አርሶ አደሩ እንኳን ለሌላዉ የሚሸጠዉ ለራሱም አምርቶ ለመብላት እንደተቸገረ ቃል ግጥሞቹ ይጠቁማሉ፡፡ አርሶ አደሩ ሰርቶ እንዳይበላ ፍርሃት፣ ስጋትና እንዲያም ሲል ጥቃት እየደሰረሰበት መሆኑን ለመጠቆም ***"ሞፈሩን ቀንበሩን ከተቱት በጎታ እናርስበታለን ቀን የወጣለታ"*** በማለት ከእርሻ ስራ መፋታቱን ይገልጻል፡፡

ይህንንም ተከትሎ አዲስ አበባ ከተማ ላይ በዚህ አመት የምርት እጥረት እና የዋጋ ግሽበት በሰፊዉ በመከሰቱ የከተማዉ ህዝብ እየተቸገረ፣ ዘመኑን፣ መንግስት እና አመራሩን እያማረረ ይገኛል፡፡ ***"ከዘንድሮዉ ችግር የከርሞዉ ይብሳል፣ በሮቻችን ሙተዉ በምን ይታረሳል"*** የሚለዉ ቃል ግጥም አርሶ አደሩ ሰላምና መረጋጋት ተፈጥሮለት ማረስ ካለመቻሉም ባሻገር በአማራ ክልል በፋኖና በመከላከያ ሰራዊቱ መካከል እየተደረገ ባለዉ ጦርነት አርሶ አደሩ እርፍ እንደጨበጠ፣ በሮቹ በቀንበር እንደታነቁ በድሮን እየደተገደሉ በመሆኑ ችግሩ ቀጣይና እንደሚሆንና ከወዲሁ እንደ ሀገር፣ እንደ መንግስትና እንደ ሕዝብ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ ካልሆነ ግን የጎጃም ችግር የመላዉ ኢትዮጵያ ችግር ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

በተለይ ***"አዲስ አበባ ላይ ቁና ጤፍ አይገኝ፣ ርሽርሹ ጎጃም ካንተ በፊት ያርገኝ"*** የሚለዉ ባለሁለት ስንኝ ቃል ግጥም ከዚህ ቀደም ጌቴ ገላዬ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ምሁር፣ የጥናቱ ርዕስም ***"ከ1983 የመንግሥት ለውጥ በኋላ የምሥራቅ ጎጃም ገበሬዎች የገጠሟቸው ፖለቲካዊ ግጥሞች"*** በሚለዉ ጥናት ዉስጥ የጎጃም አርሶ አደር ስለራሱ ችግር ለራሱ የገጠመዉ ነዉ በሚል ጥሩ ትንታኔ ሰጥዉበት ተመልክቻለሁ፡፡

ይሁን እንጂ ግጥሙ ከጎጃም ይልቅ አዲስ አበባ ላይ ያለ ሰዉ ስለራሱ ቢያዜመዉ የተሻለ ትርጉም ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም የአዲስ አበባ ሕዝብ ሸምቶ እንጂ አርሶ እንደማይበላ ስለሚታወቅ የምርቱ ባለቤት የሆነዉ የጎጃም አርሶ አደር ተቸግሮ እኛም ከምንቸገር ከርሱ በፊት እኛን ያሥቀድመን፣ ብሎ ቢዘፍን ተአማኒነቱ የጎላ ስለሚሆን ነዉ፡፡ ስለሆነም የግጥሙ ጭብጥ ጎጃምን ፈጣሪም ከክፉ ይጠብቀዉ፣ መንግስትም እጁን

ያንሳለት፣ የጎጃም ችግር የአዲስ አበባም ችግር ነዉና አዲስ አበባ እንዳይቸገር ጎጃም ክፉ አይንካዉ የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

8. ሲቀር ይቀራል፣ ሲቀር ይቀራል፣
በሽገር ዳቦ ማን ይፎገራል፡፡

ከላይ በተጠቀሰዉ ቃል ግጥም ለአዲስ አበቤ በአዲስ አበቤዎች የቀረበና በተለይም የከተማ አስተዳደሩ ህዝቡን ለመደለል የሞከረበትን የዳቦ ፖለቲካ በህዝብ ላይ መሳለቂያ መሆኑን የሚጠቁም ነዉ፡፡ እደሚታወቀዉ የኑሮ ዉድነቱ ምርትን ከክልሎች ወደአዲስ አበባ ለማስገባት ባለመቻሉ፣ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በቂ ምርት ባለመመረቱ በተፈጠረ የምርት እጥረት እና ከተጠቃሚ መብዛት ጋር ተያይዞ የዳቦ ዋጋ ጨምሯል፡፡

ይህንን ችግር ለመፍታትም ከተማ አስተዳደሩ ሸገር ዳቦ አምርቼ በቀላል ዋጋ አከፋፍላለሁ በሚል ስራ ማስጀመሩ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ዳቦዉ ጥራት የሌለዉ ከመሆኑም ባሻገር በበቂ ሁኔታ እየቀረበ አለመሆኑና በሂደትም አቅርቦቱ ተቋርጧል፡፡ ችግራችንን እና ደካማ ጎናችንን አስባችሁ መሰረታዊ መብትና ፍላጎታችን ሳይሟላ በሽገር ዳቦ አፋችንን ለመያዝ የሚደረገዉ ሙከራ ተገቢ አይደለም ለማለት ይመስላል ***"ሲቀር ይቀራል፣ ሲቀር ይቀራል፣ በሸገር ዳቦ ማን ይፎገራል"*** የሚለዉን ቃል ግጥም የተዜመዉ፡፡

9. በጸጥታ ኃይሉ እግድ ነበረብኝ፣
በቄስ በቃልቻ ዉግዘት ነበረብኝ፣
እንጎራጉራለሁ እየጎደለብኝ፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ሊተላለፍ የተፈለገዉ ሃሳብና ቁምነገር ግጥምና ዜማ ደርሰዉ፣ ከማህበረሰቡ በትዉልድ ቅብብሎሽ የወረሱትን ግጥም ይዘዉ፣ ለመዝፈንና ለመጨፈር ቀን ቆጥረዉ አመት አስበዉ በጥምቀት በዓል ላይ በመገኘት በዓሉን ለማድመቅና ሃሳብና ስሜታቸዉን ለመሰሎቻቸዉ ለማካፈል የሚመጡትን ወጣቶች ይህንኑ ወቅታዊ ስሜት የሚያመላክት ነዉ፡፡

በጥምቀት በዓል አከባበር ላይ የጸጥታ ኃይሉ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸዉ አጋጣሚዎች ሁሉ ላይ በመገኘት የተቃዉሞና ነቀፌታ ግጥም ያላቸዉ ዘፈንና ጭራዎችን እና መፈክሮችን ያስቆማሉ፣ ጨፋሪዎችንም ያባርራሉ፡፡ ከዚያም አልፎ ወጣቶችን በጅምላ አፍሰዉ ወደእስር ቤት ይወስዳሉ ከእስር ሲፈቱም በመሰል ቦታና አጋጣሚ ላይ

እንዳይገኙ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፡፡ ለአብነትም በዚህ ዓመት የዘንድሮው የጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ከፀጥታ ኃይል ባሻገር ወጣቶች ተደራጅተው እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በንቃት እንዲከታተሉ የሚል መግለጫ[17] ከበዓሉ ቀደም ብሎ ተላልፎ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ብቻ በዚህ ዓመት መሰል ነገሮችን እየተከታተሉ ለጸጥታ ኃይሉ የሚጠቁሙ፣ የሚያሥተባብሩ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር 15 ሺሕ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ዝግጁ መሆናቸው ተነግሯል።

በሌላም በኩል በወጣቶች ላይ የሚደርሰዉን እስር፣ መንገላታትና መስዋዕነት ቤተሰብ ሽማግሌዎችና ካህናት ጭምር እባካችሁ መንግስትና የጸጥታ ኃይሉን አትዳፈሩ ካልሆነ መጨፈሩ ይቅርባችሁ የሚል ምክር ይሰጧቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቃል ግጥሙ እንደተጠቀሰዉ አቀንቃኞቹ ሕዝብ ተበደለ ፍትህ ተጓደለ የሚል ጩኸታቸዉን አጠናክረዉ ቀጥለዋል፡፡ ***"በጸጥታ ኃይሉ እግድ ነበረብኝ፣ በቄስ በቃልቻ ዉግዘት ነበረብኝ፣ እንጎራጉራለሁ እየጎደለብኝ"*** የሚለዉ ቃል ግጥምም ይህንኑ የጸጥታ ኃይሉን እግድ፣ የሃይማኖት አባቶችን ዉግዘት እና የወጣቶቹን እምቢተኝነት የሚያመላክት ነዉ፡፡

10. እንኳን አማርኛ ይናገር ትግርኛ፣
    ክፉ ሀሳቡን ነዉ የጠላነዉ እኛ፡፡

የዚህኛዉ ቃላዊ ግጥም ይዘትና ዋና መልዕክት አንድ ሰዉ ሊወደድና ሊጠላ የሚገባዉ በክልል፣ በቋንቋ እና በብሔረሰብ ማንነቱ ሳይሆን በአስተሳሰቡ፣ በአመለካከቱ፣ እና በስራዉ ፍሬ፣ መሆን አለበት የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ ቃል ግጥሙ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በተከሰተዉ ጦርነት የተፈጠረዉን ቅራኔ ተከትሎ "የአማራ ጠላት ትግሬ" "የትግሬ ጠላት አማራ ነዉ" የሚለዉ አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ትግርኛ እየተናገረ ለትግሬ፣ አማርኛ እየተናገረ ለአማራ ጥሩ የማያስብ ሰዉ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህም የሰዉ ልጅ ሊወደድና ሊጠላ የሚገባዉ በማንነቱ ሳይሆን በአስተሳሰቡና በተግባሩ መሆን እንዳለበት የሚጠቁም ነዉ፡፡

---

[17] አዲስ አበባ፣ ጥር 8፣ 2016 (ኤፍ ቢ ሲ) የ2016 ዓ.ም የከተራና ጥምቀት በዓል በሰላም እንዲከበር ዕቅድ አውጥቶ ወደ ሥራ መግባቱን በሚመለከት የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል የሰጠዉ መግለጫ።

ስለሆነም በሕዝቦች መካከል መለያየትና ጥላቻን የሚሰብኩ አስተሳሰቦችን ከማቀንቀን ይልቅ የጋራ የሚያርጋቸዉን ባህል፣ እምነት፣ ታሪክና ጉርብትና መሰረት በማድረግ ፍቅር፣ ሰላምና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚሰብኩ አስተሳሰቦችን ማስተጋባት እንደሚገባም ያስረዳል፡፡ ከዚህም ባለፈ ክፉ አስተሳሰባቸዉን፣ አሰራርና አቋማቸዉን እንጂ የሰዉ ልጆችን መጥላት እንደማይገባም፤ አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ እንዳይሆን ፖለቲከኞች የጠነሰሱትን ጥፋት አጀንዳ ለሕዝብ እልቂትና ዘላቂ ጥላቻ መነሻ እንዳይሆን በማስተዋል መራመድ እንደሚገባን የሚጠቁም ነዉ፡፡

11. እኔ የራያን ልጅ አያሰማኝ ክፉ፣

እንኳንስ ልጆቹ አይቆረጥ ዛፉ፡፡

ተፈጥሮ ለሰዉ ልጅ የህልዉናዉ ምስጢርና የኑባሬዉ መሰረታዊ ምንጭ ነዉ፡፡ ስለሆነም የተፈጥሮ ዋነኛ መገለጫ የሆኑት ዛፎች በሌሉበት የሰዎች መኖር ሊታሰብ አይችልምና በቃል ግጥሙ እንኳንስ ሰዎቹ ዛፎችም አይቆረጡ ሲል ለሰላምና ለፍትህ የቆመ ሰዉ እንኳን ለሰዉ ለእጽዋትም እንደሚጨነቅ ለማሳየት የተሞከረበት ነዉ፡፡

የራያ ምድር ወቅት እና ዘመን ሲሰጠዉ የተትረፈረፈ ምርት የሚመረትበት አካባቢ የመሆኑን ያህል ድርቅ ሽዉ ሲልበት ደግሞ የተዘራዉ ደርቆ፣ ለምለሙ ገርጥቶ ህዝቡን ለስደት እና ለስቃይ የሚዳርግ አካባቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም ግጥሙ ለራያ ሕዝብና ተፈጥሮ ሰላምና ደህንነትን የሚመኝ፣ የተቆርቋሪነትና ህዝባዊ ወገንተኝነት ማሳያ፣ የወገኑንና የተፈጥሮን ክፉ የሚጠላና ከጦርነት፣ ከድርቅ እና ከመልካም አስተዳደር ችግሮች ጋር በተያያዘ ያሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉና ሕዝቡ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፣ ሰርቶ እንዲበላ የሚመኝ ነዉ፡፡

12. እባብ ሰለክላኬ መንታ ነዉ ምላሱ ፣

ሲያምኑት የከዳ ሰዉ አይማርም ነፍሱ፡፡

እባብ በተፈጥሮዉ በልቡ ተኝቶ እየተሳበና እየተንሻለለ የሚሄድ አስፈሪ እንሰሳ ከመሆኑም ባሻገር በፈሊጣዊ ትርጉሙ መርዘኛ፣ የተንኮል፣ የክፋትና የምቀኝት ተምሳሌትነት ያለዉ እንስሳ ነዉ፡፡ በቃል ግጥሙ የተጠቀሰዉ መንታ ምላሱም የማይታመን፣ በቃሉ የማይፀና ከሃዲ ሰዉ መገለጫ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ስለሆነም ይህ በእባብ ተምሳሌትነት የተቀነቀነ ቃላዊ ግጥም በአማርኛ ቃላዊ ግጥሞች ዉስጥ የተለመደና ለዘመናት በግድግዳ ላይ ለሚለጠፍ ጥቅስ፣ ለወሬ ማሳመሪያ እና ለዘፈን

ማድመቂያ በመሆን በሰፊዉ ያገለገለ ነዉ፡፡ በዚህ የጥምቀት በዓል ከበራና የክወና አጋጣሚ ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተገናኜ የለዉጡ አመራሮች ወደስልጣን ሲመጡ የነበራቸዉን እና አሁን ያላቸዉን አስተሳሰብ እና የድርጊት ልዩነት ታሳቢ በማድረግ የተዜመ ይመስላል፡፡

ይህንን ቃል ግጥም ከወቅታዊ ፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ የተኮረ የዘመኑ አመራሮች መገለጫ ስለመሆኑ በዚሁ መድረክ ላይ ***"ይነጋል ባልነዉ ቀን ጨለማ ነገሰ፣ ኑሮ ተወደደ ሰዉ እየረከሰ"*** በሚል ከቀረበዉ ተመሳሳይ ትርጓሜና ፋይዳ ካለዉ ቃል ግጥም ጋር አዛምዶ ማየት ይገባል፡፡ በመሆኑም ቃል ግጥሙ አመራሮቹ በጊዜዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በማቀንቀናቸዉ ሕዝቡ እንዳመናቸዉና በሂደት ሕዝቡ በጠበቃቸዉ እና ባመናቸዉ ልክ ስላላገኛቸዉ ሕዝቡ የመከዳት ስሜት እንዳደረበት፣ ለነርሱ የነበረዉ እምነት እንደተሟጠጠ እና ተስፋና እምነቱን ለፈጣሪ እየደሰጠ መሂዱን የሚያመላክት ነዉ፡፡

13. ወሎ ራሱን ታሞ ተኝቷል ከቤት፣
ከጋራዉ ላይ ወጥተህ ሞረሽ[18] በልለት፣
ያገኝለት እንደሁ ጎጃም መድሃኒት፡፡

ይህ ቃል ግጥም በአንድ በኩል ህወሓቶች ዳግም የአማራ ክልል በተለይም ወሎን በዋናነትም ራያን ለመቆጣጠር ያደርጉትን በትጥቅ ትግል የተደገፈ ወረራ ለመመከት የቀረበ የድረሱልን ጥሪ ይመስላል፡፡ አንድም ደግሞ ድፍን ወሎን ለመዋጥ የሚደረገዉ በፖለቲካ ሴራ የተሸረበ እንቅስቃሴ ለሌላዉም የሚተርፍ ነዉና በጋራ እንታገለዉ የሚል አንድምታ ያለዉ ለመላዉ አማራ የቀረበ ወገናዊ ጥሪ በመሆኑ ከጋራዉ ላይ ወጥታችሁ ሞረሽ ብላችሁ ለወገኑ ንገሩለት ምናልባትም የጎጃም ፋኖዎች ከጎኑ ቆመዉ ችግሩን ለመፍታት እንዲያግዙት፣ ከስጋቱ ነጻ እንዲያደርጉትና አለንልህ እንዲሉት የቀረበ የአጋርነት ጥያቄ ነዉ፡፡ በእርጥም በዚያ አስከፊ ወቅት ለወሎ ቀድሞ የደረሰዉ ጎጃም እንደነበረም መዘንጋት የለበትም፡፡

---

[18] ሞረሽ፡- የስም ምትክ፣ ስምን ወክሎ የሚገባ ህቡዕ መጠሪያ ነዉ። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አንድ ሰዉ በጨለማ፣ በዝናብና በአደጋ አጋጣሚ ዉስጥ ሲጠፋ በስሙ ቢጠራ ጠላት ወይም ሊያጠቃ የሚፈልግ ሰዉ ስሙን አዉቆ እንዳይከተለዉና እንዳያገኘዉ በዚህ ህቡዕ መጠሪያዉ ስም በሚፈልጉት ወገኖቹ ተራራ ላይ በመቆም ሞረሽ እየተባለ ይጠራል።

በሌላም በኩል “ወገን ቢረዳዳ ችግርም አይጎዳ” እንደተባለዉ፣ ሁሉም ነግ በኔ ብሎ እንዲነሳና በአንድነት፣ በመተባበር፣ በመተጋገዝና ለጋራ አላማና ግብ፣ ለጋራ ጥቅምና ስኬት በጋራ መቆም፣ እንደሚገባ ያስረዳል፡፡ በአንዱ ላይ የተከሰተ ችግር ለሌላዉም የሚቀር አይደለምና የወገንን የስቃይ ድምጽ ማድመጥ፣ ህመሙን፣ ችግርና ስቃዩን መጋራት እና ለደህንነቱ ሁሉም የድርሻዉን መወጣት እንዳለበት የሚጠቁምና የሚያስረዳ ቃል ግጥም ነዉ፡፡

14. ከፍ አረገኝ ብሎ ጊዜ እንደተራራ፣

ልርገጥህ አይልም ወንድሙን አማራ፡፡

ቃል ግጥሙ ከቋንቋ አጠቃቀም አንጻር በተነጻጻሪ ዘይቤ የቀረበ ሲሆን የአማራን ሕዝብ እንደተራራ አግዝፎ የሚያሳይ ነዉ፡፡ የግጥሙ ነባራዊ መነሻ አስተሳሰብ አንድም በጎሳ ፖለቲከኞች ማኒፌስቶና የፖለቲካ ፕሮግራም እንደሚቀነቀነዉ አማራ ገዥ መደብ እንደነበረ ሳይሆን በስልጣኔ፣ በአስተሳሰብና አመለካከት ከፍ ያለበት ዘመን እንደነበረ ይገልጻል፡፡

በስልጣኔና አስተዳደር በከፍታ ማማ ላይ በነበረበት ዘመን በስሙ በነገሱት ነገስታት ስልጣን የማይመካ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለዉ ሕዝብ በመሆኑ ማንንም አልበደለም፡፡ ይልቁንም እንደሌሎች ሕዝቦች ሁሉ በገዡ መደቦች የመደብ ጭቆና፣ ብዝበዛና በደል የደረሰበት በመሆኑ ከወንድም ሕዝቦች ጎን ቆሞ ስርዓቱን ታግሎ ለመጣል እንጂ የብዝበዛና ጭቆና አካል ሆኖ ሌሎችን ሕዝቦች ለመጨቆን ጥረት አላደረገም፡፡ ይሁን እንጂ የነገሥታቱን አገዛዝ ሥርዓት የአማራ ተወካይ አድርጎ በመቁጠር የጥላቻ ትርክት ሲነዛበት እና በማንነቱ ሲሸማቀቅ ኖሯዋል፡፡

አስተሳሰቡ በዘመናዊ የሕዝብ አስተዳደር ፍልስፍና ትክክል ባይሆንም በዘመናችን እየታየ ያለዉን የተረኝነት እና የአሸናፊነት የዘዉጌ ፖለቲካ ተከትሎ ነገም በታሪክ አጋጣሚ ወደስልጣን ቢመጣ ማንንም እንደማይበድል ማረጋገጫ የሚሰጥ ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ሰላም እና ዴሞክራሲ ያደረገዉ ተጋድሎ እንደወንጀል በመቆጠሩ የዘዉግ ፖለቲካ ማቀንቀንና የትጥቅ ትግል በማድረግ መብትና ነጻነቱን በክንዱ ለማስከበር የትጥቅ ትግል ለመጀመር መገደዱም የዚህ አብነት ነዉ፡፡

15. እንብላ እንጠጣ ነዉ ለመጣ ለሄደዉ፣

ራያ ምድር ላይ ሰዉ መሆን በቂ ነዉ፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 18 በተጠቀሰዉ ቃል ግጥም ትንታኔ ዉስጥ እንደተገለጸዉ ኢትዮጵያዉያን የምንታወቅበትና ከኬላዉ ዓለም የሚለየን ዉድና ብርቅ እሴታችን እንግዳ ተቀባይነታችን፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ የመከባበር፣ አብሮ የመስራት እና አብሮ የመብላት ባህልና በአጠቃላይም ማህበራዊ ኑሯችን ነዉ፡፡ ይህ ብርቅና ድንቅ ባህልና ዕሴታችን በባዕድ አስተሳሰብ እየተበረዘና እንደነዉር እየተቆጠረ፣ የሕዝቡን ባህልና ዕሴት፣ ቋንቋና ብሔረሰባዊ ማንነት መከለያና የግል ጥቅም ማስጠበቂያ እና የወንጀለኞ መደበቂያ ሆኖ እያገለገለ ከመደብዘዝ አልፎ እየጠፋ ይገኛል፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ለማስተላለፍ የተሞከረዉ መልዕክትም እየደበዘዘና እየጠፋ የመጣዉን ባህልና ማህበራዊ ኑሯችንን ዛሬም የራያና ቆቦ ህዝብ ጠብቆት እየኖረ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ወደራያ የመጣና የሄደዉን እንግዳን ሁሉ ዘር፣ ቀለም፣ ማንነትና መተዋወቅን ሳይጠይቅ ሲያበላና አብሮ ሲበላ የኖረና ወደፊትም በዚህ መልኩ የሚኖር መሆኑን ያሳያል፡፡ በራያ ሕዝብ እና ምድር ላይ አብሮ ለመብላትና ለመጠጣት፣ ለመከባበርና ለመረዳዳት ሰዉ መሆን ብቻ በቂ ነዉ የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

## 4.2.5. የተቃዉምና የቅሬታ ድምጽ የማሰማት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



*በ2016 ዓ.ም በካራ አርሴማ ጥምቀተ ባሕር በዉሁድ ማንነት የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት*

(Finnegan in Bauman፣ 1992፣ 126) ላይ ጠቅለል ባለ መንገድ የቃላዊ ግጥም ተግባር በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ እነሱም አመፅን መግለፅ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድረግ እና ለውጥን ማበረታታት ናቸው። በማለት አጠቃለዉ ፈርጀዉታል። በመሆኑም ቃል ግጥም በፖለቲካው መስክ በአንድ በኩል ገዢው ስርዓቱን የሚያስከብርበት፣ በአንፃሩ ደግሞ ተገዢው በገዢው ላይ ያለውን ብሶት የሚገልፅበትም ነው። ህዝብ ስልጣን ላይ ስላለው መንግስት አስተዳራዊና ፖለቲካዊ ስርዓት የተሰማውን ስሜት፣ የሚመኘውን አይነት አስተዳደር እንዲመጣለት የሚገልጽበት ነው። ገዥው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ህዝብ ጥላቻውን ይገልፅበታል።

በዚህ አምስተኛ ዐብይ ምድብ ስር የቀረቡት ቃል ግጥሞች አጠቃላይ ይዘት፣ ስሜት እና አንድምታ ሕዝቡን ማህበራዊ ረፍት የሚነሱ፣ የግዛት አንድነት የሚቃረኑና የሚነጣጥሉ፣ አስተሳሰብና ድርጊቶችን የሚነቅፉ ናቸዉ፡፡ ለአብነትም የአማራ ሕዝብ እየደረሰብኝ ነዉ ብሎ የሚያምነዉን ግፍና መከራ፤ ይህንን እያደረገ ያለዉን ስርዓት፣ መንግስትና አመራሮቹን ለመቃወምና የህዝቡን ቅሬታ የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥሎ አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን፡፡

1. ይነጋል ባልነዉ ቀን ጨለማ ነገሰ፣
   ኑሮ ተወደደ ሰዉ እየረከሰ፡፡

በሀገራችን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ደርግን በማሸነፍ ወደስልጣን የመጣዉ በህወሓት ኢሕአዴግ ይመራ የነበረዉ ስርዓተ መንግስት በኦሮማራ ጥምረት በሚመራዉ የለዉጥ ሃይል ተገፍቶ ወደ ትግራይ ማፈግፈጉ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በለዉጥ ሃይሉ የሚመራዉ የብልጽግና ፓርቲ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ስርዓቱንና ሃገሪቱን በኢትዮጵያዊነት፣ በአንድነትና በዴሞክራሲ መንፈስ ለማስተዳደር ያላቸዉን ቁርጠኝነት በመሪዎቹ በዓለ ሲመት ላይ ይፋ መደረጉና ወያኔ ያለፈበትን የጥፋት ጎዳና እንደማይግመዉ ቃል መግባቱ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ አመራሩ ቃል የገባዉን ሁሉ ረስቶ ይሁን አቋሙን ቀይሮ ሕዝቡ የሚፈልገዉን፣ የሚመኘዉን እና ይሆንለት ዘንድ የሚናፍቀዉን ሥርዓተ መንግስት እንዳላመጣ የሚጠቁሙ አስተያየቶች፣ ምሬትና ተቃዉሞዎች ይደመጣሉ፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ሕግ አስከባሪና የጸጥታ ሃይሉ የዜጎችን መብት፣ ደህንነትና ሰላም መጠበቅና ማረጋገጥ ባለመቻሉ በህገወጥ ዘራፊ ቡድኖች ከሚደርስበት እፈና፣ ስደትና ዘረፋ በተጨማሪ በታጠቁ ሃይሎችና በመንግስት መካከል በሚደረጉ ግጭቶች ሕዝቡ የችግሩ

ሰለባ እየሆነ እንደመጣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀሩ መዘገብና ሪፖርት ማዉጣት ጀምረዋል፡፡

***"ይነጋል ባልነዉ ቀን ጨለማ ነገሰ፣ ኑሮ ተወደደ ሰዉ እየረከሰ"*** የሚለዉ ቃል ግጥምም ይህንን በህብረተሰቡ ላይ የተፈጠረ ሰቆቃ፣ የተሰማዉን ስሜትና አመለካከት የሚገልጽ፣ ሕዝቡ የጠበቀዉን ከማጣቱም ባለፈ ፖለቲካዉም ሆነ ኑሮዉ ከእሾህ ወጥቶ ጋሬጣ እንደሆነበት የሚጠቁም፣ የተቃዉሞና የቅሬታ መንፈስ የሚያንጸባርቅ የሰላ ትችት ነዉ፡፡

2. ስጋዉን ሳይበሉት ደሙን ሳይጠጡት፣
   አሳምነዉ ጽጌን ለምን ገደሉት፡፡
3. ዝግባዉን ቆረጡት እነ ልክ አያዉቁ፣
   ምን ያፈራ ይሆን ብለዉ ሳይጠይቁ፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ኹለት እና ሦሥት የቀረቡት ቃል ግጥሞች የአማራ ሕዝብ እንደባለዉለታ፣ የነጻነት ታጋይና አርዓያ፤ የፌዴራሉና የክልሉ መንግስትና አመራሮች እንደአሸባሪና ስርዓት አልባ በሚፈርጁት በብርጋር ጀነራል አሳምነዉ ጽጌ ሞት ላይ ያነጣጠሩ ናቸዉ፡፡ እስከ አሁን ድረስ አወዛጋቢ በሆነ መንገድ የአማራ ክልል አመራሮች ቅዳሜ፣ ሰኔ 15/2011 ዓ.ም መገደላቸዉ ይታወቃል፡፡

በሰዓቱ ከተገደሉት የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች መካከል አንዱ በጊዜዉ የክልሉ የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ የሆነበሩት ብርጋደር ጀነራል አሳምነዉ ጽጌ ናቸዉ፡፡ ጀነራሉ የክልሉን ሕዝብ ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ጥረት ከማድረጋቸዉም ባለፈ ሕዳር 30/2011 ዓ.ም በባሕርዳርና በጎንደር ሕሕባዊ ዉይይት ላይ ያደረጉት ታሪካዊ ንግግርና አማራ ይንን ታሪካዊ አጋጣሚ በአሸናፊነት ካልተሸገረ ታካዊ ስህተት ይጽማል በማለት የሕልዉና ችግር ዉስጥ እደገባ የሰጡት ማስጠንቀቂያ ለዛሬዉ የአማራ ክልልና ሕዝብ ትግል መሰረት ስለመሆኑ ይነገራል፡፡

ለዚህም ይመስላል በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በነበሩት የጥምቀት በዓላት ላይ በነበሩት የክወና አዉዶችና ለጭፈራ በመጡ ቡድኖች ሁሉ የርሳቸዉ ስም፣ ዝናና ክብር እንዲሁም መስዋዕነት በስፋት እየተነሳ የተዜመዉና መገደላቸዉን በስፋት ሲቃወሙ የተሰማዉ፡፡ በተጨማሪም የጀመረሩት ትግል አላማና ግብ በሺህ የሚቆጠሩ ተከታዮች ሊያፈራ እንደሚችል ያመላክታልሉ፡፡ በርግጥ የርሳቸዉ ማስጠንቀቂያ የዛሬዉ የፋኖ

የትግል መርህ ሆኖ ስለመቀጠሉ በመሬት ላይ ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎች በግልጽ ያመላክታሉ፡፡

4. ወለጋ ሕዝብ ሲያልቅ ያላወጀ አዋጅ፣
   ያማራ ሕዝብ ሲያልቅ ያላወጀ አዋጅ
   ምን ብልጽግና ነዉ ብልግና ነዉ እንጅ፡፡

ወለጋ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በአራት ዞኖች የተዋቀረ በስፋት ኦሮሞዎች፣ ቀደም ሲል በስፍራዉ የኖሩና አሁንም የሚኖሩ አማራዎች፣ እንዲሁም በደርግ ሥርዓተ መንግስት በሰፈራ ፕሮግራም ከወሎ ሂደዉ የሰፈሩ አርሶ አደሮችን ጨምሮ በርካታ የልዩ ልዩ ብሔረሰብ አባላት የሚኖሩበት አካባቢ ነዉ፡፡ ስፍራዉ የኦነግ ሰራዊት በስፋት የሚንቀሳቀስበትና በተለይም የለዉጡ መንግስት ወደስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ መረጋጋት እንደሰማይ የራቀዉ አካባቢዉ ነዉ፡፡

ይህንንም ተከትሎ በአካባቢዉ የሰፈሩትን እና በልዩ ልዩ መንገድ በአካባቢዉ ለመኖር ስራና የኑሮ እጣ ፋንታ ያስገደዳቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች በጅምላ እየተጨፈጨፉ፣ የተረፉት ሃብትና ንብረታቸዉን እየተዘረፉ፣ ከአካባቢዉ ለቀዉ እየተሰደዱና እየተፈናቀሉ መኖር የእለት ከእለት እጣቸዉ እንደሆነ የኢሰመኮ ሪፖርቶች[19] ያመላክታሉ፡፡ ጉዳዩ በዓለም ዓቀፍ ሚዲያችና በሀገሪቱ ሚዲያችም ጭምር በተለይም በማህበራዊ ሚዲያዎች በሰፊዉ የተዘገበ የሀገራችን የመጨረሻዉ የታሪክ ጠባሳ የትዉልድ ጥቁር አሻራ ሆኖ የተመዘገበ አጀንዳ ነዉ፡፡

ለዚህም ነዉ ቃል ግጥሙ በአንድ በኩል በወለጋ የሚኖረዉን የአማራን ሕዝብ እልቂት፣ በሌላም በኩል መንግስት ሕግን ለማስከበርና ዜጎችን ከታጣቂ ቡድኖች ጥቃት መከላከል ባለመቻሉ ህብረተሰቡ የተሰማዉን ቅሬታና ተቃዉሞ የሚያንጸባርቅ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ይህ ሁኔታ በሥርዓቱ እና በህብረተሰቡ መካከል ጥርጣሬና አለመግባባት የፈጠረ መሆኑን ያመለክታል፡፡

5. ምን ያደርግልናል እንጠጦ ቢሰራ፣
   በጅምላ እያለቀ ሰዉ አማኙ አማራ፡፡

---

[19] በጊዳ ኪራሙ አካባቢ ተሰማርተው የቆዩ የፀጥታ ኃይሎች ማክሰኞ ወደ ሌላ አካባቢ መሄዳቸውን ተከትሎ በነጋታው ረቡዕ ነሐሴ 12/2013 ዓ.ም ታጣቂዎች "ብሔርን መሠረት ያደረገ ጥቃት ማድረሳቸው በከፍተኛ ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን" ኮሚሽኑ ገልጿል።

6. መሰደድ መታሰር ከሆነ የኛ እጣ፣

   መገደል መታገት ከሆነ የኛ እጣ፣

   መበተን መፈርከስ ከሆነ  የኛ ዕጣ፣

   መደመር መበልጸግ ባፍንጫችን ይዉጣ፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር አምስት እና ስድስት የቀረቡት ቃል ግጥሞች በተራ ቁጥር አራት ከቀረበዉ ቃል ግጥም ጋር ተመሳሳይ ፋይዳና አንድምታ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ ሥለሆነም የሕዝቡ እጣ ፋንታ መሰደድ፣ መታሰር፣ መታገት፣ መበተንና መገደል ከሆነ ልማት፣ መደመርና መበልጸግ ለእኛ አይጠቅምምና ይቅርብን የሚል ሕዝባዊ ተቃዉሞዉን የሚያንጸባረቁ ናቸዉ፡፡ ሕዝቡ ከብልጽግና በፊት ሀገራዊ ሰላምና መረጋጋት፣ ፍትህና የሕግ የበላይነት፣ የሕዝባችን ደህንነት ይረጋገጥልን የሚል አመለካከቱን ለመንግስትና ለአመራሩ በጥያቄ መልክ ማሰማቱን የሚተቁሙ ናቸዉ፡፡

አመራሩ በየመድረኩና በየሚዲያዉ እንደሚገልጸዉ መደመርና ብልጽግና የስርዓቱ ዋልታና ማገር ናቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ በነዚህ ቃል ግጥሞች ለማንጸባረቅ እንደተሞከረዉ የህልዉና አደጋ የገጠመዉ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል በመኖሩ ሥርዓቱ ከድጋፍ ይልቅ ተቃዉሞ ሊያጋጥመዉ እንደቻለና ከህዝብ የተለየ መደመርና ብልጽግና የቅቡልነት ስጋት ሊያጋጥመዉ እንደሚችል መገንዘብ የቃል ግጥሙ ጭብጥ ያመላክታል፡፡

7. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ፣

   ነፍጠኛዉ አማራ አይፈታም ትጥቁ፡፡

የትጥቅ ማስፈታትና ጥያቄን አልፈታም ዉዝግብ ከቀደመዉ የመልካም አስተዳደር፣ የልማትና የፍትህ ጥያቄ ባሻገር ዛሬ በአማራ ክልል ለተጀመረዉ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅታዊ ምክንያት (ኢሚዴት ኬዝ) ነዉ ብሎ መዉሰድ ይቻላል፡፡ መንግስት በአማራ ክልል ያለዉን የልዩ ሃይልና የፋኖ አደረጃጀት እንዲሁም ከወያኔ ማርከዉ የታጠቁትን መሳሪያ በበጎ እንዳልተመለከተዉና እንደ ስጋት ምንጭ እንደቆጠረዉ የጸጥታ ኃይሉ መግለጫና በየተቋማቱ የተካሄዱት መድረኮች ላይ የቀረቡ የመወያያ አጀንዳዎች ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም ልዩ ሃይሎች ህገወጥ አደረጃጀቶች ናቸዉና በአስቸኳይ ፈርሰዉ ከፖሊስና ከመከላከያ ጋር ይቀላቀሉ የሚል መመሪያ በመንግስት ሲወጣ ከህወሓት ጋር የተጀመረዉ ደም አፋሳሽ ቅራኔ መፍትሄ ስላልተሰጠዉና የወረራ ስጋትም ስላለብን ትጥቅ አንፈታም የሚል አቋም በክልሉ ታጣቂ ሃይሎች ተንጸባረቀ፡፡

በመሆኑም በሰላምና ጸጥታ አስከባሪ አመራሮች በኩል “ይህን ጽንፈኛ ሃይል እንኳን የታጠቀዉን መሳሪያ ቀበቶዉንም እናስፈታዋለን” የሚል መግለጫ መሰጠቱን ተከትሎ ህብረተሰቡ ራሱን ለመከላከልና ትጥቁን ላለመፍታት በፋኖ አደረጃጀት ስር ተደራጀ፡፡ ይንንም ተከትሎ ልዩ ሃይሉ ትጥቁን ለመንግስት እያስረከበና ከፊሉም ትጥቁን እደያዘ የዚህ አደረጃጀት አካል በመሆን በአማራ ክልል የተጀመረዉን የእርስ በርስ ጦርነት በይፋ እንጂጀመር ተጨማሪ ምክያት ሆኖ ግጭቱን አፋፋመዉ፡፡

ስለሆነም በቃል ግጥሙ ዉሳኔዉና መግለጫዉ ከህብረተሰቡ ባህላዊና ማኅበራዊ ማንነት፣ አቋምና ፍላጎት ጋር የሚጋጭ መሆኑን ለመግለጽ፣ ለመቃወምና ቅሬታዉን ለማሳወቅ “ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ፣ ነፍጠኛዉ አማራ አይፈታም ትጥቁ” በሚል ቃል ግጥም በጥምቀት በዓል ላይ በታደሙ ወጣቶች ዉክልና በዘፈንና በሆታ መልክ የአማራ ሕዝብ አቋምና የተቃዉሞ ድምጽ ተንጸባርቋል፡፡

8. ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣
ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም አማራ፡፡
9. ራያ ወሎ ነዉ ገለል በል ህወሃት፣
ተነጥሎ አይቀርም የጢነኞች ርስት፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ስምንትና ዘጠኝ የቀረቡት ቃል ግጥሞች በ2016 ዓ.ም የጥምቀት በዓል በሁሉም ቡድንና በሁሉም የክወና አወዶች ላይ በዘፈን፣ በጭፈራና በሆታ በተካፈሉ ወጣቶች በተደጋጋሚ የተዜሙ ናቸዉ፡፡ ራያና ወልቃይት በዘመነ ህወሃት ከአማራ ክልል ወደትግራይ ክልል የተካለሉና የአካባቢዉ ህብረተሰብ የአስመላሽ ኮሚቴ አቋቁሞ እርስቱን ለማስከበር ሲታገል መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ኹለቱም አካባቢዎች የዘመናችን፣ የሃገራችንና የህዝባችን በተለይም የሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ጂኦፖለቲካዊ ንቅናቄና የጦርነት መንስዔዎች ሆነዉ የቀጠሉ ናቸዉ፡፡

በ2013 ዓ.ም በህወሓት እና በፌደራሉ መንግስት መካከል የተፈጠረዉን ግጭት ተከትሎ በተገኘዉ አጋጣሚ ርስታችንን በትግል በማስመለስ የግዛትና ህብተሰብ ኢተነጣጣይነታችንን አዉጀናል የሚል ሃሳብ በህብረተሰቡ ዘንድ ሲንሸራሸር ይሰማል፡፡ ‹‹ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣ ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም የአማራ፡፡›› እንዲሁም ‹‹ራያ ወሎ ነዉ ገለል በል ህወሃት ተነጥሎ አይቀርም የጢነኞች ርስት፡፡›› የሚሉት ቃል ግጥሞችም ይህንኑ የሕዝቡን ተቃዉሞና ቅሬታ ለማንጸባረቅ በዘፈን፣ በጭፈራና በሆታ ለማንጸባረቅ የቀረቡ ይመስላሉ፡፡

10. ህወሓት በተንኮል የዘራዉን ዘር፣

ኦህዴድ በሰዉ ደም ያበቅለዉ ጀመር፡፡

የህወሓት አመራሮች ደርግን አሸንፈዉ ወደማዕከላዊ መንግስት ስልጣን ሲመጡ በ1987 ዓ.ም ነጣጣይና ከፋፋይ ሕገመንግስት በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ማጽደቃቸዉ ይታወሳል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሀገር በቀል የሆኑ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶቻችንን በመበረዝና በመከለሳቸዉ ሀገራዊ ፍቅርና ህዝባዊ አንድነታችን እየተዳከመ መጥቷል፡፡

ይህንን ተከትሎ ዜጎች በፈለጉበት አካባቢ ተንቀሳቅሰዉና ሰርተዉ እንዳይበሉ፣ ሃብት እንዳያፈሩና በላባቸዉ ያፈሩት ሃብትና ንብረት ባለቤት እንዳይሆኑ፣ እንደባይተዋር እንዲቆጠሩና እንዲሳደዱ ተደርገዋል በሚል ቅሬታዎች በየአጋጣሚዉ ይንጸባረቃሉ፡፡ ይህንን ስርዓተ መንግስትና የፖለቲካል ኢኮኖሚ ከነማስፈጸሚያ ሕገመንግስቱ የተቀበለዉ የለዉጡ መንግስት ደግሞ ታጣቂ ሀይሎችንና ለጥፋት የተደራጁ ህገወጥ ቡድኖችን መቆጣጠርና ህግ ማስከበር ባለመቻሉ በሰዉ ልጆች ጅምላ ግድያ፣ እገታ፣ ስደትና መፈናቀል ተጠናክሮ ቀጥሏል የሚሉ አካላት በዝተዋል፡፡

ለዚህም ይመስላል የህብረተሰቡ አካል የሆኑ የባህላዊ ዘፈንና ሆታ አቀንቃኞች በ2015 እና በ2016 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ላይ ***“ህወሓት በተንኮል የዘራዉን ዘር፣ ኦህዴድ በሰዉ ደም ያበቅለዉ ጀመር”*** በማለት በዘፈን፣ በሆታና በጭፈራዉ ስሜቱን ሲያንጸባረቅ የተሰማዉ፡፡ በግጥሙ ዉስጥ ኦህዴድ በሚል የተገለጸዉ የፖለቲካ ድርጅት በህወሓት ዘመን “የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት” ይባል የነበረዉ ሲሆን በግጥሙ የቀረበዉ ሃሳብና ይዘት አሁን ያለዉን ብልጽግና የሚባለዉን ፓርቲ (ድርጅት) ወክሎ የቆመ ነዉ የሚል አንድምታ ያለዉ ይመስላል፡፡

11. የባለስልጣን ልጅ አይሄድም ዘመቻ፣
ሰላም አስከባሪ የድሃ ልጅ ብቻ፡፡

12. ጣሊያን አልመጣብን ተኩስ አልተተኮሰ፣
ወይ ወራሪ አልመጣ ችግር አልደረሰ፣
ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አገሩ ታመሰ፤
በኮማንድ ፖስቱም አገሩ ፈረሰ፡፡

13. ያምናን ቀን አማሁት ላፌ ለከት የለዉ፣
የዘንድሮዉ ባሰ እጅም እግርም የለዉ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አስራ አንድ እስከ አስራ ሦሥት የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የመልካም አስተዳደር፣ የሰላም፣ የፍትህና ደህንነት ችግሮች እየተባባሱ መምጣታቸዉን ተከትሎ የህዝቡን ስጋትና ተቃዉሞ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡ ለአብነትም በተራ ቁጥር አስራ አንድ የቀረበዉን ብንመለከት ሀገራችን ከጊዜ ወደጊዜ የእርስ በርስ ጦርነቶች እየተባባሱ በመምጣታቸዉ ህግ ለማስከበር በሚል ስም የድሃዉ ልጅ በጦርነት እሳት እየተማገደ እንደሚያልቅና ለሀገርና ለሕዝብ ደህንነት ቁመናል የሚሉት የባለስልጣናቱ ልጆች ግን በዚህ ጦርነት ሳይሳተፉ ድሃዉን ለማስጨረስ የሚያደርጉትን ጥረት ለመቃወም የቀረበ መሆኑን ከግጥሙ አቀራረብ አዉድና ይይት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተራ ቁጥር አስራ ኹለት እና አስራ ሦሥት ላይ የተጠቀሱት ደግሞ በሀገራችን እየተካሄደ ያለዉ የእርስ በርስ ጦርነት በዉጭ ሀገራት ጣልቃ ገብነት፣ በተቃዋሚ ኃይሎች ቅስቀሳ፣ በዓለም ዓቀፍ አሸባሪዎች ጫና እና አስገዳጅ ሁኔታ የተፈጠረ ሳይሆን በመንግስት አስፈጻሚ አካላት ፍላጎት፣ በተወካዮች ምክር ቤት ዉሳኔ ጸድቆና ሀገራዊ እዉቅና ተሰጥቶት ጦርነቱን የሚመራ ኮሚቴ ተቋቁሞለት እንዲሁም ስትራቴጂ ተነድፎለት ጦር ኃይች ከጠረፍ ወደመሃል ቸገር ተንቀሳቅሰዉ የሚደርጉት መሆኑንም ይጠቁማሉ፡፡

በመጨረሻም ***"ያምናን ቀን አማሁት ላፌ ለከት የለዉ፣ የዘንድሮዉ ባሰ እጅም እግርም የለዉ"*** የሚለዉ ቃል ግጥም በሀገራችን ሕዝባችን ከዚህ በፊት መሰል ችግሮች ሲያጋጥሙ የባሰ አያምጣ በሚል ሲንጎራጎር የኖረ ቢሆንም ዛሬ የባሰዉ ከባድ ችግር እንዳጋጠመና የችግሩ መጠንም ከድሮዉ ዘመን ችግር ጋር የሚመጣጠን እንዳልሆነ የአሁኑ ወደር አልባ እንደሆነም ይጠቁማል፡፡ በግጥሙ የዘንድሮዉ ችግር የከፋና ወደር አልባ ከመሆኑ የተነሳ የባለፈዉን ስርዓና ያስከተለዉን ችግር መዉቀስ አይገባም የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

ወቅቱ እንደሚታወቀዉ ሰዉ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ ለመኖርም ሆነ ለመስራት የተቸገረበት፣ በሰላም አገር አማን ብሎ ከቤቱ የወጣ ሰዉ እንደወጣ የሚቀርበት፣ ነጋዴዉ ወረቱን ገበሬዉ ምርቱን በአባወራ ሚስቱን የመሚነተቅበት፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በጅምላ ታግቶ የሚወሰድበት፣ ክልሎች በታጠቁ ሀይሎች የሚሸበሩበት፣ የሕግ የበላይነትና ፍትህ ከመቼዉም ጊዜ በላይ የጠፋበት ጊዜ ነዉ፡፡

14. ቀና ብዬ ባየዉ ሰማዩም ቀለለኝ፣

ፈጣሪም እንደኛ ታግቷል መሰለኝ፡፡

ይህ ቃል ግጥም ከዚህ በፊት ***"ቀና ብዬ ሳየዉ ሰማዩ ቀለለኝ፣ እንተንም ሰፈራ ወስዱህ መሰለኝ"*** በሚል በደርግ ሥርዓት መንግስት የነበረዉን የአርሶ አደሩን ከቀዬዉ ተፈናቅሎ በማያዉቀዉ አካባቢ እንዲሰፍር ይደረግ የነበረበትን አስከፊ ታሪክ እና ፈጣሪ የድሆችን እንባ ለማበስ አለመቻሉን ለመግለጽ አገልግሏል፡፡ የቃል ግጥም ባህርይ ነዉና ትዉልድ ተሸግሮ ዛሬም ይዘቱን ቀይሮ መልዕክቱን እንደጠበቀ የእስርና የእገታ ወቅታዊ ችግሮችን ለመቃወም ሲያገለግል ተመልክተናል፡፡

ይህንን ማህበራዊ ዉርስ በተመለከተ (ደበበ ሰይፉ፣1975)፣ የአማርኛ ሕዝባዊ ሥነግጥም ለአብነት ያህል በሚል መጣጥፋቸዉ ሕዝባዊ ሥነ ግጥም በሕዝብ አንደበት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ሲተላለፍ የሚቆይ እንጂ እንደተደረሰ በወረቀት ላይ የሚሰፍር ጥበብ ባለመሆኑ ለተመራማርያን አንዳንድ አነስተኛ ችግሮችን መፍጠሩ አልቀረም፡፡ የመጀመሪያዉ ችግር የየግጥሞቹን ሁኔታ መልክ ማግኘቱ ላይ ነዉ፡፡

ሕዝባዊ ግጥሞች በየሰዉ አንደበት በተለያዩ ጊዜያት በሚነገሩበት ወቅት አንዳንድ ለዉጦችን እያደረጉ በይዘታቸዉም ላይ እያከሉ ወይም እየቀነሱ መሄዳቸዉ እርግጥ ነዉ፡፡ በማለት እዉነታዉን ይጠቁማሉ፡፡ ወደግጥሙ ጭብጥና አሁናዊ ዳራና ትንታኔ ስናመራ በሀገራችን የተፈጠረዉን የእርስ በርስ ጦርነትና ሕዝባዊ ንቅናቄ ተከትሎ የጥምቀት በዓል አከባበር ላይ የጸጥታ ኃይሉ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸዉ አጋጣሚዎች ላይ በመገኘት ተቃዉሞና ነቀፌታ የሚያሠሙ ዘፈንና ጭራዎችን ያስቆማሉ፡፡ ጨፋሪዎችን ይበትናሉ ከዚያም አልፎ ወጣቶችን አግተዉ ወደእስር ቤት ያግዛሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ ከመንግሰት ተስፋ ሲቆርጥ ፈጣሪዉን መማጸንና መለመን ይጀምራል፡፡

ከፈጣሪዉ የሚፈልገዉንና የሚመኘዉን ሰላምና መረጋጋት ሳያገኝ ሲቀር ደግሞ ፈጣሪንም እንደመንግስት መቃወም፣ መሞገትና መዉቀስ ይጀምራል፡፡ በዚህ ግጥም ዉስጥም የተንጸባረቀዉ የፈጣሪን ህልዉና እስከመጠራጠር የሚያደርስና የተፈጠረዉን አለመረጋጋት ተከትሎ ፈጣሪ ለሕዝቡ እዳይደርስ እንደኛ ታግቷል መሰለኝ በሚል የቅሬታና ተቃዉሞ መንፈስ ያለዉ አስተሳሰብ ተንጸባርቋል፡፡

15. አማራ ዙሪያዉን መሬቱ ተወሮ፣
ህዝቡ በያገሩ በጅምላ ተቀብሮ፣
ምን ተይዞ ጉዞ ይታሰባል ኑሮ፡፡

በዘመነ ህወሓት ኢ.ሕአዴግ አንዴ እና ጠባቧ የትግራይ ክፍለ ሀገር በቋንቋ ተናጋሪዎች መስፈርት ከጎንደርና ከወሎ ሰፊ ግዛት ተቆርጦ ተጨምሮላት አንድ ክልል ስትሆን ሰፋፊ ግዛቶች የነበሯቸዉ ሸዋ፣ ወሎ፣ ጎንደርና ጎጃም ግዛቶቻቸዉን ለአፋር፣ ለትግራይ፣ ለኦሮሚያ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካፍለዉ፣ በዉስጣቸዉም ትናንሽ ራስ ገዝ የብሔረሰብ ግዛቶችን አቅፈዉ አንድ ክልል ብቻ ሆነዉ መዋቀራቸዉ ይታወቃል፡፡ የአማራ ክልልና ሕዝብ በዚህ መልኩ ከተዋቀረ በኋላ በየጊዜ የስልጣን ወንበር ላይ ለተፈናጠጡ ገዢዎች ተላላኪ በመሆን በሚያገለግሉ ደካማ አመራሮች እየተመራ ሰላም፣ ልማት፣ ፍትህና የእኩልነት መብቱን ተነፍጎ የኖረ ብቻ ሳይሆን የህልዉና ስጋት ዉስጥ ያለ ሕዝብ ነዉ የሚሉ አስተያየቶች እና ቅሬታዎች ይነሳሉ፡፡

"ቤት ዘግተዉ የደበደቡት ዉሻ ባለቤቱን ይናከሳል" እንዲሉ የአማራ ሕዝብ ከሰላማዊ ሰልፍ እስከ ትጥቅ ትግል ባደረገዉ ተሳትፎ በጥገናዊ ለዉጥ አዲስ አገዛዝ እንዲመጣ ሁነኛ ተሳትፎ እንደነበረዉም ይታወቃል፡፡ በለዉጡም ሎሌ ከመርገጥ አልፎ ከማንም በላይ የስርዓቱና የመሪዎቹ ደጋፊ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ በሂደት የጠበቀዉን ካለማግኘቱም ባሻገር ከጊዜ ወደ ጊዜ ህይወቱ ከድጡ ወደማጡ እየሆነበት እንደመጣም ይነገራል፡፡ የኢሰመኮ ሪፖርት[20] እንደሚያሳየዉ የአማራ ሕዝብ ከመላዉ ሀገሪቱ በተለይም ከኦሮሚያ ወለጋ ዞኖች በጅምላ እየተገደለና እየተሳደደ ወደአማራ ክልል መጉረፍ ቀጥሏል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በራሱ ክልል ዉስጥ በኦነግ ሸኔና በመንግስት ታጣቂ ኃይሎች የመኖር መብታችንን ተነጥቀናል በሚል ቅሬታዉን ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ እያሰማ ይገኛል፡፡ ቃል ግጥሙ ይህንን ተከትሎ ሕዝቡ ለጥያቄዉ ምላሽ በማጣቱ ተስፋ ስለቆረጠ ካልተሰማ ድምጻችን ይመዘዛል ሰይፋችን በሚል አቋም ጎጆና ኑሮዉን ጥሎ፣ ዱር ቤቴ ብሎ በክንዱ መብቱን ለማስከበር ትግል ለመጀመር መገደዱንም ያመላክታል፡፡

---

[20] በኦሮምያ ክልል ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም. በምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ በመንግሥት እና በኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት (በተለምዶ 'ኦነግ ሸኔ') ታጣቂዎች መካከል ሲደረግ ከነበረው ውጊያ ጋር በተያያዘ በታጣቂው ቡድን በአካባቢው በሚኖሩ በአብዛኛው የአማራ ብሔረሰብ ሲቪል ሰዎች ላይ በተፈጸመ ጥቃት በሰው ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። የምርመራ ሥራው ገና ያልተጠናቀቀ ቢሆንም በጥቃቱ ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል።

16. ጁንታዉ ሲለቀቅ በግርግር፣

ዘመነ ካሴ ለምን ይታሰር፡፡

ይህ ቃላዊ ግጥም በሀገራችን የህግ የበላይነት፣ የፍትህና ተጠያቂነት አሰራር እንዳልጎለበተና በአስፈጻሚ አካላት ጣልቃ ገብነት ተጽዕኖ እንዳረፈበት የሚያመላክት ነዉ፡፡ በመሆኑም አስፈጻሚ አካላቱ ሕግን የሕዝብን መብትና ጥቅም ለማስከበር ሳይሆን የራሳቸዉንና የደጋፊዎቻቸዉን ስልጣን፣ ዝናና ክብር ለማስጠበቅ እንደሚጠቀሙበት ያሳያል፡፡

ለአብነትም በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ በህገወጥ መንገድ የተደራጀ ወታደራዊ ኃይል (ጁንታ) መሪ፣ የሰሜን እዝን ከድተዉ ያሥጨፈጨፉ፣ ተብለዉ በሀገር ክህደት ወንጀል ከተከሰሱት የህወሃት ጉምቱ መሪዎች አቦይ ስብሃት አንዱ ናቸዉ፡፡ አዛዉንቱ ፖለቲከኛ ከተደበቁበት ዋሻ በመከላከያ ሰራዊቱ በቁጥጥር ስር ዉለዉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ተደርጎም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት ከህወሓት ጋር ባደረገዉ ድርድር እና በአመራሩ ጣልቃ ገብነት፣ በእድሜ የገፉ ናቸዉ በሚል ከእስር እንዲለቀቁ እና ክሱም እንዲሰረዝላቸዉ ተደርጓል፡፡

በአንጻሩ የህወሓትን ወረራ ለመቀልበስ በመንግስት የተደረገዉን ህዝባዊ ጥሪ ተከትሎ ለሀገሩና ለሕዝቡ ክብርና ነጻነት ከመከላከያ ጎን በመዝመት፤ በመዋጋትና በማዋጋት ሀገራዊ አስተዋጽኦ ያበረከተዉ ዘመነ ካሴ በጽንፈኝነት ተከሶ ወህኒ ተወርዉሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ግለሰቡ በተከሰሰበት ወንጀል ተጠያቂ ሊያደርገዉ የሚችል ጥፋት እንዳላገኘበት ብያኔ ሰጥቶ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ በአመራሩ ጣልቃ ገብነት ሳይፈታ ቀርቷል፡፡ ስለሆነም ቃል ግጥሙ ይህንን አድሏዊ አሰራር በመቃወም የተገጠመና በጥምቀት በዓል የክወና አጋጣሚ ላይ በአደባባይ የተዜመ ህዝባዊ ግጥም ነዉ፡፡ በመሆኑም ግጥሙ የህግ የበላይነት ይከበር፡፡ የአርበኛ ዘመነን እስርም ሆነ የአቦይ ስብሃትን መፈታት እንቃወማለን የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡

17. ለምን ይታሰራል የከተማ ልጅ፣

እምብዛም ቢጠና በዋስ ያድራል እንጅ፡፡

ከተማ በመንግስት ጥብቅ ጥበቃና ክትትል ስር የሚኖሩ በአብዛኛዉ ነጋዴና የመንግስት ሰራተኞች የሚኖሩበት አካባቢ በመሆኑ ቃል ግጥሙ የከተማ ልጅ ቢያጠፋም ዋስ ጠርቶ፣ ምክር ተቀብሎ ህግና ስርዓት አክብሮ እንዲኖር ይደረጋል እንጂ ሊታሰር እና

ሊንገላታ አይገባም የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ የግጥሙ ታሪካዊና ወቅታዊ መነሻ ሃሳብ በአዲስ አበባ ከተማ ህዝቡ መብቱን ለማስከበር በሚያደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች፣ ከኦነግ ሸኔ፣ ከፋኖና ከህወሃት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ጋር በተገናኘ ወጣቶች በጅምላ እየታፈሱ ወደእስር ቤት የሚጋዙበትን[21] ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡

18. አትግፉኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ፣
    እንኳን የሰዉ ሃገር የኔንም ትቻለሁ፡፡

ይህ ቃል ግጥም መረጃ ለመሰብሰብ በተመረጡ የክወና አጋጣሚዎችና በሁሉም ቡድኖች ብቻ ሳይሆን በሁሉም አቀንቃኞች በተደጋጋሚ የተቀነቀነ ነዉ፡፡ ግጥሙ የተለየና ድብቅ የሆነ ምስጢራዊ መልዕክት የለዉም፡፡ ግጥሙን በተለያዩ ቡድኖች መካከል መገፋፋት ሲኖር፣ ፖሊሶች ወጣቶችን ዘፈንና ጭፈራዉን እንዲያቋርጡ ጫና ሲያደርጉባቸዉ የሚያቀነቅኑት ከመሆኑም ባሻገር ሀገራዊ የመገፋፋት ፖለቲካዉን ታሳቢ በማድረግም ጭምር የያዜሙት እንደሆነ ነባራዊ ሁኔታዎች ይጠቁማሉ፡፡

የግጥሙን ታሪካዊ ዳራና መልዕክት ለመገንዘብ ዘፈኑን የሚያዜሙት በአብዛኛዉ የአማራ ወጣቶች ስለሆኑና ጨዋታዉም የአማራ ባህል በመሆኑ ከክልላቸዉ በመልካም አስተዳደር እጦት ተገፍተዉ የመጡ ወጣቶች ስለመሆናቸዉና የሕዝባቸዉን ብሶት የሚያንጸባርቁ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላም በኩል እንደ ሐገር አንዱ በሌላዉ አካባቢ መኖር፣ መስራት፣ ሃብትና ንብረት ማፍራት እንዳይችል ያደረገዉን የዘዉጌ ፖለቲካ ፍሬና የመልካም አስተዳደር ችግርም ይጠቁማል፡፡

ስለሆነም አትግፉኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ እንኳን የሰዉ ሃገር የኔንም ትቻለሁ የሚለዉ ቃል ግጥም በሚፈጸመዉ የመገፋፋት ድርጊት ቅሬታና ተቃዉሞ የሚያሳይና የመጋፋፋት ሂደቱ ካልቆመ ተሸማቆ ከመኖር በአሳዳጆቹ ላይ እርምጃ ወስዶ ወደሌላ ቦታ ለመሰደድ ዝግጁ መሆኑንም ያመላክታል፡፡ እንኳን የሰዉ ሀገር የኔንም ትቻለሁ የሚለዉ ስንኝም ይህንኑ የሚጠቁም ነዉ፡፡

---

[21] በሪፖርት ዘመኑ በአንድ ክስተትም ሆነ ረዘም ላለ ጊዜ በሚቆይ እና በተለምዶ ወቅታዊ ሁኔታ በመባል በሚታወቁ ምክንያቶች ሳቢያ ሰዎች ለዘፈቀደ እስር እንዲሁም ለአስገድዶ መሰወር የተዳረጉበት በርካታ ክስተቶች ተመዝግበዋል። ኢሰመኮ 2014-2015 ዓመታዊ ሪፖርት። ገጽ 3

### 4.2.6. የማዉገዝና የመተቸት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



በ2016 ዓ.ም በካራ አርሴማ ጥምቀተ ባሕር በባህላዊ አለባበስ የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት

በዚህኛዉ ዐብይ ምድብ ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች የሕዝቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና፣ ፖለቲካዊ ፍላጎትና ጥያቄዎች ተገንዝበዉ ምላሽ መስጠት ያልቻሉትን በየደረጃዉ ያሉ መሪዎችን፣ የአመራር ተላላኪዎችን፣ ፈሪዎችን እንዲሁም መሰል ጸረሰላም፣ ጸረልማት፣ ጸረፍትህና ጸረሕዝብ ፍላጎት ያላቸዉን አካላት፣ የማዉገዝና የመተቸት ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

ይህ ተግባራቸዉም ቃል ግጥም ትችት ለማቅረብና ጫና የመፍጠር እንደሚያገለግል Finnegan ከገለጹት ፋይዳ አንጻር በትይዩ የሚገለጽ ነዉ "ቃላዊ ግጥሞች ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማንፀባረቅም ይጠቅማሉ፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በሚታዩ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ይዘትና መልዕክት ያላቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገጠማሉ፣ ይዘፈናሉ፡፡ ትኩረታቸውም ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፌጠርና፣ ለቅስቀሳ ሆኖ፣ የህዝብን አመለካከት ማንፀባረቅ ይሆናል፡፡" (Finnegan 1970፡ 272-284)

1. እናቴስ መች ወልዳኝ እኔስ መች ተወለድኩ፣
   ከጠላቶቼ ጋር አብሬ እየዶለትኩ፡፡

ዉግዘትና ትችት ከሌላዉ በፊት በራስ ላይ ሲያነጣጥር ራስን አርሞ፣ ዉስጣዊ ዝንባሌን አጥርቶ፣ ኑሮና ትግልን በትክልክለኛዉ ፈር ለመምራትና ለስኬት ለመበቃት ያግዛል፡፡ በምሁራንና በራሱ በህብረተሰቡ በተደጋጋሚ ሲተች እንደሚሰማዉ የአማራ

አመራሮችና  ተምሬያለሁ የሚለዉ አማራ ሆዳም፣ ባንዳና ተላላኪ ነዉ በሚል ሲወገዝና ሲነቀፍ ይሰማል፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወድህ ወደአመራርነት ሰንሰለቱ ተስበዉ የሚመጡ አካላት የወከሉትን ህዝብና ክልል ጥቅምና ፍላጎት ሳይሆን በታሪካዊ አጋጣሚ ወደስልጣን የመጡትን ተረኛ ፖለቲከኞች ፍላጎት ለማሳካት እንደሚሰሩ አስተያየቶች ሲሰጡ ይደመጣል፡፡

*"እናቴስ መች ወልዳኝ እኔስ መች ተወለድኩ፣ ከጠላቶቼ ጋር አብሬ እየዶለትኩ"* የሚለዉ ይህ ቃል ግጥምም ይህንኑ ታሪካዊ ሀቅና በራስ ላይ የተሰነዘረ ሒስ በመሆኑ ጠላቶቹ መሆናቸዉን ከሚያዉቃቸዉ አካላት ጋር በመዶለቱ[22] መጸጸቱን ይነግሩናል፡፡ ዶለተ የሚለዉ ቃልና ጽንሰ ሐሳብ ደግሞ የሴራ የአድማና ክፉ ምክር መገለጫ በመሆኑ በራሱ ሕዝብና ክልል ላይ የሚሰራዉ የፖለቲካ ሴራ ክፋት ራሱን ጭምር የሚያጠፋ በመሆኑ በሰራዉ ስራ ማፈርና መጸጸት እንደሚገባዉ እና እንዲህ አይነቱ ተግባር ሊወገዝና ሊተች እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

2. እዩት መጡ መጡ ደረሱ እዛ ማዶ፣
   እየሸሹላቸዉ መከተል ተለምዶ፡፡

ግጥሙ በአማራ ክልል የጎረምሶች በባህላዊ  ሆታና ጭፈራ ዉስጥ ተደጋግሞ የሚዜም ነዉ፡፡ የሚያስተላልፈዉ መልዕክትም በሰርግ፣ በዘፈንና በጭፈራ አዉድ ላይ ተገኝተዉ የሚጨፍሩ ኹለት ቡድኖች መካከል የሚኖረዉን ቅራኔና አንዱ ለሌላዉ የሚኖረዉን ግምትና ነቀፌታ የሚያመላክት ነዉ፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹ ቡድኖች የጀግንነት ስም የወጣላቸዉ በነሱ ብርታት ሳይሆን በተጋጣሚዎቻቸዉ ፍርሃትና ስንፍና ምክንያት እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ለዚህም ነዉ ጀግና ነን ያሉትን አካላት ዉስጣቸዉን የሚያዉቁ ሌሎች ጀግኖች ሲመጡ እየዉ መጡ መጡ ደረሱ እዚያ ማዶ፣ እየሸሹላቸዉ መከተል ተለምዶ፡፡ በሚለት በሆታቸዉ፣ ዘፈንና ጭፈራቸዉ የተጋጣሚዎቻቸዉን ጀግና አለመሆን ያጋልጣሉ፡፡ አንድምታዉም ፈሪዎች እየሸሹላችሁ መከተል ለምዳችሁ ዛሬ ጀግኖች ይጠብቋችኋልና ጉዳችሁ ፈልቷል የሚሸሽ ሳይሆን የሚያባርር ቡድን ነዉ ያጋጠማችሁ እንዳትሞክሩን የሚል ነዉ፡፡

---

[22] ዶለተ የሚለዉ ቃል ትርጉም በደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሰበሰበ፣ አደመ፣ ከንቱ አሳብ አሰበ፣  ክፉ ምክር መከረ፣ አሴረና ነገር ቋጠረ ማለት እንደሆነ ያስረዳል።

ይህንን ነባር ቃል ግጥም በጥምቀት በዓል የክወና አጋጣሚ ከቀረበዉ ግጥም አንድምታ ጋር አያይዞን ስንመለከተዉ በህወሃት እና በፌደራሉ መንግስት መካከል ተፈጥሮ በነበረዉ ግጭት ወቅት የነበረዉን ሁኔታ ያስታዉሰናል፡፡ የአማራ ክልል የትግራይ ድንበርተኛ በመሆኑ በጦርነቱ ወቅት ሕዝቡ በራሱ ባንዳ አመራሮችና በጥቂት ተላላኪዎች ፕሮፓጋንዳ ተታሎና ተሸንፎ ከተማና ሰፈሩን እየለቀቀ ያደረገዉን ሽሽት በገደምዳሜ የሚያወግዝና የሚነቅፍ ነዉ፡፡

አንድም ደግሞ በነዚህ የባንዳና ተላላኪ ሃይሎች ፕሮፓጋንዳ ተታለዉ ሕዝቡም ሆነ ታጣቂ ሃይሎች ሲሸሹላቸዉ እየተከተሉ ዉድመት የፈጸሙትን፣ ያልታጠቀ ሕዝብ ሲሸሽላቸዉ እየተከተሉ የገደሉትን ኀወሓቶች ድርጊት የሚያወግዝ ነዉ፡፡ ስለሆነም መከላከያ ወደአማራ ክልል ሲዘምት ዛሬም እንደትናንቱ ወደአማራ ክልል መዝመታችሁ ህዝቡ እንደተለመደዉ በሴራና በተንኮል ሽሽቱን ይቀጥላል ብላችሁ ከሆነ ተሳስታችኋል እና አትሞክሩት የሚል አንድምታ ያለዉ ነዉ ፡፡

3. እናቱ አስተምራዉ ቂጣ በደንደሱ፣
   ና ተሸከም አለኝ እኔንም እንደሱ፡፡
4. ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻዉ፣
   አተላ መሸከም ይችላል ትከሻዉ፡፡

ሆድ ሲሰፋ ጭቅላት ይጠባል እንዲሉ ከላይ በተራ ቁጥር ሦሥትና አራት የቀረቡት ግጥሞች የሆዳምነትን አስከፊ ገጽታ የሚጠቁሙ ሆዳም ለሆዱ እንደሚገዛና ለሆዱ ሲል የጫኑትን ነገር ሁሉ እንደሚሸከም የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡ የጅብ ጓደኛ ወደጥንብ ይጎትታል እንዲሉ እንዲህ አይነቱ ሆዳምና ፈሪ ሆዳምነትንና ፍርሃትን እንደ መጥፎ ነገር ስለማያየዉ ሌላዉም እንደርሱ የጫኑትን ሁሉ እየተሸከመና በፍርሃት እየተለማመጠ ሆዱን እንዲሞላ እንደሚጋብዝም እየጠቆሙ በሰላ ትችት ሆዳምና ፈሪን የሚያወግዙ ናቸዉ ፡፡

የዚህ ዓይነቱ ሰዉ ደግሞ ፈሪ፣ ሰነፍ፣ ባንዳ፣ ተላላኪ እየሆነ የመጣ የሄደዉ ተረኛ ሁሉ ርካሽ ሃሳብና ተግባሩን የሚጭንበት፣ ለምን? ለማን? እንዴት? ብሎ የማይጠይቅ ሆዱ ሰፍቶ ጭቅላቱ የጠበበ አለቆቹ በራሱ ሕዝብ ላይ የጭቆና ቀንበር ጭነዉ ሲሰጡት ወገኑን በጅራፍ እየገረፈ የሚነዳ ሆዳም አመራር ምሳሌ ነዉ፡፡ ጀግና ግን ያሸከሙትን ሁሉ አይሸከምም፣ ህሊናዉ መንፈሱ፣ ባህልና ማህበራዊ ዳራዉ ይህን እንዲያደርግ አይፈቅድለትም፡፡ እንኳን ሰዉ የሙዝ ልጣጭም ሲረግጡት ያንሸራትታል

እንደሚባለዉና በቃል ግጥሙ እንደተመላከተዉ የተጫነበትን ቀንበርና ሸክሙን አሽቀንጥሮ ለመጣል እምቢ አሻፈረኝ በማለት ለቆመለት ዓላማና ለሕዝቡ ነጻነት ራሱን መስዋዕት ያደርጋል፡፡

የግጥሞቹ ይዘትና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ሲመረመር ሕዝብ በመረጠዉና የኔ በሚለዉ አመራር ሳይሆን በፖለቲካ ድርጅቶችና በፌደራሉ መንግስት ፍላጎትና ጣልቃ ገብነት እየተሾሙ የሕዝቡን ፍላጎት ወደጎን ትተዉ ለሾማቸዉ አካል የሚላላኩ ሆዳም አመራሮች መኖራቸዉን ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በቃል ግጥሞቹ የተላለፈዉ መልዕክት እነዚህ አካላት ርካሽ ባህርይ፣ ህቡዕ ተልዕኮና የሴራ ፖለቲካ ያላቸዉ በመሆናቸዉ የራሳቸዉ ፍላጎት እስከተሟላ ድረስ ሕዝቡ ከችግር አረንቋ ዉስጥ ቢዘፈቅ ቅር የማይላቸዉ ህሊና ቢስ አመራሮች ናቸዉ የሚል የዉግዘትና ነቀፌታ ስሜት የሚያንጸባርቅ ነዉ፡፡

5. እደግ እደግ ብለን ያሳደግነዉ ቀጋ፣
   አለ ዘመም ዘመም እኛኑ ሊወጋ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በተምሳሌታዊ ዘይቤ የትርጉም ስልት ተዋዝቶ ምስጢሩን በምሳሌዉ አጉልቶ ለማሳየት የቀረበ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ቀጋ ሁለት አብነት አለዉ፡፡ ሰዉ ተንከባክቦ ካሳደገዉ በኋላ አንድም የሚበላ ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ አንድም ደግሞ ተንከባክበዉ ያሳደጉትን ሰዎች የሚዋጋ እሾህ ነዉና በግጥሙ ዉስጥ በጭብጥነት የተመላከተዉ መልዕክት ይህንን የእሾህነት ባህሪዉን ተከትሎ የሚመዘዝ ትርጓሜ ያለዉ ነዉ፡፡ ቀጋ የሚለዉ ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ ክፉ፣ ተንኮለኛ፣ መሰሪ፣ ወደዉስጥ ሲገቡ ዝም ብሎ ወደዉጭ ሲወጡ የሚዋጋ ሰዉ ተምሳሌትነት ያለዉ ነዉ፡፡

የኦሮማራን ጥምረትና በሰዓቱ የብዙሃኑን ቀልብ የገዛዉን የኢትዮጵያዊነት ፕሮፓጋንዳ አምኖ በመቀበል የብልጽግና የለዉጥ አመራሮች ወደስልጣን ሲመጡ ከማንም በፊት የስርዓቱና የአመራሩ ደጋፊ፣ አለኝታና መከታነት ሆኖ አለንላችሁ ያላቸዉ ሕዝብ በተለይ አማራዉ ነዉ ይባላል፡፡ በለዉጡ ሰሞን የኢህአደግ አራቱ ድርጅቶች እንደ ክልል ፓርቲ ለዉድድር በቀረቡ ጊዜ አዴፓ ራሱን ከምርጫ አግልሎ ድምጹን ለብልጽግና በመስጠት ታማኝነቱን በተወካዮቹ አማካኝነት አረጋግጧል፡፡

ይሁን እንጂ በሂደት ነገሮችን ሁሉ እንደጠበቃቸዉ ሆነዉ አላገኛቸዉም እንዲያዉም የአማራ ሕዝብ በጥርጣሬ አይን እየታዬ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ የመሰሳደድ፣ የመፈናቀልና የመገደል እጣፋንታ እየደረሰበት ይገኛል፡፡ እደግ እደግ ብለን ያሳደግነዉ

ቀጋ፣ አለ ዘመም ዘመም እኛኑ ሊወጋ፡፡ የሚለዉ ይህ ቃል ግጥምም ይህንኑ ሕዝባዊ ስሜት፣ ተቃዉሞና ነቀፌታ የሚያመለክትና የመክዳት ስሜት የፈጠረዉን ቅሬታ የሚገልጽ ነዉ፡፡

6. ጎንደር ላይ ተወልደህ የፈራህ እንደሆን፣
   እናትህን ጠይቃት ዘር ቀይራ እንዳይሆን፡፡

የጎንደር ህዝብ በራሱ የሚተማመን የራሱን የማይሰጥ የሌላዉንም የማይነካ ጀግናና ኩሩ ህዝብ ነዉ፡፡ ጀግንነትን እያወደሰ ፍርሃትን የሚያወግዝ ከአያት ከቅድመ አያቶቹ የወረሰዉ ብርቅና ድንቅ ባህልና እሴት ያለዉ ነዉ፡፡ በተፈጥሮና በሳይንስ ህግ ጎንደር ተወልዶ ያደገ ሁሉ ጀግና ይሆናል የሚል አመክንዮ ተጠየቃዊነት የሚጎድለዉ ቢሆንም በዚህ ባህልና እሴቱ ፍርሃትን እያወገዘ ጀግንነትን በማወደስ የፈሪዉ ቁጥር እየቀነሰና የጀግናዉ ቁጥር እያደገ እንዲሄድ አስተዋጽዖ እንዳለዉ ግን የሚካድ አይደለም፡፡

ለዚህም ነዉ ሕዝቡ ጎንደር ላይ ተወልደህ የፈራህ እንደሆን፣ እናትህን ጠይቃት ዘር ቀይራ እንዳይሆን፡፡ በማለት የጎንደር አባት ፈሪ አይወልድምና ከሌላ ዘር ቀላቅላ ሊሆን ስለሚችል እናትህን ጠይቃት በማለት ፍርሃት የተጠናወተዉን ሰዉ በዜማዉ ይነቅፋል፡፡ በዚህ ቃል ግጥም የተቃጣበትን ጥቃት፣ የተጫነበትን ግፍና በደል፣ የወደቀበትን የህልዉና አደጋ የማይታገል ሰዉ ጎንደሬ አይደለም በሚል ፈሪና ወላዋዮችን የሚያወግዝና የሚነቅፍ ነዉ፡፡

7. ከቶ ምን ሊሆን ነዉ ፈሪ ማቶንቶኑ፣
   ቅጠል አይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ፡፡
8. እኔ ለፊሪ አልሰጥም ልብሴን
   ያስጠይቃታል በሰማይ ነፍሴን፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ሰባት እና ስምንት የቀረቡት ቃል ግጥሞች በተራ ቁጥር አምስት እንደተገለጸዉ ፍርሃትን የሚያወግዙ፣ የሚኮንኑና የሚነቅፉ ናቸዉ፡፡ ፈሪና ፍርሃት በሚወገዙበት ማህበረሰብ ዉስጥ ተወልዶ ማደግ ፍርሃትን ለመጠየፍ ብቻ ሳይን ለጀግንነትም በር የሚከፍት ነዉ፡፡ ግጥሞቹ ማንም ሰዉ ቀኑ ካልደረሰ ሊሞት እንደማይችል እና ፍርሃት አጉል በሽታ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ማህበረሰቡ ከፈሪ ጋር መዋዋል እንኳን በዚህኛዉ በዚያኛዉም ዓለም ያስጠይቃል ብሎ እንደሚያመን ያመላክታሉ፡፡

9. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ፣

ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡

ይህ ግጥም በተነጻጻሪ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት የቀረበ ሲሆን ለንጽጽር የቀረቡትም ወንድ ልጅና በሬ ናቸዉ፡፡ አጅሬ[23] የሚለዉ ቃል ለደፋር፣ ጎበዝ፣ ጀግና፣ ሳታናና ቆራጥ ሰዎች የሚሰጥ ቅጽል ስም ነዉ፡፡ እናም ወንድ ልጅ አካባቢና ማህበረሰቡን የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለበትና በማህበረሰቡ የሚለካዉም በዚህ የጀግንነት ባህሪና ተግባሩ በመሆኑ ከርሱ የሚጠብቀዉ ይሄዉ ማንነቱ ብቻ ነዉ፡፡

ስለሆነም ወንድ ልጅ ጀግና ካልሆነ በማህበረሰቡ በኩል የሚኖረዉ አቀባበል በግጥሙ ላይ እደተመላከተዉ በአመለካከት ደረጃም ቢሆን ከሰዉ ተራ አዉጥቶ በእንሰሳት ጎራ ሊያስመድበዉ ይችላል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ለፍርሃት ያለዉን ጥላቻና ንቄት፣ ዉግዘትና ነቀፌታ የሚያመላክት ነዉ፡፡ ማህበረሰቡ ፈሪን ጀግኖች ታግለዉ ድል በሚያስመዘግቡበት ጎራ ላይ ሳር እንደሚግጥ እንሰሳ አድርጎ በመሳል በዘፈን በእንጉርጉሮዉ ስለሚወርፈዉ ከፍርሃት ለመፋታት እድልና እንዲያገኝ ሊያደርገዉ ይችላል፡፡

10. በለዉ በለዉና አሳጣዉ መድረሻ፣

የሰዉ ልክ አያዉቅም ባለጌና ዉሻ፡፡

ባለጌና ዉሻ ዘለዉ ከሰዉ ላይ ጉፍ ይላሉ፡፡ የቆሙበት ምድር፣ የደረሱበት ስፍራ ሁሉ የነርሱ ስለሚመስላቸዉ በሰዎች ላይ ይጮሃሉ፡፡ የሰዉን ልጅ ክብርና ማንነትን አያዉቁም፡፡ ይሉኝታና ርህራሄ የላቸዉም፡፡ ለባለጌ ከሳቁለት ለዉሻ ከሮጡለት ሰዉን ማዋረዳቸዉን አይተዉም፡፡ ስለሆነም ቃል ግጥሙ ይህንን መሰል የዉሻ ባህሪና ድርጊት ያላቸዉን ሰዎች ያወግዛል ማንኛዉም ሰዉ ከዚህ ጥፋታቸዉ እንዲመለሱ ሊቀጣቸዉ ካልሆነም ከአካባቢዉ ሊያርቃቸዉ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

በዚህ ብያኔና ትርጓሜ አንድምታ ወስደን ቃል ግጥሙ በቀረበበት አዉድ ዉስጥ ስንመለከተዉ ደግሞ አምላኩን ፈርቶ፣ ህግን አክብሮና መንግስትን አምኖ ችግር፣ ብሶትና ቅሬታዉን በሆዱ ይዞ የተሻለ ቀን ይመጣል በሚል ትዕግስቱ የበዛዉ የአማራ ሕዝብ እንደፈሪ ተቆጥሯል፡፡ ይህንን ተከትሎም የሰዉ ልክ የማያዉቀዉ ባለጌ ሁሉ

---

[23] አጅሬ:- የሚለዉ ቃል ፍቺ ወኔያም, ጉብዝና ያለው, ቂጡ ቀበጥባጣ ,ዐመለ ሸካራ, በጉብዝና ተፈርቶና ተከብሮ የሚኖርን ሰዉ መለያና መጠሪያ ነዉ።

እንደዉሻ እየጮኸብን ይገኛል የሚል ቅሬታና ተቃዉሞ በማህበረሰቡ ዉስጥ በስፋት ይንሸራሸራል፡፡ ‹‹በለዉ በለዉና አሳጣዉ መድረሻ፣ የሰዉ ልክ አያዉቅም ባለጌና ዉሻ፡፡›› የሚለዉ ይህ ቃል ግጥምም ይህንን መረን የለቀቀ የባለጌዎች ዘለፋና ስድብ ለመቃወም፣ ለማዉገዝና ለትንኮሳዉም ምላሽ ለመስጠት  የተሰነዘረ ይመስላል፡፡

11. ዘንድሮ ኢትዮጵያ ታሪክ ተበላሼ፣

ባለክላሽ ቁሞ ባለመድፉ ሸሼ፡፡

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ ከገገርዎቿ የጎደለዉን በፈጣሪዋ እየሞላች መቻቻል፣ መከባበር፣ መተዛዘን አብሮ መብላትና አንዱ ለሌላዉ ማዘንን የተሰጠች ሀገር ነበረች፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘዉጌ ፖለቲካ አስተምህሮ ከእኛነት ይልቅ እኔነት፤ ከአብሮነት ይልቅ የእኛና እናንተ የመገፋፋት ፖለቲካ ግዝፈት ነስቶ አንዱ ሌላዉን በጥርጣሬ ማየትና ማሳደድ ከጀመረ ዉሎ አድሯል፡፡

ጀግናዉ ስመጥሩና ገናናዉ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ድንበርና ጠላት ጋር መዋጋትና በክብር በመዉደቅ የገነባዉን ስም፣ ዝናና ክብር በዘዉጌ ፖለቲካ አራማጆች ትዕዛዝ በእርስ በርስ ጦርነትና የመንደር ግጭት ዉስጥ እየተሳተፈ ከህዝብ ልብ ዉስጥ መዉጣት ጀምሯል፡፡ በዚህም ምክንያት በህዝቡ ላይ ላለመተኮስ በማያምንበት ግዳጅ ላይ መዝመት አስጠልቶት መሸሽና መማረክ የታጠቀዉን መሳሪያ አስረክቦ መክዳት ጀምሯል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ቁመህ ጠብቀኝ የታጠቀዉ አርሶ አደር ሁሉ ደፍሮ ይተኩስበት ጀምሯል፡፡ ይህ ሁኔታ የመከላከያ ሰራዊቱን ብቻ ሳይሆን የሀገርንም ክብርና ዝና የሚንድ የታሪክ መታጠፊያ ላይ መድረሳችንን ያመላክታል የሚሉ አስተያየቶችም ይሰነዘራሉ፡፡

“ዘንድሮ ኢትዮጵያ ታሪክ ተበላሼ ባለክላሽ ቁሞ ባለመድፉ ሸሼ” የሚለዉ ይህ ቃል ግጥምም ይህንን የታሪክ ጠባሳና የሰራዊታችንን ኢሞራላዊ ባህሪ በማዉገዝና በመንቀፍ በታሪክ አጋጣሚ ይህችን ሀገር ለመምራት እድሉ ያጋጠማቸዉ አካላት መፍትሄ ሊፈልጉለት ይገባል የሚል አንድምታ ያለዉ ይመስላል፡፡ እዚህ ላይ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠትና የነገሩን ክብደት ለመጠቆም የአንድን የሕዝብ አንቂ ትዝብት[24] መመልከት ተገቢ ነዉ፡፡

---

[24] አሳዬ ደርቤ
ሲያዘምቱበት ከርመው
አየር ሀይል፣ ባሕር ሀይል፥ ኮማንዶ እና እግረኛ፤
አለቀለት ሲሉ...

12. ዉሃ ቁልቁል እንጂ መች ሽቅብ ይፈሳል፣
ትንሽ ከፊት ሲሆን ሀገር ያሳንሳል፡፡

ይህ ቃል ግጥም ዉሃና ትንሽነትን በንጽጽር ያላቸዉን የጉዞ መስመርና የቁልቀለት መንገድ፣ የዉድቀትና የኪሳራ ጉዞ የሚያመላክት ነዉ፡፡ ዉሃ ቁልቁል እጂ ሽቅብ አይፈስም፤ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ በአነጋገር፣ በተግባርና በአመራር ብቃት የሌላቸዉ ሰዎች በታሪክ አጋጣሚ ከፊት ሲሆኑ ሙት ይዞ ይሞታል እንዲሉ ሕዝብና ሀገርን ያሳንሳሉ እንጂ ወደስኬት ጎዳና ሊያደርሱ አይችሉም ተብሎ ይገመታል፡፡

የግጥሙ ባለቤት ህብረተሰቡ ስለሆነ በተለያየ ጊዜና አግባብ ለሆታና ለዘፈን ማድመቂያና ስርአትና አመራሩን ለመተቸት ተጠቅመዉበታል፡፡ ለአብነት የህወሓት ኢሕአዴግን የቁልቁለት ጉዞ እና አመራሩን ዝቅጠት ለማዉገዝና ለመተቸት አገልግሏል፡፡ ስርዓቱና አመራሩም ቢሆኑ በየአደባባዩ ታላቅ ነበርን ታላቅም እንሆናለን እያሉ ሕዝብና ሀገሪቱን በቋንቋ ከፋፍለዉ ትንሽ በማድረግ ተወግዘዉና ተችተዉ ከስልጣን መንበራቸዉ ተወግደዋል፡፡

13. መስሎ ማደር ይብቃ ለእዉነት እንኑር፣
ወሎ ላይ ተወልደን ካሳምነዉ ሃገር፡፡

14. ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፣
ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፡፡

15. አትግፋኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ
እንኳን የሰዉ ሀገር የራሴን ትቻለሁ፡፡

16. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነዉ
ከተጣሉ ወዲ ድርድር ምንድነዉ?

17. የተላላኪዎች ሆድ ነዉ አምላካቸዉ
ሐገር ስትደፈር ቅርም አይላቸዉ፡፡

18. ትመታ እንደሆነ እኛን አይተህ ምታ፣
የማትመታ እንደሆን ልቀቅ የሰዉ ቦታ፡፡

---

"ይሄ ፎጣ ለባሽ ፥ የአማራ ነፍጠኛ"
በክላሽ፣ በሱኪ
በአልቤን፣ በውዥግራ፥ ቀይ ቦኔት ደምስሶ፤
ዲሽቃ እየተኮሰ
ሞርታር እያሽካካ ፥ መጣ ተመልሶ።

ከላይ ከተራ ቁጥር አስራ ሦሥት እስከ አስራ ስምንት የቀረቡት ቃል ግጥሞች ዉሸትና ዋሾዎችን፣ ተላላኪና ባንዳዎችን፣ ቅጥረኝነትና ቅጥረኛን፣ ሆድን ሞልቶ ለማደር ጠላትን መስሎ ማደርና መገፋፋትን፣ በሁለት ቢለዋ ወገናቸዉን በመገዝገዝ እርም እየበሉ ለጠላትም ለወዳጅም የሚዋጉ አካላትንና ጠላትን ፈርቶ እርቅ መጠየቅን የማዉገዝና የመተቸት ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

በአንድ ሀገርም ሆነ በአንድ ክልልና አካባቢ ሕዝብ ተበደለ፣ ፍትህ ተጓደለ፤ የመልካም አስተዳደር ችግር አጋጥሞናል፣ የልማት ተቋዳሽ አልሆንም እና ልክ በአማራ ክልል እንደሚታየዉ ሁሉ የህልዉና ችግር ደርሶብኛል በሚል በስልጣን ላይ ያለዉን ስርዓት የሚቃወሙ፣ የሚተቹና ለትግል የሚሰለፉ አካላት የመኖራቸዉን ያህል በአንድም ሆነ በሌላ በሌላ መልኩ በሥርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ፣ የሀገራቸዉ መደፈር፣ የሕዝባቸዉ መበዝበዝ፣ መሳደድና መገደል፣ የማይቆጫቸዉ አካላት ይኖራሉ፡፡

እነዚህ አካላት በቅጥረኝነትና በተላላኪነት ለጠላት የሚያገለግሉ፣ ከሥርዓና ከጠላት ባይጠቀሙ እንኳን ጠላትን መስሎ በማደር ጊዜ እስኪያልፍ የአባትህ ባሪያ ይዛህ በሚል ፈሊጥ እየተመሩ ተመሳስለዉ ለማደር፣ ግፍና በደሉን ችለዉ ለመኖር የሚወስኑ ከጠላትም ከወዳጅም ጎን ሳይሰለፉ መሃል ሰፋሪ ሆነዉ ለሸናፊዉ አካል ለመገዛት ራሳቸዉን የሚያዘጋጁ አካላት ናቸዉ፡፡

ችግሮቻችን ይፈቱ፣ ሰላምና ደህንነታችን ይረጋገጥልን ሳይሆን በፍርሃት በዳይ በበደሉ ተበዳይም በስቃዩ ጸንቶ እንዲኖር ታረቁ፣ አንደኛ ሁሉን ችላችሁ ኑሩ፣ ሰላም በትግል ሳይሆን በጊዜ ብዛት ያልፋልና ለትግል አትሰለፉ የሚሉ፣ ትግልን አጥብቀዉ የሚፈሩ ናቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ ለዝሕብ እንታገላለን ብለዉ ዱር ቤቴ በረሃ እርስቴ ብለዉ የወጡ አካት በአሸናፊነት ከወጡ እንደለመዱት በተላላኪነት፣ በባንዳና እና በቅጥረኝነት ለማገልገል ቀድመዉ የሚሰለፉ ናቸዉ፡፡ ለዚህም ነዉ ኅብረተሰቡ በቃል ግጥሞቹ አጥብቆ በማዉገዝና በመተቸት ከጥፋታቸዉ እንዲመለሱ ወይም ትግሉን ከማደናቀፍ እንዲቆጠቡ የሚያስጠነቅቃቸዉ፡፡

በመጨረሻዉም ***"ትመታ እንደሆነ እኛን አይተህ ምታ የማትመታ እንደሆን ልቀቅ የሰዉ ቦታ"*** በሚል የቀረበዉ ቃል ግጥም ደግሞ ከሌሎቹ ግጥሞች በተለየ መልኩ ወደትግል ጎራዉ ተቀላቅለዉ ነገር ግን ትግላቸዉ የግል ጥቅማቸዉን፣ ፍላጎትና የተቃራኒ ኃይሎችን ዓላማ ለማሳካት በህቡዕ የሚታገሉ አካላትን አስተሳሰብና ድርጊት የሚያወግዝና የሚተች ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ ከታገላችሁ እንደኛ ፈር ይዛችሁ ለዝሕቡና

ለሀገራችሁ ታገሉ ካልሆነላችሁ ከትግሉ ጎራ ገለል በሉልን እምቢ ካላችሁ ከቦታችን ገለል ለማድረግ እርምጃ ለመዉሰድ እንገደዳለን የሚል አንድምታ ያዉ ነዉ፡፡

## 4.2.7.የሕዝቡን ፍላጎትና ምኞት የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች ትንተና



*በ2016 ዓ.ም በእድር ሜዳ ጥምቀተ ባሕር በባህላዊ አለባበስ የደመቁ ወጣቶች የዘፈንና የጭፈራ ቡድን አባላት*

ስነቃል በፖለቲካው መስክ በአንድ በኩል ገዢው ስርዓቱን የሚያስከብርበት፣ በአንፃሩ ደግሞ ተገዢው በገዢው ላይ ያለውን ብሶት የሚገልፅበትም ነው፡፡ ህዝብ ስልጣን ላይ ስላለው መንግስት አስተዲራዊና ፖለቲካዊ ስርዓት የተሰማውን ስሜት፣ የሚመኘውን አይነት አስተዳደር የሚገልጽበት ነው፡፡ ገዥው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ህዝብ ጥላቻውን ይገልፅበታል፤ መልካም ከሆነ ደግሞ ያወደስበታል፡፡ ስነቃል ከተለለያዩ የልማት ፖሊሲዎችም ጋር በማያያዝ የህዝቡን ፍላጎት በማጥናትና በህዝቡም ውስጥ የቅስቀሳ ስራ ለመስራት የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ በስራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችንም ለማጥናትና በጊዜ ለመፍታት መንገድም ይከፍታሉ (ፈቃደ፣1995፣17-20)፡፡

ከዚህ በያ በመነሳትም በዚህ የመጨረሻዉ ዐብይ ምድብ ስር ተሰብስበዉ የተተነተኑ ቃል ግጥሞችም የህዝቡን ፍላጎት፣ ምኞት፣ አቋምና አስተሳሰብ የሚያንጸባርቁ ስለመሆናቸዉ የሚያጠራጥ አይደለም፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ በህወሓት እና በፋኖ መሪነት ከመንግስት እና ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር ከተደረገዉና እየተደረገ ካለዉ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የፍትህና እኩልነት ጥያቄና

አለመረጋጋት ጋር ተያይዞ ሕዝቡ የተሰማዉን ስሜት፣ የፈጠረበትን ስጋት፣ ፍላጎትና ምኞት የማመለካከት ፋይዳ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

1. እስኪ መጀመሪያ ሀገር ደህና ትሁን፣
   እስኪ መጀመሪያ እኛ ደህና እንሁን፣
   ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ይሰራናል አሁን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአብነትም አማራ ህግን የሚፈራና የሚያከብር፣ ዳኛ በሌለበት በህግ አምላክ!! በባንዲራዉ አምላክ!! ብሎ ወይም የነገስታቱን ስም ጠርቶ ጥቃትን የሚያስቆም ለፍትህና ለህግ ጥብቅና የሚቆም ሕዝብ ስለመሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል፡፡ በሌላም በኩል ይሉንታና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለዉ በመሆኑ ህግና ፍትህ እንኳን ባይኖር የህሊና ወቀሳና ፈጣሪን አምኖና ፈርቶ፣ ከክፉ ነገር ርቆ በጎዉን የሚከተልና የራሱን የማይሰጥና የሌላዉን የማይፈልግ ሕዝብ ነዉ፡፡ ለዚህም ይመስላል በአሁኑ ወቅት ከላይና ከታች የጦርነት አረር እየወረደበት፣ በድርቅና በበሽታ፣ በስደትና መፈናቀል እየተንገላታ ፈጣሪዉን ተስፋ በማድረግ ከራሱ ይልቅ ቅድሚያ ለሀገሩ ደህንነት የሚቆረቆረዉ፡፡

ከላይ በቀረበዉ ቃል ግጥም ***"እስኪ መጀመሪያ ሀገር ደህና ትሁን፣ ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ይሰራናል አሁን"*** በማለት የዛሬዉን በደልና ስቃይ ሳይሆን የነገዉን ተስፋ እያሰበ ስለሀገርና ስለራሱ ደህንነት የሚጨነቀዉ ከዚህ ጠንካራ እምነቱ የተነሳ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሕዝብ ሐገር ደህና ከሆነች፣ ለሕዝቡ ፈጣሪ እድሜና ጤና ከሰጠዉ ጊዜ መሃንድስ ነዉ ብሎ ስለሚያምን ሁሉም በጊዜ ብዛት መቀየሩ አይቀርም ብሎ ያምናል፡፡ የተሻለ ነገር ይመጣል፣ የተቸገረ ያልፍለታል፣ የተራበ ይጠግባል፣ የሚበድል ይጠፋል የተበደለም በጊዜ ይካሳል የሚል እምነትና ፍላጎት እንዳለዉ በጥምቀት በዓል ላይ የተዜመዉ ይህ ቃል ግጥም ይጠቁማል፡፡

2. ቀረርቶ ብቻ ነዉ ሲሉን እንዳልኖሩ፣
   ፎክረን ስንተኩስ ዛሬስ ምን አወሩ፡፡

መልካም ታሪክና የአሸናፊነት ሥነልቦና ያለዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአባቶቹ ገድል እየኮራና እየፎከረ የዛሬዉን ድል በትናንትና ባህልና እሴቱ ያጅባል፡፡ ሽለላና ፉከራ ደግሞ በተለይም ለአማራ ሕዝብ የባህሉና የታሪኩ ማድመቂያ፣ የጀግንነቱ መፍለቂያና የስኬቱ መፈንደቂያ ማህበራዊ ዕሴቶቹ ናቸዉ፡፡ ጥንት በአድዋና በኦጋዴን፣ በቅርብ

ጊዜም በባድመና በጸረና፣ ዘምቶ እየሸለለና እየፎከረ ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር በመሆን ጠላትን ከነክፉ ሴራዉ አሸንፏል፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ጠንካራ ሥነልቦና ለሕዝብ ሰላምና መረጋጋት፣ ለሀገር ሉአላዊነት መከበር እንዲጠቀምበት ከማበረታታት ይልቅ እንደ ጽንፈኛና ትምክህተኛ እየተቆጠረ የጠላትነት ፕሮፓጋንዳ እየተሰራጨበት ይገኛል፡፡ ከላይ የተጠቀሰዉ ቃል ግጥም እንደሚያመለክተዉም ህዝብ ተበደለ፣ ፍትህ ተጓደለ የሚለዉን ጥያቄና አትግደሉኝ የሚል ጩኸቴ ተራ ፉከራና ቀረርቶ ተደርጎ ተቆጥሮብኛል ብሎ ያምናል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በጠላት ላይ የሚያነሳዉን ክንዱንና ትጥቁን በወገኖቹ ላይ እንዲያነጣጥር፣ በወንድሞቹም ላይ እንዲተኩስ መገደዱንም ይጠቁማል፡፡ ቀረርቶ ብቻ ነዉ ሲሉን እንዳልኖሩ፣ ፎክረን ስንተኩስ ዛሬስ ምን አወሩ፡፡ የሚለዉ ይህ ቃል ግጥም ሳይወድ በግዱ ወደትጥቅ ትግል ገፋፍተዉ እንዳስገቡትና በእርስ በርስ ጦርነቱ የተፈጠረዉን አስከፊ ገጽታ ለማመላከት የቀረበ ይመስላል፡፡

3. አይ አማራ ክልል አቤት ወይ እድልህ፣

እንዲያዉ መቼ ይሆን ቀን የሚወጣልህ!?

የአማራ ሕዝብ በአጼዎቹ ዘመነ መንግስት እንደማንኛም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካመረተዉ ምርት ሲሶዉን ወስዶ እርቦዉን ለፊዉዳሎቹ ከመገበር ባሻገር በጉልበቱም በነጻ እንዲያገለግልና በበዓላት እየተሳበበ የእጅ መንሻ በመስጠት ድርብ ጭቆና የደረሰበት ሕዝብ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በደርግ ሥርዓት መንግስት ደግሞ አርሶ አደሩ በሕብረት ስራ ማህበራት በግዱ እንዲደራጅ፣ ያመረተዉን ምርት በርካሽ ዋጋ እንዲሸጥና ልጆቹን ለብሔራዊ ዉትድርና መርቆ እንዲልክ እየተገደደ ሀገር አስከባሪና ድንበር ጠባቂ ሆኖ ኖሯል፡፡ በተመሳሳይ በዘመነ ህወሃት ኢህአዴግ ከዉስጡ የወጡ ፊዉዳሎች ጨቁነዉናል በሚል የሴራ ፖለቲካ ጭቁኑ የአማራ ሕዝብ እንደጨቋኝና በዝባዥ የሚያሥቆጥር የፈጠራ ትርክት ከጀርባዉ ላይ ተለጥፎበት ተሸማቆ እንዲኖር ተደርጓል፡፡ አሁንም እንደ ሕዝብ ግፍና መከራዉ ተጠናክሮ በመቀጠሉ የመጥፋትና የህልዉና አደጋ ዉስጥ ወድቀናል ብሎ ያምናል፡፡

የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ይህንን ታሪካዊ የዘመናት የጭቆና፣ የብዝበዛ፣ የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የሰላም፣ መረጋጋትና የህልዉና ችግር በመገንዘብና የህብረተሰቡን ስሜት ለማንጸባረቅ ይመስላል "አይ አማራ ክልል አቤት ወይ እድልህ፣

እንዲያዉ መቼ ይሆን ቀን የሚወጣልህ?” በማለት የዘፈንና በሆታዉ ደጉን ጊዜ እየተመኘና እየናፈቀ ያዜመዉ፡፡

4. እዘምታለሁ እንጂ አንጀቴን አስሬ
   እንዴት ዝም ልበል ሲደፈር ሀገሬ፡፡
5. ምን አለ? ሸዋ ምናለ?
   ምን አለ? ጎንደር ምናለ?
   ምን አለ? ጎጃም ምናለ?
   ምን አለ? ወሎ ምናለ?
   ሐገሬን ለሰዉ አልሰጥም አለ፡፡
6. የሚሾመዉ ሁሉ ባንዳ ሁኗልና፣
   አማራ መሪ አጥቶ ተበትኗልና፣
   አሳምነዉ ጽጌ ቶሎና ቶሎና፡፡
7. መተከል ራያ ወልቃይት ሀገሬ
   ያማራ ርስት ነዉ ጥንትም ሆነ ዛሬ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አራት እስከ ሰባት የቀረቡት ቃል ግጥሞች በአማራ ክልል የተፈጠረዉን የሰላምና መረጋጋት እንዲሁም የግዛት አንድነት ጥያቄ፣ ታማኝ መሪ የመሻትና ራስን የመከላከል አስፈላጊነትና ግዴታን የሚያመላክቱ ናቸዉ፡፡ ለአብነት በተራ ቁጥር አምስት የቀረበዉ ቃል ግጥም አማራ አጽመ ርስቱን በጉልበት ተቀምቶ እንደነበረና በህወሓትና በፌዴራሉ መንግስት ግጭት ታሪካዊ አጋጣሚ ግዛቴን በጉልበቴ አስመልሻለሁ ከዚህ በኋላ ርስቴን ለማንም አሳልፌ አልሰጥም ብሎ እንደሚያምንና ይህ እምነቱም የድፍን አማራ እንጂ ግዛቱ ወደሌሎች ክልሎች የተካለለበት አከባቢ ብቻ እንዳልሆነ ይጠቁማል፡፡

ይህንንም ተከትሎ መብትና ነጻነቱን የሚያስከብርለት፣ የግዛት አንድነቱን የሚያረጋግጥለት፣ ከባንዳነት፣ ከተላላኪነትና ከአድርባይነት ነጻ የሆነ እንደራሴ እንደሌለዉና በክልሉ የሚሾሙት አመራሮች ላይም እምነት በማጣቱ የኔ የሚለዉ እንደ አሳምነዉ ጽጌ አይነት ቆራጥና ለክልሉና ለሕዝቡ ዘብ ቆሞ የሚሟገትና በክብር የሚሰዋ ጀግና መሪ እንዲናፍቅ እና እንደሚፈልግ ይጠቁማል፡፡ ይህንን ፍላጎትና ምኞቱን ለማረጋገጥ፣ የክልሉንና የሕዝቡን ግዛታዊ አንድነት፣ ኢተነጣጣይነት፣ ሰላምና

መረጋጋት መልሶ ለማምጣት ችግርና ስቃዩን ችሎ ራሱን ለትግል ዝግጁ እንዳደረገም በተራ ቁጥር የቀረበዉ ቃል ግጥም ያረጋግጣል፡፡

8. እንኳን አሁንና እስካፍንጫ ታጥቀን
   ባሮጌ ምንሽር ታንክ እንማርካለን፡፡
9. ከእንግዲህ አይኖርም አማራ ታፍኖ፣
   የቁርጥ ቀን ልጁ እያለለት ፋኖ፡፡
10. ትጥቄ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ
    በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ፡፡
11. ተዉ አትከልክሉኝ ልዉጣ ከቤቴ፣
    ዝም ስላልኩኝ በዝቷል ጠላቴ፡፡
12. ይዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
    ፋኖ ቁሞ አያይም ሲደፈር ሀገሩ፡፡
13. ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣
    አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር ስምንት እስከ አስራ ሦሥት የቀረቡት ቃል ግጥሞች አማራ ጭቆና፣ ብዝበዛ፣ አፈና፣ ስደት፣ መፈናቀል፣ ሰብአዊና ቁሳዊ ሃብት ዉድመት ደርሶብኛል ብሎ እንደሚያምንና በመንግስትና በሥርዓቱ ላይ ቅሬታም እንዳለዉ ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሕዝቡ በሰላማዊ ሰልፍ ለጠየቀዉ ጥያቄ የተሰጠዉ መልስ አሉታዊና የንቄት በመሆኑ የተሻለ የትግል አማራጭ አጥቶ፣ ወደትጥቅ ትግል እንደገባ፣ በድህነቱ አንጀቱን አስሮ አሮጌ ምንሽር፣ አልቤንና መዉዜር ታጥቆ እንደዘመተና ይህንን ትጥቁን መፍታት እንደማይፈልግ ያረጋግጣሉ፡፡ ህግ ለማስከበር በሚል በክልሉ ላይ የተጀመረዉን ዘመቻ የታወጀዉን አዋጅና የሚደረገዉን ጦርነት እንደወረራ እንጂ እንደሰላም ማስከበር እንደማይመለከተዉም ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም ምክንያት በትግል አዉድማዉ ላይ ቆርጦ በመታገል ባልቤን በመዉዜሩ ዘመናዊ ትጥቅ ማርኮ እስካፍንጫዉ እንደታጠቀ፣ እንኳን እስካፍንጫዉ ታጥቆ በአሮጌ ምንሽር ታንክም የመማረክ ልማድ እንዳለዉም ይነግሩናል፡፡ እጅና እግሩን አጣጥፎ እቤቱ መቀመጡ፣ በትዕግስት አንገቱን መድፋቱ ስላስናቀዉና መዚህም ምክንያት ጠላቱ ስለበዛ ለትግል ለመነሳት መወሰኑን ያብራራሉ፡፡ ***"ይዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ፣ ፋኖ ቁሞ አያይም ሲደፈር ሀገሩ"*** እና ***"ከእንግዲህ አይኖርም አማራ***

***ታፍኖ፣ የቁርጥ ቀን ልጁ እያለለት ፋኖ"*** የሚሉት ኹለት ቃል ግጥሞች ትግሉን እየመራ ያለዉ ፋኖ የተባለዉ ነባር አደረጃጀትና እንደ አዲስ ወጣቱ ትኩስ ኃይል በስፋት ስለተቀላቀለዉ የተጠናከረዉ የአማራ ሕዝባዊ ኃይል ሕዝቡ እንደብቸኛ አዳኝ ሀይል አድርጎ እንደተቀበለዉ ይህም የፌደራሉና የክልሉ መንግስታት በተከተሉት የተሳሳተ መርህ ምክንያት የፋኖ ትግል የአማራ ሕዝብ ትግል ለመሆኑን መብቃቱን ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም አማራ በኢትዮጵያዊነቱ ሲኮራ እንጂ በብሄር ሲደራጅ አያምርበትም!! የትምክህተኛዉ፣ ነፍጠኛዉና ጽንፈኛዉ ፋኖ ትግል ኢትዮጵያን ያፈርሳታል፣ ፋኖ ጽንፈኛ ዘራፊ ቡድን (ጃዊሳ) ነዉ ለሚሉ ወገኖች ***"ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣ አፍርሷ አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ"*** በማለት የአማራ ትግል ለኢትዮጵያ መድህን እንጂ ሀገር አፍራሽ እንደማይሆን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

14. የራያ ልጅ ታሞ ወሎ ከሚጨነቅ፣
 ወልቃይትም ታሞ ጎንደር ከሚጨነቅ፣
 አንድ ሽህ ወያኔ ሆዱን ታሞ ይለቅ፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ሊተላለፍ የተፈለገዉ ሃሳብ በህወሓት ትንኮሳ ምክንያት በሰሜኑ የሐገራችን ክፍል በተጀመረዉ ጦርነት የአማራ ሕዝብ ገፈት ቀማሽ እንደነበረ የባለቤትነት ጥያቄ የሚነሳባቸዉን ራያና ወልቃይት ለአብነት የሚጠቅስ ነዉ፡፡ የኢሰመኮ ሪፖርት[25] እንደሚጠቁመዉ በዚህ ጦርነት ህወሓቶች በተለይ በአማራ ክልል ባደረጉት ወረራ ተቋማትን አዉድመዋል፡፡ ሀብትና ንብረት ዘርፈዋል፡፡ ሰላማዊ ነዋሪዉን ወንዱን እየገደሉና ሴቱን እየደፈሩ የበቀል እርምጃ ወስደዋል፡፡

ስለሆነም የቃል ግጥሙ ይዘትና ጭብጥ እነዚህ በአማራ ሕዝብ ላይ አስከፊ ጦርነት የከፈቱ አፈንጋጭ የፖለቲካ ሃይሎች እንጂ የአማራ ሕዝብ ሊጨነቅ አይገባም የሚል

---

[25] ኢሰመኮ:- በሀገሪቱ የተከሰቱ ግጭቶችን ተከትሎ በግጭቶቹ ተሳታፊ የነበሩ ኃይሎች በበርካታ ሴቶች እና ሕፃናት ላይ መጠነ ሰፊና ስልታዊ በሆነ መንገድ፣ የተናጠል እና የቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃትን ጨምሮ፣ አካላዊ ጥቃቶችን፣ ግድያን እና የማሰቃየትን የመሳሰሉ አስከፊ ጥቃቶችን ፈጽመዋል። እነዚህ ጥቃቶች አንዳንዶቹ ሰብአዊ ክብርን ለማዋረድ ሆን ተብሎ ታቅዶ በግልጽ የበቀል ስሜት የተፈጸሙ በመሆናቸውና በጦርነት አውድ ውስጥ በመፈጸማቸው የጦር ወንጀል ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። የተፈጸሙት ወሲባዊ ጥቃቶች ሕፃናትን ለሞት፣ ለአካልና ለሥነ ልቦና ጉዳት እንዲዳረጉ፣ ቤተሰቦቻቸው ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን ጥበቃ እንዲያጡ ምክንያት ሆነዋል። www.ehrc.org የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት

እንድምታ ያለዉ ነዉ፡፡ አንድም ደግሞ በፈሊጣዊ አነጋገር ሆዱን ታሞ ይለቅ ሲል ወያኔንና የህወሓት አመራሮችን ቅሬታ ይሰማቸዉ፣ ይጭነቃቸዉ ይክፋቸዉ እንጂ ወሎና ጎንደር ሊጨነቅ አይገባም፡፡ የአማራ ሕዝብ በጋራ ቆሞ ራሱን ለመከላከል አያንስም የሚል አንድምታም ያለዉ ነዉ፡፡

15. ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣

ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም አማራ፡፡

እንደሚታወቀዉ ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሑመራ ትናንትናም ሆነ ዛሬ የየሀገራችን የግጭት፣ ፖለቲካና የጦርነት የስበት ማዕከላት ናቸዉ፡፡ ይህ አካባቢ ለዘመናት የጎንደር ግዛት ሆኖ ከኖረ በኋላ ህወሓት በ1982/3 ዓ.ም ጎንደርን በከፊል ሲቆጣጠር ይህም ማለት ህገመንግስቱ ከመጽደቁ ከአራት አመታት በፊት የትግራይ ግዛት አድርጎ የከለለዉ አካባቢ ነዉ፡፡ በሌላም በኩል ሱዳን አዋብቃ የምትመኘዉና በተደጋጋሚ ለመዉረር ሙከራ የምታደርግበት የአልፋሽቃ ለም መሬትንም የያዘ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ህወሓት ከመላዉ የሀገሪቱ ክፍል ከሚዘርፈዉ ሀብት እና ንብረት በተጨማሪ ከዚህ አካባቢ ለም ምድር በሚያፍሱት ሰሊጥ ሐብታም የሆኑበትና ከኢትዮጵያ ተገንጥለን ብንኖርም ህዝባችንን ለመመገብ የሚያስችል ግዛትና አቅም ይኖረናል ብለዉ የሚመኙት አካባቢ ነዉ፡፡ ይህንን ታሪካዊና ፖለቲካዊ እዉነታ ተከትሎ ወልቃይት ጠገዴ ዳናሻና ሁመራ አካባቢዉ የኢትዮጵያ ታላቁ ክፍል የሆነዉ ጎንደር ህዝቡም የአማራ ልጅ ጎንደሬ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቀደም ሲል ትግራይን ያስተዳደሩ አባቶች[26] ጭምር በቃላቸዉ ያረጋገጡት እዉነት ስለሆነ ህወሓትና መንግስት ኹለቱም ሕዝቦች ተስማምተዉ በጋራ እንዲኖሩ ለማድረግ እንዲሰሩ የሚጠይቅና ሀቁን የሚነግር ወቅታዊ የህዝብ እስትንፋስ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

[26] የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩት ልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ በሰጡት ቃለምልልስ ትግሬ ከተከዜ ምላሽ አስተዳድሮ አያዉቅም አሁን ያመጣችሁትን ፖለቲካ አላዉቅም ሲሉ ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ማጠቃለያ ሐሳብና አስተያየት

በዚህ የጥናቱ የመጨረሻዉ ዐብይ ክፍል በሆነዉ ምዕራፍ አምስት ስር የጥናቱ ማጠቃለያ ሐሳብ፣ አስተያየቶችና በጥናቱ ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች ፋይዳ ተመርምሮ የተደረሰበት ግኝት እንደሚከተለዉ ተመላክቷል፡፡ ቃል ግጥም የማኅበረሰቡ የጋራ ሀብት ነው፤ የጋራ ስለሆነም የጋራ ተቀባይነት ያለው ተፈጥሮ አለው በመሆኑም ከዚህ ተፈጥሮዉ አያፈነግጥም፣ በአዉድና በነገሮች ክብደት አይደነግጥም፤ ባለማፈንገጡ ከማኅበረሰቡ እውነታዎች ውጭ አይዘልም፣ ባለመደንገጡ የማኅበረሰቡ የሆኑ እውነታዎችን ችላ ብሎ አያልፍም፡፡ ስለሆነም ታሪክን ቀርሶ ያስቀምጣል፣ ባህልን ለትዉልድ ያስቀጥላል፣ ትውልድን ከትውልድ ያጋምዳል፡፡ የሕዝቡን አመለካከት፣ ስሜትና የዘመኑን መንፈስ ለዛ ባለዉ ጥበቡ ያንጸባርቃል፡፡

በኢትዮጵያ የሕዝቡን አመለካከትና ስሜት እንዲሁም ሥለሕዝብና መንግስት መግባባት የሚያመለክት የሕዝብ አስተያየት የሚሰፈርበት ዘመናዊ ቁና የለም። ስለሆነም በዚህ ጥናት ባህላዊና ማኅበራዊ ዕሴቶቻችንን ለአብነትም ሕዝቡ የልቡን የሚናገርበትን፣ በፍርሃትና በአድርባይነት የማይበገረዉንና ያልተበረዘ እና ያልተከለሰ የሕዝቡን አመለካከት፣ ስሜትና አስተያየት ለመገንዘብ የቃል ግጥም እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገል እንደሚችል ተመላክቷል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ተሰብስበዉና ተደራጅተዉ ትንተና የተደረገባቸዉ ቃል ግጥሞች በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ በጥምቀት በዓል ላይ በተለይም በየካ ክፍለ ከተማ በሦሥት የታቦታት ማደሪያ ስፍራዎች በዓሉን በባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ለማጀብ በታደሙ አስር የባህል ጨዋታ ቡድኖች በአማርኛ ቋንቋ የተዜሙ ናቸዉ፡፡

እነዚህ ቃል ግጥሞች የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊና ሥነልቡናዊ የሆኑ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎች የሚያንጸባርቁ በመሆናቸዉ የማመስገንና የማወደስ፣ የምክርና የማስጠንቀቅ፣ የመቀስቀስና የማነቃቃት፣ ባህልና ማህበራዊ ጉዳዮችን የማጠናከር፣ የመቃወምና ቅሬታን የማንጸባረቅ፣ የማዉገዝና የመንቀፍ እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎትና ምኞት የመግለጥ ፋይዳ ያላቸዉ ቃል

ግጥሞች በሚሉ አበይት ክፍሎች ተደራጅተዉ ከሚያሥተላልፉት መልዕክት፣ ይዘትና ፋይዳ አንጻር ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ በትንታኔዉም ቃል ግጥሞቹ የኅብረተሰቡን ስሜት፣ ፍላጎት፣ ጥያቄ እና አመለካከት የሚያንጸባርቁ፣ የዘመኑን መንፈስ፣ የሕዝቡን ሥነልቦና፣ የሀገርና የሕዝቡን ወቅታዊ ገጽታ የሚያመላክቱና የሀገረሰባዊ እሴቶቻችንንና የባህሎቻችንን እምርታ የሚያመላክቱ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በተለይም ወቅታዊ ችግሮችን መነሻ አድርገው የተፈጠሩት ቃል ግጥሞች ማኅበረሰቡ ያለበትን ሰው ሰራሽ ችግሮች የፈጠሩትን ስጋት፣ ሕዝቡ የተሰማዉን ስሜትና ያለዉን አመለካከት በብቃት ለማሳየት የቻሉ ናቸው። የሰው ልጅ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ብዙ ጊዜ በግጭት የተሞላ ነው። ለዚህ ምክንያቱ በሀሳብ ያለመግባባት፣ አንዱ ሌላዉን ለማስገበርና ምጣኔ ሀብትና ሥልጣን ለመቆጣጠርና አንዱ የሌላውን መብት በሀይል ለመጣስ የመሞከር አባዜ የሚፈጥዉ ጦስ ነዉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በአፍሪካ ቃል ግጥሞች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚንጸባረቅና፣ በብዙ ምክንያቶች ግጭቱ ወደ ትግል ወይም ወደ ጦርነት የሚያመራ መሆኑን (Okpewho 1992፡ 151) ያስረዳሉ። በዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች መካከል በሀገራችን የታዩት ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግሮች ግጭትን ሊፈጥና ወደጦርነትም ሊያድጉ እንደሚችሉ የሚያመለክቱ ቃል ግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ።

ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች ከትዉልድ በቃል የተላለፉትን በማስታወስ ቀደም ሲል የተነገሩትን እንዳለ በመዉሰድና በማሻሻል በአመዛኙ ግን ለዘመኑ፣ ለነባራዊ ሁኔታና ለክወና አዉዱ በሚመጥን መልኩ በአዲስ መልክ ተደርሰዉ የተዜሙ ናቸዉ፡፡ የቃል ግጥሞቹን ተስተላልፎ ስንመለከት ከቀደመዉ ትዉልድ ወደአሁኑ ትዉልድ፤ ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላዉ አካባቢ፤ ከአንዱ ከዋኝ ወደሌላዉ ከዋኝ በቃል በመተላለፍ መዜማቸዉ እንዳለ ሆኖ ማህበራዊ ሚዲያዉ የክዋኔዉን ሙሉ ገጽታና ቃል ግጥሞችን በሰዓታት ዉስጥ በመላዉ ሃገሪቱ በማሰራጨት ረገድ ትልቅ ሚና ነበረዉ፡፡

ለአብነትም "የቄስ ቀበሌዉ ልጅ የፋፉ ያፋፉ እየገፋዉ መጣ እየደፋዉ ባፉ"፣ "ወለጋ ሕዝብ ሲያልቅ ያላወጇ አዋጅ፣ ምን ብልጽግና ነዉ ብልግና ነዉ እንጂ"፣ "መቃጠልህ ቢኖር አይሞቅህም ወይ? ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ!" የሚሉት ቃል ግጥሞች ወልድያ ላይ በነበረዉ የጥምቀት በዓል ክዋኔ ላይ የተዜሙ ሲሆኑ በሰዓታት

ዉስጥ አዲስ አበባ ላይ በተደረገዉ ተመሳሳይ የክዋኔ አዉድ ላይ ለዉጥ ሳይረግባቸዉ ተቀንቅነዋል፡፡

በ2015 እና በ2016 ዓ.ም በጥምቀት በዓል ላይ የታየዉ የክወና አዉድና የተዜሙት ቃል ግጥሞች ፎክሎራዊ ገጽታቸዉ የጎላና የሥነቃል ባህርያትን ያሚሉ ሆነዉ ትዉልዱ የአባቶቹን ማህበረ ባህላዊ አስተምህሮ የከለሰበትና መብቱን ለማስከበር የተጠቀመበት፣ ማህበረ ባህላዊ እሴቶቻችን ጎልተዉ የተስተዋሉበት ነበር፡፡

በጥናቱ የተተነተኑት የአማርኛ ቃል ግጥሞች በብዛት የአማራን ክልልና ሕዝብ፣ ወቅታዊና ታሪካዊ የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን የሚያንጸባርቁ ሆነዉ ታይዋል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ አንድም አቀንቃኞቹ አማራ በመሆናቸዉና ባህሉም የአማራ በመሆኑ፤ አንድም ደግሞ በሀገራችን በተከሰቱት የመልካም አስተዳደር ችግሮችና ጦርነቶች የአማራ ሕዝብ ገፈት ቀማሽ በመሆኑና ከክልሉ እየተፈናቀለ በአዲስ አበባ እየኖረ በመሆኑ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ብሔር ተኮር አፈሳ፣ እስራትና ቤት ፈረሳዎች ተጠቂ የሆነዉ አማራ ከመሆኑ ጋር የተያያዙ ስለመሆኑ ቃል ግጥሞቹ ያመላክታሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ተሰብስበዉና በሰባት አበይት ክፍሎች ተደራጅተዉ የተተነተኑት የአማርኛ ቃል ግጥሞች የሚከተሉት ዋና ዋና ፋይዳዎች እንዳሏቸዉ መረዳት ተችሏል።

1. ጠቃሚ እሴቶቻችንን፣ ተወዳጅ አካላትንና ተግባራትን ማበረታታት፣ ማወደስና ማሞገስ፡፡
2. ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማኅበረ ፖለቲካዊ ችግሮችን የሚፈጥሩ አካላትን መምከርና ማስጠንቀቅ፡፡
3. ኅብረተሰቡ ማኅበረ ፖለቲካዊ ችግሮችንና ችግር ፈጣሪዎችን እንዲቃወም መቀስቀስና ማነቃቃት፡፡
4. የኅብረተሰቡን ባህላዊና ማኅበረ ፖለቲካዊ አንድነት ማጠናከር፤ ማስተሳሰርና ማስተባበር፡፡
5. ባህላዊና ማኅበረ ፖለቲካዊ ችግሮችን እና ችግር ፈጣሪ አካላትን መቃወም፣ ማዉገዝና መንቀፍ፡፡
6. የኅብረተሰቡን ወቅታዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ምኞትና ፍላጎት ማንጸባረቅ፡፡

7. ወቅታዊና የታሪካዊ የሆኑ ማህበረ ፖለቲካዊ አዉድና የዘመን መንፈስ መመዝገብና ለትውልድ ማስተላለፍ፣

8. የማሕበረሰቡን ቡድናዊ ስሜት፣ መስተጋብርና የፋክክር ስሜት ማጠናከርና የጀግንነት ስሜትን መቀስቀስ፡፡

## 5.2. አስተያየቶች (የይሁንታ ሃሳቦች)

ተሰብስበዉ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም አማራዉ የፍትህና የሕግ የበላይነት፣ የሰላምና መረጋጋት፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት፣ ብቻ ሳይሆን የሕልዉና ችግር እንዳጋጠመዉ ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ሕዝቡ ችግር ጥያቄና ፍላጎቱን በሰላማዊ መንገድ ለመንግስት አቅርቦ የተሰጠዉ መልስ አሉታዊ በመሆኑ በትጥቅ ትግል መንግስትን ለመታገል የሚሰሩ አደረጃጀቶችን አዳኝና አሌኝታ አድርጎ መቀበሉንም ያስረዳሉ፡፡ በዚህ የዘመን መንፈስ ዉስጥ ቃል ግጥሞቹ ያላቸዉ የቁጣ፣ የቅሬታና ተቃዉሞ መንፈስና ስሜትን የማንጸባረቅ ፋይዳና አስተምህሮ ተመላክቷል፡፡ በመጨረሻም በዘርፉ ላይ እንደ ተቋማቸዉ ራዕይና ተልዕኮ ለሕዝብ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚሰሩ አካላት ይህንን ጥናት ወስደዉ እንዲጠቀሙበት የጥቆማ ሃሳቦች እንደሚከተለዉ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1. የትምህርት ባለሙያዎች በጥናቱ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች በየደረጃው በሚዘጋጁ የማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በይዘት መልክ አሳትመዉ ለማስተማሪያነት ቢጠቀሙባቸው፤
2. የቃል ግጥሞቻችንን ፋይዳና አስተምህሮዎች ለህብረ ብሔራዊ አንድነትና ጠንካራ ሀገረ መንግስት ግንባታ ስራ ለማዋል የሚመለከታቸዉ አካላት ቢሰሩባቸዉ፤
3. የተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች በአግባቡ ተሰንደዉ እንዲቀመጡ በማድረግ በሥነቃል ጥናት ዉስጥ ቋሚ የመረጃ ምንጭና ሀገራዊ የጥበብ ሀብታችን አካል ሆነዉ እንዲቀመጡ ቢደረግ፤
4. ጥናቱን የሥነጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የማህበረ ባህላዊ ጉዳይ ተመራማሪዎች ለጥናታቸዉ የመረጃ ምንጭ አድርገዉ ቢጠቀሙበት፤
5. ቃል ግጥሞች የሕዝቡን እዉነተኛ ስሜት የሚጠቁሙ ከመሆናቸዉም ባሻገር የመንግስትና የፖለቲካ አመራሮች አስተዳደራዊ ጥንካሬና ድክመታቸዉን

የሚያዩበት በመሆኑ የሕዝቡን ስሜት ከማፈን ይልቅ አንድምታቸዉን ተረድቶ የአሰራርና የፖሊሲ ለዉጥ ለማድረግ ቢጠቀምባቸዉ፤

6. ፎክሎራዊ እሴቶቻችን ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸዉ ቢሆኑም ከዘመናዊነትና ሥልጣኔ ጫና ባሻገር ትምህርት ክፍሎች እየተዘጉ፣ በአደባባይም እንዳይከወኑ ክልከላ እየተደረገባቸዉ በመሆኑ የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ትምህርቱ በቋሚነት እንዲሰጥና ትዉልድ እንዲማረዉ፣ አጥኚዎች እንዲያጠኑትና የባህልና ቱሪዝም አመራርና ባለሙያዎች እንዲንከባከቡት ቢደረግ መልካም ነዉ::

# ዋቢ ጽሑፎች

## ሀ. በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ


1. ሀና ደባልቄ፡፡ 2015 ዓ.ም የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና በደብረታቦር ከተማ፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
2. ሊ/ብርሃናት ኢሳይያስ፣ 2018፣ "በዓለ ጥምቀት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቀ)
3. መኮንን አስማማው፡፡ 2007 ዓ.ም በደላንታ ወረዳ የአቡሸቴ እና የአኸይ ቦሌ ቃል ግጥሞች አዲስ አባባ ድህረ ምረቃ ትምህርት
4. ሰለሞን ተሾመ፡፡ 2007 ዓ.ም ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ፡፡ ሀትመት ፋርስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ
5. በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2015 ለበዓለ ጥምቀት የተዘጋጀ ጽሑፍ፡፡ያልታተመ
6. በጅጋ ፡፡ 2008 ዓ.ም በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡
7. ብርሃኑ ገበየሁ:: 1995 ዓ.ም የስነቃል ምንነት፣ ዘውጎችና አተናተን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ፣ አ.አ.ዩ /ያልታተመ/::
8. -----------(1999)፡፡ የአማርኛ ስነግጥም ፡ ንድፈ ሀሳብ፤ ማብራሪያ፤ ትንታኔ፡፡ አዲስ አበባ፤
9. አማረ ሞላ፡፡ 2009 ዓ.ም. የአማርኛ ቃሌግጥሞች ምደባ፣ አውዳዊ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ፡፡ አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ ፡፡
10. አስቴር ሙሉ፡፡ 1991 ዓ.ም
11. አዜብ ታደሰ፡፡ 2002፡ የጥምቀት በአል ባህላዊዉ ወጉና ፍችዉ በሚል ርዕስ በማህበራዊ ሚዲያ ያቀረበችሁ ጽሑፍ፡፡
12. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡
13. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ 1993 ዓ.ም የአማርኛ መዝገ በቃላት፡፡ አዲስአበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

14. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል 1993 ዓ.ም የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡
15. የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል፡፡ ጥር 08/2016 (ኢ.ዜአ)፡፡ አዲስ አበባ፡፡
16. የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ፣ 2006፣ የጥምቀት በዓል አጀማመር እና ታሪካዊ ጉዞ
17. ያለዉ እንዳወቀ:: 2004 ዓ.ም የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር:: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች::
18. ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ 1962 ዓ.ም ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡
19. ደበበ ሰይፉ፣ 1975 ዓ.ም፣ የአማርኛ ሕዝባዊ ሥነግጥም ለአብነት ያህል
20. ደብረ ወርቅ ሞላ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡
21. ጋሻው አሻግሬ፡፡ 2013 ዒ.ም የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታና ፋይዳ በጎንደር፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
22. ጌቴ ገላዬ፡፡ 2000 ከ1983 የመንግስት ለዉጥ በኋላ የምስራቅ ጎጃም ገበሬዎች የገጠሟቸው ፖለቲካዊ ግጥሞች
23. ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991:: የሥነቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች:: (1991፣ 1992፣ 1995፣ 2001)
24. ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1992 ዓ.ም የሥነጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ንግድ ማተሚያ ቤት፤ አዲሰ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
25. በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና ማስተባበሪያ ማህበረ ቅዱሳን፡፡ 20015 ዓ.ም ለጥምቀት በዓ ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ያልታተመ ጽሑፍ፡፡

## ለ. በእንግሊዝኛ የቀረቡ


1. Abebaw Y. Adamu 2006 Epiphany: Socio Cultural Contexts and Significance. Article in Journal of Ethiopian studies / Haile Sellassie I University, Institute of Ethiopian Studies Addis Ababa University
2. Bascom, R. William (1954). "Four Function of Folklore." The Journal of American Folklore,Vol.67,No.266.pp.333-349.Apr,2007,From http://www.jstor.org/about/terms.html.
3. Bascom, William R. (ed). Four functions of Folklore Hand Book of American Folklore. Bloomington: Indiyana University Press, 1965.
4. Bauman, Richard. (ed). (1992). Folklore, Cultural Performances and Popular Enterainment: A communication- Centered Handbook. New York; Oxford University Press.
5. Bauman, Richard. Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments. New York: Oxford University Press, 1992.
6. Bauman, Richard. Verbal Arts as Performance. Long Grove Il; Wave Land Press, 1977.
7. --------. (Ed). Folklore cultural performance and Popular entertainment; New York፡ Oxford University Press, 1992.
8. --------.2002.Toward New Perspectives on Verbal Art as Performance." Journal of The American Folklore, Vol. 115, No. 455, (pp. 62-91, Published by: University of Illinois Press on Stable URL: http://www.jstor.org/stable/542079,
9. ______. "The Field Study of Folklore in Context: A handbook of American Folklore." Ed, Richard M. Dorson, New York: New York University Press, 1983.
10. Ben- Amos, Dan. "Context" in Context. Western Folklore Vol.52, No, 2/4, in Theorizing Folklore; Toward New Perspective on the Politics of Culture. (Apr. - Oct., 1993). 209-226.
11. Ben-Amos, Dan. "Folklore in African Society."Vol, no 6, pp, 165-198, Indiana University Press, 1975.
12. -----------. Folklore in context. New Delhi: Madras South Asian Publishiers, 1982.
13. -----------. "Toward New Perspectives in Folklore" The Journal of American Folklore, Vol. 84, No. 331, (Jan.- Mar., 1971), pp. 3-15. published URL: http://www.jstor.org/ Thu Apr 12 06:33:25, 2007

14. Birhanu Gebeyehu (1998) "Islamic Oral poetry in Wollo" Apreliminary Descriptive Analysis.School of Graguate Studies, A.A.U.
15. Birhanu Gebeyehu (1998). ‹‹Islamic Oral Poetry in Wollo:›› A Preliminary Descriptive Analyisis; School of Graguate Studies;AAU.
16. Creswell, John W. Research design qualitative, quantitative, and mixed methods Approaches. (2nd edition), Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc. 2007.
17. Dan, Ben Amos. (1982). Folklore in Context Essays. New Delhi; India, South Asian Publisher.
18. Dorson M, Richard. (Ed), Folklore and Folk Life; An introduction, Chicago: University press, 1972.
19. Dorson, M. Richard (1963)."Current Folklore Theories." Current Anthropology, Vol.4, No.1, .92-113. In Fekad Azeze (com). (2009). Reader for Folk 805- Folklore: Theories and debates. Vol. I, Department of Ethiopian Language and Literature; Addis Ababa University.
20. --------- (ed). (1972). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago; The University of Chicago Press.
21. ----------."Mythology and Folklore." vol. 2.1973, http://wwwjstororg/ pp 107-126,wed May 1707:38:56 pp 107-126, 2006.
22. Dundes, Alan (2005)."Folkloristics in the Twenty- First Century." The Journal of American Folklore; 118(407),pp.384-408.by the Board of Trustees of the University Of Illinois.
23. -----------. "What is Folklore The Study of Folklore." New Jersey: Prentice- Hall, 1-3 1965. .
24. -----------. Intrpriting Folklore. Bilumington: Indiyana university, Press 1980.
25. -----------. "Folklore Matters." The Folklore Scholarship of Alan Dundes and the New American Studies Perin Gürel, 2005.
26. Fekade Azeze. (2001). "The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect." Journal of Ethiopian Studies; Addis Ababa University; Institute of Ethiopian Studies; Vol. xxxiv; No. 1. pp. 43-85.

27. ----------. (2010). “A Folklore Guidebook For Ethiopia: An Introduction to Definitions and Categories,Field Methods,and Resources for Revitalising Foklore,” Department of Ethiopia Lnaguage and Litrature, Addis Abeba University (unpublished).
28. ---------. (1994) `Some Aspects of Peasant Respons to Famine in Ethiopia Oral Poetry A paper of the 12th International conference of Ethiopian studies. Michigan State University.
29. ---------. (2001): The state of Oral Literature Research in Ethiopia: Retorospect and Prospect. Journal of Ethiopian Studies, Addis Ababa Unversity. Institute of Ethiopia studies፡ Vol XXXIV:No.1 PP (48-85)
30. Finnegan, Rut. Oral Literature in Africa. Nairobi: Oxford University Press, 1970.
31. ----------.Oral Poetry its nature significance and social context. Cambridge: Cambridge University Press, 1977.
32. ________.(1992). ‘Oral Poetry: in Richard Bauman (ed). Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments: A Communication Centered Handbook. Pp. 119-128. New York: Oxford University Press.
33. ----------.Oral traditions and the Verval arts; A Guide to Research practices. London: Alan Barnard and Anthony Good Acadamic press, 1992.
34. Getie G. (2000).”Peasants and The Ethiopian State: Agricaltural Producers’ Cooperatives and Their Reflections in Amharic Oral Poetry”;A case study in yetnora;East Gojjam;1975-1991;Hmburg:LiT.
35. ---------.(2001 ). Amharic Oral Poems of East Gojjam: Text; classification Translation; and Commentary; Hamburg Germany.
36. Goldstein, Kenneth S. “Ridding Traditions in North Eastern Scotland.” Journal of American Folklore 76:330,336. 1963.
37. Goldstein, Kenneth. S.A A Guide for field works in folklore. Detroiter: Gale Research Company, 1964.
38. Goldstein, Kenneth S. “Ridding Traditions in North Eastern Scotland.” Journal of American Folklore 76:330,336. 1963.
39. ----------.(1964). A Guide for Field workers in Folklore. Hatboroo; Pennsylvania; Folklore Associates inc.

40. Green, Thomas A. (Ed), Folklore an Encyclopedia of beliefs, customs, tales, music and art. California: Santa Barbara 1997.
41. Islam Gazi and J. Zyphur Michael. “Rituals in Organizations: A Review and xpansion of Current Theory” DOI: 10.1177/1059601108329717, Washington: Sage Publications 2009, 34; 114.
42. Kapchan, Deborah A. “Performance.” The Journal of American Folklore, Vol. 108, No. 430, pp. 479-508.
43. Kay, Milton. Enviromentalism the view from anthropology. Published in the Taylor & Francis Library, 2005.
44. Mccormick, and White; K.K. (eds). "Folklore an Encyclopedia of Beliefs Custms, Tales, Music and Art" 973-980, 2011.
45. Mesfin messele (2000). Abbawude Oral Poetry in South Wollo. A Descriptive Analysis; School of Graduate Studies; AAU.(M.A Thesis)
46. Okpewho, Isidore. (1992). African Oral Literature: Background, Character, and Continuity. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.
47. Okpewho, Isidore. African Oral Literature: Backgrounds, Characters and continuity. Bloomington: Indiana University Press, 1992.
48. Peek, Philip M and Yankah Kwesi. (Ed). African Folklore an Encyclopedia. New York London: Rout ledge Published 2004.
49. Rappaport, Ray A. The abivious aspects of ritual in Ecology meanining and Religion. Atah state: Atah state university press, 1997.
50. ---------. Ritual and religion in the making of humanity. Cambridge University Press, 1999.
51. Schoemaker H George ed (1990) The Emergence of Folklor in Everyday Life A Fieldguide and Sourcebook Tickster Press Bloomington Indiana
52. Sims, C. Martha and Stephen, Martine. (2005). Living Folrlore: An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan; Utah state University Press.
53. Sims, M.C and Martine Stephen. Living Folklore. an Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan: Utah state University Press, 2005.
54. Sims, Martha C., Martine Stepens. Living Folklore An Introduction to the Study of People and Their Traditions. Utah: Utah State University Press, 2005.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- በጥናቱ ትንታኔ የተደረገባቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥም አይነቶች

### 1. የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸው ቃል የአማርኛ ግጥሞች

### 1.1. የአማራን ሕዝብ የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. እየፎከረበት ያባቶቹን ገድል፣
   የዘመተ ለታ ይመለሳል በድል፡፡
2. አማራ አሳረኛዉ ግፍ የሚሰራበት፣
   ዋልታና ማገር ነዉ ለኢትዮጵያዊነት፡፡
3. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ፣
   ሞትን አይፈራዉም  አማራዉ መብረቁ፡፡
4. ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣
   አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ፡፡
5. አሁን ያማራን ልጅ ማን ይለዋል ፈሪ፣
   ነፍጠኛ ነዉ እንጂ ሐገር አስከባሪ፡፡
6. እኔ ከአማራ ልጅ ፈሪ ቢገኝብኝ፣
   ሦሥት ዓመት እስራት ሞት ይፈረድብኝ፡፡

### 1.2. የሸዋን ሕዝብ የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

7. አትንኩኝ ነዉ እንጂ ከልክ አትለፉ፣
   አሁን ሰሜን ሸዋን ማን ይለዋል ክፉ፣
8. አይንኩት እንጂ ከነካኩት፣
   የሸዋ ልጅ ነዉ ሰደድ እሳት፡፡
9. አይታሰስም ምጣድ ባሸዋ
   የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ሸዋ፡፡
10. ሸዋ  ሞት አይፈራም ደንዳና ነዉ ቀልቡ
    መገዘዝ ተራራ እመጓ ነዉ ልቡ፡፡
11. መገን የሸዋ ልጅ አይጨበጥ እጁ፣
    ላገሩ የሚሞት አባትና ልጁ፡፡

12. ሸዋ ባላመጠ ይዉጣል ባመቱ ፣
ጠላት አይፈታዉም ቅኔ ነዉ ብልሃቱ ፡፡

**1.3. የጎንደርን ሕዝብ የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

13. እኔስ ያኮራኛል ጎንደር መወለዴ፣
ሴቲቱ ሁመራ ወልቃይት ጠገዴ፡፡
14. አይታሰስም ምጣድ በዘገር፣
የጀግኖች ሀገር እንዴት ነዉ ጎንደር፡፡
15. አገራችን ጎንደር መልሶ አገራችን
ጓያችን ይሰብራል እንኳን ጥይታችን፣
16. ሲሆን አንሸሽም ብንሸሽም ተጓደን
ከጎበዞች አገር ጎንደር ላይ ተወልደን፡፡
17. ሰሜን አርማጭሆ ወልቃይት ጠገዴ፣
ማረሻዉ ምንሽር መጎልጎያዉ ጓንዴ
18. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር፣
በርስትና በእምነት የማንደራደር፡፡

**1.4. የወሎን ሕዝብ የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

19. የወሎ ልጆች ቀጫጭኖቹ
ይናደፋሉ እንደንቦቹ፡፡
20. አይታሰስም ምጣድ ባለሎ፣
የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ወሎ፡፡
21. የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ
ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ፡፡
22. ራያና ቆቦ ዙሪያዉ በራበሩ
እንኳን ሰዉ ቁሞበት ያሥፈራል ግራሩ፡፡
23. ከመቃብር በላይ ስም ይዉላል ብሎ፣
ፍቅርና ጀግንነት ያዉቅበታል ወሎ፡፡
24. ሀገራችን ደሴ ስማችን ወሎዬ፣
በነካኩንና ጉዳችን በለዬ፡፡

**1.5. የጎጃምን ሕዝብ የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

25. የዓባይ ውሃ ቀመስ አያዉቅም ሽሽት
አስተምሮት በላይ ለእምነቱ መሞት፡፡
26. አይታሰስም ምጣድ በአጋም፣
የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ጎጃም፡፡
27. ትጥቁ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ
በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ፡፡
28. ደብረ ኤልያስን የነካት ሰዉ ማነዉ፣
እንኳንስ ልጆቹ ምድሩም ተዋጊ ነዉ፡፡

29. ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሀገርህ፣
አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ፡፡
30. አረንቋ ነዉ ጎጃም ዝናቡ እየናጠዉ፣
እየዋጠዉ ቀረ እየሰለቀጠዉ፡፡

**1.6. ማህበራዊ ቡድኖችን የማሞገስና የማወደስ ሚና ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

31. ምንጨነቀኝ ብዬ ይሳሳል ገላዬ፣
ያሳምነዉ ሚዜ ካለ ከኋላዬ፡፡
32. የሐገር አርበኛ የድል ችቦ ለኳሽ፤
አመጸኛዉ ፋኖ አራሽ ቀዳሽ ተኳሽ ፡፡
33. አሳምነዉ ጽጌ ደረሰ አዝመራህ፣
አጨረደዉ ከመረዉ ያዉ ፋኖ ልጅህ፡፡
34. ዛሬ እሞት ነገ እሞት እያልኩኝ ስከሳ
ያማራዉ ልጅ ፋኖ ደረሰልኝሳ፡፡
35. ይዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
ፋኖ ቁሞ አያይም ስትፈርስ ሀገሩ፡፡
36. ተወረረ ሲባል ሐገር ተደፈረ፣
አመለኛዉ ፋኖ ወጣ እየፎከረ፣

**1.7. ታዋቂ ግለሰቦችን የማሞገስና የማወደስ ሚና ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

37. አሳምነዉ ፅጌ ሞተ ያለዉ ማነዉ?
ሰፍቷል እንደ ዋርካ ቀንዘሉ ብዙ ነዉ፡፡
38. ማን ሊኖርበት ይሰራል ጎጆ፣
በለስ ካልቀናዉ ምሬ ወዳጆ፡፡
39. የለበሰዉ ልሚል የታጠቀዉ ልሚል፣
የምሬ ወዳጆ የፋኖዉ ባለሚል፡፡
40. አሳምነዉ ጽጌ ሙቶ አይቀርምና፣
ሐገሩ ሲደፈር ሆዱ አይችልምና፣
አፈር አታብዙበት ይበቃል ሶስት ቁና፡፡
41. ብረቱ መዉዜር ነዉ ጥይቱ ዘጠና፣
ደስ ሲለዉ ቆቦ ሲከፋዉ ጎሊና፣
ምሬ አባ ድፈቅ የትግሉ ፋና ፡፡
42. የወሎዉ ጀግና ምሬ ወዳጄ፣
የቁርጥ ቀን ልጅ አለ ቀኝ እጄ፡፡
43. ፍርድ ቤት ፍለጋ ለምን እለፋለሁ፣
ለምሬ ወዳጆ እነግርብሃለሁ፡፡
44. በአምስት አቦ ናቸዉ በሰባት ሥላሴ፣
የአሳምነዉ ምትክ ልጅ ዘመነ ካሴ፡፡
45. ነፍሱን የሰጠዉ ከልጁ ጋራ፣

እሸቴ ሞገስ ሸዋ ላይ በራ፡፡

## 1.2. የመምከር እና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

46. እየነገርናቸዉ እያረጉት ዋዛ፣
የሚፈናቀለዉ የሚሞተዉ በዛ፣
መንግስትን የሚንቅ የሚጠላዉ በዛ፡፡
47. ህዝብ እንዲያስተዳድር ቢሰጡ ሀገር፣
እንደልጅ አማረዉ መጫወት ባፈር፡፡
48. አመለ ልስልሱን የዋህ ገራም በሬ፣
ነካክተዉ ነካክተዉ አደረጉት አዉሬ፡፡
49. አይተነዉ አይተነዉ ካላማረ ቀኑ፣
እኛም አዉሬ እንሁን እነሱም ያድኑ፡፡
50. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር፣
በርስትና በእምነት የማንደራደር፡፡
51. ንቃ ራያ ቆቦ ንቃ ሰሜን ጎንደር፣
ባገርና በርስት እንዳትደራደር፣
52. ጭናና ማይካድራ የፈሰሰዉን ደም፣
ቁመህ እንዳትረሳዉ በድንህ ሳይጋደም፡፡
53. ጎንደር ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ጎጃም ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ወሎ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ሸዋ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይላሉ፣
ለካስ ይዘነዋል በራበሩን ሁሉ፡፡
54. ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፣
ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፡፡
55. እንኳን በለዉ ብለዉ ልከዉ ሰደዉት ፣
እንዳዉም አማራ አመል አለበት፡፡
56. አምናም አስሮኝ ነበር ዘንድሮም አጋዘኝ፣
እንደማንላቀቅ ገብቶታል መሰለኝ፡፡
57. ጠ/ሚኒስቴር ኬኛ ከንቲባዋ ኬኛ፣
ኢታማጆር ኬኛ ደህንነቱም ኬኛ፣
ብሔር ብሔረሰብ ተከናንበህ ተኛ፡፡
58. እንኳንስ መታሰር መገደል ቢመጣ፣
ማንንም አልሰማ በፋኖ የመጣ፡፡
59. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡
60. ተዉ እርገጥ እርገጥ እርገጥ ባንድ ላይ፣
ተወልደህ አድገህ ሰሜን ሸዋ ላይ ፣

ተዉ እርገጥ እርገጥ እርገጥ ባንድ ላይ፣
ተወልደህ አድገህ ቤተ አማራ ላይ፡፡

61. አዉድማዉም ይስፋ በሮችም አይራቁ፣
መናዱ የማይቀር ዉሽልሽል ነዉ እርቁ፡፡

62. ጠላትን ሳይገድሉ ምን ያደርጋል አፍሮ፣
መቀሱን ላኪልኝ ቁርጥ ነዉ ዘንድሮ፡፡

63. እንጫወት እንደሁ እንጫወት ዛሬ፣
ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡

## 1.3. የመቀስቀሳና ማነቃቃት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

64. በረቱን ከፍታችሁ በሮቹን ላኳቸዉ፣
ሽገር ከተማ ላይ በራይ አለባቸዉ፡፡

65. ያገር ያለህ እያልን ዝም አላችሁ ምነዉ!?
ያማራዉ በሽታ የናንተም ህመም ነዉ፡፡

66. ታምሜያለሁና ሁላችሁ ታመሙ፣
ያንድ ሰዉ በሽታ ይበቃል ለሁሉ፡፡

67. እንኳንስ ጎጃም አይዞህ እያለዉ፣
እንኳንስ ጎንደር አይዞህ እያለዉ፣
እንኳንስ ወሎ አይዞህ እያለዉ፣
እንኳንስ ሽዋ አይይህ እያለዉ፣
እንዳዉም ፋኖ አመጸኛ ነዉ፡፡

68. ምን ያደርጋል ጎመን ስጋ ሳይታጣ፣
ተሰቅሎ እያለልን ያምስት ዓመት ቋንጣ፡፡

69. ኧረ ተዉ ተረኛዉ ግፉ አይብዛ  በቃ!!
ፀሀይ ትጠልቃለች እንኳንስ ጨረቃ፡፡

70. ሞቅ በል! ሞቅ በል! ሞቅ በል! ቀዝቃዜ፣
ያአማራዉ ነፍጠኛ የአሳምነዉ ሚዜ፡፡

71. መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ?
ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ፡፡

72. በታጣፊ ክላሽ ክንዱን ካልሰበሩት፣
ጠላት መች ይተዋል በሥላሴ ቢሉት፡፡

73. በል ጠመንጃ ግዛ በሬህን ሸጥና፣
መሬትህን በታንክ አርሰዉታልና፡፡

74. ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሐገርህ፣
አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ፡፡

75. ኧረ ተይ እናቴ ፈሪ አታርጊዉ ልቤን፣
እቤት እንድቀመጥ አጣጥፌ ክንዴን፣
ማን ባቀናዉ ሃገር ላሳድግ ነዉ ልጄን?

76. ዝም ሲል አማራ የሌለ መስሏቸዉ፣
ትዕግስቱ ሲበዛ የፈራ መስሏቸዉ፣
ሰበርነዉ ያሉትን እዩት ሲሰብራቸዉ፡፡
77. ምነዉ በሰማይ ላይ እንዳሞራ ልጅ፣
ወርደህ በጠብመንጃ ይለይልን እንጅ፡፡
78. አሻቅበህ በለዉ ሰማዩን በእንቧይ፣
ጊዜዉ ካልደረሰ ሰዉ ይሞታል ወይ?
79. ሳንጃዉን አግለህ ከቂጡ ለኩሰዉ፣
መቼም አይነሳ ወኔ የሌለዉ ሰዉ፡፡
80. አይዟችሁ ጋሞቼ ሆዳችሁ አይባባ፣
ይጋጠም የለም ወይ ሰባትና ሰባ፡፡
81. ጃሎ መንገዱን እስኪ አለስልሰዉ፣
ቀድሞ ይመጣል ያልሞተ ሰዉ፡፡
82. ዘንድሮ ጉልበቴ ዉለታ ዋለልኝ፣
አንገቴን ስደፋ ቀና አደረገልኝ፡፡

### 1.4. ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ የማጠናከር ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

83. ሀገሬ ላይ ሁኜ ናፈቀኝ ሀገሬ፣
ከማን ጋር ይዋላል ሁሉም ሆኗል አዉሬ፡፡
84. አትግፋኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ፣
እንኳን የሰዉ ሀገር የኔንም ትቻለሁ፡፡
85. ከፍ አረገኝ ብሎ ጊዜ እንደተራራ፣
ልርገጥህ አይልም ወንድሙን አማራ፡፡
86. እንብላ እንጠጣ ነዉ ለመጣ ለሄደዉ፣
ራያ ምድር ላይ ሰዉ መሆን በቂ ነዉ፡፡
87. እኔስ አራሽ ነበርኩ የገበሬ ልጅ፣
ሰርቼ እንዳልበላ አደረጉኝ እንጂ፡፡
88. አዲስ አበባ ላይ ቁና ጤፍ አይገኝ፣
ርሽርሹ ጎጃም ካንተ በፊት ያርገኝ፡፡
89. ሞፈሩን ቀንበሩን ክተቱት በጎታ፣
እናርስበታለን ቀን የወጣ ለታ፡፡
90. ከዘንድሮዉ ችግር የከርሞዉ ይብሳል፣
በሮቻችን ሞተዉ በምን ይታረሳል?
91. እንጫወት እንደሁ እንጫወት ዛሬ፣
ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡
92. ሲቀር ይቀራል፣ ሲቀር ይቀራል፣
በሸገር ዳቦ ማን ይፎገራል፡፡
93. በጸጥታ ኃይሉ እግድ ነበረብኝ፣

በቄስ በቃልቻ ዉግዘት ነበረብኝ፣
አንጎራጉራለሁ እየጎደለብኝ፡፡

94. እንኳን አማርኛ ይናገር ትግርኛ፣
ክፉ ሀሳቡን ነዉ የጠላነዉ እኛ፡፡

95. እኔ የራያን ልጅ አያሰማኝ ክፉ፣
እንኳንስ ልጆቹ አይቆረጥ ዛፉ፡፡

96. እባብ ሰለክላኬ መንታ ነዉ ምላሱ ፣
ሲያምኑት የከዳ ሰዉ አይማርም ነፍሱ፡፡

97. ወሎ ራሱን ታሞ ተኝቷል ከቤት፣
ከጋራዉ ላይ ወጥተህ ሞረሽ በልለት፣
ያገኝለት እንደሁ ዘመድ መድሃኒት፡፡

98. ከፍ አረገኝ ብሎ ጊዜ እንደተራራ፣
ልርገጥህ አይልም ወንድሙን አማራ፡፡

99. እንብላ እንጠጣ ነዉ ለመጣ ለሄደዉ፣
ራያ ምድር ላይ ሰዉ መሆን በቂ ነዉ፡፡

## 1.5. የተቃዉሞና የቅሬታ ድምጽ የማሰማት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

100. ይነጋል ባልነዉ ቀን ጨለማ ነገሰ፣
ኑሮ ተወደደ ሰዉ እየረከሰ፡፡

101. ስጋዉን ላይበሉት ደሙን ላይጠጡት፣
አሳምነዉ ጅጌን ለምን ገደሉት፡፡

102. ዝግባዉን ቆረጡት እነ ልክ አያዉቁ፣
ምን ያፈራ ይሆን ብለዉ ሳይጠይቁ፡፡

103. ወለጋ ሕዝብ ሲያልቅ ያላወጄ አዋጅ፣
ያማራ ሕዝብ ሲያልቅ ያላወጄ አዋጅ
ምን ብልጽግና ነዉ ብልግና ነዉ እንጅ፡፡

104. ምን ያደርግልናል እንጦጦ ቢሰራ፣
በጅምላ እያለቀ ሰዉ አማኙ አማራ፡፡

105. መሰደድ መታሰር ከሆነ የኛ እጣ፣
መገደል መታገት ከሆነ የኛ እጣ፣
መበተን መፈርከስ ከሆነ  የኛ ዕጣ፣
መደመር መበልጸግ ባፍንጫችን ይዉጣ፡፡

106. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ፣
ነፍጠኛዉ አማራ አይፈታም ትጥቁ፡፡

107. ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣
ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም አማራ፡፡

108. ራያ ወሎ ነዉ ገለል በል ህወሃት፣
ተነጥሎ አይቀርም የጢነኞች ርስት፡፡

109. ህወሓት በተንኮል የዘራዉን ዘር፣
ኦህዴድ በሰዉ ደም ያበቅለዉ ጀመር፡፡
110. የባለስልጣን ልጅ አይሄድም ዘመቻ፣
ሰላም አስከባሪ የድሃ ልጅ ብቻ፡፡
111. ጣሊያን አልመጣብን ተኩስ አልተተኮሰ፣
ወይ ወራሪ አልመጣ ችግር አልደረሰ፣
ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አገሩ ታመሰ፤
በኮማንድ ፖስቱም አገሩ ፈረሰ፡፡
112. ያምናን ቀን አማሁት ላፌ ለከት የለዉ፣
የዘንድሮዉ ባሰ እጅም እግርም የለዉ፡፡
113. ቀና ብዬ ባየዉ ሰማዩም ቀለለኝ፣
ፈጣሪም እንደኛ ታግቷል መሰለኝ፡፡
114. አማራ ዙሪያዉን መሬቱ ተወሮ፣
ህዝቡ በያገሩ በጅምላ ተቀብሮ፣
ምን ተይዞ ጉዞ ይታሰባል ኑሮ፡፡
115. ጁንታዉ ሲለቀቅ በግርግር፣
ዘመነ ካሴ ለምን ይታሰር፡፡
116. ለምን ይታሰራል የከተማ ልጂ፣
እምብዛም ቢጠና በዋስ ያድራል እንጂ፡፡
117. አትግፉኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ፣
እንኳን የሰዉ ሃገር የኔንም ትቻለሁ፡፡

## 1.6. የማዉገዝና የመንቀፍ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

118. እናቴስ መች ወልዳኝ እኔስ መች ተወለድኩ፣
ከጠላቶቼ ጋር አብሬ እየዶለትኩ፡፡
119. እዩት መጡ መጡ ደረሱ እዛ ማዶ፣
እየሸሹላቸዉ መከተል ተለምዶ፡፡
120. እናቱ አስተምራዉ ቂጣ በደንደሱ፣
ና ተሸከም አለኝ እኔንም እንደሱ፡፡
121. ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻዉ፣
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻዉ፡፡
122. እደግ እደግ ብለን ያሳደግነዉ ቀጋ፣
አለ ዘመም ዘመም እኛኑ ሊወጋ፡፡
123. ጎንደር ላይ ተወልደህ የፈራህ እንደሆን፣
እናትህን ጠይቃት ዘር ቀይራ እንዳይሆን፡፡
124. ከቶ ምን ሊሆን ነዉ ፈሪ ማቶንቶኑ፣
ቅጠል አይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ፡፡
125. እኔ ለፈሪ አልሰጥም ልብሴን

ያስጠይቃታል በሰማይ ነፍሴን፡፡

126. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ፣
ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡

127. በለዉ በለዉና አሳጣዉ መድረሻ፣
የሰዉ ልክ አያዉቅም ባለጌና ዉሻ፡፡

128. ዘንድሮ ኢትዮጵያ ታሪክ ተበላሼ፣
ባለክላሽ ቂሞ ባለመድፉ ሸሼ፡፡

129. ዉሃ ቁልቁል እንጂ መች ሽቅብ ይፈሳል፣
ትንሽ ከፊት ሲሆን ሀገር ያሳንሳል፡፡

130. መስሎ ማደር ይብቃ ለእዉነት እንኑር፣
ወሎ ላይ ተወልደን ካሳምነዉ ሃገር፡፡

131. ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፣
ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፡፡

132. አትግፉኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ
እንኳን የሰዉ ሀገር የራሴን ትቻለሁ፡፡

133. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነዉ
ከተጣሉ ወዳ ድርድር ምንድነዉ?

134. የተላላኪዎች ሆድ ነዉ አምላካቸዉ
ሐገር ስትደፈር ቅርም አይላቸዉ፡፡

135. ትመታ እንደሆነ እኛን አይተህ ምታ፣
የማትመታ እንደሆን ልቀቅ የሰዉ ቦታ፡፡

## 1.7. የሕዝቡን ፍላጎት እና ምኞት የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

136. እስኪ መጀመሪያ ሀገር ደህና ትሁን፣
እስኪ መጀመሪያ እኛ ደህና እንሁን፣
ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ይሰራናል አሁን፡፡

137. ቀረርቶ ብቻ ነዉ ሲሉን እንዳልኖሩ፣
ፎክረን ስንተኩስ ዛሬስ ምን አወሩ፡፡

138. አይ አማራ ክልል አቤት ወይ እድልህ፣
እንዲያዉ መቼ ይሆን ቀን የሚወጣልህ!?

139. እዘምታለሁ እንጂ አንጀቴን አስሬ
እንዴት ዝም ልበል ሲደፈር ሀገሬ፡፡

140. ምን አለ? ጎንደር/ጎጃም/ወሎ/ሸዋ ምናለ?
ሐገሬን ለሰዉ አልሰጥም አለ፡፡

141. የሚሸመዉ ሁሉ ባንዳ ሁኗልና፣
አማራ መሪ አጥቶ ተበትኗልና፣
አሳምነዉ ጽጌ ቶሎና ቶሎና፡፡

142. መተከል ራያ ወልቃይት ሀገሬ

ያማራ ርስት ነዉ ጥንትም ሆነ ዛሬ፡፡
143. እንኳን አሁንና እስካፍንጫ ታጥቀን
ባሮጌ ምንሽር ታንክ እንማርካለን፡፡
144. ከእንግዲህ አይኖርም አማራ ታፍኖ፣
የቁርጥ ቀን ልጁ እያለለት ፋኖ፡፡
145. ትጥቄ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ
በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ፡፡
146. ተዉ አትከልክሉኝ ልዉጣ ከቤቴ፣
ዝም ስላልኩኝ በዝቷል ጠላቴ፡፡
147. ይዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
ፋኖ ቁሞ አያይም ሲደፈር ሀገሩ፡፡
148. ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣
አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ፡፡
149. የራያ ልጅ ታሞ ወሎ ከሚጨነቅ፣
ወልቃይትም ታሞ ጎንደር ከሚጨነቅ፣
አንድ ሺህ ወያኔ ሆዱን ታሞ ይለቅ፡፡
150. ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣
ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም አማራ፡፡
151. ወይኔ አበቤ ወይኔ አበቤ፣
አልወደደሽም ሂጂልኝ ቀልቤ፡፡
152. ወይኔ ቀጀላ ወይኔ ቀጀላ፣
መኖሩ ይብቃህ በኦነግ ጥላ፡፡
153. ቢመችሽም ባይመችሽም
ሸገር ፊንፊኔ አይሆንልሽም፡፡

# አባሪ ኹለት፡-

## 2. በጥናቱ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የአማርኛ ቃል ግጥሞች በአይነት

### 2.1. የማሞገስና የማወደስ ፋይዳ ያላቸው የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. አትንኩኝ ነዉ እንጂ ከልክ አትለፉ፣
አሁን ሰሜን ሸዋን ማን ይለዋል ክፉ፡፡
2. እኔ ከአማራ ልጅ ፊሪ ቢገኝብኝ፣
አንገቴ ላይ ገመድ ማነቆ ይግባብኝ፡፡
በመኪናዉ መንገድ ጋሪ ይነዳብኝ ፡፡
3. እንዴት ነዉ ወልቃይት ሳሩ ቀጤማዉ?
እንዴት ነዉ ራያ ሳሩ ቀጤማዉ?

ፋኖ አጭዶ ከምሮ የጎዘጎዘዉ፡፡

4. እኔስ ያኮራኛል ጎንደር መወለዴ፣
   ሴቲቱ ሁመራ ወልቃይት ጠገዴ፡፡
5. ያሳምነዉ ግልገል የአማራዉ ግስላ፣
   ጎንደር አባጃሌ ራያ አባ መላ፡፡
6. ሽኔዉም ቢተኩስ በህዝብ ሊያሽብር ነዉ
   ጁንታዉም ቢተኩስ ጀሌ ለመግደል ነዉ
   ያሳምነዉ ግልገል ሕዝብን ሊጠብቅ ነዉ፡፡
7. አሳምነዉ ጽጌ ሙቶ አይቀርምና
   ሐገሩ ሲደፈር ሆዱ አይችልምና
   አፈር አታብዙበት ይበቃል ሶስት ቁና፡፡
8. የቁስ ቀበሌዉ ልጅ ያፋፉ ያፋፉ
   እየኖ ጋዉ መጣ እየደፋዉ ባፉ፡፡
9. ብረቱ መዉዜር ነዉ ጥይቱ ዘጠና
   ደስ ሲለዉ ቆቦ ሲከፋዉ ጎሊና
   ምሬ አባ ድፊቅ የትግሉ ፋና ፡፡
10. ምንጨነቀኝ ብዬ ይሳሳል ገላዬ
    ያሳምነዉ ሚዜ ካለ ከጓላዬ፡፡
11. አሁን ያማራን ልጅ ማን ይለዋል ፈሪ
    ነፍጠኛ ነዉ እንጂ ሐገር አስከባሪ፡፡
12. የሐገር አርበኛ የድል ችቦ ለኳሽ፣
    አመጸኛዉ ፋኖ አራሽ ተኳሽ ቀዳሽ፡፡
13. አይታሰስም ምጣድ ባሸዋ
    የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ሸዋ፡፡
14. አይታሰስም ምጣድ ባለሎ፣
    የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ወሎ፡፡
15. አይታሰስም ምጣድ በአጋም፣
    የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ጎጃም፡፡
16. አይታሰስም ምጣድ በዘገር፣
    የጀግኖች ሀገር እንደት ነዉ ጎንደር፡፡
17. ሲሆን አንሽሽም ብሽሽም ተጓደን
    ከጎበዞች ሀገር ጎጃም ላይ ተወልደን፡፡
18. የወሎ ልጆች ቀጫጭኖቹ
    ይናደፋሉ እንደንቦቹ፡፡
19. እኔ ከአማራ ልጅ ፈሪ ቢገኝብኝ
    ሦሥት ዓመት እስራት ሞት ይፈረድብኝ፡፡
20. ሸዋ ሞት አይፈራም ደንዳና ነዉ ቀልቡ

መገዘዝ ተራራ እመጓ ነዉ ልቡ፡፡

21. ጎጃም ዘመነ ጎንደር ደመቀ
   ጠላቱን መካች እየደፈቀ፡፤
22. የወሎዉ ጀግና ምሬ ወዳጆ
   የቁርጥ ቀን ልጅ አለ ቀኝ እጄ፡፡
23. ነፍሱን የሰጠዉ ከልጁ ጋራ፣
   እሸቴ ሞገስ ሸዋ ላይ በራ፡፡
24. የዓባይ ዉሃ ቀመስ አያዉቅም ሽሽት
   አስተምሮት  በላይ ለእምነቱ መሞት፡፡
25. አሳምነዉ ጽጌ ደረሰ አዝመራህ፣
   አጨረደዉ ከመረዉ ያዉ ፋኖ ልጅህ፡፡
26. በሬ በሬ ሲሉኝ የላም ልጅ ነዉ ብዬ
   የሰዉም በሬ አለዉ ኧረ እናንተ ሆዬ፡፡
27. መገን የሸዋ ልጅ አይጨበጥ እጁ፣
   ላገሩ የሚሞት አባትና ልጁ፡፡
28. አሳምነዉ ጽጌ ሞተ ያለዉ ማነዉ
   አሁንም አማራን ይመራል በወኔዉ፡፡
29. ዛሬ እሞት ነገ እሞት እያልኩኝ ስከሳ
   ያማራዉ ልጅ ፋኖ ደረሰልኝሳ፡፡
30. አሳምነዉ ጽጌን ሞተ ያለዉ ማነዉ
   ዛሬም ጉድጓዱ ዉስጥ እንደታጠቀ ነዉ፡፡
31. ድንጋይ ተንከባሎ ቢመታዉ ጉልበቱን
   ምነዉ ባልወለድሽኝ ብሎ አላት እናቱን፡፡
32. አሁን ምን ሊሆን ነዉ ፈሪ መወለዱ
   መሸሸ የለመደዉ ባርባር ሊለዉ ሆዱ
33. የለበሰዉ ልሚል የታጠቀዉ ልሚል፣
   የምሬ ወዳጆ የፋኖዉ ባለሚል፡፡
34. በግፍ የገደለህ ጠላት ቢጠላህም፣
   አሳምነዉ ጽጌ እኛ አንረሳህም፡፡
35. ሲሆን አንሸሽም ብንሸሽም ተጓደን
   ከጎበዞች አገር ጎንደር ላይ ተወልደን፡፡
36. ምንሸር ሆዳሙ ጓንዴ ቀፈታሙ
   ስጋ በልቶ ያድራል በሁዳዴ ጾሙ፡፡
37. አገራችን ጎንደር መልሶ አገራችን
   ጓያችን ይብራል እንኳን ጥይታችን፡፡
38. እየፎከረበት ያባቶቹን ገድል
   የዘመተ ለታ ይመለሳል በድል፡፡

39. አማራ አሳረኛዉ ግፍ የሚሰራበት፣
ዋልታና ማገር ነዉ ለኢትዮጵያዊነት፡፡
40. ተወረረ ሲባል ሐገር ተደፈረ፣
አመለኛዉ ፋኖ ወጣ እየፎከረ፣
ያባቱ ታሪክ ነዉ በርሱ አልተጀመረ፡፡
41. አገራችን ጎንደር መልሶ አገራችን
ጓያችን ይብራል እንኳን ጥይታችን፡፡
42. አሳምነዉ ጽጌ ሞተ ያለዉ ማነዉ?
ሰፍቷል እንደ ዋርካ ቀንዘሉ ብዙ ነዉ፡፡
43. ማን ሊኖርበት ይሰራል ጎጆ
በለስ ካልቀናዉ ምሬ ወዳጆ፡፡
44. አትንኩኝ ነዉ እንጂ ከልክ አትለፉ፣
አሁን ሰሜን ሸዋን ማን ይለዋል ክፉ፡፡
45. ያዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
ፋኖ ቁሞ አያይም ስትፈርስ ሀገሩ፡፡
46. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ
እስካፍንጫዉ ታጥቋል አማራዉ መብረቁ፡፡
47. ህይወቴን ላማራ ስጋዬን ላሞራ
ፋኖ ነኝ እኔ ማንንም አልፈራ፡፡
48. ነፍጠኛ ነኝ ማለት አይቻልም እንዴ፣
አማራ ነኝ ማለት ተከልክሏል እንዴ፣
ሁሉ የሚሳደደን በጦር በጎራዴ፣
እድሜ ለምንሽር አልቤንና ጓንዴ፡፡
49. አንበሳን አንበሳ አይፈራዉምና፣
ያራዊቶች ንጉስ ከጫካ ዉጣና፣
መጥቷል ተቀበለዉ ሞትአይፈሬዉ ጀግና፡፡
50. እንኳን አሁንና እስካፍንጫ ታጥቀን
ባሮጌ ምንሽር ታንክ እንማርካለን፡፡
51. አትንኩኝ ነዉ እንጂ ከልክ አትለፉ፣
አሁን ሰሜን ሸዋን ማን ይለዋል ክፉ፡፡
52. የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ
ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ፡፡
53. አማራዉ ተራራዉ ተገፍቶ የማይወድቀዉ
ሲተኩስ ሲጸልይ ብቻ ነዉ የሚንበረከከዉ፡፡
54. እንኳን ቃታ ከፍቶ ሲያጓራ መዉዜሩ፣
ነፍጠኛዉ የአማራ ያስፈራል ግንባሩ፡፡

## 2.2. የመምከር እና የማስጠንቀቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. እየነገርናቸዉ እያረጉት ዋዛ፣
የሚፈናቀለዉ የሚሞተዉ በዛ፡፡
መንግስትን የሚንቅ የሚጠላዉ በዛ፡፡
2. ፍርድ ቤት ከምሄድ ፍትህ ከሌለበት፣
እነስበር ጋራ ብሄድ ምናለበት፡፡
3. አንተ ኦነግ ሸኔ አላዉቅህ አታዉቀኝ
ከበሬ ላይ መጥተህ ምነዉ ባትነካካኝ፡፡
4. መስሎ ማደር ይብቃ ለእዉነት እንኑር
ወሎ ላይ ተወልደን ካሳምነዉ ሃገር፡፡
5. ፍራት የሚንደዉ ልቦናም የለን
በሚግ በድሮኑ አታስፈራሩን፡፡
6. የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ
ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ፡፡
7. እናቴስ መች ወልዳኝ እኔስ መች ተወለድኩ፣
ከጠላቶቼ ጋር አብሬ እየዶለትኩ፡፡
8. ወዳማዶ ሆኖ ጠላት ምን ቢያሽካካ፣
የወንዶችን ሀገር ማነዉ የሚነካ፡፡
9. ደብረ ኤልያን የነካት ሰዉ ማነዉ፣
እንኳንስ ልጆቹ ምድሩም ተዋጊ ነዉ፡፡
10. ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፣
ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፡፡
11. ወልቃይት ጸገዴ አዲረመጽ ዳንሻ፣
ፋኖ የአማራ ልጅ ጀግና ነዉ ሀበሻ፡፡
12. እንኳን በለዉ ብለዉ ሰደዉ ልከዉት፣
እንዳዉም አማራ አመል አለበት፡፡
13. ምንም ቢዘገይም ፍርድና ብያኔ፣
ነገ ጠዋት ያለቅሳል የሳቀብን ያኔ፡፡
14. ጥሬዉን ከብስሉ ጊዜ ሲለየዉ፣
ነገ ጠዋት አይኖርም ዛሬ የምናየዉ፡፡
15. አይተነዉ አይተነዉ ካላማረ ቀኑ
እኛም አዉሬ እንሁን እነሱም ያድኑ፡፡
16. አመለ ልስልሱን የዋህ ገራም በሬ
ነካክተዉ ነካክተዉ አደረጉት አዉሬ፡፡
17. ነካክተዉ ነካክተዉ አንድ አረጉንና
እያፈሱት ሄዱ በሰፈሩት ቁና፡፡
18. አንተ ያገሬ ልጅ የአማራዉ ወጣት
አማራን አደራ ኢትዮጵያን አትርሳት፡፡

19. ወሎማ አማራ ነዉ የማይጠረጠር
    አትፈታተኑት እርስቱ ላይ ይደር፡፡
20. ይነጋል ባልነዉ ቀን ጨለማ ነገሰ፣
    ኑሮ ተወደደ ሰዉ እየረከሰ፡፡
21. ባየር ባየር ሲሉት ይዘላል አንበጣ
    የሌባ ቀን መሽቶ የጀግና ቀን መጣ፡፡
22. አትግፉኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ
    እንኳን የሰዉ ሀገር የራሴን ትቻለሁ፡፡
23. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር
    በርስትና በእምነት የማንደራደር፡፡
24. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ
    የአማራ ልጅ ፋኖ አይፈታም ትጥቁ፡፡
25. አሳምነዉ ጽጌ ሞተ ያለዉ ማነዉ
    አሁንም አማራን የሚመራ እሱ ነዉ፡፡
26. ጎንደር ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይሉ፣
    ጎጃም ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይሉ፣
    ወሎ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይሉ፣
    ሸዋ ላይ ባስጠይቅ የኛ ነዉ ይሉ፣
    ለካስ ይዘነዋል በራበሩን ሁሉ፡፡
27. ንቃ ራያ ቆቦ ንቃ ሰሜን ጎንደር፣
    ባገርና በርስት እንዳትደራደር፡፡
28. ደራና ማይካድራ የፈሰሰዉን ደም፣
    ቁመህ እንዳትረሳዉ በድንህ ሳይደም፡፡
29. አረንዛዉ ጎጃም ይመጣል ገና፣
    ዝናብ ያዘለ መስሎ ደመና፡፡
30. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነዉ
    ከተጣሉ ወዳ ድርድር ምንድነዉ?
31. አምናም አስሮኝ ነበር ዘንድሮም አጋዘኝ
    እንደማንላቀቅ ገብቶታል መሰለኝ፡፡
32. እኛ ምን ቸገረን እኛ ምን ከዳችን
    ሐገራችን ሸዋ እርሻዉ ከበራችን፡፡
33. ጋሻ መከታችን የአማራ ፋኖ ነዉ
    የጠሉናል እንጂ የሚነካን ማነዉ፡፡
34. ንቃ ያገሬ ሰዉ ንቃ ሰሜን ጎንደር
    ባገርና በርስት እንዳትደራደር፡፡
35. እንኳን ጤፍ አዝመራ ማሽላም ቢሆን
    ለጠላት አንሰጥም ርስታችንን

36. ዉሸቱ ይብቃና እዉነት እንናገር
ወሎ ላይ ተወልደን ካሳምነዉ ሃገር፡፡
37. ለዘረፋ መጥቶ ሽሮና በርበሬ
ወሎ ገብቶ ቀረ የትግራይ ገበሬ፡፡
38. ወንድ ልጅ ነኝና ሳልነካህ አትንካኝ፣
ሰፊዉን አዕምሮ በጠባቡ አትለካኝ፡፡
39. ቁጣዬ ገንፍሎ ንደት ካሰከረኝ፣
ኋላ አንላቀቅም ብምርህ አይማረኝ፡፡
40. ከእንግድህ አይኖርም አማራ ታፍኖ፣
የቁርጥ ቀን ልጁ እያለለት ፋኖ፡፡
41. ጠ/ሚኒስቴር ኬኛ ከንቲባዋ ኬኛ
ኢታማጆር ኬኛ ደህንነቱም ኬኛ
ብሔር ብሔረሰብ ተከናንበህ ተኛ፡፡
42. ኦነግም ብሎናል ቆቦ ነዉ ድንበሬ
ሃወሃት ብላለች ወልቃይት ሀገሬ
እምቢአለ እንጂ ፋኖ ተጠምዶ አንደበሬ፡፡
43. የተገላቢጦሽ ነዉ የኦህደድ ስራ
አንድኛዉ ያፈርሳል አንደኛዉ ሲሰራ፡፡
44. ጀግናዉ የሸዋ ልጅ ይመጣል በድንገት
ዝናሩ ሙሉ ነዉ ጎዶሎም የለበት፡፡
45. ከነኩትማ ከነካኩት፣
የሸዋ ልጅ ነዉ ሰደድ እሳት፡፡
46. መተኮሱንማ ሁሉም ይተኩሳል
ጀግናዉ የአማራ ልጅ አንገት ይበጥሳል፡፡
47. ምንሽር ሆዳሙ ጓንዴ ቀፈታሙ
ስጋ በልቶ ያድራል በሁዳዴ ጾሙ፡፡
48. ምድር ከሰማይ ቢደበላለቅ
አረንዛዉ ጎጂ ከያዘም አማይለቅ፡፡
49. ግፉ በዛ ብሎ ከተነሳ አማራ
አራግፎ ይጥላል በሰማይ አሞራ፡፡
50. እንዳትፈራ እዳትፈራ በለዉ
ቅጠል ነዉ እንጂ እሾህም የለዉ፡፡
51. ግፉ በዛ ብሎ ከተነሳ አማራ
አድቅቆ ይጥላል ለጠላት አይራራ፡፡
52. እንኳንስ መታሰር መገደል ቢመጣ
ማንንም አልሰማ በፋኖ የመጣ፡፡
53. በህግ አምልክ ብዬ ለምን እጮሃለሁ

ለምሬ ወዳጅ እነግርብሃለሁ፡፡

54. ያም ወርዶ ያም ወርዶ ድቡን ነቀነቀዉ
ፋኖ ሊዋጋበት ፈሪን ምን ጨነቀዉ፡፡

55. አይዟችሁ ጓዶቼ ሆዳችሁ አይፍራ
እንጓዛለን ከወንዶች ስፍራ፡፡

56. መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ
ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ፡፡

57. ወንድ ልጅ ነኝና ሳልነካህ አትንካኝ፣
ሰፊዉን አዕምሮ በጠባቡ አትለካኝ፡፡

58. ቁጣዬ ገንፍሎ ንደት ካሰከረኝ፣
ኋላ አንተን አያርገኝ ብምርህ አይረኝ፡፡

59. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ
እስካፍንጫዉ ታጥቋል አማራዉ መብረቁ፡፡

60. መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ
ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ፡፡

61. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡

62. አንተ ሆዳም በሬ የገደሉ ላይ
ሳሩን ብቻ ሳይሆን ገደሉንም እይ፡፡

63. ወይኔ አበቤ ወይኔ አበቤ፣

አልወደደሽም ሂጂልኝ ቀልቤ፡፡

164. ወይኔ ቀጀላ ወይኔ ቀጀላ፣

መኖሩ ይብቃህ በኦነግ ጥላ፡፡

165. ቢመችሽም ባይመችሽም

ሽገር ፊንፊኔ አይሆንልሽም፡፡

## 2.3. የመቀስቀስና የማነቃቃት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. ጠላትን ሳይገድሉ ምን ያደርጋል አፍሮ
መቀሱን ላኪልኝ ቁርጥ ነዉ ዘንድሮ፡፡

2. አሻቅበህ በለዉ ሰማዩን በእንቧይ
ጊዜዉ ካልደረሰ ሰዉ ይሞታል ወይ?

3. አዉድማዉም ይስፋ በሮችም አይራቁ
መናዱ የማይቀር ዉሽልሽል ነዉ እርቁ፡፡
እርባና የሌለዉ ዉሽልሽ ነዉ እርቁ፡፡

4. አማራ ዙሪያዉን መሬቱ ተወሮ፣

ህዝቡ በያገሩ በጅምላ ተቀብሮ
ምን ተይዞ ጉዞ ይታሰባል ኑሮ፡፡

6. አዉድማ አረብርበን እየጠበቅናቸዉ
ቀሩ እነዚያ በሮች እንዳናሂዳቸዉ፡፡

6. አይዟችሁ ጋሞቹ ሆዳችሁ አይባባ፣
ይጋጠም የለም ወይ ሰባትና ሰባ፡፡

7. እንበለዉና እናት እናቱን፣
እንከፍለዋለን የየግምቱን፡፡

8. እንበለዉና ጉልበት ጉልበቱን፣
እያነከሰ ይዉጣዉ ዳገቱን፡፡

9. እንበለዉና ባጭር መዋጣጣ
ከሽማግሌ ቃልም አይወጣ

9. እንበለዉና በወይራ ጎመድ
እንደለመደች እናቱ ትበድ፡፡

10. ወሎ ራሱን ታሞ ተኝቷል ከቤት፣
ከጋራዉ ላይ ወጥተህ ሞረሽ በልለት፣
ያገኝለት እንደሁ ጎንደር መድሃኒት፡፡

11. ተዉ እርገጥ እርገጥ እርገጥ ባንድ ላይ፣
ተወልደህ አድገህ ሰሜን ሸዋ ላይ ፡፡
ተወልደህ አድገህ ቤተ አማራ ላይ፡፡

12. ንቃ ያገሬ ሰዉ ንቃ ሰሜን ጎንደር
ባገርና በርስት እንዳትደራደር፡፡

13. በረቱን ከፍታችሁ በሮቹን ላኳቸዉ
ሸገር ከተማ ላይ በራይ አለባቸዉ፡፡

19. ትወጋ እንደሆነ ዉጋ እንደሞፈር
ጆሮ ከተማ ነዉ ይሰማል ጎንደር፡፡

20. ፈረሱንም ጋልበዉ ላቡ እስኪንቀረቀር
በልጅጉን ተኩሰዉ ቃታዉ እስኪሰበር
ጦሩንም ወርዉረዉ ሰማዩ ይሰንጠር
ኋላ በታሪክ ፊት አንገት ከማቀርቀር፡፡

21. ድሮም ለጭንቅ ነዉ ጀግና የሚፈለገዉ፣
ይምጣ ያማራዉ ልጅ በትግል ያደገዉ፡፡

22. ያገር ያለህ እያልን ዝም አላችሁ ምነዉ፣
ያማራዉ በሽታ ለናንተም ህመም ነዉ፡፡

23. በል ተነሳ ፋኖ የአማራዉ ነፍጠኛ
ነቃቅለህ ጣለዉ ያንን ጎጠኛ፡፡

24. ታምሜያለሁና ሁላችሁ ታመሙ

ያንድ ሰዉ በሽታ ይበቃል ለሁሉ፡፡

25. እንኳንስ ጎጃም አይዞህ እያለዉ
እንኳንስ ጎንደር አይዞህ እያለዉ
እንኳንስ ወሎ አይዞህ እያለዉ
እንዳዉም ሸዋ አመጸኛ ነዉ፡፡

26. አይዟችሁ ጋሞቹ ሆዳችሁ አይባባ
ይጋጠም የለም ወይ ሰባትና ሰባ

27. ለፍትህ ልታገል ለሕዝቤ ልዝመት
ለሞት አይደለም ወይ የተፈጠርኩት፡፡

28. በለዉ በጎራዴ ድገመዉ ባጣና
ምንጊዜም ደህና ሰዉ አልተባልክምና፡፡

29. ምን ያርጋል ጎመን ስጋ ሳይታጣ
ተሰቅሎ እያለልን ያምስት ዓመት ቋንጣ፡፡

30. በታጣፊ ክላሽ ክንዱን ካልሰበሩት
ጥላት መች ይተዋል በሥላሴ ቢሉት፡፡

31. በረቱን ከፍታችሁ በሮቹን ላኳቸዉ
ሽገር ከተማ ላይ በራይ አለባቸዉ፡፡

32. ትወጋ እንደሆነ ዉጋ እንደሞፈር
ጆሮ ከተማ ነዉ ይሰማል ጎንደር፡፡

33. ህይወቴን ላማራ ስጋየን ላሞራ
ፋኖ ነኝ እኔ ማንንም አልፈራ፡፡

34. ያዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
ፋኖ ቁሞ አያይም ስትፈርስ ሀገሩ፡፡

35. ሞቅ በል! ሞቅ በል! ሞቅ በል! ቀዝቃዜ
ያማራዉ ጢነኛ ያሳምነዉ ሚዜ፡፡

36. ፈረሱንም ጋልበዉ ላቡ እስኪንቆረቆር
በልጅጉን ተኩሰዉ ቃታዉ እስኪሰበር
ጦሩንም ወርዉረዉ ሰማዩ ይሰንጠር
በታሪክ ፊት አንገት ከማቀርቀር፡፡

37. መቃጠልህ ቢቀር አይሞቅህም ወይ
ከኋላህ ተነስቶ ሲሆን ዘመናይ፡፡

38. ይበላሃል ፋኖ ይቆረጥምሃል፣
ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፡፡

39. በገዛ ሀገርህ ላይ የምትሳደደዉ፣
በቃ በል አማራ ትግስትም ልክ አለዉ፡፡

40. ድሮም ለጭንቅ ነዉ ጀግና የሚፈለገዉ፣
ግባ የጎጃም ልጅ በትግል ያደግከዉ፡፡

41. ያገር ያለህ እያልን ዝም አላችሁ ምነዉ፣
ያማራዉ በሽታ ለናንተም ህመም ነዉ፡፡
42. ቋያ ሰደድ እሳት ጎጃም ላይ ለኩሰዉ
ነደዉ አለቁበት እንደሻማ ቀልጠዉ፡፡
43. ካልደፈረሰ አይጠራምና
ግድቡን ናደዉ ፋኖ ግባና፡፡
44. በል ጠመንጃ ግዛ በሬህን ሽጥና
መሬትህን በታንክ አርሰዉታልና፡፡
45. ኧረ ተዉ ተረኛዉ ግፉ አይብዛ በቃ፣
ፀሀይ ትጠልቃለች እንኳንስ ጨረቃ፡፡
46. ይለያል ይለያል ይለያል ዘንድሮ፣
እንክርዳድ ከስንዴዉ በዉል ተበጥሮ፡፡
47. ጎጃም ዝናብ ጥሎ ጎርፍ ሆኗል ሀገርህ፣
አረንዛዉ ጎጃሜ ግባ ባጭር ታጥቀህ፡፡
48. ኧረ ተይ እናቴ ፈሪ አታርጊዉ ልቤን፣
እቤት እንድቀመጥ አጣጥፌ ክንዴን፣
ማን ባቀናዉ ሃገር ላሳድግ ነዉ ልጄን?
49. ዝም ሲል አማራ የሌለ መስላቸዉ
ትዕግስቱ ሲበዛ የፈራ መሰሏቸዉ
ሰበርነዉ ያሉትን እዩት ሲሰብራቸዉ፡፡
50. አባይ በረሃ ማን ግቡ አላቸዉ
አረንዛዉ ጎጄ መነጠራቸዉ፡፡
51. አረንቋ ነዉ ጎጃም ዝናቡ እየናጠዉ
እየዋጠዉ ቀረ እየሰለቀጠዉ፡፡
52. ምነዉ በሰማይ ላይ እንዳሞራ ልጅ
ወርደህ በጠብመንጃ ይለይልን እንጂ፡፡
53. ታገሰህ ለምነህ ካልቻለ ሊተዉህ
እጅን የሚወጣ እጅ ነዉ እንግድህ፡፡
54. ዉረድ እንዉረድ እንተያይ
በሩቅ አይሆንም የኛ ጉዳይ
55. አረም አትፍራ ንቀል በጅህ
እሾህም የለዉ የሚወጋህ፡፡

## 2.4. ባህላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን የማጠናከር ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. ሰማይ ሲደማምን ገደል ይረዛል
ይዘገያል እንጂ በደል መች ይረሳል፡፡
2. እርሱ ነዉ ሚዛኑ እነሱም ያዉቃሉ
መች ጎድሎ ያዉቃል አማራዉ ከቃሉ፡፡

3. አትግፋኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ
እንኳን ያንተን ሃገር የኔንም ትቻለሁ፡፡
4. እኔ ላንቺ ላንቺ አንቺ ለሌላ ሰዉ
የየካዉ ሚካኤል አይንሽን ያፍስሰዉ፡፡
5. ይሄዉ መጡ መጡ ደረሱ እዛማዶ
እየሸሹላቸዉ መከተል ተለምዶ፡፡
6. በመኪናዉ መንገድ በወለሊማዉ
አንቺን ተከትዬ ይብላኝ አሞራዉ፡፡
7. ሌት ስሄድ አድሬ ሲነጋ ልሙት
ለሞት አይደለም ወይ የተፈጠርኩት፡፡
8. እንኳንስ ወዳጁ ያዉቀዋል ጠላቱ
ሸዋ ባላመጠ ይዉጣል ባመቱ ፡፡
9. ወንዛችን ተከዜ ሀገራችን ጎንደር
ባገርና በእምነት የማንደራደር፡፡
10. ሸዋ ባላመጠ ይዉጣል ባመቱ
ጠላት አይፈታዉም ቅኔ ነዉ ብልሃቱ፡፡
11. ሐገሬ ላይ ሁኜ ናፈቀኝ ሐገሬ፣
ከማን ጋር ይዋላል ሁሉም ሆኗል አዉሬ፡፡
12. ዳኛዉ ተኩላ ነዉ ፈራጁ ቀበሮ፣
ባንድ ላይ ሆኑና ቀበሩን ዘንድሮ፡፡
13. ከፍ አረገኝ ብሎ ጊዜ እንደተራራ፣
ልርገጥህ አይልም ወንድሙን አማራ፡፡
14. እንብላ እንጠጣ ነዉ ለመጣ ለሄደዉ፣
ራያ ምድር ላይ ሰዉ መሆን በቂ ነዉ፡፡
15. አሁን ምን ያደርጋል ነገር ማመላለስ፣
እነሱም አይመጡ እኛም አንመለስ፡፡
16. ሸዋ ጎንደር ጎጃም ወሎም አንድ አገር ነዉ
አመራር አጥቶ ነዉ የተበታተነዉ፡፡
17. አስተምራዋለች ቂጣ በደንደሱ
ተሸከም አለችኝ እኔንም እንደሱ፡፡
18. ምን ይጎዳ ይሆን ተካፍለዉ ቢበሉ፣
ሁሉን ለኛ ብቻ ካልሆነ የሚሉ፡፡
19. እንጫወት እንደሁ እንጫወት ዛሬ
ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡
20. ባባቴ በአያቴ ጀግንነት የሞላኝ፣
ቀብረር ያልኩ ሐበሻ ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡
21. አዲስ አበባ ላይ ቁና ጠየፍ አይገኝ

ርሸርሹ ጎጃም ካንተ በፊት ያርገኝ፡፡

22. እንጫወት እንጂ እንጫወት በጣም
እንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም፡፡

23. በሆድህ ያለዉን ሁሉንም አታዉጣዉ
አይመስሌ ሰላይ ነዉ የዛሬ ዘመን ሰዉ፡፡

24. ለምን ይታሰራል የከተማ ልጅ
እምብዛም ቢጠና በዋስ ያድራል እንጂ፡፡

25. እኔንም ግደሉኝ ንብረቴንም እንኩ
የሬሳየን መዉጫ ጎጆን አትንኩ፡፡

26. ወሎነኝ አልልም ስሜን አሳንሼ
አማራ ነዉ ክብሬ ትልቁ አዳራሼ፡፡

27. ክብሬን ከወገኔ አስበልጨዉ ብገኝ
የቴወድሮስ አጥንት እሾህ ሆኖ ይዉጋኝ፡፡

28. ሀቅ ነዉ መርሁ እዉነት ነዉ መለያዉ፣
አይበላም አደራ ጨዋ ነዉ ጃዊሳዉ፡፡

29. ጎጆ ትዳሩ ተዉት ይቅርብኝ፣
መዉደድ መወደዱ ተዉት ይቅርብኝ፣
ማረስ ማፈሱ ተዉት ይቅርብኝ፣
ያያት ያባቴ አደራ አለብኝ፡፡

30. እኔስ አራሽ ነበርኩ የገበሬ ልጅ፣
በሮቹን በድሮን ገደሏቸዉ እንጂ፡
አርሼ እንዳልበላ ከለከሉኝ እንጂ፡፡

31. እንኳንስ ትግርኛ ያዉራ ጣሊያንኛ
ክፉ ሀሳቡን ነዉ የጠላነዉ እኛ፡፡

32. እባብ ሰለክላኬ መንታ ነዉ ምላሱ ፣
ሲያምኑት የከዳ ሰዉ አይማርም ነፍሱ፡፡

33. እስኪ እርግ እርጉን  አይኔ ይንከራተት
እንደልቡ አይበላም እረኛ ያለዉ ከብት፡፡

34. የዱላ ስባሪ ብታጣበት በጁ
አንተምሴት እኔምሴት አለችዉ ወዳጁ፡፡

35. እንበለዉና ሀገር ይዋሰዉ
በስንቱ ባንዳ ይቸገራል ሰዉ፡፡

36. በገዛ አገራቸዉ የተሳቀቁ
ሊቃዉንቱ ሁሉ ተሰደዉ አለቁ፡፡

37. እኔ የወሎን ልጅ አይንካብኝ ክፉ
እንኳንስ ሞቱና ያሳሳል እንቅፉ፡፡

38. እንጫወት እንደሁ እንጫወት ዛሬ

ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡

39. ምንሽር ሆዳሙ ጓንዴ ቀፈታሙ
ስጋ በልቶ ያድራል በሁዳዴ ጾሙ፡

## 2.5. የተቃዉሞና የቅሬታ ድምጽ የማሰማት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. ሌባዉ ሲለቀቅ በግርግር፣
ዘመነ ካሴ ለምን ይታሰር፡፡
2. እኒህ የቀን ጅቦች ሆድ ነዉ አምላካቸዉ
ሐገር ስትደፈር ቅርም አይላቸዉ፡፡
3. ስጋዉን አይበሉት ደሙን አይጠጡት
አሳምነዉ ጽጌን ለምን ገደሉት፡፡
4. ራያ ወሎ ነዉ ገለል በል ህወሃት
ባንዳ የማይፍረዉ የጢነኞች ርስት፡፡
5. ሲቀር ጥቀራል፣ ሲቀር ይቀራል
በሽገር ዳቦ ማን ይፎገራል፡፡ተ
6. ወለጋ ሕዝብ ሲያለቅ ያላወጀ አዋጅ፣
አማራን ለማጥፋት የሚያዉጅ አዋጅ
ምን ብልጽግና ነዉ ብልግና ነዉ እንጅ፡፡
7. ወይ እገድልሃለሁ ወይም እኔ ሙቼ
እስከመቼ ድረስ ግልምጫ ፈርቼ፡፡ አቋ
8. አንገቴን ስደፉ ፈሪ መስያቸዉ
አገር አሰለቼ ስድብ ድንፋታቸዉ
ነፍጠኛ መሆኔን ማን በነገራቸዉ፡፡ አቋ
9. ምን ያደርግልናል እኝጦጦ ቢሰራ
በጅምላ እያለቀ ሰዉ አማኑ አማራ፡፡
10. በሬዉ አምና ሙቶ ቆዳዉ ተወጥሯል፣
መኾገር ታማኝ ሊሆን አሁንም ተጣብቋል፡፡
11. ባማራ ርስት ላይ አልደራደርም
በወገኖቼ እምባ ተሞሽሬ አልኖርም፡፡አቋ
12. ዘመናችን አልቆ አለን በሰዉ ዘመን
ሕዝብ አንገቱን ደፍቶ በተረኞች ዘፈን፡፡
13. መፈተን አልወድም እኔም እንዳባቴ
ማንም አይበጥሰዉ ማተቤን ካንገቴ፡፡
14. እኛ መች አማረን የኦሮሞ ጠጅ
እኛ መች አማረን የወያኔ ጠጅ
እኛ መች አማረን የተረኞች ጠጅ
እየበጠበጡ ይጠሩናል እንጅ፡፡
15. መሰደድ መታሰር ከሆነ የኛ እጣ

መገደል መታገት ከሆነ የኛ እጣ
መበተን መፈርከስ ከሆነ  የኛ ዕጣ
መደመር መበልጸግ ባፍንጫችን ይዉጣ፡፡

16. አንተ ሰዉ አትግፋኝ ግፊ ሰልችቻለሁ፡፡
እንኳን የሰዉ ሀገር ሀገሬን ትቻለሁ
17. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ
ነፍጠኛዉ አማራ አይፈታም ትጥቁ፡፡
18. ህዝብ እንዲያስተዳድር ቢሰጡ አገር
እንደልጅ አማረዉ መጫት ባፈር፡፡
19. ተረኛ ቤቴን አፈረሰዉ
አዳነች አበቤ ነብስሽን አይማረዉ፡፡
20. ፍቅር ባማርኛ ጠብ በኦሮምኛ
ሲሰብከን ይዉላል የዘንድሮ ዳኛ፡፡
21. አዉድማዉም ይስፋ በሮችም አይራቁ
መናዱ የማይቀር ዉሽልሽል ነዉ እርቁ፡፡
እርባና የሌለዉ ዉሽልሽ ነዉ እርቁ፡፡
22. አማራ ዙሪያዉን መሬቱ ተወሮ፣
ህዝቡ በያገሩ በጅምላ ተቀብሮ
ምን ተይዞ ጉዞ ይታሰባል ኑሮ፡፡
23. ወልቃይት ጠገዴ ዳንሻና ሁመራ፣
ሰዉም ጎንደሬ ነዉ መሬቱም አማራ፡፡
24. ደራና ማይካድራ የፈሰሰዉን ደም፣ ምክ
መቼም እንዳትረሳዉ  ደግሞ እንዳይገም፡፡
25. እንኳንስ መታሰር መገደል ቢመጣ
ማንንም አልሰማ በፋኖ የመጣ፡፡ አቋ
26. ትመታ እንደሆነ እኛን አይተህ ምታ
የማትመታ እንደሆን ልቀቅ የሰዉ ቦታ፡፡
27. በገዛ ሀገርህ ላይ የምትሳደደዉ፣ ቅስ
በቃ በል አማራ ትግስትም ልክ አለዉ፡፡
28. ህወሃት በተንኮል የዘራዉን ዘር
ኦህዴድ በሰዉ ደም ያበቅለዉ ጀመር፡፡
29. ቢመችሽም ባይመችሽም
ሸገር ፊንፊኔ አይሆንልሽም፡፡
30. ዝግባዉን ቆረጡት እነ ልክ አያዉቁ
ምን ያፈራ ይሆን ብለዉ ሳይጠይቁ፡፡
31. ካሳምነዉ ሀገር ላስታ ተወልጄ
በነጋ በጠባ ይታሰራል እጄ፡፡

32. ነፍጠኛ ነኝ ማለት አይቻልም እንዴ፣
አማራ ነኝ ማለት ተከልክሏል እንዴ፣
ሁሉ የሚሳደደን በጦር በጎራዴ፣
እድሜ ለምንሽር አልቤንና ጓንዴ፡፡
33. አባቱ እንቢተኛ ልጁ ሞገደኛ፣
ነገር የገባዉ ቀን እንቅልፍ የማይኛ፣
ጠላቱን ያምሳል ደርሶ እንደመጋኛ፡፡
34. የባለስልጣን ልጅ አይሄድም ዘመቻ
ሰላም አስከባሪ የድሃ ልጅ ብቻ፡፡
35. ጣሊያን አልመጣብን ተኩስ አልተተኮሰ
ወይ ወራሪ አልመጣ ችግር አልደረሰ
ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አገሩ ፈረሰ፡፡
በኮማንድ ፖስቱ አገሩን ያመሰ፡፡
36. ያምናን ቀን አማሁት ላፌ ለከት የለዉ፣
የዘንድሮዉ ባሰ እጅም እግርም የለዉ፡፡
37. መስሎ ማደር ይብቃ ለእዉነት እንኑር፣
ወሎ ላይ ተወልደን ካሳምነዉ ሃገር፡፡
38. ገለል በል ቅጥረኛ ገለል ይሻልሃል፣
ይበላሃል ፋኖ ይቀረጥምሃል፡፡
39. አትግፋኝ ወንድሜ ግፊያ ጠልቻለሁ፣
እንኳን የሰዉ ሀገር የራሴን ትቻለሁ፡፡
39. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነዉ፣
ከተጣሉ ወዳ ድርድር ምንድነዉ?
40. የተላላኪዎች ሆድ ነዉ አምላካቸዉ
ሐገር ስትደፈር ቅርም አይላቸዉ፡፡
41. ትመታ እንደሆነ እኛን አይተህ ምታ፣
የማትመታ እንደሆን ልቀቅ የሰዉ ቦታ፡፡

## 2.6. የማዉገዝ እና የመተቸት ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች

1. ይሄዉ መጡ መጡ ደረሱ እዛማዶ፣
እየሸሹላቸዉ መከተል ተለምዶ፡፡
2. ዳኛዉ ተኩላ ነዉ ፈራጁ ቀበሮ፣
ባንድ ላይ ሆኑና ቀበሩን ዘንድሮ፡፡
3. አሁን ምን ያደርጋል ነገር ማመላለስ፣
እነሱም አይመጡ እኛም አንመለስ፡፡
4. እናቱ አስተምራዉ ቂጣ በደንደሱ
ና ተሸከም አለኝ እኔንም እንደሱ፡፡
5. በሆድህ ያለዉን ሁሉንም አታዉጣዉ

አይመስሌ ሰላይ ነዉ የዛሬ ዘመን ሰዉ፡፡

6. እንኳንስ ትግርኛ ያዉራ ባሊያንኛ
ክፉ ሀሳቡን ነዉ የጠላነዉ እኛ፡፡

7. እባብ ሰለክላኬ መንታ ነዉ ምላሱ ፣
ሲያምኑት የከዳ ሰዉ አይማርም ነፍሱ፡፡

8. የዱላ ስባሪ ብታጣበት በጄ
አንተም ሴት እኔም ሴት አለችዉ ወዳጄ፡፡

9. እንበለዉና ሀገር ይዋሰዉ
በስንቱ ባንዳ ይቸገራል ሰዉ፡፡

10. ድንጋይ ተንከባሎ ቢመታዉ ጉልበቱን
ምነዉ ባልወለድሽኝ ብሎ አላት እናቱን፡፡

11. አሁን ምን ሊሆን ነዉ ፈሪ መወለዱ
መሸሽ የለመደዉ ባርባር ሊለዉ ሆዱ

12. እደግ እደግ ብለን ያሳደግነዉ ቀጋ
አለ ዘመም ዘመም እያኑ ሊወጋ፡፡

13. እኒህ የቀን ጅቦች ሆድ ነዉ አምላካቸዉ፣
ሀገር ሽጦ መብላት ማን አስተማራቸዉ፡፡

14. ያም ወርዶ ያም ወርዶ ድቡን ነቀነቀዉ
ፋኖ ሊዋጋበት ዛርጢን ምን ጨነቀዉ፡፡

15. እናቴስ መችወልዳኝ እኔስ መች ተወለድኩ፣
ከጠላቶቼ ጋር አብሬ እየዶለትኩ፡፡

16. ታጥቆ የመጣዉን ጀግና ሊገዳደር
ነዳነዉ እንደላም የሸኔን ወታደር፡፡

17. ትኳኩለዋለች ምን ይረባኝ ብላ
ወገኑን የሚሸጥ ገድሎ የሚበላ፡፡

18. ለዘረፋ መጥቶ ሽሮና በርበሬ
ወሎ ገብቶ ቀረ የትግራይ ገበሬ፡፡

19. አንተ ሆዳም በሬ የገደሉ ላይ
ሳሩን ብቻ ሳይሆን ገደሉንም እይ፡፡

20. ሆዳምና ባንዳ ትራፊህን አንሳ
ይሆንህ እንደሆን ራትና ምሳ፡፡

21. ጎንደር ላይ ተወልደህ የፈራህ እንደሆን
እናትህንጠይቃት ሽል ቀይራ እንደሆን፡፡

22. ከቶ ምን ሊሆን ነዉ ፈሪ ማቶንቶኑ
አይበጠስ ቅጠል ካልደረሰ ያቀኑ፡፡

23. እኔ ለፊሪ አልሰጥም ልብሴን
ያስጠይቃታል በሰማይ ነፍሴን፡፡

24. ሸኔ አይመጣም እንጂ ቢመጣም ግደለኝ
ጥሎት የሚሸሼዉ መሳሪያ እየታየኝ፡፡
25. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
ልቀቁት በዳገት ሳር ይብላ እንደበሬ፡፡
26. ሞቅ በል ሞቅ በል ሞቅ በል ቀዝቃዜ
ያማራዉ ጢነኛ ያሳምነዉ ሚዜ፡፡
27. እንበለዉ ካለችሁ እንበለዉ ባቱን
እናቱ ቀልባ ያሰባችዉን፡፡
28. እንበለዉና የመጣዉ ይምጣ
ከሽማግሌ ቃልም አይወጣ፡፡
29. ብረቱን አግለህ እቂጡ ለኩሰዉ
መቼም አይነሳ ወኔ የሌለዉ ሰዉ፡፡
30. ያንን ቀዳዳ ያንን ጉረኛ፣
ወገቡን በለዉ እንደመጋኛ፡፡
31. በለዉ በለዉና አሳጣዉ መድረሻ
የሰዉ ልክ አያዉቅም ባለጌና ዉሻ፡፡
32. እንበለዉ እና ጉልበት ጉልበቱን
እያነከሰ ይዉጣዉ ዳገቱን፡፡
33. ዘንድሮ ኢትዮጵያ ታሪክ ተበላሼ
ባለክላሽ ቁሞ ባለመድፉ ሸሼ፡፡
34. እቤት ተደብቄ ፈሪ አድርጌዉ ልቤን፣
ማን ባቀናዉ ሀገር ላሳድገዉ ልጄን፡፡
35. አጣማጁን ሲያጣ እምቧ ይላል በሬ
ያማራዉ ልዩ ሐይል ወዴት ዋለ ዛሬ፡፡
36. ሳንጃዉን አግለህ ከቂጡ ለኩሰዉ
መቼም አይነሳ ወኔ የሌለዉ ሰዉ፡፡
37. ርስቱን ሲወስዱት ሽንሽነዉ እንደቦይ
አባትዮዉ ቢሞት ልጅየዉ የለም ወይ!?
38. ዉሃ ቁልቁል እንጂ መች ሽቅብ ይፈሳል
ትንሽ ከፊት ሲሆን ሀገር ያበላሻል፡፡

**2.7. የሕዝቡን ፍላጎት እና ምኞት የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸዉ የአማርኛ ቃል ግጥሞች**

1. ያለዉ እየበላ የሌለዉ ያለቅሳል፣
ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ይሰራል ያፈርሳል፡፡
2. ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ሲሰራም ሲያፈርስ
አንዱ ሲያሸበርቅ አንዱ አፈር ሲለብስ፡፡
3. እስኪ መጀመሪያ ሀገር ደህና ትሁን
እስኪ መጀመሪያ እኛ ደህና እንሁን

ጊዜ መሃንዲስ ነዉ ይሰራናል አሁን፡፡

4. ለሁሉም ጊዜ አለዉ ብሏል ሰለሞን
መታገስ ነዉ እንጂ መቸኮል ለምን፡፡

5. እንደቤት ጥራጊ እንደ ጉድፍ ወድቀን
መታገስ ሰለቸን ይህንን ክፉ ቀን፡፡

6. ቀረርቶ ብቻ ነዉ ሲሉን እንዳልኖሩ
ፎክረን ስንተኩስ ዛሬስ ምን አወሩ፡፡

7. ስንሸልል ስንፎክር ስናንጎራጉር
ጽንፈኛ ነፍጠኛ እንባል ነበር፡፡

8. ፍትህና ጸሀይ ሁሉም በጊዜ ነዉ፣
ከመሸማ ወዳማ የጉልበተኛ ነዉ፡፡

9. ያንተ ልጅ ሲበላ የኔ ልጅ ያለቅሳል፣
ያንተ ቤት ተሰርቶ የኔ ጣራዉ ፈርሷል፤
ያንተ መሬት ታርሶ የኔ ዳዋ ለብሷል ፣
ወይ ካንተ ወይ ከኔ ያንዳችን ቀን ደርሷል፤
ጊዜ መሃንድስ ነዉ ይሠራል ያፈርሳል፡፡

10. እንኳን እኛ እያለን እኛም ባንኖር
ማንም አይነካትም የአማራን ምድር፡፡

11. እዘምታለሁ እንጂ አንጀቴን አስሬ
እንደት ዝም ልበል ሲደፈር ሀገሬ፡፡

12. ምን አለ ጎንደር ምናለ
ምን አለ ጎጃም ምናለ
ምን አለ ወሎ ምናለ
ምን አለ ሸዋ ምናለ
ሐገሬን ለሰዉ አልሰጥም አለ፡፡

13. አጣማጁን ሲያጣ እንቧ ይላል በሬ
ያማራ ልዩ ሃይል ወደት ዋለ ዛሬ፡፡

14. የሚሾመዉ ሁሉ ሌባ ሁኗልና፣
ሐገርህ መሪ አጥቶ ተበታትኗልና፣
አሳምነዉ ጽጌ ቶሎና ቶሎና ፡፡

15. አይ አማራ ክልል አቤት ወይ እድልህ
እንዳዉ መቼ ይሆን ቀን የሚወጣልህ፡፡

16. ሲቀር ይቀራል ሲቀር ይቀራል፣
በሸገር ዳቦ ማን ይፎገራል፡፡

17. ወሎነኝ አልልም ስሜን አሳንሼ
አማራ ነዉ ክብሬ ትልቁ አዳራሼ፡፡

18. አንገቴን ስደፋ ፈሪ መስያቸዉ

ነፍጠኛ መሆኔን ማን በነገራቸዉ፡፡

19. አማራዉ ተራራዉ ተገፍቶ የማይወድቀዉ
ለጸሎት/ለፍቅር ብቻ ነዉ የሚንበረከከዉ፡፡

20. እንኳን ቃታ ከፍቶ ሲያጓራ መዉዜሩ፣
ነፍጠኛዉ የአማራ ያስፈራል ግንባሩ፡፡

21. እንጫወት እንጂ እንጫወት ዛሬ
ነገማ ስራ ነዉ ይጠመዳል በሬ፡፡

22. ብታዉቁም እወቁ ባታዉቁም ጠይቁ
እስካፍንጫዉ ታጥቋል አማራዉ መብረቁ፡፡

23. እንኳን አሁንና እስካፍንጫ ታጥቀን
ባሮጌ ምንሽር ታንክ እንማርካለን፡፡

24. የአማራዉ ፋኖ መጣ ገሰገሰ፤
ምን ይዉጠዉ ይሆን ድንገት የነገሰ፡፡

25. ራያ ወሎ ነዉ ገለል በል ህወሃት
ዓለም ያዉቀዋል የአማራን ርስት፡፡

26. የወልድያ አሞራ አይበላም ብርንዶ
ቆላ የወደቀ ጥብስ ስጋ ለምዶ፡፡

27. ይቆጡኝ ይሆን ወይ ነገር ባዉደመድም
ይሄ የሸዋ ልጅ ያደርገዋል ዉድም፡፡

28. እኔ የራያን ልጅ አያሰማኝ ክፉ
እንኳንስ ልጆቹ አይቆረጥ ዛፉ፡፡

29. የራያ ልጅ ታሞ ጎንደር ከሚጨነቅ
የአገዉ ልጅ ታሞ ወሎ ከሚጨነቅ
ወልቃይትም ታሞ ጎጃም ከሚጨነቅ
ድፍን ወሎ ታሞ ሸዋ ከሚጨነቅ
አንድ ሽህ ወያኔ ሆዱን ታሞ ይለቅ፡፡

30. ከእንግድህ አይኖርም አማራ ታፍኖ፣
የቁርጥ ቀን ልጁ እያለለት ፋኖ፡፡

31. ትጥቁ ከሚፈታ ጎጃም ያስታጠቀኝ
በላይ የሞተበት ገመዱ ይነቀኝ፡፡

32. ሰዉ ነገረኛ ዳኛዉ ነገር ሰሚ፣
እኛስ እንሄዳለን ይብላኝ ለከራሚ፡፡

33. ያዋደቃል እንጂ ባልቤን በመዉዜሩ
ፋኖ ቁሞ አያይም ስትፈርስ ሀገሩ፡፡

34. ተዉ አትከልክሉኝ ልሂድ ከቤቴ፣
ዝም ስላልኩኝ በዝቷል ጠላቴ፡፡

35. እዘምታለሁ እንጂ ስንቄን ቋጥሬ

እንደት ዝም እላለሁ ሲደፈር ሀገሬ፡፡
36. እናት ዓለም ጎንደር ቀኖ ይበል ሰንደቅሽ
ደመቀና እስክንድር እንደፎከሩልሽ፡፡
37. ወንድ የወለደዉ የጀግና ወንድም፣
እንበለዉ እንጂ እንሽሽ አይድም፡፡
38. ያምናን ቀን አማሁት ላፌ ለከት የለዉ፣
የዘንድሮዉ ባሰ እጅም እግርም የለዉ፡፡
39. ያነግሳታል እንጂ ደሙን እያዘራ፣
አፍርሷት አያዉቅም ኢትዮጵያን አማራ፡፡
40. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነዉ
ከተጣሉ ወዳ ድርድር ምንድነዉ?
41. እንኳን ጤፍ አዝመራ ማሽላም ቢሆን
ለጠላት አንሰጥም ርስታችንን፡፡
42. ኦነግም ብሎናል ቆቦ ነዉ ድንበሬ
ሃወሃት ብላለች ወልቃይት ሀገሬ
እምቢ አለ እንጂ ፋኖ ተጠምዶ አንደበሬ፡፡
43. ሰሜን አርማጭሆ ወልቃይ በረደዉ፣
ዱሮም አሳምነዉ ነበር የጋረደዉ፡፡
44. በምንሽ ታጭዶ ባልቤን ተበራዬ፣
ጎጃም ዝር አይልም የጨረቃን ያዬ፡፡

# አባሪ ሦሥት፡-

## ከትንታኔዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ፎቶዎች

ሀ. በ2016 የጥምቀት በዓል በጃንሜዳ ጥምቀተ ባሕርና ታቦታት ሽኝት የተነሱ ፎቶዎች






ለ. በ2016 የጥምቀት በዓል በዕድር ሜዳ ጥምቀተ ባሕርና ታቦታት ሽኝት የተነሱ ፎቶዎች






### ሐ. በ2016 የጥምቀት በዓል በካራ አርሴማ ጥምቀተ ባሕርና ታቦታት ሽኝት የተነሱ ፎቶዎች






*አጥኚዉ በመኖሪያ ቤቱ በጥትና ምርምር ስራ ላይ*

# አባሪ አራት፡-

## ደብዳቤዎችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች



አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

Reçu CLT / CIH / ITH
Le - 3 AVR. 2018
N° 0186

ቁጥር ል8/184/329/2010
Ref. No.
ቀን 2-5-10 ዓም
Date

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የጥምቀት በዐል አከባበርን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ የሚደረገውን ዝግጅት ይመለከታል፡፡

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ የትምህርት የባህል ማዕከል /ዩኔስኮ/ በሰው ልጆች ወካይ የክብር መዝገብ ከአስመዘገበቻቸው በርካታ ተፈጥሮአዊና ታሪካዊ ባህላዊ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አብዛኛዎቹ በቤተ ክርስቲያኗ የሚገኙ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

በዚሁ ረገድ ቤተ ክርስቲያኗ ካሏት በርካታ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች መካከል የጥምቀት በዐል አከባበር በኢትዮጵያ በማይዳሰሱ ቅርሶች (Untangeble Heritage) ለማስመዝገብ ባለፈው ዓመት ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጥያቄው ቀርቦ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለዩኔስኮ የሚቀርቡ የጥምቀት በዐልን የሚገልፁ ልዩ ልዩ የፎቶ፣ የቪዲዮና የጽሑፍ መረጃዎች እንዲሁም ከልዩ ልዩ አካላት ከ300 በላይ የያዘ የፊርማ ድጋፍ /ፒቲሽን/ እንዲዘጋጅ ሲጠየቅ በዋናነትም ለዩኔስኮ ከሚላከው ሠነድና ማስረጃ ጋር ስለ በዐሉ አመጣጥና ታሪካዊ ሒደት ሁለት ገጽ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብም ተጠይቋል፡፡ በጥያቄው መሠረት የጥምቀት በዐልን ታሪካዊ ይዘት የሚያሳይ ሁለት ገጽ ጽሑፍ በአማርኛና በእንግሊዝኛ እንዲሁም የተዘጋጀው ፒቲሽን ፊርማ በዚህ የመሸኛ ደብዳቤ የላክን መሆኑን እናስታውቃለን ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

አባ ማትያስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
Abba Matthias I Patriarch
Ethiopia, Archbishop of Axum
Echegue of the see of St. Tеklehaimanot

ግልባጭ
- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ

251-111-550577
251-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com
www. eotc.patriarch.org



### የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስና ከሐዋርያት እንዲሁም ከመምህራን በተማረችው ትምህርትና ቀኖና መሠረት በራሷ ቋንቋ የምትገለጠውና የምታከብረው ይህ ጥንታዊ የሆነ የጥምቀት በዓል በአፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት በ530 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ደረጃ በሜዳና በወንዝ ዳር መከበር ተጀመረ፡፡

በቀጣይም ክህነትን ከንግሥና ጋር አስተባብሮ የያዘው ጻድቅና ሐናጼ መቅደስ የሆነው ቅዱስ ላሊበላ በ1140 ዓ.ም. በየአካባቢው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የጥምቀት በዓልን አከባበር በተናጠል ሳይሆን በአንድ ላይ ወደ ባህረ ጥምቀቱ ወርደው በማደር በዓለ ጥምቀቱን እንዲያከብሩ አዋጅ በማወጅ የጥምቀተ ባህርን ሥርዓት እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

በ1426 የነገሡት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከሊቃውንቱ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የበዓል አከባበር ሥርዓት መነሻነት ታቦታት ወደ ወንዝ ወርደው በእለቱ እንዳይመለሱ የጥምቀት ዋዜማ ጥር 10 ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ባህረ ጥምቀት እንዲወርዱና ሀገርን በኪደተ እግር /በእግር በመንዝ/ እንዲባርኩ ሥርዓትን ሰርተዋል፡፡

በቤተክርስቲያኗ ሊቃውንትና በነገሥታት ውሳኔ መሠረት ሕዝቡ በከተራ እለት በየአካባቢው ለባህረ ጥምቀት በተመረጠው ወንዝ ውሃውን በህብረት በመከተር /በመገደብ/ አካባቢውን አጽድቶ ታቦት የሚያድርበትን ቦታ አዘጋጅቶ ታቦተ ሕጉን በዝማሬ በሆታና በእልልታ አጅቦ ወደ የባህረ ጥምቀቱ እየወጣ የባህረ ጥምቀት በዓል አከባበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሁን በምናከብረው ሁኔታ በተናጠል ሳይሆን በሕብረት በየዓመቱ ከጥር 10 እስከ 11 እንዲከበር ተደረገ፡፡

### የጥምቀት አከባበር በዘመናችን


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓላት አስተዳደራዊ መዋቅር በሀገር ውስጥ 50 አህጉረ ስብከት በአራቱም የኢትዮጵያ መዓዘናት 40ሺ አብያተ ክርስቲያናት ያላት ሲሆን ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ከእምነት ተቋማት በእምነቷ ተከታዮች ትልቁን ቁጥር የያዘች አንጋፋ ሐዋርያዊት ታሪካዊትና ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ስትሆን በውስጧ በታላቅ ድምቀት ጥር 10 እና 11 የምታከብረው የጥምቀት በዓል አከባበር መነሻ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 እንደተገለጸው 72ቱ አርድዕትና ከ7ቱ ዲያቆናት አንዱ የነበረው ወንጌላዊ ፊልጶስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በጋዛ የኢትዮጵያዊቷን የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ባጠመቀው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ጥምቀት /መጠመቅ/ በጃንደረባው/ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ገባ፡፡

በቀጣይም የክርስትና እምነትና ጥምቀት በአክሱምና በአካባቢው በሚኖሩ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚገባ ተቀባይነት አግኝቶ እየተስፋፋ ፍሬምናጦስና ወንድሙ ኢዴሲዮስ ወደ አክሱም እስከመጡበት ድረስ ቆይቷል፡፡ ከዚያም በመላው ኢትዮጵያ እየተስፋፋ መጣ፡፡

የሰው ልጅ በሥጋ ከእናት ከአባት ይወለዳል፡፡ በጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ይወለዳል፡፡

ጥምቀት የቃሉ ፍቺ በውሃ መታጠብ መዘፈቅ፣ መነከር፣ መጥለቅ ማለት ሲሆን መሠረተ ሃሳቡ መንፃትን ያመለክታል፡፡ የክርስትና እምነት ተከታይ ለመሆንና በእምነቱ አምኖ ለመኖር በጥምቀት ከእግዚአብሔር በዳግም ልደት መወለድ ይገባዋል፡፡

1



- የበዓሉ አከባበር ከዋናው የሃይማኖት መሠረታዊ ትርጉሙ በአሻገር በአሉ ለሰው ልጆች ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነጥበብ ማደግ ተፋቅሮና ተከባብሮ መኖር ለቱሪስት መዳረሻነት፣ ለገጽታ ግንባታ ታላቅ ጠቀሜታን አበርክቷል እያበረከተም ይገኛል፡፡

የጥምቀት በዓል በመላው ኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያኗ እምነትና ዶግማ ቀኖናና ትውፊት መሠረት አድርጎ እንደ የአካባቢው ባህል ቋንቋና ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ ይከበራል፡፡ በተለይም የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ፡-

- በአዲስ አበባ ጃን ሜዳ
- በጎንደር በአፄ ፋሲል መዋኛ
- በአክሱም ማይ ሹም
- በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ዮሐንስ አምባ ገብርኤ ባህረ ጥምቀት በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል፡፡

### ከጥምቀት በዓል ትሩፋቶች

- ብሔር፣ ባህል፣ ቋንቋ ሳይለያይ በዓሉ በአንድነት የሚከበር መሆኑ፣
- በዓሉ የወግ፣ የባህል አልባሳት፣ የእጅ ሥራ ጥበባት የሚታዩበት ኢትዮጵያዊ ስንኝ ግጥም፣ ዜማ የሚማሩበት የሚነገሩበት ትሩፋት መሆኑ፣
- ሥርዓቱና ወጉ ሳይፋለስ ወጣቱ ባህሉን እምነቱን ወጉና ክብሩን ጠብቆና አስጠብቆ ይዞ ማስቀጠሉ፣
- በየጊዜው በዓሉ መደብዘዝ ሳይታይበት እየደመቀ እየፈካ መከበሩ፣
- የአገር ውስጥም የውጪውንም ጎብኚ ቀልብና አይን መማረኩ፣
- ረጅም ዓመታዊ የእግር ጉዞ በማድረግ የአካል ጥንካሬና በሕብረት መኖዝ የሰላም ምሳሌነት ማስፈኑ ነው፡፡

### ማጠቃለያ


ይህ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ክርስትና ወደ ሀገራችን ሲገባ የመጣውን የጥምቀት በዓል አከባበር በአፄ ገብረ መስቀል 530 ዓ.ም. የአደባባይ በዓል ሆኖ መከበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 1500 ዓመታት ቤተ ክርስቲያኗ በሀገር ደረጃ በአደባባይ ጥምቀተ ባህር እየወጣች ስታከብር ቆይታለች፡፡

የጥምቀት በዓል ታሪካዊና ባህላዊ ሃይማኖታዊ እሴቱ ተጠብቆ እንዲቀጥል በተለይም በሰው ልጆች ወካይ የዓለም ድንቅ መዝገብ በዩኔስኮ /በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ የባህልና የትምህርት ማዕከል/ ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል በሀገር ደረጃ እንዲመዘገብልንና በዓሉ ጥንተ መሠረቱ ተጠብቆ ወደ ትውልድ እንዲሻገር ለማድረግ ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝቶ በሰው ልጆች ወካይ የቅርስ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብልን እንጠይቃለን፡፡

2

*የጥምቀተወ በዓልን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ በኢኦተቤክ የተጀመረ ጥረት*

## ሠ. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናትና ምርምር ማዕከል የተጻፈ የትብብር ደብዳቤ



ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ
የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ
ትምህርት ክፍል

Kotebe University of Education

Department of Amharic
Language & Literature

ቁጥር
ቀን 16/06/2016 ዓ.ም

ለ፡- ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ትብብርን ይመለከታል።

ተማሪ አባተ አሰፋ የመታወቂያ ቁጥር PGW/25983/14 በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በማምንት መጨረሻ መርሃብር የኤም ኤ ተማሪ ናቸው፡፡ በ2016 ዓ.ም የመመረቂያ ወረቀት በመስራት ላይ መሆናቸዉን እየገለጽን በእናንተ በኩል አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው እንጠይቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

ለአማርኛ ቋንቋና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ
የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ
ትምህርት ክፍል

Kotebe University of Education

Department of Amharic
Language & Literature

ቁጥር
ቀን 16/06/2016 ዓ.ም

ለ፡- ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ትብብርን ይመለከታል።

ተማሪ አባተ አሰፋ የመታወቂያ ቁጥር PGW/25983/14 በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በማምንት መጨረሻ መርሃብር የኤም ኤ ተማሪ ናቸው፡፡ በ2016 ዓ.ም የመመረቂያ ወረቀት በመስራት ላይ መሆናቸዉን እየገለጽን በእናንተ በኩል አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው እንጠይቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

ለአማርኛ ቋንቋና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል